

# አርአያ

## ሴት ኢትዮጵያውያን

ታህሳስ፡ 2017 ዓ.ም

CECOE
Multiparty Democracy

# አርአያ ሴት ኢትዮጵያውያን

ሕዳር፤ 2017 ዓ.ም

ኅብረት ለምርጫ|CECOE
Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections
Netherlands Institute for Multiparty Democracy
Funded by the European Union

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

ምስጋና ........ 2

ማስታወሻ ........ 3

ሴቶች በፖለቲካ፣ የህዝብ አገልግሎት እና ........ 4

ዓለም አቀፍ ግንኙነት ........ 4

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ (1866-1922 ዓ.ም.) ........ 5

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ ........ 6

ስንዱ ገብሩ ደስታ (1908-2001 ዓ.ም.) ........ 7

ቆንጂት ሥነ ጊዮርጊስ (አምባሳደር) ........ 8

ታደለች ኃይለሚካኤል (አምባሳደር) ........ 11

ክብርት ሎሚ በዶ ........ 12

መዓዛ አሸናፊ ........ 13

ኤርጎጊ ተስፋዬ (ፒ.ኤች. ዲ) ........ 15

አረጋሽ አዳነ ........ 16

ብርቱካን ሚደቅሳ ........ 17

ሙፈሪሃት ካሚል ........ 18

ዶ/ር ሊያ ታደሰ ........ 19

አዳነች አቤቤ ........ 21

ፍፁም አሰፋ (ፒ.ኤች. ዲ) ........ 22

አይሻ መሀመድ ....... 23

ሃና አርአያስላሴ ....... 24

ፍሬህይወት ታምሩ ....... 25

አምባሳደር አጸደ ኪዳኑ ....... 26

አምባሳደር ሂሩት ዘመነ ....... 26

ኬሪያ ኢብራሂም ....... 27

ሽታዬ ምናለ ....... 28

ቢለኔ ስዩም ....... 29

ራሄል ባፌ (ፒ.ኤች.ዲ) ....... 30

ፊልሳን አብዱላሂ ....... 31

**ቀዳማዊት እመቤቶች ....... 32**

እቴጌ ጣይቱ ብጡል (1832-1910 ዓ.ም.) ....... 33

ግርማዊት  እቴጌ መነን አሥፋው (1883-1954 ዓ.ም) ....... 34

ውባንቺ ቢሻው ....... 35

አዜብ መስፍን ....... 36

ሮማን ተስፋዬ ....... 36

ዝናሽ ታያቸው ....... 37

**ሴቶች በሰብዓዊ ዕርዳታ፣ በሰብዓዊ መብቶች ትግል እና በሲቪል ማህበራት ....... 39**

የቃቂ ውርድወት ....... 40

አበበች ጎበና (1928 – 2013 ዓ.ም) ....... 42

ቦጋለች ገብሬ (ፒ.ኤች.ዲ) (1952-2012 ዓ.ም) ....... 43

ዘሚ የኑስ (1951- 2013 ዓ.ም) ........................................ 44

ዘቢዳር ዘውዴ (ሲስተር) ........................................ 47

ትርሃስ መዛገበ ........................................ 48

ማሪያ ሙኒር ........................................ 49

ሳባ ገብረመድህን ........................................ 50

የትነበርሽ ንጉሴ ........................................ 52

ሀናን ማህሙድ ........................................ 53

ስህን ተፈራ (ፒ.ኤች.ዲ) ........................................ 54

መስከረም ገስጥ ........................................ 55

ሌንሳ ቢየና ........................................ 56

ሀና ለማ ........................................ 57

## ሴቶች በኪነ ጥበብ እና ጋዜጠኝነት ........................................ 58

እማሆይ ፅጌ ማርያም ገብሩ (1916-2015) ........................................ 59

ሮማን ወርቅ ካሳሁን (1914_1964) ........................................ 60

መዓዛ ብሩ ........................................ 62

ሰሎሜ ታደሰ ምህረቱ ........................................ 64

ሜሪ አርምዴ (1923-1981 ዓ.ም) ........................................ 65

ዓለም ፀሐይ ወዳጆ ........................................ 66

የምወድሽ በቀለ ........................................ 68

ፈርማዩ ዓለሙ ........................................ 69

ህይወት ተፈራ ........................................ 70

መዓዛ መንግስቴ ....................................................................................................71

ጸዳለ ለማ ....................................................................................................72

## ሴት ተመራማሪዎች ........................................................................ 73

ሶስና ሀይሌ (ፕሮፌሰር) ....................................................................................................74

ሰገነት ቀለሙ (ፒ.ኤች.ዲ) ....................................................................................................75

የዓለም ፀሐይ መኮንን (ፕሮፌሰር) ....................................................................................................76

ዶክተር ተዋበች ቢሻው ....................................................................................................78

ትምኒት ገብሩ (ፒ.ኤች.ዲ) ....................................................................................................79

ረድኤት አበበ (ፒ.ኤች.ዲ) .................................................................................................... 80

## ሴቶች በሥራ ፈጠራ እና ንግድ ........................................................................ 81

ጽዮን ሚካኤል አንዶም (1915 - 2015 ዓ.ም) ....................................................................................................82

እሌኒ ዘውዴ ገብረ መድኅን (ፒ.ኤች.ዲ) ....................................................................................................83

ሚሚ አለማየሁ .................................................................................................... 84

ፍሬዓለም ሽባባው ....................................................................................................85

ቤቴልሄም ጥላሁን ....................................................................................................87

ፀደይ አስራት ....................................................................................................88

ሳራ መንክር ....................................................................................................89

ሳምራዊት ፍቅሩ .................................................................................................... 90

ቤተልሄም ደሴ ....................................................................................................92

## ሴቶች በስፖርት ዓለም ........................................................................94

ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ ....................................................95
ፋጡማ ሮባ ....................................................96
ጥሩነሽ ዲባባ ....................................................97
መሰረት ደፋር ....................................................98
ሎዛ አበራ ....................................................99

## ሴት አውሮፕላን አበራሪዎች ....................................................101

ሙሉ እመቤት እምሩ ....................................................102
አሰገደች አሰፋ ....................................................103
አምሳለ ጓሉ (ካፒቴን) ....................................................104

## ሴት አርበኞች ....................................................106

ሸዋረገድ ገድሌ (1878-1942 ዓ.ም) ....................................................107
ልክየለሽ በያን (1902-1972 ዓ.ም) ....................................................109
ከበደች ስዩም መንገሻ (1904-1976 ዓ.ም) ....................................................110

# መግቢያ

በኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት ታሪክ ውስጥ ፤ በተለያየ ዘርፍ እና በተለያየ መንገድ ሴት ኢትዮጵያዊያን ለሀገራቸው ያበረከቱት አስተዋፅዖ ተፅፎ እና ተሰንዶ ሊቀመጥ ከሚችለው በላይ ሰፊ እና መልከ ብዙ ነው። እነዚህ ሴቶች ቤታቸውን ከማቆም ጀምሮ በሀገር መሪነት ፤ በፖለቲካ ፤ በህክምና ፤ በሳይንስ፣ ኪነጥበብ እና ማህበራዊ አንቂነት የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ለህብረተሰባቸው እና ለሃገራቸው ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል። ለመጪው ትውልድም ፈር በመቅደድ አራአያ መሆን ችለዋል።

ይህ ኢንሳይክሎፔዲያ በተለያዩ ዘርፎች አርአያ መሆን የቻሉ ሴቶችን ታሪክ ይዟል። ብዙውን ጊዜ በባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች ተለይቶ በሚታወቅ ማህበረሰብ ውስጥ፣ እነዚህ አበረታች ሴቶች እንደ መሪ፣ አዲስ ነገር ጀማሪ እና የመብት ተሟጋች ሆነው ብቅ አሉ፣ ጽናትን እና ቆራጥነትንም አሳዩን። የእነዚህን አራአያ ሴቶች አብርክቶዋቸውን በመዘከር ሌሎች ሴቶች ራሳቸውን አብቅተው እውቀት እና ችሎታችውን ለህበረተሰባቸው ትርጉም ያለው አስተዋጻኦ እንዲያደርጉ የማነሳሳት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ፅኑ እምነት አለን ።

# ምስጋና

ይህንን “አርአያ ሴት ኢትዮጵያዊያን” የተባለ ኢንሳይክሎፔዲያ እንድናዘጋጅ ምክንያት በመሆን በዚህ ሰነድ ታሪካቸው ለተካተቱ ሴቶች ታላቅ ክብር እና ምስጋና እናቀርባለን። በዚህ ኢንሳይክሎፔዲያ ታሪካቸው ያልተካተቱ እውቀት እና ችሎታቸውን ተጠቅመው  የማይተካ ሥራ ለሰሩ እና እየሰሩ ለሚገኙ ሴቶች ምስጋና እና ክብር ይገባቸዋል እንላለን።

ኅብረት ለምርጫ ይህንን ኢንሳይክሎፔዲያ አሰናዶቶ ወደ አንባቢያን እንዲያደርስ ድጋፍ ላደረጉት ለአውሮፓ ህብረት እና NIMD | Netherlands Institute for Multiparty Democracy እንዲሁም በዝግጅቱ ሂደት ጉልህ አበርክቶ ለነበራቸው ሁሉ ኅብረት ለምርጫ ምስጋና ያቀርባል።

# ማስታወሻ

ይህ ኢንሳይክሎፔዲያ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ከNIMD | Netherlands Institute for Multiparty Democracy ጋር በመተባበር ከአውሮፓ ሕብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ነው። ይህን ኢንሳይክሎፔዲያ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የተካተቱ የሴት ኢትዮጵያን ታሪኮች እና በጥቅም ላይ የዋሉ ፎቶግራፎች ከተለያዩ ሰነዶች፣ የበይነ መረብ ልጥፎች እና ለተመሳሳይ ዓላማ ከዚህ ቀደም በሌላ አካላት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች የተገኙ ናቸው። ኅብረት ለምርጫ ይህ ኢንሳይክሎፒዲያ ለማዘጋጀት የተጠቀማቸው ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፤

1. EIGHT ETHIOPIAN WOMEN OF THE “ZEMENE MESAFINT
2. Top 17 of the Most Influential Ethiopian Women
3. Women in Ethiopia - Oxford
4. Most Powerful Women in Ethiopia
5. Seven Women
6. 10 Inspiring Women to Know
7. ተምሳሌት ፡ ዕጹብ ድንቅ ኢትዮጵያውያን ሴቶች

በዚህ ኢንሳይክሎፒድያ ውስጥ በተካተቱ ታሪኮች ውስጥ ለሚያጋጥሙ ማንኛውም ስህተቶች እና ጉድለቶች ከወዲሁ ይቅርታ እየጠየቅን ለነዚህ ስህተቶች እና ጉድለቶች ሃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ ኅብረት ለምርጫ ይወስዳል።



# ሴቶች በፖለቲካ፣ የህዝብ አገልግሎት እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት

# ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ (1866-1922 ዓ.ም.)



በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቀዳሚ ሴት መሪ በመሆን ይታወቃሉ። ለ14 ዓመታት ኢትዮጵያን ንግሥት ሆነው መርተዋል። እኚህ ንግሥት ወደ ንግሥናው መንበር የወጡት መስከረም 21 ቀን 1909 ዓ.ም ነበር። ዘውዲቱ ምኒልክ የተወለዱት ከንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ እና ከ አብቸው በያን በ1866 ዓ.ም በእነዋሪ ከተማ ሰገነት የተባለች መንደር ነው። ገና የስድስት ዓመት ተኩል ልጅ ሳሉ ለንጉሰ ነገሥት አጤ ዮሐንስ ፬ኛ ልጅ ለራስ አርዓያሥላሴ ዮሐንስ ተዳሩ።

ከአምስት ዓመታት በኋላም ራስ አርዓያሥላሴ ዮሐንስ ስለሞቱ ዘውዲቱ ወደ ሸዋ ተመለሱ። በ1884 ዓ.ም ደግሞ ደጃዝማች ውቤ አጥናፍሰገድን አግብተው መኖር ጀመሩ። ይህ ጋብቻም ፈረሰና፣ በ1893 ዓ.ም የእቴጌ ጣይቱ የወንድም ልጅና የጎንደር ገዢ የሆኑትን ራስ ጉግሳ ወሌን አገቡ። ደጃዝማች ጉግሳ ወሌ በወቅቱ በጌምድርን ያስተዳድሩ ነበር።

ነገር ግን ንግሥት ዘውዲቱ ወደ አዲስ አበባ የሚመልሳቸው አንድ ጉዳይ ተፈጠረ። አባታቸው አፄ ምኒሊክ በፀና መታመማቸውን ሰሙ። ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ በ1901 ዓ.ም በታመሙ ጊዜ ንግሥት ዘውዲቱ ከደብረታቦር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አባታቸውን ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመሆን ማስታመም ጀመሩ። ለተከታታይ 6 ዓመታት ያስታመሟቸው አባታቸው በ1906 ዓ.ም መሞታቸውን ተከትሎ እጅጉን ኅዘን ዋጣቸው። በኋላም ልጅ ኢያሱ እቴጌ ጣይቱና ንግሥት ዘውዲቱ ከቤተ መንግሥት እንዲወጡ ባልታወቀ ምክንያት ባዘዙ ጊዜ ከቤተ መንግሥት ለመውጣት ተገደዱ። ፋሌ ወደሚገኘው እርስታቸው ሄደው ተቀመጡ። ልጅ ኢያሱም ንግስት ዘውዲቱን ከሌላ ሰው ጋር ሊያጋቧቸው ብዙ ቢጥሩም በቁርባን ያገባሁት ጉግሳ ወሌ እያለ ሌላ አላገባም በማለታቸው፤ ባላቸው ከበጌ ምድር እንዲመጡና አብረው እንዲኖሩ አደረጉ። በዚህ ሁኔታ ፋሌ ላይ የቆዩት ንግሥት ዘውዲቱ ወደ ስልጣን የሚመጡበት ጉዳይ ተከሰተ። እርሱም ልጅ ኢያሱ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ከስልጣን እንዲወርዱ ተፈረደባቸው። ልጅ ኢያሱ ከንግሥና ስልጣን ሲወርዱ፤ መኳንንቱና ሕዝቡ ስልጣን ለማን ይገባል በማለት መክሮና ዘክሮ አንድ ውሳኔ አሳለፈ።

ዘውዲቱን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥት፣ ራስ ተፈሪ መኮንንን አልጋ ወራሽ እና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እንዲሆኑ ወስነው፤ መስከረም 21 ቀን 1909 ዓ.ም ዘውዲቱ “ንግሥተ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” ተብለው ነገሡ።

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በስልጣን ዘመናቸው ብዙ ዓበይት ተግባራትን ፈጽመዋል። የኢትዮጵያን የዓለም መንግሥታት ማኅበር(ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል ማድረጋቸው ተጠቃሹ ነው። ንግሥቲቱ በስልጣን ላይ ሳሉ፤ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላው ጉባዔ መስከረም 17 ቀን 1916 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ኢትዮጵያ አባል እንድትሆን ፈቃዱ መሆኑን ያሳወቁበት ጊዜ ነበር። ሌላው የባሮች ነፃነት ደንብ ነበር። ይህ ደንብ ምንም እንኳን በወቅቱ በመኳንንቱ ባይወደድም ባሮችን ነፃ የሚያወጣና በአንፃራዊነትም ፍትሕ የሚያሰፍን ስለነበር በብዙዎች የተወደሰ ነበር። በልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን መጋቢት 16 ቀን 1916 ዓ.ም በግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ፈቃድ ስለ ባሮች ነፃነት የወጣው ደንብ “ስለ ባሮች አስተዳደርና ነፃነት የቆመ ደንብ” የሚል ርዕስ ነበረው።

ንግስት ዘውዲቱ አባታቸው አፄ ምኒልክ የምዕራባውያንን ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የነበራቸውን ፍላጎት በሚገባ የተገነዘቡ ስለነበሩ በበኩላቸው ትምህርት እንዲስፋፋ አዋጅ አወጡ። አዋጁም እድሜው ከ7 እስከ 21 አመት ድረስ የሚደርሱ ልጆች ያሏቸው ወላጆች የንባብና የፅሕፈት ትምሕርት እንዲሁም በአገራችን ካሉ የእጅ ሥራ ሙያዎች ውስጥ ልባቸው የወደደውን ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ የሚደነግግ ነበር። ይህን ያላደረጉ ወላጆች 50 ብር ቅጣት እንዲቀጡ የደነገገ አዋጅ ነበር። ይህንንም የመቆጣጠሩ ሃላፊነት በንሥሐ አባቶች ፣ በገጠር መሪጌታዎች እና በደብር አለቆች ላይ ተጥሎባቸው ነበር። ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በነገሡ በ13 ዓመት ተኩል ረቡዕ መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም በ10 ሰዓት አረፉ። የሞታቸው ዜና እንደተሰማም በከተማው የኅዘን ጥላ አጠላበት። አባታቸው ዐፄ ምኒልክ በተቀበሩበት በታዕካ ነገሥት በዓታ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሴቶች በአመራርነት ላይ ቢሳተፉ ብቁ መሆናቸውን በነገሡበት ዘመን በሠሩት ሥራ አሳይተዋል። በኢትዮጵያ አዳዲስ ሕጎችን በማውጣትና በመተግበር ሕግና ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረዋል። ኢትዮጵያ በዓለማቀፍ ደረጃ እውቅና እንድታተርፍና ተሳትፎዋ ከፍ እንዲልም ሠርተዋል። የጥንካሬ ተምሳሌት፣ የሩህሩህነትና አዛኝነት አብነት እንደነበሩ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

## ሣህለ ወርቅ ዘውዴ



በመላው አፍሪካ “አስታራቂዋ ዲፕሎማት” በመባል የሚታወቁት ርዕሰ ብሔር ሣህለ ወርቅ ዘውዴ የመጀመሪያዋ ሴት የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት ናቸው። ፕሬዝደንት ሣህለ ወርቅ የእድሜያቸውን ግማሽ ያሳለፉት በዓለም ዓቀፍ ግንኙነት አገራቸውን በማገልገል ነው። ርእሰ ብሔር ሣህለ ወርቅ በወርሃ የካቲት 1942 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተወለዱ ሲሆን ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዘኛ እና አማርኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገራሉ። ከፈረንሳዩ ሞንተፔለ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ምሩቅ ሲሆኑ፤ እ.ኤ.አ. ከ1989-1993 ዓ.ም ተቀማጭነታቸውን ሴነጋል በማድረግ የማሊ፣ የኬፕ ቨርዴ፣ የጊኒ ቢሳው፣ የጋምቢያና የጊኒ አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል። እ.ኤ.አ. ከ1993-2002 ደግሞ በጅቡቲ አምባሳደር ሆነው የሠሩ ሲሆን፤ በወቅቱ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢ.ጋ.ድ) ቋሚ ተወካይም ነበሩ። ከዚያም በመቀጠል እ.ኤ.አ ከ2002-2006 በፈረንሳይ አገር አምባሳደር እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም ተወካይ ሆነው ሠርተዋል።

በኋላም በተባበሩት መንግሥታት ልዩ መልዕክተኛ ውስጥ የተቀናጀው የሰላም አስከባሪ ኃይል (BINUCA) ተወካይ በመሆን በሴንትራል አፍሪካ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። በአፍሪካ ሕብረት ውስጥና በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ ኮሚሽን ውስጥም የኢትዮጵያ ቋሚ ተወካይ ሆነው አገልግለዋል። በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥም የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ሆነው ሰርተዋል።

እ.ኤ.አ በ2011 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ባን ኪሙን፤ በኬንያ የተባበሩት መንግሥታት ዳይሬክተር ጄነራል አድርገው ሾመዋቸው አገልግለዋል። በቀጣይም በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬስ በአፍሪካ ሕብረት ልዩ ተወካይ እንዲሁም በአፍሪካ ሕብረት የተባበሩት መንግሥታት ቢሮ ኃላፊ ሆነው ተሾመዋል።

ከጥቅምት 15 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ርዕሰ ብሔር (ፕሬዚደንት) ሆነው አገልግለዋል። የኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዝዳንት ሆነው በተመረጡ እለት ለፓርላማ ባደረጉት ንግግር ለሴቶች ድምፅ ለመሆን ቃል ገብተዋል።

የሣህለ ወርቅ ርእሰ ብሔርነት ለሴቶች የ “ይቻላልን” ጠንካራ መልዕክት ያስተላለፈ ሲሆን በኢትዮጵያም ያለውን የፆታ እኩልነት ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት አራምዶታል። ርዕሰ ብሔር ሣህለ ወርቅወርቅ ዘውዴ ሴቶች እምብዛም በአመራርነት በማይገኙበት የዓለም አቀፍ ግንኙነት እና የፖለቲካ ተሳትፎ ጉልህ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በርዕሰ ብሔርነት ቆይታቸው አበክረው ካተኮሩባቸው ጉዳዮች መካከል የሴቶች እኩል ተጠቃሚነትና ተሣታፊነት ዋነኞቹ ናቸው። በኢትዮጵያ ያለው የሴቶች ጥያቄ ሙሉ በሙሉ እንዳልተፈታ፣ በተለያየ መንገድ የሴቶች ሁለንተናዊ መብቶች እንደሚደፈጠጡ እና የፆታ ማነቆዎች ሊወገዱ እንደሚገባ ይወተውታሉ። ሀገር ትርጉም ባለው መንገድ ሁሉን አቀፍ እድገት እንድታድግ የሴቶችን ዙሪያ መለስ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ እንዲሁም የማህበራዊ ፍትህን ማስፈን እንደሚገባ በየመድረኩ ይናገራሉ። ርእሰ ብሔር ሣህለወርቅ ዘዉዴ የፎርብስ መጽሔት የ2014 ዓ.ም. ተፅዕኖ ፈጣሪ 100 ሴቶች ዝርዝር ዉስጥ የገቡ ብቸኛዋ አፍሪካዊት ናቸው። ርእሰ ብሔር ሣህለወርቅ ዘዉዴ በአስተዳደር ውስጥ በመኖራቸው ለሌሎች ሴቶች የተስፋ ብርሃን መሆን ችለዋል “ሴቶች ከጓዳ ወጥተው አደባባይ መዋል ይችላሉ” የሚለውንም ስሜት በብዙ ኢትዮጵያውያን ውስጥ ማሥረፅ ችለዋል።

## ስንዱ ገብሩ ደስታ (1908-2001 ዓ.ም.)



ክብርት ዶ/ር ስንዱ ገብሩ የመጀመሪያዋ ሴት የሕግ አውጪው ምክር ቤት ተመራጭ፣ አርበኛ፣ ፀሐፊ-ተውኔት፣ ደራሲ፣ የመጀመሪያዋ ሴት ዲፕሎማት፣ የሴቶች ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች እንዲሁም ፖለቲከኛ ነበሩ። ስንዱ ገብሩ በቀድሞው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት በመናገሻ አውራጃ፣ በአዲስ ዓለም ከተማ ጥር 6 ቀን 1908 ዓ.ም. ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከቤታቸው አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የአማርኛን ትምህረት ከፊደል መቁጠር እስከ ዳዊት መድገም ተማሩ።

ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሄደው በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል። በ1921 ዓ.ም ወደ ስዊስ እና ፈረንሳይ በማቅናት በሁለት ኮሌጆች የስነ ጽሁፍ እና የቋንቋ ትምህርት በአጠቃላይ ለአምስት ዓመታት ተምረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱም በአዲስ አበባ በቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ሥነ-ጽሁፍን፣ የእንግሊዝኛ እና የፈረንሳይኛ ቋንቋዎችን፣ እንዲሁም ጤና አጠባበቅን አስተምረዋል። የፋሽስት ኢጣልያ ወረራ ያንዣበበት ወቅት ስለነበር በፀረ ፋሽስት እና በአርበኝነት ላይ ያተኮሩ ከ20 በላይ የመድረክ ተውኔቶችንም ፅፈው አዘጋጅተዋል። የፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ በቀድሞ አጠራሩ በኢሉባቡር ጠቅላይ ግዛት በጎሬ አውራጃ የቀይ መስቀል ቅርንጫፍን መስርተው የ "ጥቁር አንበሳ" የነፃነት እንቅስቃሴን ተቀላቀሉ። የጥቁር አንበሳ አርበኞች ቡድን የጣሊያን ወራሪ ሃይሎችን የሚታገል የአርበኞች ስብስብ ነበር።

አርበኛ ስንዱ ተቀላቅለውት የነበረው የጥቁር አንበሳ ጦር ሲመታ በመማረካቸው ጣሊያኖች አስረው ወደ አዲስ አበባ አመጧቸውና የቁም እስረኛ ሆኑ። የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ግራዚያኒን ለመግደል በተደረገ ሙከራ ወንድማቸው መሸሻ ገብሩ አሉበት በመባሉ ይታሰሱ ስለነበር ወንድማቸውን ከአደጋ ለማዳን ሲፈልጉ በድጋሚ በፋሺስቶች እጅ ወደቁ። በወቅቱ ግራዚያኒ ይኖርበት የነበረው የጃንሆይ ቤተመንግሥት ታሰሩ። ቀጥሎም ወደ አስመራ፣ ከዚያ ወደ ምጽዋ ተወሰዱ። ከምጽዋ ወደብ አዚናራ ወደተባለች የኢጣሊያኖች እስር ቤት ተወስደው ዘጠኝ ወራትን ታሰሩ።

ከእስር በኋላም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በእንደዚህ ያለ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፤ ማስፈራሪያው ሳይበግራቸው አርበኞችን በግጥም፣ በወኔ ቀስቃሽ ጽሑፎች በማበረታታት፣ መረጃ በማቀበል፣ መሣሪያ በማዳረስ የጀግንነት ተግባር ፈጽመዋል። የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ወይዘሮ ስንዱ ለሁለት ዓመታት ደሴ ከተማ የሚገኘው የወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን አገልግለዋል። በኋላም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት በምክትል ርዕሰ መምህርነት፣ ከዚያም በርዕሰ መምህርነት የመጀመሪያዋ ሴት ርዕሰ መምህር ሆነው ሰርተዋል። ከዚህ በኋላ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ተሣትፎአቸው እየሰፋና በቁጥርም እየተበራከተ መጣ።

ከ1948 ዓ.ም. እስከ 1952 ዓ.ም. ድረስ የመጀመሪያዋ የሴት የፓርላማ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ም/ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ሥራ አስኪያጅ፣ የህዝባዊ ኑሮ ዕድገት ዋና ፀሐፊነትና አስተዳዳሪነት፣ በምዕራብ ጀርመን ለሦስት ዓመት የትምህርት አታሼ በመሆን አገልግለዋል። ስንዱ ገብሩ በፓርላማ የነበራቸው ተሳትፎ አብረዋቸው ለነበሩት እና በኋላም ለተመረጡት ሴት የፓርላማ አባላት ትልቅ ብርታት ነበሩ። በዚህ ምክር ቤት አባል በነበሩበት ጊዜ ብቸኛዋ ሴት ከመሆናቸውም ባሻገር የሴቶች እኩልነት በማይከበርበት ጊዜ እና "የወንድ ዓለም" በገነነበት የታሪክ ምዕራፍ የሴቶችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበርና እኩልነትን በሕግ ለማስተማመን በብዙ የታገሉ ሴት ነበሩ።

በሴቶች መብት ጉዳይ ድርድር የማያውቁት የመጀመሪያዋ ሴት የፓርላማ አባል ክብርት ስንዱ በፖለቲካ ውይይቶች ላይ በሚያነሷቸው ጭብጦች ዘመናቸውን የቀደሙ ነበሩ። በሞጋች የፆታ እኩልነት ጥያቄዎቻቸው ምክንያት ጓዶቻቸው "አቶ ስንዱ" እያሉ ያሾፉባቸው ነበር። ይህ አንዳችም ያልገደባቸው ክብርት ስንዱ ባልን የቤተሰብ ራስ አድርጎ የሚሾመውንና በትዳር፣ በመኖሪያና በገንዘብ ጉዳይ የመወሰን ሙሉ ስልጣንን ለወንድ የሰጠውን የ1960 ዓ.ም የፍትሐ ብሄር ህግን በፅኑ በመቃወም ይታወሳሉ።

በሰዓቱ እንደድፍረት ቢቆጠርባቸውም፣ ጊዜ ቢፈጅም እርሳቸውና መሰሎቻቸው ያነሱትን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ የህግ መሻሻያዎች እንዲቀረፁ ሆኗል።

ስንዱ በፖለቲካና በአስተዳደር መስኮች ካበረከቱት አስተዋፅኦ በተጨማሪ ማህበራዊ ተሣትፏቸውም እጅግ ሰፊ ነበር። በሴቶች የበጐ አድራጐት ድርጅቶች፣ በቀይ መስቀል ማኅበር፣ በአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እና በሌሎችም ማህበራት ያለመታከት ሲያገለግሉ ኖረዋል። ስንዱ ከ10 በላይ መጻሕፍት የጻፉና፣ ስድስት ስክሪፕቶችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማስቀመጣቸውም ታውቋል። ስንዱ ገብሩ ላበረከቷቸው አስተዋጽዖዎች የወርቅ ሜዳሊያ፣ የንግሥት ሣባ የወርቅ ኒሻን፣ የቀይ መስቀል የወርቅ ሜዳሊያ እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ተሰጥቷቸዋል።

ክብርት ዶ/ር ስንዱ ገብሩ የኖሩበትን ዘመን፣ ሁኔታና አካባቢ አልፈው ዓላማቸውን ያሳኩ አንቱ ለተባለላቸው የአገልግሎቶችና የሥራ አይነቶች ከውጊያ እስከ ውሳኔ ሰጪነት በመቀመጥ ለመላው ሴት ኢትዮጵያዊያን ተምሳሌት ለመሆን የበቁ ታላቅ ሴት ነበሩ።

## ቆንጂት ሥነ ጊዮርጊስ (አምባሳደር)



አምባሳደር ቆንጂት ሥነ ጊዮርጊስ ለ52 ዓመታት አገራቸውን በዓለም አቀፍ ግንኙነት መስክ ያገለገሉ አንጋፋ ዲፕሎማት ናቸው። አምባሳደር ቆንጂት ከዮዲት እምሩ በመቀጠል በኢትዮጵያ ሁለተኛዋ ሴት አምባሳደር ሲሆኑ የሙያ አጋሮቻቸው “ተንቀሳቃሿ የአፍሪካ ጉዳዮች ኢንሳይክሎፒዲያ” (The Walking Encyclopedia of African Affairs) ብለው ይጠሯቸዋል።

አምባሳደር ቆንጂት በ1932 ዓ.ም በሐረር ከተማ ነው የተወለዱት። ከልጅነታቸው  ጀምሮ በራስ የመተማመን ስሜት ያዳበሩት ቆንጂት ከሐረር እስከ አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ እስከ እንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ፣ ከለንደን እስከ አሜሪካን አገር ኒውዮርክ ፣ድረስ  በተማሩባቸውና በሰሩባቸው አመታት በሴትነታቸው ምክንያት ይደርስ የነበረውን መድሎ ታግለው አሸንፈዋል። አስተዳደጋቸው በራስ የመተማመንና የነፃነት ስሜት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። ለዚህም የእናታቸው እና የታላቅ ወንድማቸው ድርሻ የጎላ ነበር። በተለይ ታላቅ ወንድማቸው በቆንጂት እንቅስቃሴዎች ላይ ያልተገባ ጥብቅ ቁጥጥር ከማድረግ ይልቅ ነፃነትን ከኃላፊነት ጋር ይሰጣቸው ስለነበር ወንድሟቸው የጣለባቸውን እምነት እንዲያከብሩ፣ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ እንዲያስቡ፣ ውሳኔዎችን ራሳቸው እንዲወስኑ፣ በሌሎች ላይ ጥገኛ እንዳይሆኑ እና በኃላፊነት ስሜት እንዲንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል። ይህ አስተዳደጋቸው ከሁሉም በላይ ለራስ ክብር መስጠት እንደሚገባና ይህንንም ለማሳካት ታማኝና ሐቀኛ መሆን እንደሚያስፈልግ እንዳስተማራቸው ይናገራሉ።

አምባሳደር ቆንጂት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከታላቅ እህታቸው ጋር ወደ እንግሊዝ አገር ተጓዙ። ከዚያም በለንደን የጽህፈት ት/ቤት ገብተው በጣም ፈጣን የአጽርኦተ-ጽሁፍ(ሾርት ሃንድ) ፀሐፊና ታይፒስት ሆኑ። ነገር ግን ይሄ ስራ ከሳቸው ህልም ጋር እንደማይሄድ ደምድመው ራሳቸውን በትምህርት ለማሳደግ ቆርጠው ተነሱ። በታዋቂው በለንደን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ዓለም አቀፍ ግንኙነትም ማጥናት ጀመሩ። የዓለም አቀፍ ግንኙነት ኮርሶችን እየወሰዱ ስለ አለም አቀፍ ተቋማት በተለይም ስለተባበሩት

መንግስታት በርካታ መጻሕፍትን ያነበቡ ሲሆን በድርጅቱ ልዕለ ሀሳቦችም በእጅጉ ይደነቁ ነበር። እንዲህ እንዲህ እያሉም እኤአ በ1954 እንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው ከለንደን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በአለም አቀፍ ጉዳዮች የመጀመሪያ ዲግሪያቸዉን አግኝተዋል።

ትምህርታቸውን በእንግሊዝ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በወቅቱ የሥራ ምደባ ወደሚካሄድበት ቢሮ በመሄድ የተማሩት ዓለም አቀፍ ግንኙነት ስለሆነ መሥራት የሚፈልጉት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ መሆኑን ማመልከቻ ቢያስገቡም የውጭ ጉዳይ ስራ "ለሴት የሚሆን ቦታ አይደለም" የሚል ምላሽን ነበር ያገኙት። በምላሹ ቢደነግጡም በተለመደው አይበገሬነታቸው ገፉበት በየቀኑ ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እየሄዱ ይሟገቱ ጀመር። ከብዙ ትግል በኋላ የውጭ ጉዳይ ሃላፊዎች "ይቺ ልጅ አልለቀቀችንም፤ ደብዳቤ ተጽፎላት ትግባ" ተብሎ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ሕብረት) ከመመሥረቱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በ1954 ዓ.ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ሊቀላቀሉ በቁ።

አምባሳደር ቆንጂት መጀመሪያ የተመደቡት በሚኒስቴሩ የተባበሩት መንግሥታት ክፍል ውስጥ ነበር። ከሦስት ዓመታት በኋላ ዕድገት አግኝተው በሁለተኛ ፀሐፊ ማዕረግ ኒውዮርክ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ ልዑክ ጽሕፈት ቤት ውስጥ እንዲሰሩ ተመደቡ። ነገር ግን አሁንም ፈተናዎች ተከትለዋቸው መጓዛቸው አልቀረም። ምንም እንኳ እሳቸው በዋና የዲፕሎማሲ ሥራ መስማራት ቢፈልጉም፣ መጀመሪያ የተሰጣቸው መደብ የየለት አስተዳደርዊ መደብ ነበር። ነገር ግን ከብዙ ትግል በኋላ ቀድሞውኑ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተመደቡበት የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ቅኝ ግዛት ኮሚቴ ውስጥ ለአምስት አመታት በኒውዮርክ አገልገለዋል።

ከአምስት ዓመታት የሥራ ቆይታ በኋላ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አሰራር ተስፋ መቁረጥ ጀመሩ። እሳቸው እንደሚሉት የተባበሩት መንግስታት ውስጥ ብዙ ይወራል እንጂ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ተፈፃሚነት ወይም ውጤታማነት ለመገምገም እምብዛም ዕድል የለም። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ጥያቄ አቀረቡ። ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ለ10 ዓመታት ያህል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ገለልተኛ አገራት መምሪያ ውስጥ ሠሩ። በነዚህ አመታትም ንብረታቸው በደርግ የተወረሰባቸውን ቤተሰቦቻችውን የማስተዳደር ሃላፊነት ነበረባቸው።

ከዚያም የደርግ አገዛዝ ጠንካራ አፈና በቀነሰበት 1970ዎቹ፣ በጄኔቫ የተባበሩት መንግስታት ቢሮ ቋሚ የኢትዮጵያ ልኡክ ምክትል ቋሚ ተወካይ ሆነው ተመደቡ። በዚህ ኃላፊነት ለ10 ዓመት ከሰሩ በኋላ፣ በ1980ዎቹ በአምባሳደርነት ደረጃ በመሾም በጄኔቫ የተባበሩት መንግስታት ቢሮ ቋሚ የኢትዮጵያ ተወካይና የኦስትሪያ አምባሳደር ሆኑ።

ይሄ ሹመት የመጣው ከ28 ዓመታት የዲፕሎማሲ አገልግሎት በኋላ ነበር። በመቀጠልም ከመጋቢት 1984 ዓ.ም ጀምሮ በካናዳ፣ በሜክሲኮና በእሥራኤል የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው እስከ ነሐሴ 1987 ዓ.ም ድረስ ሠርተዋል። ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ሕብረት) የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው እንዲሠሩ ተሹመው ነበር።

ከአንድ ዓመት በኋላ በግብጽ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው ተሹመው ከአራት ዓመታት በላይ አገልግለዋል። ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ለሁለተኛ ጊዜ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የአፍሪካ ጉዳዮች ጄኔራል ዳይሬክተር ሆነው እንዲሠሩ ተሹመው ሠርተዋል።

በ1998 ዓ.ም በኦስትሪያ ፌዴራል ሪፐብሊክና በቪየና በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው እንዲሠሩ በድጋሚ ተሾሙ። ከመስከረም ወር 2002 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በክብር በጡረታ እስከተሰናበቱበት ድረስ በአፍሪካ ሕብረት (African Union) እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) የኢትዮጵያ ቋሚ ተወካይና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው አገራቸውን በትጋት አገልግለዋል። አምባሳደር ቆንጂት በአፍሪካ ሕብረት የኢትዮጵያ ቋሚ ተወካይና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር በነበሩበት ወቅት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቋማዊ ለውጥ እንዲያመጣና አወቃቀሩም የተቋሙን ዓላማዎች በሚያሳካ መልኩ እንዲደራጅ እና ወደ "የአፍሪካ ሕብረት" እንዲለወጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የአፍሪካ ሕብረት በኅዳር ወር 2008 ዓ.ም ለአምባሳደር ቆንጂት ደማቅ የስንብትና የምስጋና መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ሽኝት አድርጎላቸዋል፤ አመስግኗቸዋል። በወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር የነበሩት ንኮሳዛና ድላሚኒ ዙማ በስንብት/ምስጋና መርሐ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር “ ... አምባሳደር ቆንጂት ከአፍሪካ ምርጥ ሴት ልጆች መካከል አንዷ ናቸው። አምባሳደር ቆንጂት አገራቸውንና አህጉራቸውን ከልብ የሚወዱ ዲፕሎማት ናቸው” በማለት አምባሳደሯ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ጭምር የታገሉ አንጋፋ ባለውለታ እንደሆኑ መስክረዋል። ከዚህ በተጨማሪም አምባሳደር ቆንጂት በቀጣይ ጊዜያት ተዝቆ በማያልቀው የካበተ የዲፕሎማሲ ልምዳቸው የአፍሪካ ሕብረትን በምክር እንዲያግዙም ሊቀ መንበሯ ጠይቀዋቸው ነበር።

በጊዜው በአፍሪካ ሕብረት የኡጋንዳ አምባሳደር የነበሩት ሙል ሰቡጃ ካቴንዴ በበኩላቸው፤ አምባሳደር ቆንጂት ለአገራቸው፣ ለአህጉራቸውና ለሙያቸው የተለየ ፍቅር ያላቸውና ልዩ የሆኑ አንጋፋ ባለሙያ እንደሆኑ ተናግረው ነበር። በወቅቱ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር የነበሩት ብሪዢት ኮሌትም አምባሳደር ቆንጂት ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ላበረከቱት አስተዋጽኦ አድናቆታቸውን ገልፀውላቸዋል።

በሩስያ የዚምባብዌ አምባሳደር ማይክ ኒኮላስ ሳንጎ አምባሳደር ቆንጂትን “አንጋፋ አርበኛ፣ ዲፕሎማትና ሁለ ገብ ሰው ... ሁላችንም ልንደርስበት የምንመኘው አስደናቂ ደረጃ ላይ የደረሱ ጠንካራ ሴት” በማለት ገልፀዋቸዋል።

አምባሳደር ቆንጂት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን እንዲሻሻል በተለይም የአፍሪካ አዳራሽ (Africa House) ተብሎ የሚታወቀው የኮሚሽኑ ክፍል አፍሪካዊ ማንነትን የሚያንፀባርቅ ሙዚየም እንዲሆን የተጫወቱት ሚና የሚዘነጋ እንዳልሆነ የኮሚሽኑ የቀድሞው ዋና ጸሐፊ ካርሎስ ሎፔዝ ተናግረዋል።

የቀድሞው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የአሁኑ የዓለም ጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴድሮስ አድሓኖም “ ... አምባሳደር ቆንጂት ወደ 53 ዓመታት በተጠጋው አገልግሎታቸው ሕዝብን በማገልገል ስለሚገኝ ክብርና ኩራት አስተምረውናል። በረጅም ዓመታት አገልግሎታቸውና በካበተ ልምድ ባለቤትነታቸው ምክንያት “የአፍሪካ ጉዳዮች ኢንሳይክሎፒዲያ (Encyclopedia of African Affairs) እንላቸዋለን። አፍሪካ በዲፕሎማሲው መስክ ወደፊት እንድትራመድ በትጋት ሲሠሩ የኖሩ ጠንካራና ልዩ ሰው ናቸው ...” በማለት ስለአምባሳደር ቆንጂት አበርክቶ ተናግረዋል። ለ52 ዓመታት ከ10 ወራት ያህል ኢትዮጵያንና አፍሪካን በትጋት ያገለገሉት የዲፕሎማሲዋ እናት አምባሳደር ቆንጂት ይህን ያህል ጊዜ አገልግለው እንኳ አሁንም ለተጨማሪ ዓመታት ቢያገለግሉ ደስታቸው ነው። ለዚህም ነው የአፍሪካ ሕብረት በኅዳር 2008 ዓ.ም ባዘጋጀላቸው የስንብትና የምስጋና መርሐ ግብር ላይ “ ... ወዳጆቼ ኢትዮጵያና አፍሪካ ታላቅ ግስጋሴ እያደረጉ በሚገኙበት በዚህ ጊዜ በሚከናወኑ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ ስል የጡረታ ጊዜዬ ባይደርስ ጥሩ ነበር የሚል ምኞት አድሮብኛል ...” በማለት ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ባስቆጠረው አገልግሎታቸው ላይ ተጨማሪ ዓመታትን ቢቆዩ ፍላጎታቸው እንደነበር የተናገሩት።

አምባሳደር ቆንጂት ለረጅም ዓመታት አገልግሎታቸው ሽልማቶችን አግኝተዋል። ለአብነት ያህል በጥር ወር 2011 ዓ.ም ለረጅም ዘመናት የዲፕሎማሲ አገልግሎታቸው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ የምስጋናና የእውቅና ሰርተፊኬት ተቀብለዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2008 ዓ.ም የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል።

አምባሳደር ቆንጂት ከጸሃፊነት እስከ ሙሉ አምባሳደርነት ኢትዮጵያን በተለያዩ ቦታዎች ወክለው ያገለገሉ ትጉህ እና ለመላው አፍሪካውያን ተምሳሌት ናቸው።አምባሳደር ቆንጂት ለራሳቸው ባደረጉት ትግል ሴቶች በዚህ የሙያ ዘርፍ ተወስኖ የተቀመጠላቸውን የገደብ ጣራ ገፍተውታል።

በሳቸው ጥረት በ አለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ የተሰማሩ ወንዶችና ሴቶች በእኩል ደረጃ መፎካከር ችለዋል። በመሰናክሎች የተሞላውን የሙያ ዘርፍ በድል ተወጥተው ለስኬት የበቁት ለምንም ነገር አይበገሬ ስለሆኑ ነው። የሚገባቸውን ዕድገት ለማግኘት በእጅጉ ከተፋለሙና ከሥራው ውጭ ያሉትን ነገሮችን ትዳርን ጨምሮ መስዋዕት እያደረጉ ነበር። በአስተዳደር አከባቢ ሴት ልጅ ማግባትና ልጆች መውለድ ከዚያም ሥራዋን መልቀቅ አለባት የሚል ሥር የሰደደ እምነት ስለነበር ቆንጂት አለቆቻቸው ሴት በመሆናቸው ብቻ እድገት አትጠብቅም ብለው እንዳያስቡ፣ ፈጽሞ በዝምታ አያልፉም ነበር። አምባሳደር ቆንጂት ባገኙት መድረክ ሁሉ ለዛሬ ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ራሳቸውን ማስተማር ከዚያም በመረጡት ሥራ ተግተው መስራት እንዳለባቸው እና መሰናክሎችን እንዴት እንደሚያስወግዱና ህልማቸውን የማሳካት ጉዟቸውን እንደሚቀጥሉ ማወቅ አለባቸው በማለት ይመክራሉ።

# ታደለች ኃይለሚካኤል (አምባሳደር)



አምባሳደር ታደለች ኃይለሚካኤል የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ታጋይ፣ የመጀመርያዋ የሴቶች ጉዳይ ሚንስቴር ሴት ሚኒስትር እና ኢትዮጵያን ወክለው በተለያዩ ሃገራት አምባሳደርነት ያገለገሉ የጥንካሬ ምልክት ናቸው። አምባሳደር ታደለች ኃይለሚካኤል በመሃል አዲስ አበባ ፒያሳ ነው የተወለዱት። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሊሴ ገብረ ማርያም እና ልዕልት ዘነበወርቅ ትምህርት ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት አጠናቀዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአንድ አመት ከቆዩ በኋላ በ1963 ዓ.ም ወደ ስዊዘርላንድ አገር በፍሪቦርግ ስቴት ዩኒቨርስቲ የታሪክ እና የጋዜጠኝነት ሙያ ትምህርት ለመከታተል አቅንተው ነበር።

ታደለች በስዊዘርላንድ አንድ አመት በትምህርት ከቆዩ በኋላ ነበር ሀገር ቤት የሸኙትን የፖለቲካ ሂወት የጀመሩት። እርሳቸው እንደሚሉት በስዊዘርላንድ የመጀመሪያ ዓመት ቆይታቸው ሙሉ ትኩረታቸውን ለትምህርታቸው ሰጥተው ስለነበር በ አውሮፓ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ለመቀላቀል ብዙ ጊዜ ወስዶባቸዋል። በተማሪዎች እንቅስቃሴው ለመሳባቸው ዋነኛ ምክንያቶች የነበሩት ደግሞ በአጋጣሚ መንገድ ላይ የተዋወቋቸው የንቅናቄው ተሳታፊዎች ተስፋዬ ደበሳይ እና አክሊሉ ኅሩይ ናቸው። ኢህአፓ ሲቋቋም ከመስራቾቹ አንዱ ለመሆን የበቃው ተስፋዬ ደበሳይ፤ በታደለች ህይወት ጉልህ ስፍራ ለሚይዝ ሌላ ክስተት መንስኤም ሆኗል።

ተስፋዬ በስተኋላ የታደለች የትዳር እና የትግል አጋር የሆነውን ብርሃነመስቀል ረዳን ከታደለች ጋር በማስተዋወቅ፤ ሶስት ልጆችን ያፈራው ጥምረት እንዲወለድ ምክንያት ሆኗል። ብርሃነመስቀል ረዳ በስደት ከሚኖርበት አልጄሪያ ወደ ስዊዘርላንድ በመጣበት ወቅት፤ ምስጢር ለመጠበቅ ታስቦ በተማሪዋ ታደለች ቤት እንዲያርፍ መደረጉ ነበር ትውውቁን የወለደው። በአጋጣሚ የተጀመረው ግንኙነት ወደ ፍቅር አድጎ እስከ ትዳር ብሎም በመርሃ ቤቴ እና መንዝ የትጥግ ትግል እስከመታገል ተጉዟል። የኢህአፓ የገጠር ውስጥ ትጥቅ ትግል ሲያይል አምባሳደር ታደለች ስዊዘርላንድን በመተው ከባለቤታቸው ጋር በመሆን በግዜው የነበረውን ወታደራዊ መንግስት በሀይል ለመታገል ኢትዮጵያ ይገባሉ። ብዙ ሳይቆዩ ሁለቱም በወታደራዊው መንግሰት ተይዘው ለእስር ከተዳረጉ በኋላ ብርሀነመስቀል ረዳ ሲገደል ታደለች ኃይለሚካኤል ለአስራ ሶስት አመታት ገደማ በእስር ቤት ቆይተዋል። ሶስተኛ ልጃቸውንም የወለዱት በማረሚያ ቤት ሳሉ ሲሆን በዚያው ማረሚያ ውስጥ በሚገኝ ትምህርት ቤት የታሪክ መምህር በመሆን አገልግለዋል።

ከእስር ከተፈቱም በኋላ የመጀመሪያዋ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በመሆን ለ11 ዓመታት እንዲሁም በባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርነት በኮትዲቯር እና በፈረንሳይ ለስምንት ዓመታት አገልግለዋል። አምባሳደር ታደለች የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን በመሩበት ዘመን ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር መስሪያቤቱን በማደራጀት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አማካሪ ቀጥሮ ባስጠናው ጥናት ግኝት ላይ በመመርኮዝም አምባሳደር ታደለች ሴቶች በተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሴቶች ኃላፊ ሆነው መሾም አለባቸው በማለት መንግስት ላይ ተጽእኖ ሲያደርጉ ነበር። ነገር ግን መንግስት በተጠቀሱት ኃላፊነቶች ቦታዎችን ለመያዝ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሴቶች የሉም በሚል ታደለች ያቀረቡትን ምክረ ሃሰብ ውድቅ አድርጎ ነበር። አምባሳደር ታደለች ግን አስቀድመው ብቃት የነበራቸውን ሴቶች መልምለው ስለነበር መንግስት ጥያቄያቸውን ሊቀበል ችሏል። በየመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ ብቁ ሴቶች ኃላፊ ሆነው መሾማቸውን ካረጋገጡም በኋላ፣ የሴቶች ኃላፊዎችን አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን እንዲያገኙም አደርገዋል።

አምባሳደር ታደለች ሴቶች፣ ሕፃናት እና አካል ጉዳተኞች እንደ አናሳ ተቆጥረው በአንድ ምድብ ውስጥ መፈረጅ የለባቸውም "ሴቶች አናሳ አይደሉም፣ ይልቁንም የህዝቡ ግማሽ ያህሉ ናቸው" የሚለውን ሃሳብ በማራመድ ይታወቃሉ።

ከሴቶች መብት እና ተጠቃሚነት አኳያ ካበረከቷቸው አስተዋጽዖዎች መካከል ለአስር አመታት በስራ ላይ የቆየውን የሴቶች ልማት ፈንድ እንዲቋቋም አድርገዋል፤ እንዲሁም የመጀመሪያው ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ እንዲጸድቅ ያበረከቱት አስተዋፅኦ የሴቶችን ችግሮች ወደ ፖሊሲ ጠረጴዛ ለማምጣት መሰረት የጣሉ ናቸው።

አምባሳደር ታደለች በ1987 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚቴ ውስጥ ሴቶች አባላት እንዲኖሩበት ተነሳሽነቱን በመውሰዳቸው፤ የሴቶችና ሕፃናትን መብትን የሚያረጋግጡ ጠንካራ ድንጋጌዎች እንዲወጡ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል። በተጨማሪም የነበራቸውን መልካም ግንኙነትን ተጠቅመው በፈረንሳይ አገር የሚገኙ አምስት ከተሞች ከአዲስ አበባ ጋር እህት ከተሞች እንዲሆኑ አስችለዋል ይህም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መጠናከር አስተዋፅኦ ማደረጉን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

አምባሳደር ታደለች በቅርቡ ደግሞ "የአፍሪካ ሴቶች ሰላምና ደህንነት ተቋምን" አቋቁመዋል። የአፍሪካ ሴቶች ሰላምና ደህንነት ተቋም በአምባሳደር ቆንጂት ሥነጊዮርጊስ እና አምባሳደር ታደለች ኃይለሚካኤል ጠንሳሽነት በ2015 ዓ.ም. የተቋቋመ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅት ነው። እንደ ስያሜው በሰላምና ደህንነት ላይ ከሀገርም አልፎ የአህጉራችንን ሴቶች ኢላማ ያደረገ ግብ ያለው ነው። የተቋሙ ቀዳሚ ተግባር ሴቶች በየትኛውም ሀገራዊ ብሎም አህጉራዊ ሰላምን በማስጠበቅ፣ ግጭትን በመፍታት፣ ሰላምን በመገንባት ወዘተ ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ማብቃት፣ ማመቻቸትና ማገዝ ነው።

በ 2012 ዓ.ም አምባሳደር ታደለች "ዳኛው ማን ነው?" የተሰኘ መጽሃፍ ያሳተሙ ሲሆን በንቃት ስለተሳተፉበት ትግል፣ በፅናት ስለተቀበሉት የመከራ ዘመን፣ ለእምነትና ለፍቅር ስለከፈሉት መስዋዕትነት የሚያወሳ ድርሳን ነው። የአምባሳደር ታደለች የህይወት መንገድ በአላማ መፅናትን፣ ሀቀኝነትን፣ ሰብዓዊንትን ለአሁኑ ትውልድ ባያሌው ያስተምራል።

## ክብርት ሎሚ በዶ



የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ ከመስከረም 2014 ዓ.ም ጀምሮ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን እያገለገሉ ያሉ የፖለቲካ አመራር ናቸው። ክብርት ወ/ሮ ሎሚ በዶ በትምህርት ዝግጅታቸው የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በህግ እንዲሁም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአመራርነት (Leadership) አግኝተዋል። የሥራ ልምዳቸውን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ዕርከኖች በአመራርነት ያገለገሉ ሲሆን በወረዳ ዋና አፈ ጉባኤነት ፤ በወረዳ ዋና አስተዳዳሪነት እንዲሁም በክልል ደረጃ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ሲያገለግሉ ከነዚህ ውስጥ የኦሮሚያ ክልል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ፤ የኦሮሚያ የንግድ ቢሮ ሃላፊ ፤ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ ሆነው አገልግለዋል።

በ1997 ምርጫ ተወዳድረው የዱግዳ መቂ ምርጫ ክልል ሕዝብን በመወከል ከ1998 – 2002 ዓ.ም ድረስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እና የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል በመሆን ከምክር ቤት አባልነት በኋላም የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባል የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልና የሕገ መንግስትና ማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነበሩ። ከዚህም በተጨማሪ የህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ አባል ፤ የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ፤ ለሁለተኛ ጊዜ የዱግዳ መቂ ምርጫ ክልል ሕዝብን በመወከልም ከመስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እና ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

ክብርት ወ/ሮ ሎሚ የወጣት ሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሥልጠናዎችን በመስጠት እና ልምዳቸውን በማጋራት አርአያ ለመሆን ችለዋል።

## መዓዛ አሸናፊ



መዓዛ አሸናፊ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመርያዋ ሴት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የመጀመሪያውን የሴቶች ባንክ በማቋቋም ለአምስት ዓመታት ያህል የቦርድ ሰብሳቢ እንዲሁም የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር መስራች ናቸው። የኢትዮጵያ ህገ መንግሥት፣ የቤተሰብ፣ የወንጀል፣ የጡረታና የዜግነት ህጎች ሴቶችን አግላይ በመሆናቸው ሊሻሻሉ ይገባል በሚሉ ዘመቻዎች፤ የሴቶችን መዋቅራዊ ጥያቄ እና ድርብርብ ጭቆናዎች ወደ ፖለቲካ ተዋስኦ በማምጣትና ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የሴቶችን መብት ማስከበር ላይ የላቀ አስተዋጽዖ አበርክተዋል።

ስመጥር የሴቶች መብት ተሟጋቿ መዓዛ አሸናፊ በሀምሌ ወር 1956 ዓ.ም በአሁኑ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ተወለዱ። ወይዘሮ መዓዛ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያገኙ ሲሆን፥ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ከአሜሪካው ኬንት ዩኒቨሪሲቲ በአለም አቀፍ ግንኙነት አግኝተዋል።

መዓዛ አሸናፊ በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል። በአገር ውስጥ ከ1982 እስከ 1985 ዓ.ም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ሰርተዋል።

በ1986 በኢትዮጵያ የህገ- መንግሥት ኮሚሽን ውስጥ በህግ አማካሪነት ከሰሩ በኋላ፤ በ1987 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበርን በመመስረት የመጀመሪያዋ ዋና ዳይሬክተር በመሆን መርተዋል።

ከዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ውስጥ በሴቶች እና ህጻናት መብቶች በህግ አማካሪነት ለስድስት ዓመታት አገልግለዋል። ኢንተር አፍሪካ በሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ዳይሬክተር ሆነው ሰርተዋል። በአፍሪካ ቻይልድ ፖሊሲ ፎረም ውስጥ ደግሞ በአማካሪነት፤ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በአፍሪካ ህብረት አማካሪ በመሆን አገልግለዋል።

የ መአዛ አሸናፊ ፍትህ በትር ብዙ እምባዎችን አብሷል። ከሚታወቁባቸው የችሎት ሜዳዎች መካከል አንዱ በ1996 ዓ.ም. የተካሄደ የፍ/ቤት ክርክር ላይ የሰጡት የነጻ ጥብቅና አገልግሎት ነው። የችሎቱ ጉዳይ አበራሽ በቀለ የተባለች በወቅቱ የ14 አመት ታዳጊን የሚመለከት ነበር። አበራሽ በወቅቱ በፍ/ቤት ተከሳ የነበረ ሲሆን የተከሰሰችበትም ክስ ጠልፎ የደፈራትን ግለሰብ ራሷን ለመከላከል ባደረገችው ጥረት በመግደሏ ነበር። ታዳጊዋ አበራሽ በተከሰሰችበት ወቅት መዓዛ ጠበቃዋ በመሆን በፍ/ቤት ሙግት አበራሽ ነጻ እንድትወጣ አስችለዋታል። ጉዳዩ የዓለምን ትኩረት ስቦ በኢትዮጵያ ያለውን የተንሰራፋ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መደፈር እና መሰል ጾታዊ ጥቃቶችን አጉልቶ አሳይቷል። የኋላ ኋላም ይህ የፍ/ቤት ጉዳይ 'ድፍረት' ወደሚባለው ፊልም ተቀይሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተመልካቾች ቀርቧል። እውቋ ተዋናይት አንጀሊና ጆሊ ዋና ፕሮዲዩሰር ሆና የተሳተተፈችበት ይህ ፊልም በ "Sundance" የፊልም ፌስቲቫልም በ "Dramatic Audience Award" በሚለው ምድብ ለማሸነፍ ችሏል። የሴቶችን ውክልና ለማሳደግ በተነሳው የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የፖለቲካ ማሻሻያ ሂደት ውስጥ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው በህዳር 2011 ዓ.ም ተሾመው ነበር። በዚህ ሹመትም መዓዛ በኢትዮጵያ የፍ/ቤቶች ታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዜዳንት ሆነው ለማገልገል በቅተዋል።

መዓዛ አሸናፊ የችሎት ንግስት ናቸው። በተለይም የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ህጎች እንዲቀረፁ በማድረግ በኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓት አሻራቸውን በጉልህ አኖረዋል።

በአገር ውስጥ እና በአፍሪካ ደረጃም እንደ እሳቸው ካሉ ለሴቶች መብት ከቆሙ የሰብዓዊ መብት ሞጋች ሴቶች ጋር በመሆን የሴቶች እኩልነትን የሚያረጋግጡ ህጎች እንዲቀረፁ በማድረግም ስኬታማ ናቸው። የኢትዮጵያ ሴቶች ፍትሕ ለማግኘት የሚያደርጉትን ተጋድሎ በመደገፍ፣ የዳኞች ነጻነትን በማረጋገጥ እና ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ እንዲሆኑ እና ህዝባዊ አመኔታ እንዲጎናጸፉም በብርቱ ደክመዋል።

መዓዛ ላበረከቱት ከፍተኛ የአመራርና የበጎ አድራጎት አስተዋጽኦና ላስመዘገቡት ስኬት በርካታ ሽልማቶችን ተቀዳጅተዋል። ለአብነት ያህልም የአፍሪካ የአመራር ሽልማት፣ የ"Hunger Project" ሎሬት፣ በአፍሪካ ደረጃ የሚሰጠውን የኢትዮጵያ ባለተሰጥኦ እንስት ሽልማት ያገኙ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ2005 ለኖቤል የሰላም ሽልማት ታጭተው የነበሩ ስኬታማ ኢትዮጵያዊ ናቸው። መዓዛ "ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደ ችሎት" ይሉትን ብሂል የሰባበሩ የፍትህ እመቤት፣ የችሎት አርበኛ የሴቶች መብት አምባሳደር እና የብዙ ሴቶች አርአያ መሆን የቻሉ ስኬታማ እንስት ናቸው።

# ኤርጎጌ ተስፋዬ (ፒ.ኤች. ዲ)



በ 1978 አ/ም በሆሳዕና ከተማ የተወለዱት ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ በትምህርት ዘርፍ ከተሰማሩ ቤተሰቦች የተገኙ ናቸዉ፡፡ ዶ/ር ኤርጎጌ በቤተሰቦቻቸዉ ዝዉውር ምክንያት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን በሆሳዕናና በአዲስ አበባ ከተሞች ከተከታተሉ በኋላ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመከታተል ችለዋል፡፡

በመሆኑም የባችለር ዲግሪያችዉን በዉጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፡፡ማህበረሰብን ማገልገል የጀመሩት ገና የመጀመሪያ ዲግሪያቸዉን እንደያዙ ሲሆን ለዚህም የአባታቸው ምክር ቀላል ሚና እንዳልነበረው ይናገራሉ፡፡ ዶ/ር ኤርጎጌ ገጠር በሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በእንግሊዘኛ መምህርነት

አገልግለዋል፡፡ ምንም እንኳ የተዛባ ስርዓተ ፆታ አመለካከት የሰፈነበት ማህበረሰብ ዉስጥ ቢያድጉም ሴትነታቸው የፈለጉትን ከመሆንና የፈለጉበት ከመድረስ እንደማያግዳቸው እየተነገራቸዉ እንዳደጉ ይናገራሉ፡፡ የዶ/ር ኤርጎጌ በመምህርነት በቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ ከማገልገላቸው ባሻገር በአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን

በግብርናና ስርዓተ ፆታ ክፍል በትርፍ ጊዜ ያገለግሉ ነበር፡፡ የትምህርት ጉዞአቸዉንም በመቀጠል ሁለተኛ ዲግሪያቸዉን በስርዓተ ፆታ እንዲሁም ሶስተኛ ዲግሪያቸዉን በሶሻል አንትሮፖሎጂ ህንድ ሀገር ከሚገኝ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፡፡ የመመረቂያ ጽሁፋቸዉም ፖለቲካ አንትሮፖሎጂ በተለይም በኢትዮጵያ የብሄር ግጭት አፈታት ላይ በማተኮር ሰርተዋል፡፡

የተለያዩ ግጭት አፈታት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን እንደ አፍሪካ ህብረት እና የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ለመሳሰሉ ተቋማት ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡ የግል የስልጠና ተቋምም አቋቁመው በመምራት ለግለሰቦችና ድርጅቶች የአመራር ክህሎት፣ ቋንቋና የኮምፒዩተር ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ቆይታቸው ወቅት ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላከል፣ ፍልሰተኝነትና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ከፍተኛ አስተጽኦ አበርክተዋል፡፡ ወደ ከፍተኛ የመንግስት ስራ ሃላፊነት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስተርነት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትርነት ሀገርን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ወሎ ዩኒቨርሲቲን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንና የተለያዩ የረድኤትና የልማት ተቋማትን በቦርድ አባልነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

# አረጋሽ አዳነ



አረጋሽ አዳነ ቀደምት የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ታጋይ እና የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት ፓርቲ ትግራይ ሥራ አስፈጻሚ አባል ናቸው። ተወልደው ያደጉት በትግራይ መዲና መቐለ ከተማ ሲሆን ያደጉትና ትምህርታቸውን የተከታተሉት ግን በአድዋ ከተማ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዛው በአድዋ ከተማ በሚገኘው ንግስተ ሳባ ትምህርት ቤት ተምረዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በሶሻል ወርክ ዘርፍ አግኝተዋል። በተማሩበት የትምህርት ዘርፍ በውጭ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ሰርተዋል። ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ የህዝቡ የድህነት ኑሮ እየተባባሰ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የችግሮቹ ምንጭ ዘውዳዊው የፖለቲካ ስርዓት እንደሆነ በማመናቸው ስርዓቱን ለመጣል ከተደራጁ ወገኖች ጋር ህብረት ፈጠሩ።

አረጋሽ በ1968 ዓ.ም ህወሓትን የተቀላቀሉ ሲሆን ድርጅቱ የደርግ ስርዓትን ለመጣል ባደረገው ብርቱ ትግል ውስጥ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። በተለይም ሴትነታቸው ሳይበግራቸው የሚያምኑበትን ነገር ያለአንዳች ስጋት በመናገርና ያንኑ ሃሳብ በማራመድ ረገድ በርካቶች በአርዓያነት ያነሷቸዋል። አረጋሽ በትጥቅ ትግሉ 16 ዓመታትን አሳልፈዋል። ከትግል በኋላ የህወሓት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበሩ። በሽግግሩ ወቅትም የትግራይ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳደር በመሆን አገልግለዋል። ከዚያም ደግሞ የትግራይ ክልል የምክር ቤት ጸኃፊና ሥራ አስፈፃሚ ነበሩ።

በ1992 ዓ.ም ምርጫ ተወዳድረው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነው ነበር። በኋላም በሚኒስትር ደረጃ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ሆነው ሰርተዋል። በ1993 ዓ.ም በህወሓት ውስጥ በተፈጠረው ልዩነት ምክንያት ከህወሓት ተሰናብተው ወጡ። እሳቸው ግን ዲሞክራሲና ፍትህ የሰፈነባትን ኢትዮጵያ ተገንብታ ማየት ስለነበር ህልማቸው ደማቸውን ካፈሰሱለትና ህይወታቸውን ከከፈሉበት የፖለቲካ ድርጅታቸው መሰናበታቸው ተስፋ ሳያስቆርጣቸው ከሌሎች ተሰናባች ታጋዮች ጋር በመሆን “ህዝባዊ” የሚባል ጋዜጣ ማሳተም ጀመሩ። በዚህ ጋዜጣ ታዲያ በ17 ዓመት የትግል ሂደታቸው ብሎም መንግስት ከተመሰረተ በኋላ አሉ የሚሏቸውን ጉድለቶች እየፃፉ ያወጡ ነበር።  ይሁንና ጋዜጣው እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ እየታተመ ከቆየ በኋላ ታገደ።

ጋዜጣው ከታገደ በኋላ በ2002 ዓ.ም ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት ፓርቲን አቋቋሙ። በምርጫ 2002 ወቅትም ለህዝቡ አንድ አማራጭ ሆነው ነበር። በ 2002 ዓ.ም በተካሄደው በአራተኛው ጠቅላላ ምርጫ የቀድሞዋ ሕወሓት ታጋይ አረጋሽ አዳነ ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት ፓርቲ አባል የሆነበትን መድረክ የተባለ የፖለቲካ  ፓርቲን በመወከል፣ ከቀድሞ የትግል ጓዳቸው ከአቶ መለስ ጋር በ አድዋ ከተማ መፎካከራቸው አይዘነጋም። ታጋይ አረጋሽ በትግሉ ሂደት በጣሙን ተሳትፎ የነበራቸው ሴቶች ከድሉ በኋላ ያላቸው ተሳትፎም ሆነ ተጠቃሚነት ከትግሉ ሚናቸው አንጻር እጅጉን ያነሰ መሆኑ ይቆጫቸዋል። ከድል ማግስት በነበረው ሂደት ውስጥ ሴቶች የነበራቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ብዙ ደክመዋል። “ፍትሃዊ ስርዓት እስኪሰፍን ድረስ እታገላለሁ” የሚሉት ብርቱዋ አረጋሽ  ብዙ ወጣቶች ለፍትህ እና ለርትዕ እንዲታገሉ አነሳስተዋል።

## ብርቱካን ሚደቅሳ



ብርቱካን ሚደቅሳ የጽናትና ለሕግ ልዕልና የመቆም አርዓያ ተደርገው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚታዩ የሕግ ባለሙያ  እና የሰብዓዊ መብቶች ተቆርቋሪ ናቸው። በአገራችን የነበረውን የዴሞክራሲና የፍትሕ ዕጦት ለመታገልም የተፎካካሪ ፓርቲ አመራር በመሆን ታግለዋል። በዚህም ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። ብርቱካን ሚደቅሳ በ1967 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ የተወለዱ ሲሆን ሚያዚያ 23 የሚሽነሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኋላም የካቲት 12 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይን እቴጌ መነን ት/ቤት ተብሎ በሚታወቀው ተምረዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀዋል። እ.ኤ.አ. በ2014 ደግሞ ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ አስተዳደር ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪ አግኝተዋል።

በሥራው ዓለም በፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆንም ከ1989 ዓ.ም. እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ ድረስ ከመሥራታቸውም በተጨማሪ፣ ለእስር እስከተዳረጉበት ጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም. ድረስ ጠበቃና የሕግ አማካሪ ሆነው ሠርተዋል።

ብርቱካን በፖለቲካ ተሳትፏቸው ዕውቅና ከማግኘታቸው በፊት፣ በ1993 ዓ.ም. ታዋቂው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ታጋይና የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ፣ በሙስና ተጠርጥረው በተከሰሱበት የወንጀል ክስ በነፃ እንዲሰናበቱ በሰጡት የዳኝነት ፍርድ ታዋቂነትን አግኝተዋል። ይሁን እንጂ የዳኛዋ ውሳኔ ለአቶ ስዬ የሰጠው ነፃነት ከፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ እስኪወጡ ብቻ ነበር። የዳኛዋ ብርቱካን ውሳኔም በሌላ ውሳኔ እንዲቀለበስ ተደረገ። የተወሰደው ዕርምጃ ሕጋዊ ልባስ እንዲኖረው ሲባልም፣ በሙስና የተጠረጠረ የዋስትና መብት እንዳይኖረው የሕግ ማሻሻያ በቀናት ውስጥ በፓርላማው ፀደቀ። ውሳኔው በኢትዮጵያ የፖለቲካና የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ እስከ ዛሬ የዘለቀና መደብዘዝ ያልቻለ አሻራ እንዳለው ሁሉ፣ የብርቱካንንም ሕይወት ቀይሮታል። ይህ ክስተት ብርቱካን ወደ ፖለቲካ ትግል እንድትገባ ገፊ ምክንያት ቢሆንም፣ የፖለቲካ መንገድ ግን አልጋ ባልጋ አልሆነላትም።

ብርቱካን ከዳኝነት ወደ ፖለቲካ ስትዘልቅ የቀስተ ዳመና ፓርቲን በመቀላቀል ነበረ። ቀስተ ዳመና ፓርቲ ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ጋር ውህደት ፈጥሮ የውህዱ ፓርቲ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር እስከመሆን ደርሳ ነበረ። በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. በተደረገው ሦስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን በመወከል በአዲስ አበባ ተወዳድረው ማሸነፋቸውም አይዘነጋም። ነገር ግን ድህረ ምርጫውን ተከትሎ በተነሳ ግርግር መንግስት "ህገመንግስቱን በሃይል ለመናድ የተንቀሳቀሱ" ብሎ ካሰራቸው ፖለቲከኞች አንዷ ሆኑ።

ብርቱካን ለተከታታይ ሁለተ አመታት በቃሊት ማረሚያ ከታሰሩ በኃላ ከትግል አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ተፈቱ። ከእስር በኃላም በ2000 ዓ.ም አንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲን ፓርቲን መሰረቱ። የፓርቲውም ሊቀመንበር በመሆን በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት የፖለቲካ ፓርቲ ሊቀመንበር ለመሆን በቅተዋል። ያቋቋሙትን ፓርቲ በማጠናከር ሂደት ላይ ባሉበት ወቅት፣ በ2001 ዓ.ም በስዊድን ሀገር ያደረጉት "ቃሌ" በመባል የሚታወቀው መግለጫቸው በመንግስት ዘንድ ስላልተወደደ ወደ ሀገር ሲመለሱ እንደገና ታስረው ለሁለት አመታት እስር ቤት ቆይተዋል።

ብርቱካን ከእስር እንደተፈቱ ፖለቲካውን በመተው ወደ አሜሪካ ሄደው ስምንት ዓመታት ቆይተዋል። ከዚያም በ2011 ዓ.ም. በመንግሥት ጥሪ ወደአገር ቤት የገቡ ሲሆን በህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም. በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አቅራቢነት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሀላፊ በመሆን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አብላጫ ድምፅን በማግኘት ተመርጠው በፈቃዳቸው እስከለቀቁበት ሰኔ 2015 ዓ.ም ድረስ በኃላፊነት ቆይተዋል። የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው በሰሩባቸው አመታት የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ፣ ነፃ፣ በህግ የሚመራ ፣ ህግ የሚያከብርና በመርህ የሚሰራ እንዲሆን ጥረዋል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማሻሻያ ሂደት እና አጠቃላይ የተቋም ለውጥ ላይ ትልልቅ የለውጥ ጅማሮዎችን መርተዋል። በአገልግሎት ዘመናቸውም በ2013 ዓ.ም የተካሄደውን ስድስተኛውን ጠቅላላ አገራዊ ምርጫ፣ ሁለት ክልላዊ ህዝበ ውሳኔዎችን እና ድጋሚ ምርጫን በሰላም እና ተዓማኒነት ባለው መልኩ በማስፈጸም ረገድ የመሪነት ድርሻቸውን ተወጥተዋል።

ብርቱካን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በህግ ፊት በእኩል ዓይን መታየት አለበት፤ ህግ ሁሉንም የሚያስተዳድርና የሚገዛ መሆን አለበት የሚል ፅኑ አቋም ያላቸው እና ይህንንም ለህዝባቸው በተግባር ያረጋገጡ ሴት ናቸው።

ፍርድ ቤትን ባገለገሉበት ወቅት ባለመደለልና ባለመፍራት ፍትህን በማረጋገጥ የሚታወቁ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው። በኢትዮጵያ ታሪክ በተቃዋሚ ፓርቲ አባልነትም ሆነ በግል ተወዳዳሪነት ሴት ፖለቲከኞች ወደ አደባባይ በማይወጡበት ወቅት ምርጫ በመሳተፍ ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ፣ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ባህል ለማጎልበት፣ ለነጻነት እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የሚታይ አሻራ አሳርፈው ለብዙ ሴት ወጣት ፖለቲከኞች የጽናት አርአያ ሆነዋል።

## ሙፈሪሃት ካሚል



አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች ጉልህ ተሳትፎ በማይስተዋልበት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከመሳተፍ ባሻገር፣ ተጽዕኖ ፈጣሪም ጭምር መሆን የቻሉ ናቸው ሙፈሪሃት ካሚል። ሙፈሪሃት ካሚል በ1968 ዓ.ም በጅማ ከተማ የተወለዱ ሲሆን በ1992 ዓ.ም ከሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ በግብርና የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በትራንስፎርሜሽናል ሊደርሺፕ እና ለውጥ አመራር ሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም የሥርዓተ-ጾታ እና የልማት ጥናት የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ አግኝተዋል። ሙፈሪሃት ከ 1994 እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ህዝባቸውን ሲያገለግሉ የቆዩ ሲሆን ወደ ፖለቲካው ዘርፍ በጉልህ የተቀላቀሉት በ1999 ዓ.ም የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ተደርገው ከተሾሙ በኋላ ነው።

በ2000 ዓ.ም በቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በተቋቋመው ካቢኔ ውስጥ የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን የተሾሙ ሲሆን በዛን ወቅት እድሜያቸው 32 ነበር። ይህም በግዜው ከተመረጡት ሚንስትሮች በእድሜ ትንሿ ያደርጋቸዋል። ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለ ማርያም ደሳለኝ የማህበራዊ ጉዳይ አማካሪ ሚኒስትር በመሆን ያገለግሉ ሲሆን በ 2010 ዓ.ም ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በመሆን አገልግለዋል። ከ2011 እስከ 2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሰፊ እና ትልቅ የሚባለውን የሠላም ሚንስቴርን በሠላም ሚንስትርነት መርተዋል። ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚንስትር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

ሙፈርያት በተለያዩ መድረኮች ላይ ስለ ሠላም፣ ፍትህ፣ ስለወንድማማችነት በሚያደርጓቸው ንግግሮች የታዳሚውን ልብ በመንካት የሚታወቁ ሲሆን በተደጋጋሚ ያደረጓቸው ንግግሮች ታዳሚዎችን በእንባ ያራጩ ናቸው።

ክብርት ሙፈሪያት የሰላም ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት በስልጤ ማህበረሰብ ጥንታዊና ረጅም ታሪክ ትልቅ ክብር የሚሰጠው የጀግኒት (የጊስትነት) ማዕረግ ተበርክቶላቸዋል። ከስልጤ ቀደምት አባት ሀጂ አሊዬ ከአረብ ሀገር ወደ ስልጤ ምድር መጥተው ሲያርፉ አብረዋቸው የነበሩ አምስት ሴቶች መጠሪያ "ጊስቴ" የሚል የማዕረግ ስም መሆኑን ታሪክ ይናገራል። እነዚህም ጊስትት ጠህረት፣ ጊስቲት ሙሉካ ፣ጊስቲት ሽምስያ እና ሌሎችም ጊስቴ ተብለው ይጠሩ እንደነበር የታሪክ አዋቂ ሽማግሌዎች ይናገራሉ። ለዘመናት በነበረው የስልጤ ማህበረሰብ ታሪክ በክፈለ ዘመናቱ ለ5 እንስቶች ብቻ የተሰጠ ማዕረግ ሲሆን ክብርት ሙፈሪሃትም 6ኛ የክብር እንስት ሆነው 6ተኛዋ ጀግና እናት በሚል እውቀና ተሰጥቷቸዋል። ብዙ ታዛቢዎች እንደሚመሰክሩት ሙፈሪያት ካሚል ጠንካራ፣ ለእውነት የሚቆሙ፤ ሰው ሰው የሚሸቱ አመራር፣ ከተገፉ ሰዎች ጋር አብረው ሲያነቡ፣ ባልንጀሮቻቸው እርስ በርስ እየተናቆሩ ሲጎነታተሉ ታረቁ እያሉ በእንባ የሚማጸኑ እሩህሩህ ባለሥልጣን ብቻ ሳይሆኑ መልካም እናትም ናቸው።

ሙፈሪያት ካሚል ብዙ ሴቶች በማይሳተፉበት እና በ ኢትዮጵያ የ ተሳለበት መንገድ ትክክል አይደልም በሚባልለት የፖቲካ ዘርፍ በመሳተፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን የቻሉ እና ያሉባቸውን ግፊቶች በመቋቋም የ አይቻልምን አስተሳሰብ በመገርሰስ የ ይቻላልን መንፈስ በመሰነቅ ሴቶች በማንኛውም መስከ ውጤታማ ከመሆን የሚያግዳቸው እንደሌለ አብይ ማሳያ መሆን የቻሉ እንስት ናቸው።

## ዶ/ር ሊያ ታደሰ



ዶ/ር ሊያ ታደሰ የኮሮና ወረርሽኝ በነበረበት ግዜ ከስጋት ይልቅ ተስፋን፤ ከሞት ይልቅ ህይወትን፤ ከህመም ይልቅ ፈውስን የያዙ መልዕክቶች አንግበው የጤና ባለሙያዎችን አትግተው፤ ህሙማንና ቤተሰቦቻቻውን በማበረታታት ብዙ ኢትዮጵያውያን ያውቋቸዋል። በአዲስ አበባ ከተማ የተወለዱት ዶ/ር ሊያ ታደሰ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፅንስና የማህፀን ህክምና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ሁለተኛና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በህብረተሰብ ጤና አጠባባቅ ትምህርት ከጂማ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። የጤና ባለሙያ ከሆኑ ወላጆች የተገኙት ዶ/ር ሊያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምርታቸውን በምስካዬ ኅዙናን ትምህርት ቤት፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በእቴጌ መነን በከፍተኛ ማዕረግ አጠናቀዋል።

ዶ/ር ሊያ የጤና ሚኒስትር ሆነው ከመሾማቸው በፊት የአስተዳደር ችሎታ እንዳላቸው ያሳዩት በ1999 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተዘጋጀ የጤና ጉባኤ ላይ ባሳዩት ብቃት እንደሆነ ይነገርላቸዋል። ጉባኤው የኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሀኪሞች ማህበር ያዘጋጀው ጉባኤ ሲሆን በዚህ ስብሰባ ላይ ዶ/ር ሊያ አንድ የተደነቀ ጥናታዊ ፅሑፍ አቅርበው ነበር። ይህ መድረክ ዶ/ር ሊያን ወደ አስተዳደር ሥራ እንዲመጡ በር ከፈተላቸው።

ዶ/ር ሊያ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው ከመመደባቸው በፊት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሰርተዋል፤ በጤና ሚኒስቴር የብሔራዊ የጤና ፕሮግራም የጤና ትራንስፎርሜሽን ዋና ስልት ነዳፊ ሆነው አገልግለዋል። የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሆስፒታል ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም በጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲና በሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ የእናቶችና ህጻናት ጤና እንክብካቤ ሃላፊና የሥነ ተዋልዶ ጤና ስልጠና ዳይሬክተር ሆነው ሰርተዋል። በነዚህ ኃላፊነቶች ሲሰሩ በኢትዮጵያ ያሉትን የማህፀን ሀኪሞች ቁጥር ለመጨመር የስልጠና መርሃ ግብሮችን በማመቻቸት የሀኪሞችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ችለዋል። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልም አምስት ያህል አዳዲስ የትምህርት ክፍሎች እንዲከፈቱ ከማድረጋቸው በተጨማሪ የድንገተኛ ህሙማን ማስተናገጃና የእናቶችና የህፃናት የጤና ማዕከልን አቋቁመዋል። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ህክምና ፋክሊቲም ከ15 ከመቶ በታች የነበረውን የሴት ተማሪዎች ቅበላ ከ20 እስከ 30 በመቶ እንዲጨምር አድርገዋል። የአዳጊ ክልል ሴት ተማሪዎች ቅበላም ከሌሎች በተለየ መንገድ በማሳደግ የክልሎቹን የጤና አገልግሎት አሳድገዋል።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ ከመጋቢት 2012 ዓ.ም. እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም. ድረስ በጤና ጥበቃ ሚኒስትርነት ያገለገሉ ሲሆን ከዚያ በፊት ለ2 አመት የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው አገልገለዋል። በመላው ዓለም የጤና ስጋት የሆነው የኮረና ቫይረስ ወደ ሀገራችን መግባቱ ከታወቀበት ዕለት አንስቶ የጤና ሚኒስትሯ ዶ/ር ሊያ ታደሰ እረፍት አልነበራቸውም። ዜጎች በቫይረሱ እንዳይያዙና እንዳያልቁ የሚያሳስቡ መረጃዎችን በየዕለቱ ወደ መገናኛ ብዙሃን በማቅረብ ትጋታቸውን አሳይተዋል። አውሮፓውያንና አሜሪካውያን በኮቪድ ምክንያት በቀን ሶስት ሺ እና አራት ሺ ዜጎቻቸውን ሲቀብሩ በኢትዮጵያ ግን በዓመቱ ውስጥ የሞቱ ሰዎች ቁጥር በንጽጽር መጠነኛ ነበር። ይህ ሊሆን የቻለው የኢትይጵያን የጤና ዘርፍ በሚመሩት ሚኒስትር ትጋትና ባስተባበሯቸው የጤና ባለሙያዎች መስዋዕትነት ጭምር ስለመሆኑ ብዙዎች ያምናሉ።

ሚኒስትሯ በኮቮድ ሳቢያ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ከመመከት በተጨማሪ በሌሎች የጤና ዘርፎች ላይ መደረግ ያለባቸውን የንቅናቄ ሥራዎች በማስጀመርና ግንባር ቀደም መሪ በመሆን የሀገራችን ጤና አገልግሎቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አድርገዋል። እንደ አብነትም “ኤች.አይ.ቪ በደማቸው በሚገኝባቸው ወገኖችና ቤተሰቦቻቸው ላይ የሚደርስባቸውን ማግለል እና አድልዎ ለመቀነስ የሃይማኖት መሪዎች እና ተቋማት ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው በማመን ከሀይማኖት መሪዎች ጋር ተነጋግረዋል። በመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭት ዘርፍ ያለውን ክፍተት ለመሙላትም “አቀርባለሁ፣ አሻሽላለሁ፣ እጠየቃለሁ” በሚል መሪ ቃል /I supply/ በሚል የተሰየመው የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ የአስር አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ማስተግበሪያ ፕሮግራም አስተዋውቀዋል።

ጤና ተቋማቶች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የመከላከል ሥራውን ራሱን የቻለ ቦታ አዘጋጅተው ከመደበኛ ጤና አገልግሎቱ ጋር አጣምረው እንዲሰጡ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረትም የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር፣ የአይን፣ የአዕምሮና የቆዳ ምርመራና ህክምና መስጫ ማዕከላት ትኩረት አግኝተው እንዲተገበሩ የሚኒስትሯ ክትትል ከፍተኛ ነበር። ዶ/ር ሊያ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር በወሰዷቸው ወሳኝ እርምጃዎች በግንቦት 2013 ዓ.ም. ከሐርቫርድ ቲኤች ቻን የኅብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት የአመቱ ኔክስት ጄኔሬሽን ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ ከጥር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የሃርቫርድ የሚኒስትሮች አመራር ፕሮግራምን እየመሩ ነው። ዶ/ር ሊያ ታደሰ በጠንካራ ራዕያቸው እና ተነሳሽነታቸው በዓለም አቀፍ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ላይ የራሳቸውን አሻራ ያሳረፉ እንስት እና ለወጣት ሴቶች ታላቅ አራአያ ናቸው።

## አዳነች አቤቤ



አዲስ አበባ በከንቲባ መተዳደር ከጀመረችበት ከ1901 ዓ.ም. ጀምሮ የመጀመሪያዋ ሴት ከንቲባ  አዳነች አቤቤ ናቸው። በተለያዩ ሃላፊነቶች የሚታወቁት ከንቲባ አዳነች አቤቤ “ትርጉም ያለው ሕይወት የምንለው ለሌሎች አገልግሎት ሲኖር ነው” የ ሚለውን የ ማህተመ ጋንዲን አባባል እንደ ሂወት መርህ ይከተላሉ።

አዳነች አቤቤ የተወለዱት በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሲሆን በተወለዱበት ቤተሰብ ከሚገኙ ስድስት ልጆች መካከል ብቸኛዋ ሴት ልጅ ናቸው። የከንቲባ አዳነች ቤተሰቦች ለትምህርት ልዩ ትኩረት ይሰጡ ስለነበር አዳነች በትምህርታቸው ጎበዝ ነበሩ። የአዳነች አባት አቶ አቤቤ በአርሲ ዞን ኢሬቻ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተባለ ትምህርት ቤት አቋቁመው ነበር። ይህም ትምህርት ቤት በአካባቢው በጣም የታወቀ ሲሆን፤ ይህ እንዲሆን ያስቻለው በዛን ወቅት ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ከማስተማር ይልቅ በጋብቻ እንዲኖሩ የሚያስገድዱብት ወቅት ስለነበር ነው። ከዚህም በላይ አቶ አቤቤ በትምህርት ቤቱ ከወላጅ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን የመጀመሪያውን እርምጃ በመውሰድ ሌሎች ቤተሰቦችን በማነሳሳት የአካባቢው ነዋሪዎች ሴት ልጆጃቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ አድርገዋል።

ትምህርት ቤቱ በ1977 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ሴት ተማሪ ልጃቸው አዳነች አቤቤ ነበረች። አዳነችም በአባቷ ምክንያት ያለዕድሜ ጋብቻ ሳያስጋቸው በነፃነት ተምረዋል። በመጀመሪያ በትምህርት ቤቱ ከተመዘገቡ አምስት ልጃገረዶች አንዷ የሆኑት አዳነች የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ብቻቸውን መውሰዳቸው ይነገራል። በከፍተኛ ትምህርትም በ1993 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በዩናይትድ ኪንግደም ከግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ  ደግሞ በአመራርነት ሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል።

አዳነች የተለያዩ የሥራ ልምዶች አሏቸው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪ እና የትምህርት ቤት ዋና ዳይሬክተር በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፣ በኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ በአቃቤ ሕግነት፣ እንዲሁም በ1997 ዓ.ም. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነው ከተመረጡ በኋላ በተለያዩ ኃላፊነቶች አገልግለዋል።

በ1998 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርጠው የፓርላማው ጸሀፊ በመሆን ለአንድ አመት ከግማሽ በአገልግሎት ቆይተዋል። በወቅቱ በፓርላማው የሚታዩትን ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶች እና እኩይ ተግባራት በመንቀፍ በሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች አማካኝነት ከሥልጣን እንዲነሱ መደረጉን በአንድ ወቅት ተናግረዋል። ሆኖም ግን ይህን አለመግባባት እንደ መልካም አጋጣሚ ወስደው የሌላ ሀገር ፓርላማ መልካም አሰራር እና ተሞክሮን በመቅሰም ወደሀገራችን እንዲመጣ ብዙ አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ከዚያም በኦሮሚያ ልማት ማኅበር የዳይሬክተርነት ቦታ በመያዝ፣ ለስድስት ዓመታት መርተዋል።  በቀጣይም የአዳማ ከተማ ከንቲባ በመሆን ሰርተዋል። አዳነች የአዳማ ከተማ ከንቲባ በመሆን በሰሩበት የአስተዳደር ዘመን ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን መቀነስን ጨምሮ ከፍተኛ ለውጥ አስመዝግበዋል። ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉ ሲሆን። ከሁለት አመት ቆይታ በኋላ የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆነው ተሾመው ነበር።

ከመስከረም 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የአዲስ አበባ 32ኛ ከንቲባ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። አዳነች ከፖለቲካው ባሻገር በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች ይታወቃሉ። እዚህ የተጠቀሱት እና ሌሎችም ዘርፈ ብዙ ስራወቻቸው የትጋት ተምሳሌት ያደርጋቸዋል።

## ፍፁም አሰፋ (ፒ.ኤች. ዲ)



ዶ/ር ፍፁም አሰፋ የ2010 ዓ.ም የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ ወደ አመራር መድረክ ከመጡ ወጣት ሴት አመራሮች አንዷ ናቸው። በ1979 ዓ.ም. በቀድሞው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አለታ ወንዶ ከተማ የተወለዱት ፍጹም በልጅነት ዕድሜ ጉበዝ ተማሪ እና ለትምህርት ልዩ ፍቅር ነበራቸው። ፍፁም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ እና በልማት ጥናት አግኝተዋል። የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ ጀርመን አገር በሚገኘው ጊሴን ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና እና በግብርና ኢኮኖሚክስ አግኝተዋል።

ዶ/ር ፍፁም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከጨረሱ ማግስት ጀምሮ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እና በተመራማሪነት ከአስር አመታት በላይ አገልግለዋል። በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸዉም የአካውንቲንግ የትምህርት ክፍል ኃላፊ በመሆን፣ ከዚያም የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅን መዋቅር በመስራት ኮሌጁን በቦርድ በማጸደቅ በ ሌጅነት እንዲቋቋም ከፍተኛ አስተዋጸኦ አድርገዋል። በተጨማሪም በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲንነት፣ በተባባሪ ዲንነት አገልግለዋል።

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ የፕላን እና ልማት ሚኒስትር፣ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ፣ በገለልተኛ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት የመንግስት ተወካይ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቦርድ አባል በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። ዶ/ር ፍጹም የፕላን እና ልማት ሚንስትር አመራርነትን ከተረከቡ ጀምሮ በኢትዮጵያ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ታቅደው የሚጓተቱበትን ችግር ለመቅረፍ፣ ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ስርዓት ለመዘርጋት፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ስልትንና የተቋማዊ አሰራረን መሰረት ለመጣል እየተጉ ይገኛሉ።

ዶ/ር ፍጹም የአስር ዓመት የልማት ዕቅድን ከሚመሩት አንዷ ሲሆኑ ፣ የሚመሩት መስሪያ ቤት የመንግስት በጀት በአብዛኛው ሰው ተኮር የሆኑ መሰረተ ልማቶችን፣ መንገዶችን ፣ የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ተቋማትን በጥራት እንዲሰሩ ክትትል ያደርጋል። የሶስተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጥናታቸው የትኩረት መስክ የሆነው ፍትሃዊ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነትን ማስፋት አንዱ የሚመሩት መስሪያ ቤት ግብ ነው።

ዶ/ር ፍጹም “ከሃምሳ በ መቶ ዘመቻ” መስራች ሲሆኑ ዘመቻው ሴቶች በመንግስት ተቋማት ቦርዶች ውስጥ ቢያንስ ግማሹን የውሳኔ ሰጭነት ሚና መውሰድ አለባቸው የሚል ነው። እንደሀገር ለሴቶች የሚሰጥ መሪነት ብዙ ጊዜ ችሮታ ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም መሪነት ለሴት ልጅ ችሮታ ሳይሆን ችሎታ ነው። ይህንን ካስመሰከሩት አንዷ ዶ/ር ፍጹም ናቸው።

## አይሻ መሀመድ



አይሻ መሀመድ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን እምብዛም በማያሳትፈው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ ከቻሉ በጣት ከሚቆጠሩ የሴት ፖለቲከኞች ተርታ ይመደባሉ። አይሻ መሀመድ በአፋር ውስጥ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ አናሳ መሆንና የሴቶች የስራ መደራረብ ጫና ከፍተኛ መሆን በብዙ አሳስቧቸው ፖለቲካ ውስጥ ከገቡ ጥቂት የአፋር ሴቶች መካከል አንዷ ናቸው።

መሰረታዊና መዋቅራዊ የሆኑ የሴቶች ጥያቄዎች በፖለቲካዊ መንገድ እንዴት ይመለሳሉ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማፈላለግ፣ የአፋር ሴቶችን ትግል ወደፊት ለመግፋት፣ ማስተካከያም ለማምጣት የኢህአዴግ አንዱ አጋር ፓርቲ የነበረውን የአፋር ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲን ተቀላቀሉ። ወደ ማዕከላዊ ኮሚቴም በአባልነት የተቀላቀሉት ወዲያውኑ ነበር።

አይሻ የተወለዱት ሰሜን አፋር አካባቢ በምትገኘው በርሃሌ ከተማ ሲሆን አባታቸው በመንግሥት ሰራተኝነት አሰብ ወደብ ተቀጥረው ይሰሩ ስለነበር ብዙውን የልጅነታቸውን ግዜ አሰብ ነው ያሳለፉት። የመጀመሪያ ዲግሪ በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋካልቲ፣ የማስተርስ ዲግሪ በለውጥና ትራንስፎርሜሽናል ሊደርሺፕ ከግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ ኢንግላንድ አግኝተዋል።

ኢንጂነር አይሻ ከ1995-1996 ዓ.ም በአፋር ክልል በስራና ከተማ ልማት ቢሮ በዲዛይን ቡድን መሪነት፣ ከ1997-1998 ዓ.ም PSCAP በአፋር ክልል የከተማ ልማት ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም አስተባባሪ፣ ከ1999-2001 በ GIZ የዩኒቨርሲቲ አቅም ግንባታ ፕሮግራም (UCBP) የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክት ምክትል ስራ አስኪያጅና ከፍተኛ የሳይቱ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ በመሆን ግንባታው በተያዘለት ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቅ ስራውን በማስተባበር ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ከ2003-2007 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ደግሞ የአፋር ክልል የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል።

በቆይታቸውም በመንግስትና በተለያዩ የልማት አጋሮች የሚሰሩ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስራዎችን በማስተባበር አደጋ ሲከሰት ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥበት በማድረግ ውጤታማ ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል። በሌላ በኩል በክልሉ የሚሰሩ መንግስታዊ ድርጅቶችንና የልማት አጋሮችን በማስተባበር የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተቀርፀው እንዲተገበሩ አድርገዋል።።

ከ2008 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ በኢፌዴሪ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር በመሆን ያገለገሉ ሲሆን በቀጣዩ ዓመትም በ2009 በተደረገው የሚኒስትሮች ሹመት የኮንስትራክሽን ሚኒስትር በመሆን ለሁለት ዓመታት አገልግለዋል። ግዙፍ ኢንዱስትሪና የሀገሪቱን ትልቅ በጀት የሚይዝ ከመሆኑ አንፃር ኃላፊነቱም ቀላል አልነበረም።

ከዚህ በመቀጠል አይሻ መሃመድ የመጀመሪያዋ ሴት የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው ጥቅምት 6 ቀን 2011 ዓ.ም ተሹመዋል። አይሻ መሃመድ በመከላከያ ሚኒስቴር ከወራት ግልጋሎት በኋላ ቀድሞ ወደ ነበሩበት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተመልሰው ነበር። በዚያም ከሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ መስከረም 2014 ዓ.ም. ድረስ የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል። በመስከረም 2014 ዓ.ም ደግሞ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል። ከግንቦት 2016 ዓ.ም ጀምሮ ቀደም ብለው ሲመሩት ወደነበሩት የመከላከያ ሚኒስትር በመዛወር እያገለገሉ ይገኛሉ። ኢንጂነር አይሻ መሃመድ "ለሴቶች ሊሰጡ አይገቡም" የሚባሉ ቦታዎች ሊኖሩ እንደማይገባ በአፍሪካ ግዙፍ፣ ታሪካዊና፣ትልቅ ዕውቅና ያለውን ተቋም የመከላከያ ሚኒስትርን በመምራት ለብዙ ሴቶች ተምሳሌት መሆን ችለዋል።

## ሃና አርአያስላሴ



ሃና የሥራ ዘመናቸውን ለሕዝብ አገልግሎት ከሰጡ ወጣት የመንግስት የሥራ አስፈጻሚዎች መካከል አንዷ ናት። ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በናዝሬት ትምህርት ቤት ተከታትላለች። የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህግ ትምህርት ስታገኝ ከፍተኛ ውጤት ያገኘች የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ነበረች። ለህግ ትምህርት በነበራት ልዩ ፍቅር ሁለተኛ ዲግሪዋን ከኒው ዮርክ የህግ ትምህርት ቤት በህግ ጽንሰ ሃሳብ እና ሃልዎቶች ትምህርት ፕሮግራም ሰርታለች።

በሥራ መስክ በህግ መምህርነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በግል አማካሪ ድርጅት ውስጥ የመጀመሪያ የሥራ ዓመታቶቿን በመስራት አገልግላለች። በጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት በከፍተኛ የፖሊሲ አማካሪነት፣ በማስከተልም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነርነት፣ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር በመሆን እያገለገለች ትገኛለች።

ሥራ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የህዝብ አገልጋይ መሆን ህልሟ እንደነበር ትገልጻለች። ለሷ አገልጋይነት የአገር ፍቅር መገለጫ ነው፣ በማገልገል ውስጥ ያለውን ለውጥም አሳምረው ተረድታለች ለዚህም ነው የተሻለ ገንዘብ ሊያስገኙላት የሚችሉ እድሎችን በመተው በተለያዩ የመንግስት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ በማገልገል የምትገኘው። ሃና አርአያስላሴ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በሰሩበት ወቅት የውጭ መዋዕለ ነዋይ በመሳብ፣ ምቹ የንግድ ከባቢን በመፍጠር፣ የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ እና የፖሊሲ ማነቆዎችን በመቅረፍ ትልቅ አገራዊ አበርክቶ አድርጋለች።

በ2012ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን በሰራችባቸው ጊዜያት የተለያዩ ድርጅታዊ ማሻሻያዎችን አድርጋለች። እርሷ የሥራ አስፈጻሚነቱን ኃላፊነት ስትረከብ የኢትዮጵያ ፖስታ ቤት ድርጅት ውስብስብ ሙስና የተንሰራፋበት፣ ለሰራተኞቹ ደሞወዝ መክፈል የተሳነው፣ በአገልግሎቱም ቀርፋፋ እና በኪሳራ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነበር። ሃና አርአያስላሴ በመራቻቸው የማሻሻያ ሥራዎች በአንድ አመት ውስጥ የኢትዮጵያ ፖስታ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ከነበረበት ከፍ ለማድረግ ተችሏል። በፖስታ አገልግሎት ዋና መለኪያ በሆነው የመልዕክት ደህንነት እና የአገልግሎት ፍጥነት እ.ኤ.አ በ2020 ከ168 አገሮች 117ኛ ደረጃ ላይ የነበረው እና በ2012 ዓ.ም 34 ሚሊዮን ብር ኪሳራ ገጥሞት ደመወዝ መክፈል ተቸግሮ የነበረው የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ሃና በመራቻቸው የማሻሻያ ሥራዎች አማካኝነት በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ከታክስ በፊት 72 ሚሊዮን ብር ትርፍ ማግኘት ሲችል በ2014 ዓ.ም ደግሞ 118 ሚሊዮን ብር ትርፍ አስገብቷል። ደረጃውን በማሻሻልም በአፍሪካ ካሉ ኦፕሬተሮች ስምንተኛ ላይ ሊቀመጥ ችሏል።

ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኃላፊነት በመቀጠል ቀድሞ ትሰራበት ወደነበረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በዋና ኮሚሽነርነት በመሾም ከጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን በኢንቨስትመንት ዘርፍ ለውጭ ባለሃብቶች የማስተዋወቅ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን የማበረታት ሥራዎችን መርታለች ። ሃና ከጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆና በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ሹመት በማግኘት በፍትህ ዘርፍ ውስጥ በማገልገል ትገኛለች። ሃና ሴቶች እድሉን ካገኙ ተቋማትን እና ሀገርን መለወጥ እንደሚችሉ የምታሳይ የህዝብ አገልጋይነት ትዕምርት የብዙ ወጣቶችም አርአያ ናት።

# ፍሬህይወት ታምሩ




በኢትዮጵያ ግዙፍ የመንግስት የልማት ድርጅት ከሆኑት ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ኢትዮ ቴሌኮምን ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በመምራት ከፍተኛ ለውጦችን እያስመዘገቡ ያሉት የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ ድርጁቱን ከዚህ በፊት ከመሩ የሥራ ሀላፊዎች መሀከል በዕድሜ ትንሿ ሊባሉ የሚችሉ ናቸው። አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው ፍሬህይወት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢንፎርሜሽን ሲስተም ሁለተኛ ዲግዋን ደግሞ ከእንግሊዝ ሀገር ኦፕን ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ አድምንስትሬሽን ተቀብላለች።

ፍሬህይወት ወደ ኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚነት ከመምጣቷ በፊት በድርጅቱ ውስጥ በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች ለአምስት ዓመታት ያህል ማገልገሏ ይነገራል፤ በገዛ ፈቃዷ ሥራዋን ከለቀቀች በኋላ 'ዶክሳ ኤቲ' የተባለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የግል ድርጅት አቋቁማ በዋና ሥራ አስኪያጅነት በመስራት ቆይታለች። በዶ/ር አብይ አህመድ የሚመራው የለውጥ ሀይል ወደ ስልጣን መምጣቱን ተከትሎ ወደ እዚህ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ከመጡ ወጣት የሥራ መሪዎች መካከል አንዷ የሆነችው ፍሬህይወት ኢትዮ-ቴሌኮምን የመምራት ኃላፊነት እንደተረከበች ከእሷ በፊት ከነበሩት አቶ አንዱአለም አድማሴ ጋር ሃላፊነት ወንበር ላይ የነበሩ 40 ያህል የሥራ መሪዎችን በመቀየር ነው ሥራዋን የጀመረችው።

ኢትዮ ቴሌኮም ከ22,000 በላይ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው። ከለውጡ ጋር ተያይዞ 40 ከመቶ የሚሆነውን የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻን ወደ ግል ባለሀብቶች የማዛወር ሂደት የዋና ስራ አስፈፃሚዋን አቅም እና ተወዳዳሪነት የፈተነ እና የድርጅቱንም ህልውና ጥያቄ ምልክት ውስጥ የከተተ ነበር። ነገር ግን በፍሬሕይወት የሚመራው ኢትዮ ቴሌኮም ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በማቀድና በማስፈፀም፣ ተጨማሪ አገልግሎቶችን በጥራት በማቅረብ፣ የደንበኞች እርካታን በመጨመር ተወዳዳሪነቱን ይበልጥ ለመጨመር ችሏል።

ፍሬህይወት ታምሩ በአመራርና አፈፃፀም ክህሎት ልህቀት በተለይም ኩባንያው ያስመዘገበውን ለውጥ እና እድገት በመምራት ልማዳዊ አሰራሮችን በአዳዲስ አሰራሮች በመለወጥ እና በማሻሻል ፣በግል ባስመዘገቡት ስኬት፣ በእውቀት ሽግግር እንዲሁም ስኬታማ መሪ በመሆን ለአፍሪካውያን ሴቶች ምሳሌ ናቸው።

## አምባሳደር አጸደ ኪዳኑ



አፀደ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት ሲሆኑ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙ የመጀመሪያዋ ሴት ተማሪ ነበሩ። በአለም አቀፍ ህግ የሁለተኛ ዲግሪም አግኝተዋል። እ.ኤ.አ. ከ2001 እስከ 2003 አምባሰደር አጸደ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቆንስላ ሚኒስትር ነበሩ። በጋና አክራ የሚገኘውን ኤምባሲ ጨምሮ በዳካር፣ ሴኔጋል እና ሌሎች የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች እና የኢትዮጵያ የአፍሪካ ሕብረት ቋሚ ተወካይ እና ተጠባባቂ እና ሚኒስትር አማካሪ በመሆን አገልግለዋል።

አጸደ የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ የአውሮፓ እና የሰሜን አሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአለም አቀፍ ስምምነቶች መምሪያን መርተዋል። በበርሊን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ምክትል ኃላፊ ሆነው ሰርተዋል። በተጨማሪ በኒውዮርክ ከተማ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተልዕኮ ውስጥ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በ2009 በሴቶች ጉዳይ ላይ በተለይም በአካል ደህንነት ላይ በተባበሩት መንግስታት ውስጥ ተጽእኖ ፈጣሪን ግግር አቅርበዋል። አፀደ ሴቶች በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና እንዲኖራቸው ዘመቻ በማድረግ እና በመወትወት ይታወቃሉ።

## አምባሳደር ሂሩት ዘመነ



አምባሳደር ሂሩት ከጀማሪ ባለሙያነት እስከ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታነት ድረስ በተለያዩ ኃላፊነቶች ከ30 ዓመታት በላይ በዓለም አቅፍ መድረክ ኢትዮጵያን አገልግለዋል። አምባሳደር ሂሩት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በ1983 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ከፍሌቸር የዲፕሎማሲ ተቋም በ1994 ዓ.ም ተምረዋል።

አምባሳደር ሂሩት ዘመነ ባለፉት ሶስት አስርት አመታት በሁለትዮሽ እና በባለብዙ ወገን የአለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያን በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች ወክለዋል። አምባሳደር ሂሩት ቀደም ሲል የፖለቲካ ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው በማገልገል በአፍሪካ ቀንድ ብሎም በአካባቢው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በዚህ ረገድ፣ የደቡብ ሱዳንን የሰላም ስምምነት እንዲካሄድ በ በይነ መንግስታት የልማት ባለስልጣን የተመሩ የሽምግልና ሂደቶችን በስኬት መርተዋል። በበይነ መንግስታት የልማት አባል ሀገራት መካከል የወሰን ተሻጋሪ ትብብርን ለማጠናከር ትልቅ ሚናም ተጫውተዋል።

አምባሳደር ሂሩት የበይነ መንግስታት የልማት ባለስልጣን አባል አገራት በቀይ ባህር እና በኤደን ባህረ ሰላጤ ሠላም እና ልማት ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እንዲይዙ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር። የባለስልጣኑን መዋቅር በማሻሻልም ለልማት እና ለደህንነት ቀጠናዊ ችግሮች አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ ጥረት አድርገዋል።

አምባሳደር ሂሩት ባላደጉ አገሮች (LDCs) እና ወደብ አልባ ታዳጊ አገሮች (LLDCs) ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ፣ ከቻይና ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በዘላቂ እና ፍትሃዊ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሰርተዋል፣ ወትውተዋል። የኢትዮጵያም አለም አቀፍ ግንኙነት በተለይ ከቤልጂየም፣ ሉክሰምበርግ፣ ኔዘርላንድስ እና በአውሮፓ ህብረት ጋር ሰላማዊ እና ዘርፈ ብዙ የትብብር መስኮች እንዲኖሯት አስችለዋል። አምባሳደር ሂሩት ዘመነ አለም አቀፍ ግንኙነት "ለሴት የሚሆን ሥራ አይደለም" የሚለዉን የተሳሳተ አመለካከት ፉርሽ ያደረጉ ባለሙያ እና የ ብዙ ኢትዮጵያውያን ኩራት ናቸው።

## ኬሪያ ኢብራሂም



ኬሪያ ኢብራሂም በትግራይና በፌደራል መንግሥቱ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ በነበረው የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ መግባት ከቻሉ ጥቂት ሴት ፖለቲከኞች አንዷ ናቸው።

በኤርትራዋ መዲና በአሥመራ ከተማ በመጋቢት ወር 1973 ዓ.ም የተወለዱት ወይዘሮ ኬሪያ የመጀመርያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በኢንቫይሮንመንታል አንትሮፖሎጂ አግኝተዋል። ኬሪያ በትግራይ ክልል ከወረዳ እስከ ክልል ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የስልጣን እርከኖች አገልግለዋል። ለአብነትም የደቡብ ምስራቅ ዞን አስተዳደር፣ የትግራይ ክልል የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ እንዲሁም በፓርቲያቸው ውስጥ የገጠር ዘርፍ ሃላፊ በመሆን አገልገለዋል። ወይዘሮ ኬሪያ ኢብራሂም ዶክተር አብይ አህመድ ስልጣን ከያዙ ከጥቂት ግዜ በኋላ ነበር የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በመሆን በሙሉ ድምጽ የተመረጡት። ወይዘሮ ኬሪያ የአገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን አካላት ከሆኑት ሁለት ምክር ቤቶች የላይኛው ምክር ቤት የሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ በመሆን ከሁለት ዓመታት በላይ የሰሩ ሲሆን፤ በዚህ የኃላፊነት ደረጃም ሁለተኛዋ ሴት ነበሩ።

በማዕከላዊው መንግስትና ህወሃት መካከል ያለመግባባቶችና ውዝግቦች እየተባባሱ በሄዱበት ወቅት አዲስ አበባ ከቀሩ ጥቂት የህወሃት ሰዎች ውስጥ አንዷ በመሆን እያገለገሉም ነበር።

ወይዘሮ ኬሪያ ኢብራሂም በግል የሚያውቋቸው ሰዎች ሳቂታና ተጫዋች እንደሆኑ ይመሰክሩላቸዋል። በአንድ ወቅት ለአንድ መገናኛ ብዙሃን በሰጡት ቃለ ምልልስ ድሮ የአስቴር አወቀ ሙዚቃን ማድመጥ ይወዱ እንደነበርና ከመጽሃፍ ደግሞ የሃዲስ አለማየሁ ዘመን አይሽሬ የሆነውን ፍቅር እስከመቃብር እንደማይረሱት ተናግረዋል። ወይዘሮ ኬሪያ ኢብራሂም በትርፍ ሰአታቸው ፖለቲካ ነክ ጽሁፎችን ማንበብ እንደሚወዱም ይነገርላቸዋል። ወይዘሮ ኬሪያ በተነጻጻሪነት በህወሓት ወስጥ ከነበሩ የሴት አመራሮች ውስጥ በእድሜ ወጣት የሴት አመራር የነበሩ ሲሆን ጠንካራ ዲሲፕሊናቸው ላመኑበት አቋም ያሳዩት ጽናት ለብዙ ሴት ኢትዮጵያውያን ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው።

## ሽታዬ ምናለ



ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ ከ2008 – 2013 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን አገልግለዋል። ወ/ሮ ሽታዬ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዴት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከታተሉ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጣና ሀይቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። በመቀጠልም የከፍተኛ ትምህርታቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፔዳጎጂካል ሳይንስ በመጀመሪያ ዲግሪ በ1982 ዓ.ም ተመርቀዋል። ቀጥለውም የትምህርት ዝግጅታቸውን በማሻሻል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥርዓተ ትምህርትና በማስተማር የማስተርስ ዲግሪ በ1993 ዓ.ም ተመርቀዋል። ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ የመጀመሪያዋ ሴት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን ያገለገሉ መሪ ናቸው።

የሥራ ልምዳቸውን በተመለከተ ከ1982 – 1984 ዓ.ም በሮቤ የመምህራን ማሰልጠኛ ፤ ከ1985 – 1988 ዓ.ም በደብረወርቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት በመምህርነት አገልግለዋል። ከመምህርነት ባሻገር ደግሞ ከ1989 – 1992 ዓ.ም የአማራ ክልል የትምህርት ቢሮ የጂኦግራፊ ኤክስፐርት/ ካሪኩለም/ በመሆን፤ ከ1993 – 1997 ዓ.ም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የመሰረተ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል በመሆን አገልግለዋል። በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሶስት ተከታታይ የሥራ ዘመናት (1998 – 2002 ዓ.ም፤ ከ2003 – 2007 ዓ.ም፤ ከ2008 – 2013 ዓ.ም) የምክር ቤቱ አባልና ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን አገልግለዋል። በምክር ቤት ቆይታቸው የተመራጭ ሴቶች ኮከስን በመምራት የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። በተጨማሪም የፓን አፍሪካ ፓርላማ የኢትዮጵያ ልዑክ መሪ በመሆን በመድረኩ የኢትዮጵያን ጉዳይ በማስተዋወቅና የኢትዮጵያን ገጽታ በመገንባታ ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋል። እንዲሁም በ2014 ዓ ም በኮትዲቫር የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው በመሾም ሀገራቸውን ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

## ቢለኔ ስዩም



ቢለኔ ስዩም የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የፐሬስ ሰክሬተሪ ናት። ቢለኔ ስዩም እ.አ.አ በ1982 ዓ.ም. አዲስ አበባ  የተወለደች ሲሆን ገና በልጅነት እድሜዋ ነው ወደዚምባቡዌ ከዛም ወደካናዳ በማቅናት አብዛኛውን ኑሮዋን ያሳለፈችው።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በዚምባቡዌ ሀራሬ ያጠናቀቀችው ቢለኔ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በማርኬቲንግ ማናጅሜንት በመቀጠልም በብሪቲሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በአለም አቀፍ ግንኙነት የሁለተኛ ዲግሪ አግኝታለች። ከዚህም በተጨማሪ በተባበሩት መንግሥታት ስር በሚገኘው የሰላም ዩኒቨርሲቲ በስረዓተ ጾታ እና ሰላም ግንባታ የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁም ከኦስትሪያው ኢንስብሩክ በሠላም፣ ደህንነት፣ ልማት እና የግጭት አፈታት ሌላ ሁለተኛ ዲግሪ አግኝታለች።

ቢለኔ እ.አ.አ በ 2010  ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች በኋላ ለሴቶች መብቶች መከበር እና መስፋፋት ከፍተኛ አስትዋጽኦ ያበረከተች ሲሆን፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ችግሮችን ነቅሶ የማውጣት እና የማኅበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎችንም ሰርታለች። ለአብነትም ስለ ኢትዮጵያ እና አፍሪካ የሴቶች መብት ንቅናቄዎች ግንዛቤ የሚሰጡ በርካታ ጽሁፎችን በማዘጋጀት በአቋቋሙት "African feminism" የተሰኘ ድረገጽ በመልቀቅ አፍሪካዊያን ሴቶች ስለሴቶች እኩልነት እና መብት የሚወያዩበት መድረክ መፍጠር ችላለች።

እ.አ.አ ከ2011-13 ቢለኔ ስዩም በአፍሪካ ሰላም እና ጸጥታ ፕሮግራም ውስጥ በአዲስ አበባ በኃላፊነት ደረጃ አገልግላለች። ከዛም በመቀጠል ቢለኔ የኢትዮጵያ ሴት ነጋዴዎች ማህበር  ፕሬዝዳንት ሆና ሰርታለች። በማህበሩ የነበራትን አገልገሎት መሰረት በማድረግ እ.አ.አ  በ2014 "Transformative Spaces: Enabling Authentic Female Leadership Through Self Transformation. The Case of AWiB." የተሰኘ መጽሀፍ አሳትማለች። ከዚህ መጽሀፏ ባሻገር በሴቶች ጉዳይ ላይ በተለያዩ ጋዜጦች እና የምርምር መጽሄቶች ላይ ጽሁፎችን አሳትማለች። ከነዚህም መካከል Pambazuka News ተጠቃሽ ነው። ከሴቶች ጉዳይ በተጨማሪም የኢትዮጵያን ገበሬዎች ህይወት ለመቀየር በሚንቀሳቀሰው Agricultural Growth Program- Agribusiness and Market Development (AGP-AMDe) project of ACDI-VOCA, ውስጥ  በአማካሪነት አገልግላለች።

ቢለኔ ስዩም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ባዋቀሩት የሚኒስትሮች ካቢኔ የጾታ እኩልነት ውስጥ የሃሳብ ድርሻ እንደነበራትምም ይነገራል። ከጥቅምት 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፕሬስ ሰክሬተሪያት ሆና እያገለገለች ትገኛለች።

## ራሄል ባፌ (ፒ.ኤች.ዲ)



ዶክተር ራሄል ባፌ ተወልደው ያደጉት በቀድሞው ከፋ ክፍለ አገር የአሁኑ ደቡብ ምዕራብ ክልል ዳውሮ ዞን ውስጥ ነው። እድሜያቸውም ለትምህርት ሲደርስ ደግሞ ዋካ ከተማ

ውስጥ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን የትምህርት ቆይታቸውን አጠናቀዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ከአካባቢያቸው ውጪ ዱራሜ የአሜሪካን ሚሽንና የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተክርስቲያን ያቋቋሙት አዳሪ ትምህርት ቤት መከታተል ችለዋል። ዶክተር ራሄል በጣም ጎበዝ የሚባሉ ተማሪ ከመሆናቸው የተነሳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሰው 12ተኛ ክፍል ሲፈተኑም ጥሩ ውጤትን በማምጣት በቀጥታ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላይ የመመደብ እድልን ያገኙም ናቸው።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት፣ ከዛም በቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የትምህርት መስክ፣ ዶክትሬት ደግሞ ከአሜሪካን አገር ካሊፎርኒያ ከሚገኝ ቪዥን ዩኒቨርሲቲ በአመራር የትምህርት ዘርፍ አግኝተዋል።

ዶክተር ራሄል ቀድሞ እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፖለቲካን በሩቁ ሲሉ ነው የኖሩት ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ከቤተሰባቸው ጀምሮ በተለይም ሀይማኖትን በተመለከተ ጠለቅ ያለ እውቀት ያላቸው አባት ስለነበራቸው ፖለቲካና ሀይማኖት አብሮ አይሄድም በሚል አመለካከት ስላደጉ ነበር። ነገር ግን የአገራቸው ፖለቲካዊ ሁኔታ ያሳሰባቸው እና እንደውም "እስከ መቼ ነው ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ እንዲወስኑ እያደረግን አገራችንና እኛ የምንፈልገውን ነገር ሳናገኝ የምንኖረው" የሚለው ጥያቄ እረፍት ይነሳቸው ነበር። በዚህ የውስጥ ጥሪ ግፊት ወደ  ፖለቲካው ውስጥ ገብቼ በመሳተፍ የማመጣውን ለውጥ ማየት አለብኝ ብለው እንደገቡ ይናገራሉ።

በፓለቲካ ተሳትፏቸውም ከ 1983 ዓ.ም. ጀምሮ  በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያሉ ሲሆን  በ ኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ፣ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ውስጥ ጉልህ እንቅስቃሴ ነበራቸው። የቀድሞዋ የፓርላማ አባል እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ነበሩ።

ከፖለቲካ በተጨማሪ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በ ኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ውስጥ ተሳትፎ አድርገዋል። ዶክተር ራሄል ባፌ እራሳቸውንና የኢትዮጵያን ሴቶች በመወከል በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ በሰብሳቢነት ለአንድ ዓመት ተኩል አገልግለዋል። አሁንም በጋራ ምክር ቤቱ እንደ ጸሃፊ እያገለገሉ ይገኛሉ። ዶክተር ራሄል ሴቶች ወደመሪነት ቢመጡ እንደማያስወቅሱ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንደሚችሉ፤ የሴቶች የአመራር አቅም በተምሳሌትነት ለማሳየት የቻሉ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳትፎ ኮከብ እንስት ናቸው።

## ፊልሳን አብዱላሂ



ፊልሳን አብዱላሂ መሐመድ በዶ/ር አብይ ካቢኔ ውስጥ ካገለገሉት ሚኒስትሮች ሁሉ በዕድሜ ትንሿ ነበረች፣ በ28 አመቷ ነበር የሴቶች የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስትር ሆና የተሾመቸው። ፊልሳን አብዱላሂ አህመድ በ1984 ዓ.ም. በድሬዳዋ የተወለደች የሴቶች መብት ተከራካሪ እና ፖለቲከኛ ናት። ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በአመራርና በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በኋላም በእንግሊዝ ከሄርትፎርድሻየር ዩኒቨርሲቲ በኮሙዩኒኬሽን ሳይንስ ዲግሪ አግኝታለች። ከተመረቀችም በኋላ በእንግሊዝ ውስጥ የንግግር እና የቋንቋ ቴራፒስት በመሆን ሠርታለች። በ2010 ዓ.ም የሶማሌ ክልል ፕሬዝዳንት አብዲ መሃሙድ ኡመር ስልጣን መልቀቃቸውን ተከትሎ የተነሳውን ሁከት እና ማህበራዊ ቀውስ ለመቀልበስ የNabad (ሠላም) ፕሮጀክትን በመንደፍ በ2011 ዓ.ም የሳተላይት ቴሌቪዝን ጣቢያን መስርታ መርታለች።

ይህ ጣቢያ ሀሳብን የመግለፅ መብትን በተገቢው መልኩ መጠቀም እንደሚገባ፣ የመነጋገርን እና የፖለቲካ ልዩነትን በንግግር መፍታት እንደሚቻል ያስተምር ነበር። በተጨማሪም በማኅበረሰቦች መካከል መግባባትን ለመፍጠር ይሰራ ነበር።

በ2012 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ፊልሳን የፌዴራል በጎ ፈቃድ አምባሳደር ሆና ተሾመች በዛው ዓመት በመጋቢት ወር በ28 ዓመቷ የኢትዮጵያ ሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስትር በመሆን በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ካቢኔ ውስጥ በእድሚ ትንሿ ሚንስትር ሆነች። ፊልሳን አብዱላሂ በሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስትርነት እስከ መስከረም 2014 ዓ.ም. ድረስ ያገለገለች ሲሆን ሚኒስትር ፊልሰን በዚህ ቆይታዋ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ከተለያዩ አጋር ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በማስተዋወቅ በኢትዮጵያ ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሕይወት ላይ ለውጥ ያመጣል ብላ ያመነችበትን አዲስ መዋቅር ዘርግታ ነበር። አዳዲስ ዘዴዎችና ፖሊሲዎችንም በመቅረጽ የ10 ዓመት እቅድ አዘጋጅታለች። በመስከረም 2014 ዓ.ም ፊልሰን አብዱላሂ በገዛ ፈቃዷ ሥራዋን የለቀቀች ሲሆን የሴቶችን አቅም ማጎልበት ላይ፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲቆሙ፣ በብሄር ብሄረሰቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን እና ሰብአዊ መብትን ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ታግላለች።





# ቀዳማዊት እመቤቶች





## እቴጌ ጣይቱ ብጡል (1832-1910 ዓ.ም.)



እቴጌ ጣይቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ እና የሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ድርሻ እና አስተዋፅኦ ያላቸው ሴት ናቸው። በዘመናቸው ሀገራቸው ኢትዮጵያን ከቅኝ አገዛዝ አፋፍ ላይ በደረሰችበት ወቅት በቆራጥነትና በአይበገሬነት ተጋፍጠው ትውልድን እና ሀገርን ለዘላለም ታድገዋል።

“ብርሃን ዘ ኢትዮጵያ” በሚል ቅፅል ስም የሚታወቁት እቴጌ ጣይቱ ከአባታቸው ደጃዝማች ብጡል ኃይለ ማርያም እና ከእናታቸው ወይዘሮ የውብዳር በነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም በጌምድር ውስጥ ደብረታቦር ከተማ ተወለዱ። በ10 አመታቸው ገደማ ለመጀመሪያ ጊዜ ተድረዋል። በወቅቱ እንዲህ አይነት ጋብቻ የተለመደ ነበር። አራት ጊዜ አግብተው የፈቱት ጣይቱ በመጨረሻ የሸዋ ንጉስ ከነበሩት እና ኋላም ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከተባሉት ንጉሠ ነገሥት ጋር ትዳር መስርተዋል።

በ40 ዓመት ዕድሜያቸው ምኒልክን ያገቡት ጣይቱ ለንጉሡ ሦስተኛ ሚስታቸው ነበሩ። በሁለቱ ጋብቻ ወቅት ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ እንደነበሩና የጣይቱ የትውልድ ማንነት ወደፊት አፄ ለመሆን ለሚያቅዱት ምኒልክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው። የምኒልክ ጣይቱን ማግባት የሳቸውን ተራማጅ አስተሳሰብና የሴቶችም አስተዋጽኦ ተቀባይነት እንደነበረው ያመላክታል። ምኒልክ ከጣይቱ በፊት ያገቧቸው ባፈናም እንዲሁ ተሰሚነት የነበራቸው፣ ከወቅቱ ከምኒልክ ዘመድ ከመሸሻ ሰይፉ ጋር በመሆን በ1870 ዓ.ም. አካባቢ ሸዋ ውስጥ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ያደረጉ ሴት ነበሩ። ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን እየሾሙ፣ በጋብቻ እያስተሳሰሩ ቆይተው በመጨረሻ የግልበጣው ሙከራ ስላልተሳካ ግዞት እንዲላኩ ተፈርዶባቸው ነው ከምኒልክ ጋር የተለያዩት። የ ባፈና እና የእቴጌ ጣይቱ መመሳሰል ምኒልክም ምን ዓይነት ሴቶችን እንደሚመርጡ በዚህ ማስተዋል ይቻላል።

እቴጌ ጣይቱ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ባለቤት ብቻ አልነበሩም። በተለያዩ የፖለቲካ ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ወታደራዊ ውሳኔዎች ላይ ተፅፅኖ ፈጣሪ ሴት ሆነው አልፈዋል። በተለይም ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለማዋል ባደረገችው ጥረት፣ እቴጌይቱ አርቀው በማሰብና የጣሊያን መንግሥት ወኪሎችን እንቅስቃሴ በቅርብና በጥርጣሬ በማጤን የግጭቱን አዝማሚያ አስቀድመው በመገመታቸውና አዝማሚያው ሲገባቸውም፣ ጦርነት እንደማይወገድ አውቀው ቁርጠኛ አቋም መያዛቸውንና ለድል የሚያስፈልገውን ዝግጅት አሰናድተው ነበር።

ጣይቱ ከጣሊያን ጋር ከተደረጉ ስምምነቶች መካከል ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ሊያስደርጋት የሚችለውን የውጫሌውን ስምምነት ውል አንቀፅ 17 ውድቅ በማድረግ ይታወቃሉ። መቀሌን ተቆጣጥረው የነበሩትንም የጣሊያን ወታደሮች ለማሸነፍ እንዲቻል ጣይቱ ባቀረቡት ሀሳብ ይታወቃሉ። በዚህም መሠረት ጣሊያኖች የሚጠቀሙበትን የውኃ ምንጭ በኃይል በመቆጣጠር ከመቀሌ እንዲወጡ ለማስደረግ ተችሏል።

ጣይቱ ብጡል ጣሊያኖች በተሸነፉበት እና በድል በተጠናቀቀው የአድዋ ጦርነት በነበራቸው ሚናም ይታወቃሉ። እሳቸውም ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሞከረውን የጣሊያን ጦር ለመዋጋት በስራቸው 5,000 እግረኛ እና 600 ፈረሰኞችን አሰልፈው ነበር። የዓድዋ ድል ለሚቀጥሉት 40 ዓመታት የአገሪቷን ነፃነት አረጋግጧል።አንድ ታላቅ የአውሮፓ መንግስት ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቁር በአፍሪካውያን ሰራዊት ድል ተመትቶ በተዋረደበት የአድዋ ጦርነት በተጫዎቱት ታላቅና አቻ የማይገኝለት የአመራርነት ብቃትና ብልሃት፣ የኢትዮጵያ ሉኣላዊነት ለማስከበር ስለፈጸሙት ጀብዱ፣ ”ብርሃነ ዘ ኢትዮጵያ” የሚል የሙገሳ ስም ወጥቶላቸዋል። ይህም ታላቅና ግርማዊ ስማቸው በማህተማቸው ላይ ይገኛል።

እቴጌ ጣይቱ በኢትዮጵያ ሴቶች ታሪክ ውስጥ እንደ ከዋክብት ብርሃን ለዘላለም የሚንፎለፎል የነጻነት፣ የ እኩልነት፣ ያልደፈር ባይነት ማህተም አሳርፈው አልፈዋል።ዛሬ በጥቁር ዓለም ውስጥ በነፃነቷ ኮርታ ለሌሎችም ምሳሌ የምትሆነውን ኢትዮጵያ ተረባርቦ ለማቆም በተከፈለው መስዋዕትነት ውስጥ ጣይቱ ብጡል ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ።

# ግርማዊት  እቴጌ መነን አሥፋው (1883-1954 ዓ.ም)



ግርማዊት እቴጌ መነን የቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት ነበሩ። መጋቢት 25 ቀን 1883 ዓ.ም. በወሎ ጠ/ግዛት በአምባሰል አውራጃ ልዩ ስሙ ዕጎ ከተባለው ቀበሌ ከጃንጥራር አስፋውና ከ ስህን ሚከኤል ተወለዱ። እቴጌ መነን በልጅነት ዘመናቸው በእናት በእባታው ቤት መምህር ተቀጥሮላቸው እማርኛ ማንበብና መፃፍ ጠንቅቀው አወቁ። በተጎዳኝ ልዩ ልዩ የቤት ባልትና ሙያዎችን ተምረው በማጠናቀቃቸው የቤት ራስ ለመባል በቅተዋል። በ1892 ዓ.ም. ማለትም በተወለዱ በአሥረኛ  አመታቸው ለመጀመሪያ ባለቤታቸው በህግ ተዳሩ። ከእኝህ ባለቤታቸው  በላይነሽ ዓሊንና ጃንጥራር አስፋው ዓሊን ወለዱ። ከዚያም  ሁለተኛ ባለቤታቸውን በማግባት ጃንጥራር ገብረእግዚአብሄር አመዴንና  ደስታ እመዴን ወልደዋል። በ1903 ዓ.ም. ወደ  መጀመሪያ ራስ ልኡልሰገድ አጥናፍሰገድን አገቡ። በዚሁ ዓመት ወደ መጨረሻም ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር ተጋቡ። የእቴጌ መነን እና  የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋብቻ ፖለቲካዊ ሂሆን የአጎታቸውን የልጅ ኢያሡንና የቀዳማዊ ኃይለሥላሤን ጠብ ለማስወገድ  ይቻላል በሚል መኳንንቱ ሁሉ  መክረው የፈፀሙት ነበር።

እቴጌ መነን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በተጋቡ በሃያ ዓመታቸው ማለትም 1923ዓ.ም.  የእቴጌነት ዘውድ ጫኑ። በእድሜ ዘመናቸው በግል ገንዘባቸው በኢትዮጵያና በእየሩሳሌም በርካታ ቤተክርስቲያናትን እና ማህበራዊ ተቋማትን አሳንጸዋል፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንም አቋቁመዋል። አንዳንዶችን ለመጥቀስ ያህል በ1923 ዓ.ም.  በመስከረም ወር እቴጌ መነን ተማሪ ቤትን አቋቁመዋል፣ በ1935 ዓ.ም. ለገሀር የሚገኘውን የእጅ  ጥበብ ት/ቤት አቋቁመዋል፣ እንዲሁም በ1943 ዓ.ም. ወደግሽን ማርያም ቤተክርስቲያን የሚወጣውን የሰርጥ መንገድ አሠርተዋል።

የጣሊያን ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን እንደሚወር  ይፋ በሆነበት ጊዜ ግርማዊት እቴጌ መነን መስከረም 1 ቀን 1928 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ ዕለት ለዓለም ሁሉ ሴቶች የትግል ጥሪ  አድርገው ነበር። በንግግራቸውም “በዓለም ያላችሁ ሴቶች ሁሉ  በዓለም ላይ እውነተኛ ፍርድና ሰላም እንዲነግስ የመንግሥት ስዎች ሁሉ በሚሠሩት ሥራ በእግዚአብሔር መንፈስ እንዲመሩ በምናደርገው ፀሎት ተባባሪዎች እንድትሆኑ እንለምናለን” የሚል ነው።

እቴጌ መነን በ1928 ዓ.ም. ግርማዊ ባለቤታቸው ጦር ሜዳ ሄደው  ከጠላት ጋራ ስላገራቸው ሢዋጉ በከተማው ያሉ ወይዛዝርትን እየሰበሰቡ ለቁስለኞች እና ለሠራዊቱ የሚሆን ስንቅ፣ ትጥቅና የህክምና ቁሳቁስ እያዘጋጁ ይልኩ ነበር። የከተማውም ፀጥታ እንዲጠበቅ ከከተማው የዘበኛ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በትጋትና በብርታት ሲሰሩ ቆይተዋል። በጦር ሜዳ ካሉት ለባለቤታቸው እና  በዚያው ከሚገኙ የመረጃ ሰዎች የጣሊያን አውሮፕላኖች በአዲስ  አበባ በሚኖረው በሰላማዊ ህዝብ ላይ የቦንብ ጥቃት ለማድረስና ህፃን፣ ሽማግሌና ሴት ሳይለይ በአንድነት ለመደምስስ እየመጡ  እንደሆነ በስልክ በተላለፈ ጊዜ ግርማዊት እቴጌ መነን በአውቶሞቢል ሆነው በድፍረት በከተማው እየዞሩ በየመንገዱና በየገብያው  ያለው ህዝብ በአንድነት እጅብ ብሎ መቆሙን ትቶ እንዲበተንና አደጋውን ወደሚከላከልበት ቦታ እንዲደበቅ በማድረጋቸው ብዙ ህዝብ ሊድን ችልሷል።

እቴጌ መነን በፖለቲካዊ አስተሳሰብ የተነሣ የእናታቸውን የ ስህን ወገኖች በተለይም አያታቸው ንጉሥ ሚካኤልና አጎታቸው ልጅ ኢያሱ ከባለቤታቸው ከቀዳማዊ ኃይለሥላ ሴ ጋር በፈጠሩት ፖለቲካዊ ቅራኔ ሰበብ በተካሄደው የሰገሌ ጦርነት ከግራ ከቀኝ ተሰልፈው የተዋጉ ወገኖቻቸው ያለቁባቸው ቢሆንም በየጊዜው ሁለቱንም ወገኖች እያስማሙ በአንድነት እንዲኖሩ አስችለዋል። የገዳይና የሟችን ደም አዋህዶ ኢትዮጲያን እንደ ሃገር እንድትቀጥል የማድረግ ውስብስብ ጽናት የነበራቸው የመጨረሻዋ እቴጌ ነበሩ።

## ውባንቺ ቢሻው



የቀድሞዋ ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ውባንቺ ቢሻው የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግስት ፕሬዘዳንት መንግስቱ ሃይለ ማርያም ባለቤት ናቸው። ትውልድ አገራቸው አማራ ክልል ጎጃም ነው። ምንም እንኳ የ ውባንቺ ቢሻው ፖለቲካዊ ሚና ምን እንደነበር በውል የሚታወቅ የተሰነደ ማስረጃ ባይኖርም የሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች በተባለው መፅሃፍ ኮሎኔል መንግሥቱ ከሰጡት የምስክርነት ቃል ለመረዳት እንደሚቻለው ውባንቺ ቢሻው በቤተሰባዊ አስተዳደር ጠንካራ ነበሩ። ኮሎኔል መንግሥቱ ይህንኑ አስመልክተው ሲናገሩ “አሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ በሥልጣን ላይ ስቆይ ከውባንቺና ከልጆቼ ጋር የማሳልፈው ጊዜ በጣም ውሱን በመሆኑ አንድም ቀን ሰለቸኝ ደከመኝ ሳትል፣ ሳትማረር የልጆቿን ትምህርትና የቤተሰቡን ጣጣ ሁሉ ብቻዋን የተወጣች ነች” ብለዋል።

በተለያዩ ወቅቶች የተጻፉ ድርሳናት ውባንቺ ሩህሩህ፣ ለተቸገሩ አዛኝ እና በወንድማማችነት የተመሰረተ አመለካከት ይንጸባረቅባቸው እንደነበር ይገልጻሉ። ለምሳሌ በደራሲ ዘነበ ፈለቀ (ገስጥ ተጫኔ) በተፃፈው “ነበር” መጽሀፍ ገጽ 201 ላይ ስለ ውባንቺ ቢሻው የተጻፈው እንዲህ ይላል፡- “እሳቸው የፖለቲከኛ ሚስት መሆን የሚችሉ አልነበሩም። ምክንያቱም ፖለቲካ የዞረበትን አያውቁም ነበርና ነው። የወታደር ሚስትም መሆን አልነበረባቸውም ምክንያቱም ድንጉጥ እና ስጉ ነበሩና ነው።የነጋዴ ሚስት ሊሆኑም አይችሉም። ቸር እና ሩህሩህ በመሆናቸው። የዳኛ ሚስትም አይሆኑም፤ ከአዛኝነታቸው የተነሳ አማላጅነታቸው ስለሚያስቸግር።የቄስ ሚስት ግን መሆን ይችላሉ። ምክንያቱም ጥሩ የቤት እመቤት ሆነው ከትሁት ባል ጋር ሰላማዊ ኑሮ መኖር ያለባቸው ሴት ነበሩና። በአጭሩ ውብአንቺ ቢሻው ማለት እኚህ ነበሩ።”

## አዜብ መስፍን



ወይዘሮ አዜብ መስፍን የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ነባር ታጋይና የኢትዮጵያ የ ቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የአቶ መለስ ዜናዊ ባለቤት ናቸው። እ.ኢ.አ በ1958 ዓ.ም በወልቃይት ወረዳ በምትገኝ አንዲት ገጠራማ መንደር ተወለዱ። ወይዘሮ አዜብ መስፍን ገና በለጋ እድሜያቸው ነው ህወሓትን የተቀላቀሉት። በትግሉ ወቅት ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ጋር ተዋውቀው የኋላ ኋላ በትዳር ተጣምረው፣ ሶስት ልጆችን አፍርተዋል። ወይዘሮ አዜብ ከትግሉ በኋላ በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል። ተጠቃሽ ከሆኑት ውስጥ ቀዳማዊ እመቤት በነበሩበት ወቅት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ተቋሞች ስብስብ የሆነውን የትግራይ መልሶ ማቋቋሚያ ማህበርን (ት.እ.ም.ት) ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን መርተዋል። በምርጫ 97 ወቅት የትውልድ ወረዳቸው የሆነውን የወልቃይት እና ሁመራ የምርጫ ክልል በ መወከል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነው ተመርጠዋል። የምክር ቤቱም የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን አገልግለዋል። የባለቤታቸው መታሰቢያ የሆነውን የመለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን መስራች እና የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን ሰርተዋል። ወይዘሮ አዜብ የኢትዮጵያ የሴቶች ጥምረት በኤች አይ ቪ/ኤድስ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ የአእምሮ ጤና ተነሳሽነት በመፍጠር እና በመምራት ረገድ ከፍተኛ ሚናን የተጫወቱ ሲሆን የኤችአይቪ ኤድስን ስርጭት ለመግታት ባደረጉት ጥረት “የጆን ቶምፕሰን ሽልማት” ተሸላሚ ለመሆን ችለዋል። የአፍሪካ ቀዳማዊ እመቤቶች ድርጅትን በመወከለም ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ አቅም ከነበራቸው ሴቶች መካከል አንዷ የነበሩት ወይዘሮ አዜብ በኢትዮጵያ ሴቶች ፌደሬሽን የተቋቋመውን “የጉልት ማዕከል” የተባለውን በጎዳና የንግድ ሥራ የተሠማሩ ሴቶች የሚደገፉበት ፕሮጀክት ሃሳብ ከማመንጨት ጀምሮ እስከትግበራው ድረስ ተሳትፈውበታል። የወይዘሮ አዜብ ጽናት እና የ ህይወት ዘመን ትግል ለብዙ ወጣት ሴቶች ተምሳሌት እንደሚሆን እሙን ነው።

## ሮማን ተስፋዬ



የቀድሞዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሪ ሮማን ተስፋዬ በትምህርት፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በካንሰር እና በብሄራዊ ስርአተ ምግብ ፕሮግራም ዙሪያ በርካታ አስተዋኦ ካበረከቱ ሴት ኢትዮጵያውያን መካከል ግንባር ቀደም ናቸው።

ወይዘሮ ሮማን ተስፋዬ በሚያዝያ 16 ቀን 1968 ዓ.ም በወላይታ ተወለዱ። በኢኮኖሚክስ እና በአመራር ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በበጎ አድራጎት እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር እያደረጉ ባሉት አበርክቶ ይታወቃሉ። የባለቤታቸው የ ቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ወደ ቤተ መንግስት መግባት ተከትሎ የቀዳማዊ እመቤት ጽ/ቤትን ከመስከረም 2004 እስከ የካቲት 2010 ዓ.ም ድረስ መርተዋል። ቀዳማዊት እመቤት ከመሆናቸው በፊት በደቡብ ኢትዮጵያ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢኮኖሚክስ መምህር እና በደቡብ ክልል አስተዳደር የኢኮኖሚ አማካሪ በመሆን አገልግለዋል። በተጨማሪም በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ የቆዩ ሲሆን፥ ወይዘሮ ሮማን ለሁለት ጊዜያት በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የክልሉ የተወካዮች ምክር ቤት ተመራጭ ነበሩ።

በወይዘሮ ሮማን ተስፋዬ አነሳሽነት በ2006 ዓ.ም የተቋቋመዉ እና በአዲስ አበባ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የህጻናት የቁርስና ምሳ ምገባ ፕሮግራም አሁን በመላ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። የምገባው ፕሮግራም ቀጣይነት እንዲኖረው እና መንግስት በጀት እንዲይዝለት የ ሮማን ተስፋዬ አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም። በሀምሌ 2009 ዓም የአፍሪካ ቀዳማውያት እመቤቶች ፀረ ኤችአይቪ ኤድስ ጥምረት ቀዳማዊት እመቤት ሮማን ተስፋዬን የጥምረቱ ፕሬዚዳንት አድርጎ መርጧቸው ለሁለት አመት መርተዋል።

ጥምረቱ የአፍሪካ ቀዳማውያት እመቤቶች በየአገሮቻቸው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙርያ በተለይም የሴቶችን፣ ሕፃናትንና ወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለሚተገበሩዋቸው ሥራዎች የተለያዩ ድጋፎችን የሚያደርግ ነው። የቀድሞዋ ቀዳማዊት እመቤት ሮማን፣ የአፍሪካ ቀዳማውያት እመቤቶች ፀረ ካንሰር ኅብረትንም በሊቀመንበርነት መምራታቸው ይታወሳል።

የቀዳማዊ እመቤት ጽ/ቤትን በመሩበት ስድስት ዓመታት የ ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበት ላይ፣ የ ሴቶችና ህጻናትን መብት መጠበቅ፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በካንሰር እና በብሄራዊ ስርአተ ምግብ ፕሮግራም ላይ እጅግ ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ከቤተ መንግሥት ከወጡም በኋላ "ኃይለማርያም እና ሮማን" የተሰኘ ፋውንዴሽን በማቋቋም የሀገራቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በመቅረፍ ላይ ይገኛሉ። የአምስት ዓመታትን ዕድሜ ያስቆጠረው ፋውንዴሽኑ፣ በአሁኑ ወቅት ትኩረቱን በሴቶች ላይ አድርጎ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። የ ሮማን ሰብዓዊ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ህይወታቸውን ሙሉ ያሳዩት ጥርት ያለ አስተሳሰብና አቋም ለብዙ ወጣት ሴቶች መነሳሳትን እንደሚፈጥር ይታመናል።

## ዝናሽ ታያቸው



ወይዘሮ ዝናሽ ታያቸው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ባለቤት ናቸው። ባለቤታቸው ወደ መሪነት መምጣታቸውን ተከትሎ የታውቁት ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በልማትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ ላይ እያሳዩ ያሉት ተሳትፎና ትጋት "ስኬታማዋ ቀዳማዊ እመቤት" ያሰኛቸዋል።

በ2010 ዓ.ም የመጣውን ሀገራዊ ለውጥ ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ ለዚህ ክብርና ትልቅ ሀገራዊ ስልጣን ለመብቃት የባለቤታቸው ዝናሽ ታያቸው ወሰን የለሽ ድጋፍ ቀዳሚ ስለመሆኑ የተናገሩት በመጀመሪያው የፓርላማ ንግግራቸው ወቅት ነበር። የእሳቸውን ንግግር ተከትሎም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፓርላማ ወደ ቤተመንግስት ሲገቡ ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ይዘው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታዩ ቀዳማዊት እመቤቷ እንደ ባለቤታቸው ተናጋሪ፤ ተስፈኛና ታታሪ ስለመሆን አለመሆናቸው ይሰጡ የነበሩ ግምቶች ብዙ ነበሩ።

ውሎ ሲያድር የጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለቤት ዝናሽ ከባለቤታቸው ጋር ብቻ ተያይዘው ወደ አደባባይ መውጣታቸውን ትተው የራሳቸውን ፕሮጀክቶች ቀርፀው ትምህርት ቤት በሌለባቸው የገጠር መንደሮች በመዘለቅ ትምህርት ቤቶችን እና የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ማስገንባት ጀመሩ። እስከ ጥር 2013 ዓ.ም ብቻ ከ20 በላይ ትምህርት ቤቶችን 300 ሚሊየን ብር በሚጠጋ ወጭ አሰርተዋል።

ዝናሽ ከመንግስት በጀት ሳያስመድቡ ነው እነዚህን ሁሉ ትምህር ቤቶች ያስገነቡት፤ ከባለቤታቸው ጋር ለሥራ ጉዳይም ሆነ ለጉብኝት ከሀገር ሲወጡ ከእጃቸው የማይለይ የትምህርት ቤት ማሰሪያ ፕሮፖዛል አይጠፋም ነው የሚባለው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገራዊ አጀንዳቸውን ከጨረሱ በኋላ ዝናሽ በየገጠሩ ለሚገኙ ትምህርት ያላገኙ ህጻናት ትምህርት ቤት ማስገንቢያ ፕሮጀክት እቅዳቸውን በማቅረብ ለጋሾች የቻሉትን ያህል እንዲደግፉ ይጠይቃሉ።

ከውጭ ለጋሾች በላይ ደግሞ ባለቤታቸው ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ ከመደመር መፅሐፍ ሽያጭ ያገኙትን ከ110 ሚሊዮን ብር በላይ ለቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት በመለገሳቸው እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣባቸውን ትምህርት ቤቶች ለማስገንባት ችለዋል። በቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ያስገነቧቸው ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ባለባቸው አካባቢዎች የተገነቡ ናቸው፤ ሩቅ የእግር መንገድ በሚያስኬዱት ስፍራዎችና ምንም አይነት ትምህርት ቤቶች ባልተገነቡባቸው ቦታዎች በጥናት የተሰሩ ናቸው። ቀደም ሲል ወታደራዊ ካምፕ የነበሩባቸው ቦታዎችና እንደ ሱማሌ ክልል ባሉ ቦታዎች ደግሞ የማሰቃያ ስፍራዎች የነበሩ ስፍራዎች ዛሬ ትምህርት ቤት ተገንብቶባቸው ተማሪዎችን መቀበል ጀምረዋል። ትምህርት ቤቶች በዉስጣቸው የአስተዳደር ህንጻ፤ የመማሪያ ክፍሎች፤ ላብራቶሪ፤ የቤተ መጽሀፍ የኮምፕዩተር ላብራቶሪ እና የመጸዳጃ ህንጻዎችን ያካተቱ ሲሆን ቀዳማዊት እመቤት ከትምህርት ቤቱ ግንባታ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ ዩኒፎርም፣ ቦርሳና የሙቀት መለኪያ መሳሪያዎችን በስጦታ አበርክተዋል። ቀዳማዊት እመቤቷ ከትምህርት ቤቶች ግንባታ በተጨማሪ በልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ በመሳተፍ የህጻናት እንክብካቤ ማዕከላትን በማስገንባትና የውስጥ ቁሳቁስ እንዲያሟላ በማድረግ አርአያ የሆነ ስራ አከናውነዋል። እንደ አብነትም በቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት የተገነባው ብርሃን የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል አንዱ ነው።

ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ዝናሽ ለ30 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አይነ-ስውራን ተማሪዎች የላፕቶፕ ስጦታ ማበርከታቸው የሚታወስ ሲሆን ስጦታዉ የተበረከተላቸዉ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን ለመከታተልና የመመረቂያ ጽሁፋቸዉን ለማዘጋጀት የላፕቶፕ ችግር ያለባቸዉ ተማሪዎች ተለይተዉ ነዉ። ላፕቶፖቹ ታይዋን ከሚገኝ ASHL FOUNDATION ከተባለ ድርጅት በጽ/ቤታቸዉ በኩል የተገኙ ናቸዉ።

በተመሳሳይም በ2014 ዓ.ም የቀዳማዊ እመቤት ፅ/ቤት የዘመኑ የቴክኖሎጂ ዉጤት የሆነ ኦርካም ማይ አይ የተሰኘ አይነ ስውራንን የሚያግዝ መነፅር ለ2000 አይነስውራን ሰጥቷል።

ይህ ዘመናዊ መርጃ መሳሪያ አማርኛም ሆነ እንግሊዝኛ ያነባል የገንዘብ ኖቶችን ይነግራል ቀለም ይለያል ከፊት ለፊት ምን እንዳለ እና ማን እንደመጣ መዝግቦ በመያዝ መረጃ ይሰጣል። ከለጋሾች በተገኘ ገንዘብ ወደ ሀገር ዉስጥ የገባዉ ኦርካም ማይ አይ የአይነስራኑን ህይወት የሚያቀልና በእለትተእለት እንቅስቃሴያቸው የሰዉ እገዛ የሚቀንስላቸዉ ነዉ። በጽ/ቤቱ በተለያዩ ከተሞች እንዳደረገዉ ሁሉ የዊልቸር ድጋፍ በደቡብ እና በሲዳማ ክልሎች ለሚገኙ 28 አካል ጉዳተኞች ያበረከተ ሲሆን ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸዉ በሃዋሳ ከተማ ተገኝተው የዊልቸር ስጦታው አስረክበዋል። ዊልቸሮቹ የተገኙት ሞቢሊቲ ወርልድ ዋይድ ከተባለ የውጭ ሃገር ግብረ ሰናይ ድርጅት ሲሆን ወደ አገር ውስጥ የገባው የአብ ሜዲካል ሴንተር በተባለ ሃገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት ነዉ ተብሏል።

ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም ድረስ ከመደመር የመፅሃፍ ሽያጭ በተገኘ ገቢ 34 ትምህርት ቤቶችን ያስገነቡ ሲሆን በባህርዳር ከተማ በተገነባ ሴተኛ አዳሪዎችን መልሶ ማቋቋሚያ ተቋም 500 ሴተኛ አዳሪዎችን በማሰልጠን በሚፈልጉት የስራ ዘርፍ እንዲሰማሩ በማድረግ ህይወታቸው እንዲለወጥ ተደርጓል። ቀዳማዊት እመቤት የሚገነቡት ልማት የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን በማሰብ በ 2016 ዓ.ም ክብርት ሼይካ ቢንት ሙባረክ የአይነ ስውራን አዳሪ ትምህርት ቤትን በ አዲስ አበባ ገንብተው ለህብረተሰቡ አስረክበዋል። የካቲት 5 ቀን 1970 ዓ.ም ጎንደር ውስጥ የተወለዱት ዝናሽ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ትዳር ከመመስረታቸው በፊት ሁለቱም በውትድርና ሙያ ሀገራቸውን ያገለገሉ ሲሆን የተዋወቁትም እዚያው ነው። ዝናሽ በወቅቱ የሙዚቃ ሰው እንደነበሩ ይነገራል። አሁን በበጎ አድራጎት ስራዎችና በዘማሪነት የሚታወቁት ዝናሽ ዲቦራ፤ ርብቃና አሜን የተባሉ የሶስት ልጆች እናት ሲሆኑ ከሶስት ዓመት በፊትም ሚሊዮን የተባለ የ15 ቀን የጉጂፈቻ ልጅ ተቀብለው እያሳደጉ ነው።



## ሴቶች በሰብዓዊ ዕርዳታ፣ በሰብዓዊ መብቶች ትግል እና በሲቪል ማህበራት

# የቃቄ ውርድወት

የቃቄ ውርደት በኢትዮጵያ ብሎም በአለም ቀደምት የሴቶች መብት ታጋይ፣ የተደራጀ የሴቶች የፆታ ትግል ፋና ወጊ እና የሴቶች የነፃነት ምልክት ነች። የቃቄ ውርድወት በ1830ዎቹ አካባቢ ከጉራጌ ማኅበረሰብ የፈነጠቀች ኢትዮጵያዊት ኮከብ ነበረች። በሴቶች ላይ የነበረውን አድሏዊ ልማዳዊ ሥርዓት ለመታገል፣ በጋብቻ ሥርዓት ወንዶቹ ከሴቶቹ ይልቅ ሥልጣን ለማደላደል፤ ሴቶች ከለፉበት ትዳራቸው ያለ አንዳች ንብረት በፍቺ መባረራቸውን ለማስቀረት የታገለች ጀግኒት ነበረች።

የቃቄ የአባቷ ሥም ነበር። በቀድሞው የጉራጌ ማህበረሰብ የስም አጠራር ከታዋቂ አባት የተወለደ ልጅ የአባቱ ስም ቀድሞ የልጁን አስከትሎ የመጥራት ባህል መሰረት የምትጠራ፣ እጅግ ሃብታም ከሆኑ ቤተሰቦች ነበር የተወለደችው። ውርድወት እንደ ማናቸውም የአካባቢው ሴት ልጆች ከጓደኞቿ ጋር ወንዝ ወርዳ ውኃ እየተራጨች፣ በቤት ውስጥ ሥራ እናቷን እያገዘች ነው ያደገችው። በወቅቱ እንኳንስ ዘመናዊ ተማሪ ቤት ይቅርና የፊደል ትምህርት ቤት እንኳን አይታወቅም። ፊደል አልቆጠረችም። አቡጊዳንም አታውቅም። ግን በቤት ውስጥ ሥራዎች እናቷን እያገዘች በመልካም ሥነ ምግባር ታንፃ ተከብራ ነበር ያደገችው።

ዕድሜዋ ለአቅመ ሔዋን ሲደርስ በወላጆቿ ምርጫ እንደ እነርሱ ባለጠጋ ለነበረ አጋዝ ፉርችየ ላምቢዬ ለተባለ የባለአባት ልጅ ዳረት። 'አጋዝ' የተከበረ ባህላዊ የማዕረግ ስም ሲሆን 'አበጋዝ' የሚል ትርጉም አለው። ምንም እንኳ ወርድወት ያገባችው ወንድ ማንም የምትመኘው አይነት ጀግና ቢሆንም በትዳሯ ደስተኛ ሳትሆን ትቀራለች። በድሮው ዘመን በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ባለጠጋ የሆነ ወንድ የባለጠግነቱ ማሳያ በሀብትና ንብረቱ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በሚስቶቹም ቁጥር ጭምር ነው። ብዙ ሀብት ያለው ብዙ ያገባል ማለት ነው። ውርድወትም የገጠማት ከዚህ የተለየ አነበረም። የእኔ ነው ብላ ቤቱ የገባችለት ሰው፣ የእሷ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሴቶች ባል ነበር። ይህ ጉዳይ ውርድወትን ይቆረቁራትና ምቾት ይነሳት ነበር። በትዳር ሕይወቷ ቀናትን እያስቆጠረች በመጣች ቁጥር እልህ የታከለበት ቁጣና ንዴት እየንተከለከለ ከውስጧ መገንፈል ጀመረ። እናም በደልን በጸጋ ተቀብሎ መኖር አልሆንላት አለና አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባት ወሰነች።

ውርድወት በመጀመሪያ ያደረገችው ወደ ያኔው የ ጉራጌ የፍትህ ሸንጎ ጥያቄዋን ማቅረብ ነበር። ጥያቄዋን ይዛ እንዳሁኖቹ ዘመናዊ ፍርድ ቤቶች በሥርዓት ወደ ተዋቀረውና ጉራጌ ለዘመናት ሲተዳደርበት ወደ ኖረው ባህላዊ የቂጫ ሸንጎ በመቅረብ "አንድ አባ ወራ አንድ ሚስት ትብቃው" የሚል አስደንጋጭ ክስ አቀረበች። የመንደሯ የዠርመኘ ሸንጎ "በሚስት ላይ ሚስት መደረብ አይሞከርም። አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ብቻ " የሚለውን የ ውርድወት ቅሬታ "አያድርስ" ከማለት በስተቀር ጥያቄዋን ሊፈታላት በፍፁም አልቻለም።

ውርደውት ግን በ ሸንጎው ምላሽ ሳትደናገጥ ሴቶችን ወደ ማደራጀት ገባች። በመጀመሪያም ጎረቤቷ ከነበሩ ሴቶች ዘንድ በመሄድ ስለ ጉዳዩ አማከረቻቸው። ብዙ ሴቶችም ሀሳቧን በመደገፍ ይህንን ትግል ሊቀላቀሏት ፈቃደኛ ሆኑ። ውስጥ ለውስጥ በነበራቸው ቅስቀሳም ቁጥራቸው እየተበራከተ ሄደ። ለመጀመሪያ ግዜም የአካባቢውን ሴቶች በማሰባሰብ በጀፎረ (ባህላዊ የእርቅና የዳኝነት ስርዓቶችና ሽምግልናዎች የሚካሄዱበት የ አደባባይ መድረክ) ውይይት ማድረግ ቻለች። ይህ በሴት የተመራ የሴቶች ውይይትም ሴቶች በአደባባይ በተለይም ለወንዶች ብቻ በተከለለ ቦታ መሰብሰብ የሚያነውረውን ኋላ ቀር አመለካከት የጣሰ ነበር።

በውርድወት የሚመራው ንቅናቄ እየተደራጀ ሲመጣ፣ ልማድ ነቅናቂ የ ስርዓተ ጻታ ጥያቄዎችን አደባባይ ላይ ማሰማት ጀመረ። እነቃቄ ወርድወት ያነሷቸው ዋና ዋና የመብት ጥያቄዎች አንድ አባ ወራ አንድ ሚስት ትብቃው ፤በሴቶች ላይ የተጣለው እርግማን (አንቂት) ይነሳ ፤ሴት ልጅ እንደ ወንድ ልጅ የአባቷን መሬት ትውረስ ፤ ሴት ልጅ እንደ ወንድ ሁሉ የመረጠችውን ታግባ፤ የፍቺ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ያግኝ፣ የንብረት ክፍፍል ላይ ሴቶች ከ ወንዶች እኩል ማግኘት አለባቸው፣ ሴቶች እንደ ወንዶች በአካባቢው ሸንጎ ተሰብስበው እንዲመክሩ ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩበት።

የነውርድወት ጥያቄ ደረጃ በደረጃ የየ አካባቢውን አስተዳደራዊ እርከን እየተሻገረ የ ጉራጌ ውሳኔ ሰጪ ከፍተኛው ባህላዊ ምክር ቤት ይደርሳል። ውርድወት በመላው ጉራጌም ባህሉን እንደጣሰ አፈንጋጭ ሴት ትታያለች። ጥያቄዋ ያስደነገጣቸውና በበሳል አባቶች የሚመራው መላና ፍትህ በእጁ ነው የሚባልለት ታላቁ ሸንጎ ይኼ ፈተና ሲገጥመው ከፍተኛ አድናቆትም፣ የአደጋ ስጋትም ስላደረበት ትልቅ ጥንቃቄና ምክር ያደርጋል።

በኋላም ምሁር ወዳሉት ወደ አባቷ ወደ ዳሞ ቃቄ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የአደራ ትልቅ መልእክት ይልካል። ነገር ግን ውርድወት ከዚህ አመፅ እንድትወጣ ይመከሩና ይማፀኑ ዘንድ የተደረገው ጥረት በውርድወት እንቢታ ይከሽፋል። በመጨረሻም ውርድወት የሰበሰበቻቸውን ሴቶች በባሎቻቸው በኩል አስፈራርተውና አባብለው በጥያቄዎቻቸው እንዳይገፉበትና ከውርድወት ጋር እንዳይተባበሩ ካደረጉ በኋላ አጋዝ ፋርችየን ሸንጎው በዝግ ስብሰባ ጠርቶ “ይሄን የጉራጌ ሴቶች አመፅ ለማስቆም እንችል ዘንድ ለውርድወት አንቂት ማንሳት ግድ ሆኖ አግኝተነዋልና እባክህ የኛን የሽማግሌዎችን ቃል ሰምተህ አንቂቱን አንሳላትና እንመርቅህ” ይሉትና ተነስተው ይቆማሉ። አጋዝ ፋርችየ በአንድ በኩል ወርድወትን ማጣቱና በሴት መደፈሩ ክብሩን የሚነኩበት መሆኑ እያንገበገበው በሌላ በኩል ደግሞ ድፍን ሃገሩ የሚንቀጠቀጥላቸው የሃገር ሽማግሌዎችን ቃል መግፋቱ እንደሚያስረግመው ስለሚያውቅ “እሺ አባቶቼ፣ ከቃላችሁ አልወጣም” ይላል። ምርቃትም ይጎርፍለታል።

ፋርችየም “እኔ ፈትቼሻለሁ። ሌላ የቻለ ያግባሽ” ብሎ መርቆና ፈቅዶ ይሸኛታል። ባህሉ ያስቀመጠውን ገደብ “አንቂት” እንዲነሳ እና የ ፈለገችውን ባል ማግባት እንደምትችል ለ ሽማግሌዎቹ ይነግራል። ሽማግሌዎቹም ወርድወትን “ወስነናል አንቂት አይኑርብሽ። የፈቀድሽውን አግቢ! በፈቀድሽ ጊዜ ፍቺ! መርቀናል፡፡ ነገር ግን በሌላ ሴቶች ኑሮ አትግቢ፡፡” በማለት ቃል ያስገቧታል፡፡ ምንም እንኳ ወርድወት ነፃነቷን ያገኘችና እንዳሻት ማግባትና መፍታት የምትችል ሆኖ የተፈቀደላት ቢሆንም ስትመራው የነበረውና ተቀጣጥሎ ጫፍ የደረሰው የተበደለ ፍትህ ጠያቂ ሴቶች ትግል በወንዶች ሴራና በሴቶቹም መፍረክረክ ምክንያት እንዲህ መሆኑወርድወትን በጣም ያሳዝናታል ፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀምን በደልለማስቀረት ባስተባበረችው ፆታዊ ትግል ያለመችው ግብ ያልመታላት ወርድወት ስሜትዋ ደብዝዞባት ወደአባትዋ ዳሞ ቃቄ ቤት ትመለሳለች፡፡ ቤተሰቦቿም እሷን ደስ ለማሰኘትብዙ ይጥራሉ። ብቸኝነትና ትካዜ ታበዛለች። ብዙ ሰዎች ለትዳር ጥያቄ ሽማግሌ ቢልኩም የትዳርን ዓለም አይንህን ላፈር ብላ ትቆያለች። በኋላም የመረጠችውን የቸሃው ታዋቂ ጀግና ኤስሓርብ ፉጋ ጋር (ኤሰሓርብ ባህላዊ የማዕረግ ስም ነው) ከቀድሞ ሥርጓ የበለጠ ቅልጥ ያለ ሠርግ ተደግሶ ጋብቻ ፈጸመች። ሕይወቷ ብሩህ ሆነ። አዲስና ቀጣይ የኑሮ ምዕራፍ ጀመረች።

ውርደወት እንደ ምዕራባውያን የሴት መብት ተሟጋቾች አለም አቀፋዊ እውቅና ባታገኝም በ ዓለም ላይ የተቀጣጠለውን የሴቶች የፆታ ትግል ሻማውን ከለኮሱት ስመ ጥሮቹ የሠለጠኑ አገሮች ሴቶች ተርታ ልትመደብ ትችላለች። በዚያ የሴቶች መብት፣ የጾታ እኩልነት የሚሉ ዘመናዊ ሐሳቦች ባልዳበሩበት፤ ለሴቶች መብት ቆመናል የሚሉ ተቋማት ባልነበሩበት ዘመን ከዘመኗ ቀድማ ችግሩን የተረዳች፤ የሴቶችን ችግር ለመቅረፍና እናቶቻችን ፍትሕ እንዲያገኙ ለማድረግ የታገለችው ውርድወት በዘመኑ ከነበሩት የ ምእራባውያን የሴቶች መብት ታጋዮች ጋር የሚስተካከል ታሪክ ነው ያላት። ለምሳሌ በ 19ኛው ክ/ዘመን የፆታ ትግል ውስጥ አንፀባራቂ ሥፍራ የነበራቸው እነ ክላራ ዜትኪን (እ.ኤ.አ. በ1857 የተወለደች ፖለቲከኛና የሴቶች መብት ተከራካሪ አክቲቪስት)፣ አንጀላ እና ጀግኒቷ የጥቁሮች መብት ተከራካሪ ሮዛ ፓርክስ በከፍተኛ ትምህርት የታገዙ ናቸው። ውርድወት ግን ጆሮዋ ስለትምህርት ሰምቶ፣ ዓይኗ ፊደል ዓይቶ አያውቅም። ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ነባራዊ ሁኔታ የ ውርድወት ታሪክ እንደ ምዕራባውያኑ ተሟጋቾች በየመረጃ ቋቱ ገብቶና በተለያየ ቋንቋ ተተርጉሞ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲያየው ዕድል አልተፈጠረም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ የቃቄ ውርድወት ትግል የሚያትቱ የተወሰኑ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ተደራሽነታችው ግን ውስን ሆኖ ነበር የቆየው። ከነዚህም መካከል በጸሐፌ ተውኔት ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ የተደረሰው የቃቄ ውርድወት ቲያትር ሲሆን ለሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር መድረክ ታይቷል። ዕውቁ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር) ደግሞ “ዕምቢታ” በሚል ርዕስ የታጋይዋን ታሪክ እጅግ ማራኪ በሆነ መንገድ መጽሐፍ ደርሶና አሣትሞ አበርክቷል። ሌሎችም ጥቂት ሰዎች በመጣጥፎች፣ በግጥሞች፣ እና በሙዚቃዊ ተውኔቶች የ ውርድወትን ትግል መዘከር ችለዋል።

ከዘመኑ ቀድማ የተወለደች የምትባለው ውርድወት ያነሳቻቸው ጥያቄዎች አንዳንዶቹ ዛሬ ላይ በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር ውስጥ ሕጎች የተካተቱ ናቸው ምንም እንኳ ተፈጻሚነታቸው ላይ ውስንነት ቢኖርም። አንዳንዶቹ መብቶች ደግሞ አሁንም አልተመለሱም እሷን መሰል ሴቶችም ለመብቶቹ መከበር እየታገሉ ይገኛሉ።

# አበበች ጎበና (1928 – 2013 ዓ.ም)



ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በሰብዓዊ ምግባራቸው "የአፍሪካዋ ማዘር ተሬዛ" በመባል ይጠራሉ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የህፃናት መርጃ ማዕከል መስራች የሆኑት ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና ጥቅምት 10 ቀን 1928 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፤ በሰሜን ሸዋ ዞን፤ በግራር ጃርሶ ወረዳ፤ ቶርበን አሸ ቀበሌ ልዩ ስሙ ሸበል በሚባል ቦታ ተወለዱ።

አባታቸው ሕፃን እያሉ በኢትዮ ጣልያን ጦርነት ስለሞቱ ዘጠኝ አመት እስኪሆናቸው ያደጉት ከአያታቸው ጋር ነበር። አበበች ጎበና የመጀመሪያ ባላቸውን ገና የአስር አመት ልጅ እያሉ በቤተሠብ እና በዘመድ ግፊት ቢዳሩም በእምቢታ ጥለው ወደ አዲስ አበባ መጡ። አዲስ አበባ ከመጡም በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እድል በማግኘት ቀጥሎም የጥራት ተቆጣጣሪ በመሆን ስራ እየሰሩ ሁለተኛ ትዳርራቸውን መሰረቱ።

በ 1972 ዓ.ም. የሃይማኖታዊ በዓል ለማክበር ለንግሥ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ግሸን ማርያም በሄዱበት ወቅት በኢትዮጵያ በነበረው ድርቅ ምክንያት ከሞት አፋፍ የነበረች አንዲት ሕፃን የእናቷ አስከሬን እቅፍ ስር ሆና ጡት ለመጥባት ስትሞክር ያያሉ። ያኔ ወቅቱ በሀገሪቱ የረሃብ አደጋ ያጠላበት ጊዜ ነበርና ይህ ትዕይንት እጅግ ከፍተኛ ሐዘን ውስጥ ይከታቸዋል። አላስችል ሲላቸው ታዲያ ሕፃኗን ከሌላ አንዲት ሕፃን ጋር ወደ ቤታቸው ይዘው በመመጣት የህፃናት ማሳደጊያ ስራቸውን ሀ ብለው ይጀምራሉ። በዚህ መልኩ በጀመሩት ሥራ በአንድ ዓመት ውስጥ አበበች የሚያሳድጓቸውን ልጆች ቁጥር 21 አደረሰ። ሆኖም ባለቤታቸው ከሕፃናቱ ወይ ከትዳራችን የሚል ከባድ አጣብቂኝ ውስጥ ይከቷቸዋል። እሳቸውም ሕፃናቱን ይመርጣሉ። በዚህ ሰዓት ዘመዶቻቸውም "አብዳለችና ትታከም" ብለው አስተያየት ሰጥተው ነበር። ነገር ግን ምንም ጆሮ ሳይሰጡ ትዳር እና ቤታቸውን ጥለው ዶሮ ለማርባት ይሆነኛል ብለው ወደ ገዙት ቦታ ከሚያሳድጓቸው ህፃናት ጋር ለመኖር አቀኑ።ከትንሽ ግዜም በኋላ አበበች ጎበና የሕፃናት ክብካቤና ልማት ማኅበር (አጎሕልማ) መሰረቱ። ወላጅ አልባ ሕፃናትን በመንከባከባቸው፣ ሕይወታቸው መስመር እንዲይዙ በማስቻላቸው ብዙኃኑ "እዳዬ" እያሉ ሲያቆላምጧቸው ኖረዋል።

ሕፃናትን ከመንከባከብና ከማስተማር ባለፈ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ሴቶች በልዩ ልዩ መንገድ በመርዳት ኑሮአቸው እንዲሻሻል አድርገዋል። ድህነትን በተለይም የሕፃናት ጉስቁልናን መቅረፍ የሚቻለው በግለሰብ ደረጃ ለምፅዋት በሚወረወሩ ሽርፍራፊ ሳንቲሞች ሳይሆን፣ በአንድነት በማበርና ያለንን አቅም በማሰባሰብ በችግር ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በተለይም ሴቶችን ስናበቃ ነው፤ የሚል እምነት ነበራቸው።

አበበች ጎበና በህይወት ዘመናቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ወላጅ አልባ ህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ እንዲያገኙ በማድረጋቸው ፤ የጤና አገልግሎትን፣ የሴቶች አቅም ማጎልበቻ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎችን በማመቻታቸው እንዲሁም በርካቶችን ተጠቃሚ ያደረጉ የሰብዓዊ ድጋፍ ስራዎችን ማከናወን የቻሉ የ ሰብአዊነት አርአያ ነበሩ። አበበች ጎበና ስለ ሰብዓዊነት ላበረከቱት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከ16 በላይ ዓለም አቀፍ ፤አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ እውቅናና ሽልማቶችን ማግኘት ችለዋል። ለወላጅ አልባ ህጻናት እና ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ያላቸው ርህራሄና ባደረጉት ድጋፍ በሀገራችን በሰብዓዊነት ተግባራቸው በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ የ ሰብዓዊነት ውሃ ልክ ነበሩ።

## ቦጋለች ገብሬ (ፒ.ኤች.ዲ) (1952-2012 ዓ.ም)



ብዙዎች በቅጽል ስም «ቦጌ» እያሉ ነበር የሚጠሯቸው። የሕክምና ባለሙያዋ ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ እንደ ስማቸው ቦግ ብለው ብርሃን ያንፀባረቁበት አንዱ ተግባራቸው በትውልድ ቦታቸው፣ የከምባታ ሴቶች በአንድነት ቁሙ የሚል ፍች ያለውን “ከምባቲ ሜንቲ ጌዚማ ቶፔ” (Kembatti Mentti Gezzima-Tope) ከእህታቸው ፍቅርተ ገብሬ ጋር መመሥረታቸው ነበር።

ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ ዛቶ በሚባል በቀድሞው ከምባታ ክፍለ ሀገር ውስጥ በሚገኝ መንደር ተወለዱ። ሴትን ልጅ ማስተማር ይጠቅማል ብሎ ከማያስብ ኅብረተሰብ 14 ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ የተወለዱት ዶክተር ቦጋለች በልጅነታቸው እስከ 4ኛ ክፍል ዘልቀው መማር መቻላቸውን ተናግረዋል። ሴት ልጅ ከዚያ አልፋ እንትማር በማያበረታታው ባህል ውስጥ ቢያድጉም በሚስዮናውያን ርዳታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው አዲስ አበባ ላይ ባገኙት የነጻ ትምህርት ዕድል በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ማጠናቀቅ እንደቻሉ ታሪካቸው ያስረዳል። በዚህ አላበቁም ፊዚዮሎጂ እና ማይክሮ ባዮሎጂን ለማጥናት የነፃ ትምህርት ዕድል አግኝተው ወደእስራኤል በመጓዝ በሂብሩ ዩኒቨርሲቲ ተማሩ። ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደሀገራቸው በመመለስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እያገለገሉ ከቆዩ በኋላ በድጋሚ የትምህርት ዕድል ወደዩናይትድ ስቴትሱ ማሳቹስቴትስ ዩኑቨርሲቲ ጥገኛ ተህዋሲያንን የሚመለከተውን የፓራሳይቶሊጂ ጥናታቸውን ማካሄዳቸውን ታሪካቸው ያስረዳል።

በ1989 ዓ.ም ወደ አገራቸው በመመለስ በእርሳቸው ላይ ሲደርስ የነበረው በደል በሌሎች ላይ እንዳይደርስ ለመሞገት ከምባታ ጠንባሮ ዞን የተጀመረውን እና ‘ከምባቲ ሜንቲ ጌዘማ’ [ኬ ኤም ጂ] ወይንም የከምባታ ሴቶች ራስ አገዝ በመባል የሚታወቀውን አገር በቀል ድርጅት መስርተዋል።

በ1989 ዓ.ም. የተቋቋመው ‹ኬኤምጂ› በወቅቱ በሰፊ ተዛምቶ የነበረውን ኤችአይቪን መከላከል፣ የሴቶችን መጠቃት፣ የልጃገረዶችን ግርዛት፣ ጠለፋንና ሌሎችም ለሴቶች ጎጂ የሆኑ የልማድ ተፅዕኖዎችንና ልምዶችን የመግታት ዓላማ አንግቦ ነበር የተንቀሳቀሰው።

ቦጋለች ገብሬ ትኩረት አድርገው ሲሰሩ የነበሩት የሴቶችን ህይወት ማሻሻል ላይ ነበር። የሴት ልጅ ግርዛት እና ሌሎች እንደ ያለዕድሜ ጋብቻ እና ጠለፋ ያሉ ጎጂ ልማዶች በማህብረሰቡ ውስጥ ስር የሰደዱ ባህሎች መሆናቸውን ተረድተው ድርጊቶቹን ከመቃወማቸው በፊት የማህበረሰቡን እምነት እና ክብር ሳይነካ ማስተማር እንዳለባቸው ተገንዝበው ነበር። የሴት ልጅ ግርዛት እና ሌሎች ጎጂ ልማዶች በሴቶችና ልጃገረዶች ጤና እና ስነልቦና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለማሳየት እውነታዎችን፣ ማስረጃዎችን እና ምስክርነቶችን ተጠቅመዋል። እነዚህ ድርጊቶች በፈጣሪ እና በህግ የተደነገጉ ሳይሆኑ የሴቶች እና ልጃገረዶች ክብርና መብት የሚጋፉ መሆናቸውን ለማሳየት ሃይማኖታዊ እና የሰብአዊ መብት ክርክሮችን አድርገዋል።

የቦጋለች ገብሬ ስራ በኢትዮጵያ በሺዎች በሚቆጠሩ ሴቶች እና ልጃገረዶች ህይወት ላይ አስደናቂ ተጽእኖ አሳድሯል። ኬኤምጂ ኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭትን በከምባታ ወደ 3 በመቶ ፣ በሲዳማ ደግሞ ወደ 27 በመቶ እንዲቀንስ ማድረጉን የተለያዩ ሪፖርቶችና ጥናቶች ያመላክታሉ። ፕሮጀክቱ በተተገበርባቸው አካባቢዎች ያለዕድሜ ጋብቻ እና ጠለፋን ከ90 በመቶ በላይ መቀንስ መቻሉም ይጠቀሳል። አሥር ሚሊዮን ችግኞችንም በማስተከል የአካባቢው ሥነ ምኅዳር እንዲሻሻል ጥረት ማድረጋቸው በገጸ ታሪካቸው ተመልክቷል።

በማኅበረሰቡ አስተሳሰብ ላይ በወንዶችም ጭምር ዓይነተኛ ለውጥ እንዲመጣ የማኅበረሰብ ውይይትን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው፣ በሁሉም የገጠር ክፍሎች ተግባራዊ ማድረጋቸው ለውጡም እንዲመጣ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው እ.ኤ.አ በ2002 ከንባታ ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ ያልተገረዘች ሴት ባል ማግባት ችላለች።

ዶ/ር ቦጋለች የእናቶችና ማህፀን ሆስፒታል ከንባታ ውስጥ እንዲሠራ፣ ሴት ተማሪዎች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ አስተዋጽኦ በማድረግ አይደፈሬ የነበረውን የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተፅዕኖን ሰብረው በማኅበረሰብ ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ አስችለዋል።

ዶ/ር ቦጋለች ላከናወኑት ላቅ ያሉ ተግባራት በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አገራዊ ተቋማት ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል። ጥቂቶቹም እ.ኤ.አ. በ2005 ከአውሮፓ ምክር ቤት የኖርዝ ሳውዝ ፕራይዝ፣ መቀመጫውን አሜሪካ ባደረገው የዓለም ጤና ምክር ቤት የጆናታን ማን አዋርድ (2007)፣ ከቤልጂየም የኪንግ ባውዶዩን (Baudouin) ኢንተርናሽናል ዴቨሎፕመንት ፕራይዝ (2013) ሲሆኑ፣ በአዲስ አበባም በ2008 ዓ.ም. የበጎ ሰው ተሸላሚ ሆነዋል።

የቀድሞዋ የአሜሪካን ቀዳማዊት እመቤት ሄላሪ ክሊንተን ዶ/ር ቦጋለች  ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ዶክተር ቦጋለች ገብሬን "የኢትዮጵያ ሴቶች የትግል ጀማሪ" በማለት አወድሰዋቸዋል። ዶክተር ቦጋለች አንድ ሰው ነገር ግን ለሚሊዮኖች መፍትሔ የሆኑ ከራሳቸው ህይወት በላይ ለህዝብ የኖሩ ታላቅ የ ሀገር ባለውለታ ናቸው።

## ዘሚ የኑስ (1951- 2013 ዓ.ም)



ድምፅ አልባውን የልጆችን ስቃይ ያደመጡ፣ የእናቶችን ሀዘን ቀድመው የተረዱ ሴት ናቸው ይሏቸዋል። "ልጄን የማስርበት ሰንሰለት ስጡኝ" ለሚሉ በርካታ እናቶች ደርሰዋል። የጆይ የዘላቂ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት እክል (ኦቲዝም) ማዕከል መሥራች  ዘሚ የኑስ።

ወይዘሮ ዘሚ የተወለዱት የዛሬ ሃምሳ አምስት ዓመት በፊት ጥቅምት 7 ቀን 1951 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ጣሊያን ሰፈር በሚባለው መንደር ነው። የአቶ አህመድ የኑስና የወይዘሮ ድሐብ ፎሌ አምስተኛ ልጅ የሆኑት የዚያን ጊዜዋ ህፃን ዘምዘም በካቴድራል ሴቶች ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን የጀመሩት ገና በስድስት ዓመታቸው ነበር። በልጅነታቸው ለሥነ ጥበብ (አርት) ዝንባሌ ነበራቸው።

የስምንተኛ ክፍልን ብሔራዊ ፈተና አልፈው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ቤተሰቦቻቸው ልጃቸውን ናዝሬት ትምህርት ቤት ለማስገባት ያቅዳሉ የዚያን ጊዜዋ ተማሪ ዘምዘም ግን ከጓደኞቻቸው "አልለይም» በማለታቸው የእቴጌ መነን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ ተማሪ ዘምዘም በት/ቤቱ የቆዩት ለሦስት ወራት ብቻ ነበር።

በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር የነበሩት “ሴቶችን የሚያንቋሽሹና የሚያዋርዱ» ምሳሌያዊ አባባሎችን እንዲነግሯቸው ወይም በጽሑፍ እንዲሰጧቸው ይጠይቋቸዋል። የመምህሩ ጥያቄ ያናደዳቸው የዛኔዋ ተማሪ ፊት ለፊት ለመቃወም እንደማይችሉ ያምናሉ። ጉዳዩን ለትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ቢከሱም ተደማጩ አስተማሪው ሆነ።

የመምህሩ ፀረ-እኩልነት አስተሳሰብ ያስቆጣቸው ወይዘሮ ዛሚ ጉዳዩን ለአባታቸው በመንገር የሚወዱትን የአማርኛ ትምህርት በአግባቡ ይከታተሉ ዘንድ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲያስገቧቸው ይጠይቋቸዋል። በልጃቸው መልካም አስተሳሰብ የተስማሙት አባትም በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ በሚገኘው ንፋስ ስልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ያደርጓቸዋል። በዚሁ ትምህርት ቤት እስከ አስራ አንደኛ ክፍል ድረስ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እያሉ ያልጠበቁት ሁኔታ ይከሰታል።

ወቅቱ የአብዮት ጊዜ ስለነበር ወጣቱ በተለይም ተማሪው እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ በፀረ-ሕዝብነት ተፈረጀ። እናም ተማሪ ዘምዘም በወጣቶች ላይ የሚደርሰው ወከባ አስፈሪ ይሆንባቸዋል። የትምህርት ቤታቸው መዘጋትና መከፈት ያበሳጫቸዋል። ተማሪዎች እየተያዙ ወደ እስር ቤት ሲወሰዱ በማየታቸው ስጋት ውስጥ ይገባሉ። በወጣቱ ላይ ያንዣበበውን ዕልቂት የተገነዘቡት ተማሪ ዘምዘም ወደ ውጭ ሀገር ለመሄድ ታላቅ እህታቸው በፈጠሩላቸው ምቹ ሁኔታ ከቤተሰቦቻቸውና ከሚወዷት አገራቸው ተለይተው በ1969 ዓ.ም ወደ ኢጣሊያ በረሩ።

በጣሊያን በቤተሰብ ቤት ለዚያውም በምኞት ያደጉት ልጅ በምግብ አብሳይነትና በሞግዚትነት ለማገልገል የቤት ሠራተኛ ሆነው ይቀጠራሉ። በዚሁ ስራ ላይ ተሰማርተው በትርፍ ጊዜአቸው ታይፕ እና አረፍት ነገርን ወይም ቃላትን በአጭር የመጻፍ (shorthand) ትምህርት መከታተል ይጀምራሉ። በቤት ሠራተኛነትና በሞግዚትነት በሚያገኙት ገንዘብ እራሳቸውን በፀሐፊነት ከአሰለጠኑ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል የቆዩበትን ሥራ በማቋረጥ በአንድ የስደተኞች ዕርዳታ ድርጅት ተቀጣሪ ይሆናሉ።

በአጭር ጊዜ ውስጥም የፀሐፊነት ሥራቸውን በብቃት በመወጣታቸውና በሥራቸው ያሳዩትን ቅልጥፍናና ትጋት የተመለከቱ የድርጅቱ አመራሮችም የድርጅቱን ሥራ በጉዳይ አስፈፃሚ መኮንንነት እንዲሰሩ የደረጃ ዕድገት በመስጠት ከጣሊያኖች እኩል ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያደርጋሉ።

በአሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው የዕርዳታ ድርጅቱን ከፍተኛ ኃላፊነት ስራ ላይ በመሆን ጠንካራ ሰራተኛ ይሆናሉ። በልጅነታቸው ጥለዋት የወጡት ሀገራቸውና ቤተሰቦቻቸው ናፍቆት አላስቀምጥ ሲላቸው ቤተሰቦቻቸውን ለመጠየቅ አገራቸው ይመለሳሉ። ልክ እንደተመለሱ አስደንጋጭ ችግር ይጋረጥባቸዋል። ቀደም ሲል ፈርተውት የወጡት ደርግ “ኢጣሊያን አገር በምትሠራበት የዕርዳታ ድርጅት ለወንበዴዎች ቪዛ እያዘጋጀች ትሰጣለች» በማለት ፓስፖርታቸውን ይነጥቋቸዋል።

ቆፍጣናዋ ወጣት ግን ጥርጣሬው መሠረተ ቢስ መሆኑንና ሰላማዊ ሰው መሆናቸውን የጣሊያን ኢምባሲ ከመሰከረላቸው በኋላ ፓስፖርታቸው ተመልሶ በአዲስ አበባ የመቆያ ጊዜያቸውን በማሳጠር ወደ ሮም ይመለሳሉ። እንደተመለሱም ከኢጣሊያ እርቀው ለመሰደድ ይወስናሉ። “ዘምዘም» የሚለውን መጠሪያ ስማቸውን ቤት ውስጥ ይጠሩበት በነበረው ስማቸው በሕጋዊ መንገድ አስቀይረው “ዘሚ» በሚል አዲስ ስም ወደ አሜሪካን አገር ተሸጋገሩ።

ከአምስት ዓመት የሮም ቆይታ በኋላ በሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው አሜሪካን አገር የሎስ አንጀለስ ከተማ ነዋሪ ለመሆን ይበቃሉ። ኮዝሞቶሎጂስቷ ወጣት ዘሚ የኑስ ዳግም ለስደት ቢዳረጉም የአገረ አሜሪካ የኑሮ ዘይቤ እምብዛም እንግዳ አልሆነባቸውም። የካቴድራል ተማሪ ስለነበሩም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችግር ስላልነበረባቸው ከሕዝቡ ጋር ለመግባባትም አላዳገታቸውም።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢጣሊያን አገር ይሰሩበት በነበረው ድርጅት ተባባሪ በነበረው የካቶሊክ ወጣት ማዕከል በፀሐፊነት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ስለተፈጠረላቸው በሥራ ፍለጋም አልተንገላቱም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ከልጅነታቸው ጀምሮ በውስጣቸው ከሰረፀው ዝንባሌያቸው ጋር መገናኘት እንዳለባቸው ይወስናሉ፤ ከራሳቸው ጋርም ትግል ይገጥማሉ። ከዛም በዝንባሌያቸው የሥነ-ውበት የትምህርት ተቋም በመግባት የሙሉ ጊዜ ተማሪ ይሆናሉ። ፍላጐታቸውን ለማሳካት በፅናትና በትጋት ትምህርቱን በመከታተላቸውም ሦስት ዓመት የሚፈጀውን ትምህርት በአንድ ዓመት በማጠናቀቅ በዲፕሎማ ይመረቃሉ።

ከውስጣዊ ዝንባሌያቸው ጋር በመገናኘት በተግባራዊ ሥራውም አቅማቸውን ያጐለበቱት ወጣቷ ዘሚ በሁለት እግራቸው በሚገባ መቆማቸውን ካረጋገጡ በኋላ “ኒያና ኢንተርናሽናል» የሚባል የውበት ሳሎን በሎሳንጀለስ ይከፍታሉ።

(“ኒያ» የአረብኛ ቃል ሲሆን “መልካም መንፈስ፣ መልካም ዕቅድ...» የሚል ትርጓሜ አለው) በከፈቱት የውበት ሳሎንም ለስምንት ሰዎች የሥራ ዕድል ይከፍታሉ። በልጅነት የሙያ ዝንባሌያቸው በዕውቀት የታነጹትና በኢኮኖሚ አቅማቸው ያጠናከሩት ወይዘሮ ዘሚ የኑስ “ማን እንዳገር» በማለት ከአስራ ዘጠኝ ዓመት የስደት ህይወት በኋላ ጓዛቸውን ጠቅልለው በ1987ዓ.ም ወደ አገራቸው ይመለሳሉ።

ከዛም በሥነ-ውበት (ኮስሞቲክስ) ሙያ በአገራችን የመጀመሪያ የሆነውን “ኒያና የውበት ሥራ የሥልጠና ማዕከል» የተባለ ትምህርት ቤት በመክፈት ለሰባ አምስት ወገኖቻቸው የሥራ ዕድል ከመክፈታቸው ባለፈም ትምህርት ቤቱን ለጊዜውም ቢሆን እስከ አቋረጡበት 2004 ዓ.ም ድረስ ከስድስት ሺህ በላይ ባለሙያዎችን ማፍራት ችለዋል።

የሥልጠና ማዕከሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በአደረገባቸው ዓመታት በተለይ ችግረኛ ወጣት ሴቶችንና በሴተኛ አዳሪነት ለተሰማሩ ወገኖች ነፃ የትምህርት ዕድል በመስጠት ከችግራቸው እንዲላቀቁ በማድረግ የወገን አለኝታነታቸውን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ከሚሰጡት ሙያዊ ሥልጠና ባለፈ ኤች አይ ቪን በመከላከሉ ረገድ አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በተጨማሪም ወቅታዊ በሆኑ አገራዊ ችግሮች ላይ በንቃት በመሣተፍ በጐ ተግባራትን ፈጽመዋል። ይህ በዚህ እንዳለ የሙያው አፍቃሪዎችን በሥነ-ውበት ሙያ ከማነፅ ባሻገር የውበትን ማራኪነት በመጠቀም “... በአይነቱ የተለየ በአገራችንም የመጀመሪያ የሆነ የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ባህልና አልባሳት የሚያስተዋውቅ አውደ ርዕይ በ1997 ዓ.ም አዘጋጅተው በኤግዚቢሽን ማዕከል በሕዝብ እንዲታይ አደረጉ።”

ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ዘሚ ልጃቸው የኦውቲዝም እክል እንዳለበት ያረጋግጣሉ። በዚህ ምክንያት ሕብረተሰቡ ስለኦቲዝም ማወቅ እንዳለበት ያስባሉ። እናም በተደራጀ መልክ ለዛ በአለው የአነጋገር ብቃታቸው ስለአውቲዝም ያወቁትን ያሳውቃሉ። መገናኛ ብዙኃንም የኦውቲዝሟን “አምባሳደር» ተከትለው ስለ ኦውቲዝም አስተጋቡ።

በእርግጥ ወይዘሮ ዘሚ የኑስ የኦቲዝም እክል ያለበት ልጃቸው ከመሰል አቻዎቹ ጋር በአገሩና በወገኑ መካከል እንክብካቤና ትምህርት ማግኘት አለበት በሚል “...ልዩውንና ፈታኙን የኦቲዝም መጋረጃ በመግለጥ ለምን የብርሃን ጮራ እንዲፈነጥቅ አላደርግም...?”

በማለት ወላጆች ለልጆቻቸው ትልቅ ነገር እንደሚመኙላቸው ሁሉ በኦቲዝም ምክንያት ልጅን በእግር ብረት ማሰር ምን ያህል ዘግናኝና ኢ-ሰብአዊ መሆኑን በየአጋጣሚው ማስተማሩን በትጋት ተያያዙት። ጥረታቸው ፍሬ አፍርቶም የሕዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋሉ። መንግሥትም ድጋፉን ቸራቸው። እናም የሥነ ውበት ሥራ ሥልጠናውን እያካሄዱ በነበረበት ወቅት በተጓዳኝ የአውቲዝምን ጉዳይ ወደ አንድ ታላቅ ታሪካዊ ምዕራፍ ያሸጋግሩታል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነ “ጆይ የአውቲስቲክ ልጆች ማዕከል” የተባለ ተቋምም አቋቋሙ። በዚህም የበርካታ አውቲስቲክ ልጆችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚለውጥ፤ የእርሳቸው ቢጤ እናቶችን የሕይወት ዘመን ሰቀቀንና ሐዘን የሚቀርፍ ማዕከል በማቋቋም የሀገር ባለውለታነታቸውን አረጋገጡ። ማዕከሉ እ.ኤ.አ በ2002 ሥራውን የጀመረው የወይዘሮ ዘሚን ልጅ ጨምሮ በሌሎች ሦስት የአውቲስቲክ ልጆች ነበር።

ያልታዩትን ተመልካች፤ አፍ ለሌላቸው አፍ ሆነው ቤታቸው ውስጥ ተዘግቶባቸው የእናት እዳ የሀገር ሸክም የተባሉትን ልጆች ለማስተማር በዘርፉ መምህራንን ከማሰልጠን ባለፈ በአዲስ አበባ አስር የመንግሥት ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ ክፍል በማዘጋጀት የአውቲስቲክ ልጆች በትምህርት ገበታ ላይ እንዲገኙ ማድረግ ችለዋል።

በኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኙ አምስት ትምህርት ቤቶችም የአውቲዝም እክል ያለባቸው ሕፃናትም ከቤት ወጥተው የትምህርት ቤት ደጃፍን እንዲረግጡ ያደረጉት ወይዘሮ ዘሚ ለአውቲስቲክ ልጆች ብቻ ሳይሆን እንደ እርሳቸው ልባቸው በልጆቻቸው ምክንያት ለተሰበረ እናቶችም አለኝታ ሆነዋል።

ዘሚ የኑስ በነባራዊው ዓለም ውስጥ እውን የሆነውን የሕይወት ውጣ ውረድ በፅኑ መንፈሳዊ ጥንካሬ፤ ወሰን በሌለው የሥራ ትጋት ለዝንባሌያቸው ተገዝተው የሥነ–ውበት ምሁር በመሆን ለአያሌ ወገኖቻችን ሙያቸውንና ዕውቀታቸውን ለማካፈል በቅተዋል። በሥራ ፈጣሪነትና በችግር ፈቺነትም ተሰልፈው ስኬታማ ሆነዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ግንዛቤ አምባሳደር በመሆናቸው ታሪክ ሲዘክራቸው ይኖራል።

## ዘቢዳር ዘውዴ (ሲስተር)



ሲስተር ዘቢዳር ዘውዴ የሜሪጆይ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ በቀድሞ ጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር በጨንቻ ወረዳ በ1955 ዓ.ም ነው የተወለዱት፡፡ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨንቻ፤ የመሰናዶ ትምህርታቸውን ደግሞ በአርባ ምንጭ 2ኛ ደረጃ እና የመሠናዶ ት/ቤት ተከታትለዋል፡፡

የ ነርሲንግ ዲፕሎማ ከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የነርስ ትምህርት ቤት አግኝተዋል፣ ተጨማሪ ትምህርትም ከዲፕሎማ እስከ ማስተርስ በፕሪስተን ዩኒቨርሲቲ ተምረዋል፡፡

በስራ መስክ በጥቁር አንበሳ፣ በየካቲት 12 እና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታሎች አገልግለዋል ፡፡ በኋላም ከኖርዌይ ሴቭ ችልድረን በሊሙ ገነት እና በአዲስ አበባ ቢሮዎች ውስጥ ለስድስት አመታት ሰርተዋል፡፡

ሲስተር ዘቢደር ከነዚያ የስራ ጊዚያት በኃላ የህዝቡን የጤና ችግር ለመቅረፍ በማሰብ በወቅቱ ብዙም ያልተስፋፋ የነበረውን የግል የ ስነ ተዋልዶ ክሊንክ አነስተኛ ቤት በመከራየት ከፈቱ፡፡፡ ሶስት የወሊድ ምጥ ላይ የነበሩ ሴቶች በአንድ ወር ውስጥ ስለሞቱና የእርሳቸውም እህት ምጥ ይዟት ማዋለድ ባለመቻላቸው ነበር “አስኮ ገብርኤል ክሊኒክ” ብለው የሰየሙትን ክሊኒክ ያቋቋሙት፡፡

ይህም ክሊኒክ በሚሰጠው አገልግሎት ዝናው ከፍ እያለ መጣ፡፡ በዚህን ወቅት ነበር ሲስተር ዘቢደር ያላሰቡት የህይወት ገጠመኝ የተከሰተው፡፡ በአፍንጫቸው ውስጥ እጢ መሰል ነገር ወጣባቸው፡፡ እጢው በዘመናዊ ህክምና መዳን ስላልቻለ በሀይማኖታቸው የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታይ ስነበሩ ፀበልና ዕምነት በመውሰድ በ6ወር ውስጥ ተፈወሱ፡፡

በዚህም በ ጥልቅ መንፈሳዊ እና ሰብዓዊ መነሳሳት ክሊኒኩን ወደ በጎ አድራጎት ድርጅት ለወጡት ስሙንም ሜሪጆይ አሉት፡፡ ሜሪጆይ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ሜሪ (ማርያም) ጆይ (ደስታ) የሚል ትርጉም አለው፡፡ ሲስተር ዘቢደር ሜሪጆይን በ 1994 ዓ.ም አቋቁመው 100 ሰዎችን በመርዳት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራቸውን ጀመሩ፡፡

# ትርሃስ መዝገበ



ትርሃስ “ምኅኘኛ ሎካ” የተሰኘው የሴቶች ልማት ማህበር መስራችና ሥራ አስኪያጅ ነበሩ። ‘ምኅኘኛ ሎካ’ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚነገረው የጉሙዝ ቋንቋ የንጋት ብርሃን’ ማለት ነው። የተወለዱት በ 1962 ዓ.ም. በ አስመራ ሲሆን የሁለተኛ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ወደ አዲስ አበባ መጡ። ዘመድ አዝማዶቻቸው ሁሉ ወደ ውጭ እንዲሄዱ ጉትጎታ ያደርጉባቸው ነበር። በወቅቱም ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላት አዲስ አበባ ቢሄዱም ነገሩ አልጋ በአልጋ ስላልሆነላቸው፣ በጓደኛቸው ምክር በአሁኑ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፓዌ ወረዳ አቅንተው በሳሊኒ ኮንስትራክሽን ውስጥ የኩባንያው ሱፐርማርኬት አስተዳዳሪና ገንዘብ ተቀባይ በመሆን ሥራ ተቀጥረው በሚሠሩበት ጊዜ የነፍሳቸውን ጥሪ አገኙ።

በዚህ ጊዜ የጉሙዝ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆነው የመሥሪያ ቤታቸው የጥበቃ ሠራተኛ፣ በተለያዩ ማኅበራዊ ሥነ ሥርዓቶች ላይ እየጋበዛቸው ከአንዳንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች ጋር መተዋወቅ ጀመሩ። ኩባንያው የተለያዩ ድጋፎችን የሚያደርገው ለአካባቢው ተወላጆች ሳይሆን መንግሥት በቦታው ላይ ለመደባቸው ሰዎች ብቻ መሆኑን ሲያውቁ ጉዳዩ አስከፍቷቸው ነበር።

በወቅቱም የደርግ መንግሥት ካከተመ በኋላ፣ ከሥፍራው እንዲለቁ ቤተሰቦቻቸው ግፊት ቢያደርጉባቸውም የጉሙዝ ኅብረተሰብ ጉዳይ ያሳስባቸውና ያስጨንቃቸው ስለነበር እዚያው ለመቆየት ወሰኑ። በ1985 ዓ.ም. በጉዲፈቻ የወሰዷትን እናቷን በኤችአይቪ ያጣች የዘጠኝ ወር ሕፃን ለማሳደግ ለአንድ ዓመት እዚያው ቆዩ። የቤተሰቦቻቸውን ውትወታና ጫና ሲበረታባቸው ግን በ1986 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ሲወስኑ የሕይወት ራዕያቸውን ግልጽ የሚያደርግ አጋጣሚ ተከሰተ።

የሴቶች ቢሮ ኃላፊ ከነበረችው ከጉሙዝ ብሔረሰብ ተወላጇ አሻማ መሀመድ ጋር በመኪና በመጓዝ ላይ ሳሉ ከጫካ ውስጥ ከፍተኛ ጩኸት ሰምተው ወደሰሙበት ጫካ ሲገቡ አንዲት ሴት ራስዋን ዛፍ ላይ ሰቅላ ተመለከቱ። ከአጠገቧ ደግሞ የተወለደው ሕፃን ሕይወት አልፏል። ዙሪያውን የከበቧት ሴቶች በጩኸት ለቅሶአቸውን ያቀልጡታል። ሴቷ ከዚህ ቀደም ስድስት ጊዜ ወልዳ በተደጋጋሚ ሞተውባታል። በድጋሚ ስትወለድ ደግሞ ልጁ ሞቶ እንደተወለደና ሴትየዋ ራስዋን ሰቅላ ለመግደል የወሰነችውም፣ “ከእንግዲህ ከንቱ ነኝ ምንም አልረባም” በሚል እንደሆነ ቦታው ላይ የተገኙት ሴቶች ነገሯቸው።

ሴቶች ልጅ የሚወልዱት ብቻቸውን ጫካ ውስጥ ገብተው መሆኑን ከአካባቢው ተወላጆች ማወቅ ቻሉ። ባዩትና በሰሙት ነገር ውስጣቸው የተነካው ትርሃስ መዝገበ በዚያው ቅፅበት ነበር ውጭ አገር ሄደው የመማር ሕልማቸውን በመተው እዚያው ሆነው የሴቶችን ሕይወት ለመለወጥ የወሰኑት።

ለአንድ ዓመት ያህል ሥራቸውን እንዴት መሥራት እንደሚችሉ በማሰብና ከአካባቢው ሴቶች ጋር በመቀራረብ ከቆዩ በኋላ ሴቶቹ ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት እንዲከፍቱላቸው ጥያቄ ባቀረቡት መሠረት ትምህርት ቤት መክፈት ችለዋል። በወቅቱም በሚያገኙት ገንዘብ ሁለት አስተማሪዎችን ቀጥረዋል።

ትርሃስ “አንድም እናት በወሊድ ምክንያት አትሙት” በሚል መርህ በጫካ ውስጥ የሚወልዱ ሴቶች በቤትና ሆስፒታል ውስጥ እንዲወልዱ ማድረግ ጀመሩ። ይህንንም ለማሳካት ሥር የሰደደ ጎጂ ልማዳቸውን ለመቀየር ሳያቋርጡ ሙሉ ሕይወታቸውና ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ሕይወታቸው እስከሚያልፍበት ሰዓት ድረስ ሲሠሩ ቆይተዋል። በ1996 ዓ.ም. ከፌዴራል የመንግሥት በጎ አድራጎት ድርጅት ፈቃድ በማውጣት ምኅኘኛ ሎካ የሴቶች ልማት ማኅበርን በመሥራችነትና በዋና ዳይሬክተርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። በጉሙዝኛ “የንጋት ብርሃን” የሚል ትርጉም ያለው ድርጅቱ በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች ላይ የሠራ ሲሆን 12 ትምህርት ቤቶችን ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅት ባገኙት ድጋፍ ገንብቷል።

በገጸ ታሪካቸው እንደተጻፈው ወ/ሪት ትርሃስ የመሩት ማኅበር ከ30 በላይ የሴቶች ራስ አገዝ ማኅበራትንና የሴቶች መጠለያና የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከልን፣ ከመገንባት ባለፈ የፌስቱላና የማህፀን መውጣት ችግር የደረሰባቸውን ሴቶችን የሕክምና የኢኮኖሚ ድጋፍ አድርጓል።

በሴት ልጅ ላይ የሚደርስ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ፆታዊ ጥቃቶችን ለማስቆም ከፍተኛ ሥራ የሠሩት ወ/ሪት ትርሃስ፣ ለሴቶች ኢኮኖሚ ዕድገትና መብታቸው እንዲያስከብሩ ትምህርት ሰጥተዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ነዋሪዎችን የጤና ሁኔታ ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ምዥዥጓ ሎካ (የንጋት ብርሃን) የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። በክልሉ የማኅበረሰብ አመጋገብ ሥርዓት ለጤና ሁኔታ መሻሻል ያለውን ከፍተኛ ድርሻ በመረዳት በአመጋገብ ሥርዓት ላይ ሰፊ ትምህርት በመስጠት አመጋገባቸው እንዲሻሻል ተደርጓል።

በጤና ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ሥራ ከተሠራበት ዘርፍ በዋናነት የሚጠቀሰው የእናቶች የወሊድ ሁኔታ መሻሻል ሲሆን፣ በአካባቢው ኋላ ቀር ልማድ ምክንያት ሴቶች በጫካ ውስጥ ይወልዱ የነበረውን ልማድ በማስቀረት በመጀመሪያ ከጫካ ወደ ቤት በኋላም ከቤት ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ እንዲወልዱ በማድረግ ረገድ ወ/ሪት ትርሃስ መዝገበና ማኅበራቸው የነበራቸው ድርሻ ከፍተኛ ነበር። በእርሳቸው ያላሰለሰ ጥረትና ትጋት በአሁኑ ወቅት በጫካ ውስጥ መውለድ ሙሉ ለሙሉ ቀርቷል። ከሴቶችና እናቶች ጤና ጋር በተያያዘ ከተሠሩ ሥራዎች አንዱ በፊስቱላና በእናቶች የማህፀን መውጣት ያጋጠማቸውን ሴቶች ወደ ሕክምና ተቋማት በማድረስ ሕክምና እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

ትርሃስ ላበረከቱት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ የሴት ነጋዴዎች ማኅበርን እና የበጎ ሰው ሽልማት ካበረከቱላቸው ሽልማቶች ሌላ የእናት ባንክ ቁራ አካባቢ የሚገኘውን ቅርንጫፉን በስማቸው ሰይሟል። ትርሃስ የበጎ ፈቃድ ቱባ ምሳሌ ነበሩ። እሳቸው ቁርጠኝነትን፣ ፈቃደኝነትን፣ ነፃ አገልግሎትን፣ ሰብዓዊነትን፣ ዓለም አቀፋዊነትን እንዲሁም የማኅበረሰቡን እሴቶች ማክበርን እና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆንን የሚያሳይ ደማቅ አስተማሪ ማንነት ነበራቸው።

## ማሪያ ሙኒር



ማሪያ ሙኒር የሕግ ባለሙያ ናቸው። ረዥም ዓመታት በዳኝነት አገልግለዋል። ጠበቃም ነበሩ። የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ሲቋቋም በማኅበሩ ነፃ የሕግ ምክር አገልግሎት ይሰጡ ነበር። የማኅበሩ የቦርድ አባል የነበሩት ወይዘሮ ማሪያ በወቅቱ የማኅበሩ የሕግ ቢሮዎች እንዲከፈቱም ተንቀሳቅሰዋል። የሕግ ምክር አገልግሎት ለማግኘት ወደ ማኅበሩ ይሄዱ የነበሩ ሴቶችና ሕፃናት ማረፊያን ጨምሮ ሌሎች ችግሮች ያጋጥሟቸው ስለነበር ጥቃት የደረሰባቸውና የምክር አገልግሎት የሚሰጣቸው ሴቶችና ሕፃናት ያርፉበት ዘንድ ከሌሎች የሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የቀድሞውን ጾታዊ ጥቃት ተከላካይ ማኅበር የአሁኑን የሴቶች ማረፊያና ልማት ማኅበር እ.ኤ.አ. 2003 አቋቁመው በሥራ አስኪያጅነት በመምራት ላይ ይገኛሉ።

ማሪያ ትውልድና እድገታቸው በአዲስ አበባ መርካቶ አካባቢ ሲሆን ከአካባቢው የወረሱት አብሮ የመኖር፣ የመረዳዳት እና ጠንካራ የማህበራዊ ህይወት ለዛሬው ማንነታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይናገራሉ። ለትምህርት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጡ የነበሩት አባታቸው ከትምህርት ጎን ለጎን የበጎፈቃደኝነት ስራን ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን ራሳቸውን ችለው እንዲፈጽሙ ያበረታቷቸውም ነበር። በግል ህይወታቸው ያጋጠሟቸው ችግሮችም ለጥንካሬያቸው የራሳቸው አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ይናገራሉ። የልጅነት ባለቤታቸውን በደርግ ሥርዓት ወቅት በደርግ ግድያ ያጡት ማሪያ መሞቱን ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሁለተኛ ልጃቸውን እርጉዝ ሆነው የሰሙ ሲሆን "ጥንክር ብዬ ልጆቼን እንዳሳድግ፣ በእግሬም እየተመላለስኩ የህግ ዲፕሎማዬን እንድጨርስ ምክንያት ሆኖኛል" ይላሉ። በመቀጠልም በልጆቻቸው አነሳሽነት የህግ ዲግሪያቸውንም ሊጨርሱ ችለዋል።

በጊዜው ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ እየሠሩ የነበረ ቢሆንም ከመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት ሊያድጉ ችለዋል። በወቅቱ በሚያዩት ሁኔታ ተነሳስተው የህግ ምክር ለማግኘት አቅሙና ድጋፉ የሌላቸውን ሴቶች ለመወከል በሚል ከሌሎች ሴት የህግ ባለሙያ እህቶች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበርን(EWLA) ሊያቋቁሙ ችለዋል።

ለብዙ ግዜያት በማህበሩ ስር የነፃ ህግ ምክር መስጠት የቀጠሉ ሲሆን የሰኞ ሰኞ ተረኛ ነበሩ። ማሪያ በማእከሉ  ከ8000 በላይ ለሚሆኑ ሴቶች ነፃ የሕግ ምክር በመስጠት ከማእከሉ ሽልማት ለማግኘት በቅተዋል። በዚህም ሳያበቁ የህግ እርዳታ ፈልገው የሚመጡ ሴቶች ለዘመናት አብረው ካፈሩት ቤትና ንብረት ተባረው፣ ለዕለት መጠለያና ጉርስ ሳይኖራቸው ከልጆቻቸው ውጪ ባዶ እጃችውን እንዲሚወጡ ያስተዋሉት ማርያ “የፆታዊ ጥቃት ተከላካይ ማህበርን” ሊያቋቁሙ ችለዋል። አዲሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕግ እኤአ 2009 ከፀደቀ በኋላም ማህበሩ በድጋሚ የሴቶች ማረፍያ እና ልማት ማህበር ተብሎ ሊመዘገብ ችሏል። የፆታዊ ጥቃት ተከላካይ ማህበር ተብሎ ከተመሰረተበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ከ4,500 በላይ ለሚሆኑ ሴቶች እና ህፃናት የተለያየ ድጋፍም አድርጓል፡

በአሁኑ ወቅት ማህበሩ የፆታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴት ልጆችና ወጣቶችን ሥልጠናና የህግ ድጋፍ በመስጠት የራሳቸው ገቢ ኖሯቸው የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ ለማድረግ የሚሠራ ሲሆን በርካታ ህፃናትና ሴቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። መጠለያው ምግብ፣ ማደሪያ፣ የምክር አገልግሎትና የተለያዩ ስልጠናዎችን ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ በሁለት የተከፈለ የትምህርት ፕሮግራምም አለው። የመጀመሪያው አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥበት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ  የተለያየ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው እና ትምህርታቸውን ቤታቸው ሆነው መከታተል ለማይችሉ ሴቶች ዩኒቨርስቲ እስኪጨርሱ ድረስ የረጅም ጊዜ ድጋፍ የሚሰጥበት ነው። ከአዲስ አበባው መጠለያ በተጨማሪ በአዳማ ከተማም እንዲሁ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ደህንነታቸውን በጠበቀ መልኩ ሁለት መጠለያዎች ከ24 ሰዓት የህክምና አገልግሎት ከሚሰጥ ክሊኒክ ጋር ያቀርባል። በተጨማሪም በሐዋሳና ደሴ መጠለያዎች ሲኖሩት በአጠቃላይ በአምስት ቅርንጫፎች ተደራሽነት አለው።ወይዘሮ ማሪያ ሙኒር ዘመናቸውን ሙሉ ለጥቃት የተጋለጡ እና ችግረኛ ሴቶች እና ህጻናትን እንባ ሲያብሱ የኖሩ ፣ ዳግም የተስፋና የራዕይ ባለቤት ያደረጉ  ሰብዓዊነት ቀንዲል ናቸው።

## ሳባ ገብረመድህን



ሳባ ገብረ መድህን የህግ ባለሙያ እና የሴቶች መብት ጠበቃ ናት። አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው ሳባ የመጀመርያ ዲግሪዋን በሕግ፣ ሁለተኛ ዲግሪዋን ከአየርላንድ በስነ ጾታ መብቶች አግኝታለች። የስራ አለም የጀመረችው በፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ በልዩ አቃቤ ህግነት ነበር። በዚህ አገልግሎቷም በደርግ የአስተዳደር ዘመን የተፈጸሙ ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና ወንጀሎችን በመመርመር ፍትህ እንዲበየን አድርጋለች። በተጨማሪም በረዳት ዋና አቃቤ ህግ፣ በረዳት ዳኝነት፣ እንዲሁም በህግ አማካሪነት በሀገር በቀል እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ሰርታለች። በአለም አቀፍ ድርጅቶች በአማካሪነት የሰራች ሲሆን በምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነመንግስታት ድርጅት/ኢጋድ/ እና የአፍሪካ ህብረት የስርአተ ጾታ ቢሮዎች የነበራት አገልግሎት ተጠቃሽ ነው። ሳባ ለግፉአን በምታደርገው የችሎት ተጋድሎ በተጨማሪ ለፍትህ፣ ለርትዕ እና ለእኩልነት መስፋፋት መታገል እና ድምጻቸውን ማሰማት እንዳለባቸው የወሰነችው ገና በጠዋቱ ነበር።

ምንም እንኳ በልጅነቷ ፍቅር የተሞላበት ቤተሰብ ዉስጥ ብታድግም በኃይል አለመመጣጠን ምክንያት በሴቶችና ልጅአገረዶች ላይ የሚደርሱ ትንኮሳዎች እና አሉታዊ ተራዛሚ ተጽእኖዎቹ ያሳስባት ነበር። ሳባ በትምህርትም በችሎት አደባባይም በዋለችበት ወቅት ከቀሰመችው ልምድ በመነሳት በሴቶችና ልጃገረዶች የራስ መተማመንና ወደፊት እንዳይራመዱ የሚደርገው መሰረታዊ ምክንያት መዋቅራዊ መሰረት እንዳለው ለመረዳት ብዙ አልፈጀባትም። በዚህ መረዳት እና መግፍኤ ነበር የሴቶችን መብት ለማስከበር ከተቀነበበ የፍርድ ቤት እና የችሎት ትግል ባሻገር ሰፋ ያለ የማንቃት፣ የመወትወት፣ እና የማብቃት ስራ መስራት እንዳለባት የወሰነችው። ሳባ በ 1980ዎቹ ነበር ከችሎት ባሻገር ያታዊ ጥቃትንና ህግን መሰረት ያላደረጉና ተጠያቂነት የጎደላቸዉን አሰራሮችን ለማስወገድ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ የጀመረችው። ይህንን ራእይም ለማሳካት ከሌሎች መስራች አባላቶች ጋር በ 1987 የተመሰረተውን የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር መስርታ በደንብ እንዲቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች።

ሳባ በ1995 ዓ.ም የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅትን ከመሰረቱት መስራች አባላት አንዷ ነች። የኋላ ኋላም የተቋሚ ዳይሬክተር በመሆን በኢትዮጵያ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥና የሴቶችን መብቶች ለማስጠበቅ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች።

ሳባ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅትን ህልውና በማስጠበቅ ረገድ ስኬታማ ስራ ሰርታለች። በተለይም ከ1990ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ መጥበብ የጀመረው የሲቪክ ማህበራት መንቀሳቀሻ ሜዳ ተቋሚቱን አንገዳግዷት ነበር። በ2001 ዓም የወጣው አሳሪ የመያድ ህግ ደግሞ የሰብዐዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ከውጭ እርዳታ እንዳያገኙ በመከልከሉ በቅንጅቲቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች ሊዘጉ ችለዋል።

ሳባ የጥምረቲቱን ህልውና ለማስጠበቅ ለሁለት ከፈሏት። አንደኛዋ የተሟላ የውትወታ(lobby) እና የግፊት ስራ የምትሰራ (advocacy) ስትሆን ሌላኛዋ ደግሞ የሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ላይ ትሰራ ነበር። ሁለተኛዋ ጥምረት ማለትም የሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ላይ የምትሰራዋ ከውጭ ለጋሾች ሃብት ስታገኝ ስለነበር የውትወታ እና የግፊት ስራ ለምትሰራው ጥምረት ህልውና መረጋገጥ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ አድርጋለች።

ሳባ ከዚህ በተጨማሪም የአሳሪ ህጉ በ2011 ዓ.ም እስኪሻር ድረስ የተለያዩ የሀብት ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ አባላትን በማስፋት ጥምረቶቹ ተጽእኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ አስችላለች።

ከሳባ ታላላቅ አበርክቶዎች መካከል በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት አሳታሚነት እና በሳባ አርታኢነት በ 2007 ዓ.ም የኢትዮጵያ ስኬታማ ሴቶችን ታሪክ የሚዘክር መጽሃፍ ህትመት ነው። መጽሃፉ በኢትዮጵያ ስለስኬታማ ሴቶች የተጻፈ የመጀመሪያው መጽሃፍ ሲሆን በአሜሪካዊቷ ሜሪ ጄን ዋግል ተዘጋጅቶ በታዋቂዋ ፎቶግራፈር አይዳ ሙሉነህ የምስል ማስረጃዎች አበርክቶ እንዲሁም በ ሳባ የአርትኦት እገዛ እውን ሆኗል። መፅሃፉ የኢትዮጵያ ሴቶች ከጥንት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የተጫወቱትን ጉልህ ሚና የሚዘክር ሲሆን በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው አንፀባራቂ ውጤት ያስመዘገቡ የ64 ኢትዮጵያዊያን ሴቶችን ታሪክ አካትቷል። በጋዜጠኝነት፣ በህግ፣ በንግድ፣ በህክምና፣ በግብርና፣ በኪነጥበብ፣ በማህበረሰብ አገልግሎት፣ በግንባታ ሙያ፣ በበጐ አድራጐት፣ በአመራር እና በሌሎች የሙያ ዘርፎች ለስኬት የበቁ እንስቶች የተካተቱበት መፅሃፉ፤ 298 ገፆች ያሉት ሲሆን በላቀ ጥራትና በማራኪ ዲዛይን ተዘጋጅቶ እንደታተመና 30 ሺህ ኮፒ ለት/ቤቶች፣ ለቤተመፃህፍትና የልጃገረዶችና ወጣት ሴቶችን አቅም በማጐልበት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች በነፃ ተከፋፍሏል።

ሳባ በተለያዩ ድርጅቶች ባላት ተሳትፎ ለሴቶች መብትና ፍትህ እንዲሁም ለድህነትና ማህበራዊ ችግሮች መወገድ አበክራ እየሰራች ትገኛለች። ሴቶች እምቅ ኃይላቸዉን እና መብቶቻቸዉን እንዳይጠቀሙ የሚገድቧቸዉን ፆታዊ ጥቃትንና ህግን መሰረት ያላደረጉና ተጠያቂነት የጎደላቸዉን አሰራሮችን ለማስወገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እያደገች ነው። በተለይም የ 2010ሩን ለውጥ ተከትሎ የዕጩ ሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ፣ የተለያዩ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ሳባ የሚመሩት የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። ወይዘሮ ሳባ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ በአገራዊ ምርጫዎች እያንዳንዱ ፖለቲካ ፓርቲ ከሚያሳትፏቸው ዕጩዎች 50 በመቶ ያህሉን ሴት ዕጩዎች ማቅረብ አለባቸው በሚለው ሙግቷ ትታወቃለች።

ሳባ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሴት ዕጩዎችን ለምርጫ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማድረግ እና ሴቶችን ዕጩ አድርጎ ማምጣት የፆታ እኩልነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን መራጭ የማብዛት ጉዳይ ጭምር እንደሆነ በመጠቆም፤ እያንዳንዱ ተፎካካሪ ፓርቲ 50 በመቶ ዕጩዎችን ሴት ቢያደርግ ተጠቃሚ ይሆናል ትላለች።

ሳባ  ለውጡን ተከትለው የተጠነሰሱት የሃገራዊ ምክክር እና የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማእቀፎች እና የትግበራ ሂደቶች የ ስርዓተ-ፆታን እንዲያካትቱ እንዲሁም የሴቶችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጡ የውትወራ ሥራዎችን ትሰራለች። ይህንንም ለማሳካት የጥምረት ለሴቶች ድምፅ በሀገራዊ ምክክር መድረክ ሥራ አስፈጻሚ የኮሚቴ ሰብሳቢ ናት። ሳባ የጾታ ማነቆዎች ሳያግዷት ለሴቶች መብት የታገለች እና የርትእ አርበኛ ከሆኑት እንስቶች መካከል የምትመደብ ሲሆን ለብዙ ወጣቶች አርአያ መሆን ችላለች።

## የትነበርሽ ንጉሴ



የትነበርሽ ንጉሴ የሕግ ባለሙያ፣ የአካል ጉዳተኞች መብት ተሚጋች፣ ገጣሚ፣ የመድረክ ትንታግ ተናጋሪ፣ ፣ የአካታችነት አስተሳሰብ አራማጅ ፣ የሴቶች እና ልጃገረዶችን መብት ለማስከበር፣ አካል ጉዳተኞችን በትምህርቱ እና በሌላውም ዘርፍ የማያገል አካታች ሥርዓት ለመፍጠር ያልተቆጠበ ጥረት ካረጉ ሴት ኢትዮጵያውያን ግንባር ቀደም ናት።

የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞች እኩልነት መታገል ከጀመረች ብዙ ዓመታት ሆኗታል። በተወለደችበት እና ባደገችበት ኢትዮጵያ ውስጥ አካል ጉዳተኝነት በብዙዎች ዘንድ እንደ እርግማን እና እንደ መጥፎ ምልክት ነው የሚታየው፣ በዚህም የተነሳ አካል ጉዳተኞች የመገለል እጣ እንደሚደርስባቸው ይታወቃል። ሆኖም፣ ለአካል ጉዳተኞች መብት በተሟገቱባቸው ባለፉት ዓመታት በህብረተ ሰቡ ዘንድ  ስለአካል ጉዳት ያለው ግንዛቤ፣ በተለይ መገለሉ እንደቀነሰ ይታወቃል።

በአምስት ዓመቷ በማጅራት ገትር ህመም ምክንያት የዓይኗን ብርሀን ባጣችበት ጊዜ በተለይ ለዓይነ ስውራን በተከፈተ የመጀመሪያ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርቷን የመከታተል እድል ማግኘቷ የዕድል በር እንደከፈተላት እና አካል ጉዳተኝነት ሊያስከትላቸው ከሚችሉ ችግሮች ነፃ እንዳወጣት ዛሬ የሚትናገረው የትነበርሽ  በተለይ አካል ጉዳተኞች የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያሸንፉ የሚችሉት በትምህርት ነው ብላ ስለምታምን ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ ትሰራለች።

የከፍተኛ ትምህርቷን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመግባት በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ፤ እንዲሁም በሶሻል ወርክ የማስተርስ ዲግሪዋን ተቀብላለች። የትነበርሽ ንጉሤ ለአካል ጉዳተኞች መብት መሟገት የጀመረችው በዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርቷን በመከታተል ላይ በነበረችበት ወቅት ነው። በዩኒቨርስቲ አስተዳደር ውስጥ እርሷን ጨምሮ፣ ለአይነ ስውራን ተማሪዎች የብሬይል መጽሕፍ እንዲዘጋጅ አስተዋፅዖ አድርጋለች።

በአሁኑ ሰዓት Ethiopian Center for Disability & Development በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ በሥራ አስኪያጅነት በማገልገል ላይ የምትገኝ ሲሆን ድርጅቱ በዋናነት የሚሰራው አካል ጉዳተኞችን አጠንክሮ የልማት አጋር ማድረግ ላይ ነው። በዚህ ፕሮግራም በዓመት ከ3ሺህ በላይ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚዎች ናቸው። በተጨማሪም የሥራ ዕድል በማመቻቸት፣ እነሱን የሚመለከቱ የሥራ ማስታወቂያዎች ሲወጡ በኢሜልና በስልክ ማሳወቅ፣ ሕፃናትን ለትምህርት ማዘጋጀት በመሳሰሉት ዙሪያ ይሰራል።

በተለያዩ የአገር ውስጥና የውጪ መድረኮች ላይ በምታቀርባቸው ጥናታዊ ፅሁፎች የሚከፈላትን ገንዘብ በመቆጠብ "የትነበርሽ ቦረና አካዳሚ" የተባለ ት/ቤትም ከፍታለች። ትምህርት ቤቱ ለማንኛውም ልጅ ምቹ ሆኖ የተሠራ ነው። በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ሠላም፣ ፍትህ፣ አንድነት፣ እና የብሔራዊ መግባባት እንዲሁም እርቅ እንዲወርድ ለመስራት አልሞ በ2011 ዓ.ም ላይ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ እርቀ ሰላም ኮሚሽንን በምክትል ሊቀመንበርነት መርተዋል።

የትነበርሽ በተለያዩ ዘርፎች ላበረከተችው አስተዋጽኦ ሽልማቶችን አግኝታለች። በ2003 በአካል ጉዳተኞችና በኤችአይቪ ዙሪያ ላደረገችው ከፍተኛ አስተዋፅዖ በደቡብ አፍሪካ የሂውማኒቴሪ አለም አቀፍ ሽልማት አግኝታለች። በ2010 ዓ.ም. ለተለያዩ ችግሮች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሔዎችን በማፈላለግ የተሻለች ዓለም ለመፈጠር ለሰሩ ትጉህ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚሰጠው ራይት ላይቭሊሁድ አዋርድ የተባለው አማራጭ የኖቤል ሽልማት ተሸልመዋለች። ከዚህም በተጫማሪ እ.አ.አ በ2011 ከአሜሪካ አለም አቀፍ የሴቶች ጥምረት እንዲሁም በ2015 በሲቪል ማህበራት ዘርፍ የአፍሪካ ተፅእኖ ፈጣሪ ሴቶች በመባል ሽልማቶችን አግኝታለች። ባለብዙ ተሰጥኦ ባለቤት የሆነችው የትነበርሽ የሰው ልጅ አላማ ካለው እና ጠንከሮ ከሰራ ማሳካት የማይችለው ግብ እንደሌለ ያሳየች ተምሳሌት የሞላባት ድንቅ እንስት ናት።

## ሀናን ማህሙድ



ሀናን ማህሙድ የባቡል ኸይር በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። የመልካም በር የሚል ትርጉም ያለው ባቡል ኸይር፣ በየእለቱ ድግስ ያለበት ይመስላል። በቀን ከአራት ሺሕ በላይ ዜጎች የሚመገቡበት፣ የተቸገሩ የሚጠጉበት፣ አቅም ያላቸው ሠልጥነው ራሳቸውን የሚችሉበት ነው። በሀይማኖት ሳይለይ፣ ሰውነትን ቋንቋው አድርጎ የተቸገሩትን ሁሉ እያስጠጋ ይገኛል።

ሀናን ማህሙድ ሁለት ታዳጊ ሴቶች በትምሕርታቸው ሰዓት ምግብ ፍለጋ ሲንከራተቱ"በማየታቸው ለሐሳቡ መነሻ እንደሆናቸው ትናገራለች። ሀናን በዐይናቸው ያዩት እና የብዙ ኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው አጋጣሚ ልባቸውንን በመንካቱ፣ ምስኪኖች ምንም መስፈርት ሳያስፈልጋቸው የሚመገቡበትን የበጎ አድራጎት ማዕከል ለመክፈት በፍጥነት እንቅስቃሴ ጀመሩ። ከዚያም ከጓደኞቻቸውጋር በመነጋገር ያላቸውን ገንዘብ በማዋጣት እንዲሁም ጌጣጌጦቻቸውን ጭምር በመሸጥ "ባቡል ኸይር" የተሰኘውን እና ዛሬ የብዙ አቅመ ደካሞች መጠጊያ የሆነውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ከፈቱ።

የክርስትናም ይሁን የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደየ እምነታቸው የሚስተናገዱበት ድርጅቱ አሁን ላይ አቅመ ደካሞችን በተለያዩ ሙያዎች እያሰለጠነ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ከማድረግ ባለፈ፣ የደም ልገሳ፣ የምስኪኖችን ቤት የማደስ፣ የማማከር እና መሰል አገልግሎቶችንም ይሰጣል። በባቡል ኸይር 80 በመቶ ተረጂዎች እናቶች ናቸው።

የባቡል ኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት በየቀኑ 1500 አባወራ ከነልጆቻቸው ባጠቃላይ 4100 ሰዎችን ይመግባል። ባቡል ኸይር ዳቦና ጫማ ማምረቻ ማሽኖችን እንዲሁም የስፌት ማሽኖችን በመግዛት አቅም ያላቸው ከተረጅነት እንዲወጡም እያሰለጠነ ይገኛል። ከዚህ ባለፈም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የህክምና ወጪ ለሌላቸው ተረጅዎች ወጭያቸውን ችሎ ያሳክማል።

ሀናን "ሴቶች ሰብሰብ ሲሉ ቁምነገር አይሠሩም፣ ወሬ ያበዛሉ" የሚለውን ተተሳሳተ አመለካከት ይበልጡን ፋርሽ በማድረግ ሴቶች ሰብሰብ ሲሉ ብዙ የመሥራት አቅም እንዳላቸው ማሳየት የቻሉ እና ለብዙዎች የመኖር ተስፋን የፈነጠቁ የሰብዓዊነት ተምሳሌት ናቸው።

## ስህን ተፈራ (ፒ.ኤች.ዲ)



ዶ/ር ስህን ተፈራ የፆታ እኩልነት ባለሙያ፣ የ"ሴታዊት የጾታ እኩልነት ንቅናቄ" መስራችና የሴቶች መብት ታጋይ ናቸው። አዲስ አበባ የተወለዱት ዶ/ር ስህን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በናዝሬት ትምህርት ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በሳንፎርድ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ክአቴንስ ላ ቬርን ካምፓስ በ ሶሺዮሎጂ፣ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በስርዓተ-ፆታ ላይ በማተኮር በአለም አቀፍ ልማት ከ ክላርክ ዩኒቨርሲቲ ሲያገኙ ፣ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ በስርዓተ-ፆታ ከ ለንደን ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል።

በጥናታዊ ጽሁፎቻቸው ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ እስካሁን እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ክፍተት የታየባቸው እንደሆኑ፣ እንዲሁም የ ኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲወች የስርዓተ-ጾታ ጉዳይን በእጅጉ ያልቃኙ እንደሆነና የምርጫ ህጎች ደግሞ ሴቶች ከወንዶች እኩል ኮታ እንዲኖራቸዉ ያልደነገገ በመሆኑ ክፍተት እንደሚታይባቸው አብራርተዋል። በተጨማሪም ሴቷን ከወንዱ እኩል በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካው መስክ ተሳታፊ እንድትሆን የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ሰጥተዋል በተለያዩ ጥናቶቻቸው አመላክተዋል። ዶ/ር ስህን ይበልጥ የሚታወቁበትን የ "ሴታዊት

ንቅናቄን” በኋላም ድርጅትን በ 2008 ዓ.ም. አቋቁመው አሁን በ ሀላፊነት እየመሯት ነው።

ሴታዊት በአሁንዋ ኢትዮጵያ የመጀመርያዋ የፆታ ንቅናቄ ስትሆን ስሟ እንደሚያመለክተው የንቅናቄዋ አላማ በኢትዮጵያ የፆታ እኩልነትን ለማስከበር የሚደረገውን ትግል ማጠናከር ነው:: ገንቢ የሆነ ውይይት በማድረግ እና በህብረት የመስራት ባህልን በማጠናከር በሴቶች መካከል እህትማማችነትን ማጎልበት ነው።

በአሁኑ ሰዓት ሴታዊት በስሯ በሁለት ዋና ዘርፎች የተከፈሉ የተለያዩ መርሀ ግብሮችን ታካሂዳለች:: አንደኛዋ ክፍል ንቅናቄዋ ስትሆን ሁለተኛዋ ዘርፍ ደግሞ ንቅናቄዋን የምትደጉመው እና የንቅናቄዋም የበላይ ጠባቂ የሆነችው የንግድ ዘርፏ ናት። በንቅናቄ ዘርፏ ስር የወንዶች እና የሴቶች ወርሃዊ የውይይት ክበባት ፣ በየሁለት ወሩ የሚደረግ ወንዶችን እና ሴቶችን በጋራ የሚያሳትፍ የውይይት መድረክ እንዲሁም የማህበራዊ ሚድያ ግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎችን ስታደርግ በንግድ ዘርፏ ስር ደግሞ የስርዓተ ፆታ ምርምሮችን እና ስልጠናዎችን መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ፣ ለተለያዩ ትምህርት ቤቶች እና ለግል ድርጅቶች ትሰጣለች።

በተጨማሪም ንቅናቄዋ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በሚያጋጥሙዋት ግዜ ከኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ጋር በመሆን የህግ ድጋፍ እንዲያገኙ ስትሰራ ቆይታለች:: በአሁኑ ግዜም የራሷን ማዕከል በማቋቋም ከህግ ከለላ በተጨማሪ የስነልቦና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እያመቻቸች ትገኛለች::

ሴታዊት በሀገራችን ላለፉት አምስት ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን ግጭት አስመልክታም፤ በተደጋጋሚ በግልና ከሌሎች የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በጦርነቱ ሴቶች በተለየ ሁኔታ ተጎጂ መሆናቸውን እና ፆታዊ ጥቃት የጦርነት መሳሪያ መደረጉን በመቃወም የጦርነት ይቁም ጥሪዎችን ስታሰማ ቆይታለች።

ከዚህ ሌላ ድሮ በአደባባይ ለማንሳት የሚከብዱ ሐሳቦች ላይ ግልጽ ውይይት እንዲደረግ፣ በተለይ ሴቶችን ወደ ኋላ ያስቀሩ ልምድና እምነቶች ላይ መጠይቅና መከራከር እንዲደረግ አስተዋፅዖ ታደርጋለች። ዶ/ር ስህን ተፈራ በ ሴቶች መብቶች ላይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ከሚያሰሙ ምሁራን እና አንቂዎች መካከል ግንባር ቀደም ሲሆኑ እርሳቸው ያቋቋሙት ሴታዊት ንቅናቄ ለሌሎች መሰል ንቅናቄዎች መበራከት ፈር ቀዳጅ ሆኑዋል።

## መስከረም ገስጥ



መስከረም ገስጥ የሰብዓዊ መብት ጠበቃ፣ የሴቶች መብት ተሟጋች፣ እና የህግ ባለሙያ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በፓዶቫ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብት ማዕከል የዶክትሬት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙት መስከረም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ባችለር (ኤልኤል.ቢ) እና ከፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ የህግ ማስተርስ (ኤልኤል.ኤም) አግተዋል።

ከ ሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. እስከ መስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ኮሚሽነር በመሆን አገልገለዋል። በኮሚሽኑ በ ነበራቸው ቆይታም በኢትዮጵያ በተከሰቱት ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች ምክንያት ሕፃናት ከመንግሥት፥ ከማኅበረሰብ እና ከቤተሰብ ማግኘት ያለባቸው ጥበቃ መጓደሉን እና ለተደራራቢ የመብት ጥሰቶች መጋለጣቸውን በማውሳት የሕፃናት ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል ታግለዋል። መስከረም በተለያዩ የ ኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ ሴቶችም በደረሰባቸው ጾታዊ መድሎዎች እና በተፈጸሙባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ምክንያት መሰረታዊ መብቶቻቸውን እንደተጣሱ፣ ነፃነቶቻቸውን እንድሚገቡና ሰብአዊ ክብራቸው እንድሚጎድፍ እና ይህም መቆም እንዳለበት በተለያዩ መድረኮች አሳስበዋል። ልዩ ትኩረትን የሚሹ የመብት ጥሰቶችንም ለማረም እና ለማስተካከል መፍትሔዎች እና ምክረ-ሃሳቦችን ለግሰዋል።

መስከረም ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ እና የአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች እና ልማት ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር በመሆን በአህጉሪቱ ዋና ዋና  የሰብአዊ መብት አጀንዳዎችን መርተዋል። መስከረም ከአፍሪካ የሰብአዊ መብት ስልታዊ ማስጠቂያ ጋር በቅርበት የሰሩ ሲሆን የአፍሪካ ህብረት የሰብአዊ መብት ህጎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ጥናቶችን በማዘጋጀት ተሳትፈዋል። በአፍሪካ የሰብአዊ እና ህዝቦች መብት ኮሚሽን ውስጥ በተለያዩ የስራ ቡድኖች ውስጥ ኤክስፐርት አባል በመሆን እና ከተለያዩ የኮሚሽኑ ልዩ ራፖርተሮች ጋርም ተባብረዋል።

በሀገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የ ሴቶች ድምጽ፣ ተሳትፎ እና ውክልና እንዲያድግ ሰርተዋል። መስከረም ገስጥ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና መስፋፋት ከፍተኛ አስትዋጽኦ ያበረከቱ ሲሆን፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት እና የማኅበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎችንም ሰርተዋል።

መስከረም እንደሚሉት የሰብዓዊ መብት የህግ ባለሙያ ለመሆን የወሰኑት ሴቶች ፍትህ ሊያገኙ ይገባል ብለው ከልጅነት በማመናቸው ነው። በአነስተኛ ገንዘብና ዘዴ ፆታዊ ጥቃትን የሚዋጉ ኢትዮጵውያን ሴቶች ተነሳሽነትና ፅናት ለእኔም መነሳት ምክንያት ነው ይላሉ መስከረም።

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር በቂ የህግ አገልግሎት ለማያገኙ ሴቶች እና ህጻናት ነጻ የ ህግ ማማከር አገልግሎት እና ያልተቋረጠ ድጋፍ በመስጠት ላበረከቱት አስተዋጽኦ እውቅና እና ሽልማት ሰጥቷቸዋል።

## ሌንሳ ቢየና



ሌንሳ ቢየና የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማሕበር ዋና ስራ አስፈጻሚ ናት። መብትን ለማስከበር መነሳት ለሰዎችም ለራስም ፍትህ ዘብ መቆም መለያዋ ነው፤ ሁሉም ሰው በስነ ስርዓት መመራት ህግም መከበር አለበት ባይ ናት የህግ ባለሟሏ ሌንሳ። ሌንሳ ገና የህግ ተማሪ ከነበረችበት ጊዜ አንስቶ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበርን በበጎ ፈቃደኝነት ስታገለግል ነበር። በተለያዩ ማህበራዊ እና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት አቅም ላጠራቸው እና ፍትህ ለሚሹ ወገኖች በነጻ ጥብቅና ስትቆም መቆየቷም ይነገርላታል።

በበጎ ፈቃደኝነት የጀመረው አርአያነት ያለው ተግባር እስከ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር ዋና ዳይሬክተርነት አድርሷታል። የህግ ባለሞያ ሴቶች ማሕበር ብርቱ የ ተቋማዊ ህልውና ፈተና ገጥሞት በነበረ ጊዜ ለማህበሩ ገንዘብ እና ሃብት በማፈላለግ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ እና ውጤታማ መዋቅር በመዘርጋት ማህበሩን ታድጋዋለች። ሌንሳ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን የሚዲያ ሙገታ/ውትወታ (Media Advocacy) እና ጫና በመፍጠር የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ከሚታትሩ ጥቂት ሴቶች አንዷ ናት።

ሌንሳ በስርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ ያተኮሩ ተግባራትን ለማጠናከር በሴቶች መብት አደረጃጀቶች መካከል ጠንካራ የትብብር መንፈስ ወይንም ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ታትራለች።

ሌንሳ ቢየና ብሔራዊ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላከልና ምላሽ አሰጣጥ ረቂቅ ፖሊሲ ቶሎ ጸድቆ ወደ ስራ እንዲገባ ጫና በመፍጠር እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበርም የ ውተወታ (Advocacy) ስራ እንዲሰራ እና ረቂቅ ፖሊሲው ትኩረት አግኝቶ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ያልተቋረጠ ጥረት አድርጋለች። ሌንሳ ለሴቶች ተሳትፎ እና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ላደረገችው መልካም አስተዋጽኦ በ 2015 ዓ.ም. የአፍሪካ ሴቶች ኮንፈረንስ (AWC) የላቀ የሴቶች መብት ሻምፒዮን ተሸላሚ ሆናለች። ሌንሳ ከ በጎ ፈቃድ አገልግሎት እስከ ተቋም መሪነት የዘለቀ ጽናት ያላት የ የሴትነት ክብር ደጀን ነች።

## ሀና ለማ



ሀና ለማ የሴቶች መብት ተሟጋች እና የስርዓተ ፆታ ጥናት ተመራማሪ ነች። የአዲስ ፓወር ሃውስ ዲጂታል ፌሚኒስት ጋዜጣ ወይም መወያያ መድረክ መስራች እንዲሁም የሴታዊት ንቅናቄ የቦርድ አባል በመሆን በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተስፋፋ የመጣውን ሴቶች ላይ የሚደረግ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከል ብሎም ስለ ችግሩ ስፋት ማህበራዊ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እየሰራች ትገኛለች።

ሀና ለማ በ ኢኮኖሚክስ እና በ ልማት ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለትኛ ዲግሪ ያላት ሲሆን ከተማሪነት ግዜዋ ጀምሮ ስለ ሴቶች እኩልነት እንዲሁም የ ሴቶች ተሳትፎ ላይ ትኩረቷን አድርጋ ስትሰራ ነበር። ሀና ለማ ከ 1993 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የነበረውን የኢትዮጵያ የ ሴቶች ፖሊሲ የክለሳ ሂደት ውስጥ ከተሳተፉት ተመራማሪዎች አንዷ ነች። ሀና የተከለሰው ፖሊሲ ሁሉን አቀፍ፣ አሳታፊ፣ የተሟላና ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል፣ የሴቶችን ሁለንተናዊ መብት እንዲያስከበር፣ በየደረጃው በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ብሎም ከሚገኘው ትሩፋትም ፍትሃዊ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ የ ፖሊሲ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ምክረ ሀሳቡዋን ሰጥታለች። ሀና የመሰረተችው አዲስ ፓወር ሃውስ በ ማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት በተለያዩ የስርዓተ ጾታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ነጻ የዲጂታል መጽሄቶችን እና ውይይቶችን ያዘጋጃል። በዩቱብ ላይ የሚደረጉ ውይይቶችንም መስማት የተሳናቸውን ባማከለ መልኩ በምልክት ቋንቋ ተተርጉመው እንዲቀርቡ ያደርጋል።

አዲስ ፓወር ሃውስ የሁለተኛ ደረጃ እና የዩኒቨርስቲ ተማሪ የሆኑ ሴቶች በጾታዊ ጥቃት፣ በፍቅር እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን የሚጋሩበት የተለያዩ ነጻ የዲጂታል ህትመት ውጤቶችን አዘጋጅቷል። ቡድኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፍቃድ በማውጣት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ ሲሆን በስርዓተ ጾታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናቶችን በመስራት፣ ወጣቶች የሚወያዩበት መድረክ በመክፈት እና በከፍተኛ ግብረሰናይ ተቋማት እና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች መሃከል እንደ ድልድይ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ሀና ለማ ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም በኢትዮጵያ የሴቶች መብት ንቅናቄዎችን እና ተሟጋቾችን ድምፅ እያጎሉ ከሚገኙ እና ለብዙወች መነሳሳት ምክንያት ከሆኑ ወጣቶች መካከል ትመደባለች።



# ሴቶች በኪነ ጥበብ እና ጋዜጠኝነት

# እማሆይ ፅጌ ማርያም ገብሩ (1916-2015)



እማሆይ ፅጌማርያም በኢትዮጵያ ቀዳሚዋ የቫዮሊን እና ፒያኖ ሙዚቃ አቀናባሪ፣ አንዳዴም "የፒያኖዋ እመቤት" በመባል ይታወቃሉ። እማሆይ ፅጌማርያም በምንኩስና ወደ መንፈሳዊው ሕይወት ከመግባታቸው በፊት ቤተሰቦቻቸው የውብዳር የሚል ስም ነበር የሰጧቸው።

በ1916 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተወለዱት እማሆይ ጽጌማርያም ገብሩ በኢትዮጵያ በቫዮሊን እና በፒያኖ ሙዚቃዎችን በማቀናበር በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው። በስድስት ዓመታቸው ከእህታቸው ስንዱ ገብሩ ጋር ወደ ስዊዘርላንድ በመጓዝ ቫዮሊንና ፒያኖ ወደሚያጠኑበት የሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤት በመግባት ስለ ቫዮሊን ተምረው ሲጨርሱ አሥር ዓመትም አልሞላቸውም ነበር። እአአ በ1933 ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በእቴጌ መነን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርታቸውን ቀጠሉ። እ.ኤ.አ. በ 1937 እማሆይ እና ቤተሰባቸው በጣሊያን ጦር ተማርከው ከሰርዲኒያ በስተሰሜን ወደምትገኘው ወደ አሲናራ ደሴት እና በኋላም በኔፕልስ አቅራቢያ ወደሚገኘው መርኮሊያኖ ተወሰዱ።

ከጦርነቱ በኋላ የዉብዳር የሙዚቃ ትምህርታቸውን በካይሮ ቀጥለው ፤ አሌክሳንደር ኮንትሮቪች በተባለ ፖላንዳዊ ቫዮሊስት መምህራቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ሲሆን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአስተዳደር ረዳት ሆነው ሰርተዋል። እማሆይ በ19 ዓመታቸው ከአዲስ አበባ በድብቅ ሸሽተው ወሎ ውስጥ ወደምትገኘው ግሸን ማርያም ገዳም ከእናታቸው ጋር በመሄድ በገዳሙ ለሁለት ዓመታት አገልግለው በ21 ዓመታቸው ምንኩስናን ተቀበሉ። እማሆይ ከግሸን ማርያም ከወጡ በኋላ በጎንደር አምስት ዓመታት ተቀምጠዋል።

በተለይ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበረው ግን ግምጃ ቤት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነበር። በዚያም ያሬዳዊ ዜማን አጥንተዋል። በግምጃ ቤት ማርያም ያለውን የድንግል ማርያም ሥዕል በማየት የራሳቸውን ሥዕል ሥለዋል። ባሕር ዳርንና ጢስ ዓባይንም በጎበኙበት ጊዜም ሰለዓባይ ወንዝ "The Song of Abay" ዜማንም ደርሰዋል።

በጎንደር ከተማና በዙሪያዋ ባሉት ቤተ ክርስቲያናት የቤተ ክህነት ትምህርት ዜማና ቅኔ አድናቆት ያድርባቸውና የቆሎ ተማሪዎች የዕለት ጉርስ ለማግኘት ያለባቸውን ችግር አይተው መርዳት አለብኝ ብለው ሲነሱ መፍትሔ ብለው ያሰቡት ሙዚቃቸውን ማሳተም ስለነበር ወደ ጀርመን ጉዞ ያደርጋሉ። ሁለት አልበሞቻቸውንም ያሳትማሉ። ከአልበሙ የተገኘውን ገቢ ቤተሰብ ለሌላቸው ልጆች ማሳደጊያ አውለውት ነበር። በ1976 ዓ.ም. ወደ እስራኤል ያቀኑ ሲሆን እስከ እለተሞታቸውም ያሳለፉት እዚያው ነበር። ምንም እንኳ የመጀመሪያ የሥራዎቻቸው ስበስብ የወጣው በ1960ዎች ቢሆንም፣ ዓለም አቀፋዊ ዝናን ያገኙት ደግሞ ብቻቸውን በፒያኖ ያቀናበሯቸው ዜማዎች በኢትዮፒክስ አማካይነት በስፋት መደመጥ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ነው።

እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ከ150 በላይ የረቂቅ ሙዚቃ ድርሰቶችን የጻፉ ሲሆን፥ ሶስት አልበሞችን በሲዲ እና በሸክላ ላይ አሳትመዋል። እማሆይ ፅጌማርያም ከሰሯቸው ከበርካታ የሚዚቃ ሥራዎች ውስጥ « Homeless Wonder » /ሆምለስ ወንደር/ ፣ "The Son of Seam" ፣ "The Mad-Man's Daughter" "Mother's Love" የሚል አርዕስት ያላቸው ሙዚቃዎች ከበርካታ ሥራዎቻቸው ውስጥ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ።

የእማሆይ ቅንብሮች ለብዙ ፊልሞች እና መሰናዶዎች ማጀቢያ ሲሆኑ ከነዚህም መካከልዜና፣ ሕይወትና ጥበብ፣ ሙዚቃና ሌሎች መሰናዶዎች የሚቀርቡበት ኤንፒኤር (NPR)፣ መርሐ ግብሩን ከአንዱ ርዕስ ጉዳይ ወደ ሌላው ሲሸጋገር የሚያሰማው የመሸጋገሪያ ሙዚቃ፣ የ የፒያኖ ሙዚቃ የእማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ነው። አንደኛው ሙዚቃቸው እ.ኤ.አ. በ2020 በኦስካር የታጨው የኔፍሊክስ "Passing" ዶክመንተሪ ድራማ ላይ በማጀቢያነት ውሏል።

እማሆይ በፆታ እኩልነት የሚያምኑ ሲሆን ሴቶችን የማብቃት አስፈላጊነት ላይ በአ ገዜ ይመክሩ ነበር። በተለይም ሴት ጋዜጠኞችም ሆኑ አርቲስቶች ወደ እርሳቸው ሲሄዱ ያበረታቷቸው እና ህልማቸውን ተከትለው እንዲተጉ ይመክሩ ነበር።

## ሮማን ወርቅ ካሳሁን (1914_1964)



ጋዜጠኛ ሮማን ወርቅ ካሳሁን በሀገራችን የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ ናቸው። በ1914 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተወለዱ። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም ቅድሥት ሥላሴ ቤተ-ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው የቤተ-ክርስቲያን ትምህርት በመማር ዳዊት ደገሙ። ከዚያም ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት በጊዜው ይሰጥ የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት ተማሩ። በትምህርት ቤት ቆይታቸውም የወቅቱን "ሴት ለትምህርት አልተፃፈችም" የሚለውን ልማድ በጥረታቸውና በትጋታቸው በመቋቋም በትምህርት ቤት ቆይታቸው የአንደኛነት ደረጃን በመያዝ በአስተማሪዎቻቸው ይሸለሙ ነበር።

በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ይማሩ በነበረበት ወቅት ከአውሮፓውያን መምህራን ያገኙት ዘመናዊ ትምህርት ከተፈጥሮ ችሎታቸው ጋር ተደምሮ በጥናትና ንባብ ያዳበሩትን እውቀታቸውን ወደ አደባባይ ማውጣት ስለፈለጉ በጥር ወር 1939 ዓ.ም በወቅቱ "የማስታወቂያና ፕሮፓጋንዳ ሚኒስቴር" ተብሎ ይጠራ በነበረው መስሪያ ቤት የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ በመሆን ተቀጠሩ።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በተሰጣቸው በሬዲዮ ጋዜጠኝነት ስራቸው የተለያዩ ጽሑፎችንና ዜናዎችን በማዘጋጀት በማራኪ አንደበታቸው ሲያንቆረቁሩት በዜና አቀራረባቸውና በፕሮግራም ዝግጅታቸው በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትንና አድናቆትን ለማግኘት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር። ምንም እንኳ ስራውን ሲጀምሩ ነቀፌታ ገጥሟቸው የነበሩት ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሣሁን በትጋት እና በጽናት የመጀመሪያዋ እንስት ጋዜጠኛ ለመሆን በቁ። ጋዜጠኛ ሮማነወርቅ በኢትዮጵያ የሬድዮ አገልግሎት እንዳሁኑ ባልተስፋፋበት በዚያን ወቅት ይሰጡት የነበረው አገልግሎት እጅግ ከፍ ያለ ነበር።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ባገለገሉባቸው ጊዜያት በሬዲዮ ዜና አጠናቃሪነት፣ በዜና አንባቢነት፣ በሴቶች ፕሮግራም አዘጋጅነት ሰርተዋል። በዚሁ መስሪያ ቤት ውስጥ አንድም ቀን "ሰለቸኝ" ሳይሉ በየጊዜው ለአድማጭ አዲስ ነገር ይዞ በመቅረብ ለ25 ዓመታት ያህል ለሙያቸው በመታመን ያገለገሉት ጋዜጠኛ ሮማነወርቅ፣ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለወንዶችም (በተለይ ደግሞ ለጋዜጠኞች) አርዓያ መሆን ችለዋል። ይህም ከፍተኛ የሆነ ተወዳጅነትንና አድናቆትን አስገኝቶላቸዋል።

በወቅቱም ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁመው በዝግጅቶቻቸው ላይ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ስራዎችን በማቅረብ ሕዝቡን ሲያገለግሉ በትምህርት ገበታ ላይ ለነበሩት ሴቶች ልጆች እንደብርቅዬና የበጎ ተግባር ምሳሌ በመሆን ይታዩ ነበር። ከአድማጩ በሚደርሳቸው አድናቆትና ማበረታቻ በመታገዝ ለስራቸው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ ሰው ነበሩ። በዝግጅቶቻቸው የተለያዩ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በወቅቱ በሴቶች ዘንድ ጫና የሚፈጥሩ አመለካከቶችን ለመፋቅ በመገናኛ ብዙኃን የራሳቸውንና የብዙ ሴቶችን ድምፅ አሰምተዋል።

ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሣሁን የመጀመሪያዋ እንስት ጋዜጠኛ ብቻ አልነበሩም። ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሰልፈው መስራትና ውጤት ማምጣት እንደሚችሉ ለኢትዮጵያውን ሴቶች ምሳሌና አርዓያ በመሆን ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚመደቡ ሰው ነበሩ። በትርፍ ጊዜያቸው ደግሞ በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ጽሑፎችንም ያዘጋጁ ነበር። አብዛኞቹ ጽሑፎቻቸውም የሴቶችን ማኅበራዊ ኑሮ ማሻሻል ላይ ያተኮሩ ነበሩ።በእነዚህ ጽሑፎቻቸውም የሴቶች ኑሮ እንዲሻሻል ያበረታቱና ይቀሰቅሱ ነበር።

በ1942 ዓ.ም የመጀመሪያ ስራቸውን ለአንባቢ ያቀረቡት ወይዘሮ ሮማነወርቅ ለመጽሐፋቸው የመረጡት ርዕስ «ትዳር በዘዴ» የሚል ነበር። መጽሐፉ የገጠሩንና የከተማውን ትዳርና ኑሮ የሚያነፃፅር ሲሆን፤ በውስጡም በገጠር ያለውን የሕይወት ውጣ ውረድ ዘርዝሮ ያቀርባል። ከዚህ በተጨማሪም የመጽሐፉ ደራሲ «ለትዳር ፈላጊዎች ምክር አለኝ» በማለት ስለትዳር የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ለመዳሰስ ሞክረዋል። ሴቶች በማኅበራዊ ሕይወታቸው ውስጥ ያለባቸው ጫናም በመጽሐፉ ተዳስሷል። ወይዘሮ ሮማነወርቅ የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን ካሳተሙ ከአንድ ዓመት በኋላ፣ በ1943 ዓ.ም ሁለተኛ ስራቸውን በትያትር መልክ በማዘጋጀት ለሕትመት አበቁ።

ይህ ስራቸው «ማህቶተ ጥበብ» የሚል ስያሜ ሲኖረው፣ ታሪኩ በወቅቱ ሕይወታቸው ስላለፈው ስለ ልዕልት ፀሐይ ኃይለሥላሴ ሕይወት የሚያወሳ መጽሐፍ ነው። ወይዘሮ ሮማነወርቅ በሁለቱም ስራዎቻቸው አበክረው የመከሩት ነገር የሴቶችን ማኅበራዊ ሕይወትና ግንኙነት ስለማሻሻል እንዲሁም ማኅበረሰቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያደርገው ስለሚገባው ተሳትፎና እገዛ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ወይዘሮ ሮማነወርቅ ጽሁፎቻቸውን በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ በማሳተም በሕትመት መገናኛ ብዙኃን ላይም የፋና ወጊነት ሚናን ተጫውተዋል። የ«መነን» መጽሔት አዘጋጅ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የሴቶችን ሕይወት የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ (የምክር) ጽሑፎችን በጋዜጦችና በመጽሔቶች ላይ በመፃፍም የታወቁና የተደነቁ ነበሩ።

በየአቅጣጫው እየተጉ የሴቶችን በተፈጥሮ ደካማ ያለመሆን በስራ ያስመሰከሩት ወይዘሮ ሮማነወርቅ፣ በ1948 ዓ.ም ሦስተኛ መጽሐፋቸውን ለሕትመት አበቁ። የመጽሐፉም ርዕስ «የሕይወት ጓደኛ» የሚል ነበር። በወይዘሮ ሮማነወርቅ መጻሕፍት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚመላለሰው ርዕሰ ጉዳይ ሴት ዝቅ ተደርጋ የምትገመትበት ማኅበረሰባዊ የትዳርና የኑሮ ጣጣ ነበር። ወይዘሮ ሮማነወርቅ በሙያቸው ላበረከቱት አስተዋፅዖና ላሳዩት ከፍተኛ የስራ ብርታትና ትጋት የተለያዩ ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከሽልማቶቹ መካከልም ከኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት መንግሥት የወርቅ ሜዳልያ እንዲሁም የደራሲያን መታሰቢያ የብር ሜዳሊያ ይጠቀሳሉ።

ወይዘሮ ሮማነወርቅ ከላይ ከተገለጹት ጥረቶቻቸው በተጨማሪ የተለያዩ ድርጅቶችና ማኅበራት አባል በመሆን ለወገናቸው ሕይወት መቃናት የሃሳብ፣ የገንዘብና የጉልበት አስተዋፅኦ በማድረግም የታወቁ ሰው ነበሩ። ለአብነት ያህልም የኢትዮጵያ ሴቶች በጎ ስራ ማኅበር እየተባለ ይጠራ የነበረው ድርጅት አባል በመሆን የሚፈለግባቸውን የኢትዮጵያዊነት ግዴታ ተወጥተዋል። በወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወሴክማ)፣ በደራሲያን ማኅበር በሌሎች ማኅበራትና የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በአባልነትና በተጋባዥ እንግድነት እየተገኙ ትምህርታዊ አስተያየታቸውንና ምክራ ቸውን ይሰጡ ነበር። ወይዘሮ ሮማነወርቅ በህመም ምክንያት ሐኪም ቤት ከመግባታቸው ቀደም ብሎ «ለወይዛዝርት» የተባለውና በሳምንት ሁለት ጊዜ በኢትዮጵያ ሬዲዮ የሚቀርበው ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢ ነበሩ።

በዚህ ፕሮግራም ላይ በትያትርና በውይይት መልክ የሚያቀርቧቸው ትምህርታዊ መሰናዶዎች ስለ ቤት ባልትና፣ ስለ ልጅ አስተዳደግና ስለ መልካም ቤተሰብ ኑሮ ያወሱ ነበርና በአድማጮች ዘንድ «እውነትም ሮማነወርቅ» አሰኝቷቸዋል።

ወይዘሮ ሮማነወርቅ የጤና እክል አጋጥሟቸው በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ጥር 23 ቀን 1964 ዓ.ም አረፉ። ሞት ቀደማቸው እንጂ «ሔዋን»፣ «መልካም እመቤት»፣ «የቤተሰብ አቋም»፣ «የባልትና ትምህርት»፣ «የሕፃናት ይዞታ»፣ «ዘመናዊ ኑሮ»፣ «የኑሮ መስታዎት»፣ «ጋብቻና ወጣቶች»፣ እንዲሁም «የባልና የሚስት ጠብ» በሚሉ ርዕሶች መጻሕፍትን አዘጋጅተው ለሕትመት ለማብቃት እየጠበቁ ነበር። በሀገራችን ብዙም ሴቶች ይሳተፉበት ባልነበረው የጋዜጠኛነት ሙያ ላይ ፈር ቀዳጅ በመሆን ብዙ ስራን የሰሩት ጋዜጠኛ እና ደራሲ ሮማነወርቅ ለብዙ አንጋፋ እና ወጣት ጋዜጠኞች አርአያ ሁነዋል።

## መዓዛ ብሩ



ጋዜጠኛ፣ የሸገር ኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያ መስራች እና ባለቤት መዓዛ ብሩ በ1950 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደች። እስከ 9 አመቷ ድረስ በምዕራብ ሐረርጌ በምትገኘው ትንሿ የሂርና ከተማ ያደገችው መዓዛ ከተለያየ የማህብረሰብ ክፍል ከተውጣጡ ጎረቤቶች መሃል የየመን፣ የኦሮሞ፣ የሐረሪ እና የሶማሌ ባህሎችን እየቀሰመች አደገች። ከነጋዴ ቤተሰቦች የተወለደችው መዓዛ በእጃቸው ጋዜጣ እና መጻህፍት የማይጠፋው አባቷ የማንበብ ባህል እንድታዳብር ረድተዋታል። በ9 አመቷ አዲስ አበባ ከተማ ተመልሳ በሚገኘው የቅድስት ማርያም አዳሪ ትምህርት ቤት ተመዘገበች። የአዲስ አበባ ኑሮ ከአዳሪ ትምህርት ቤት ጋር ተዳብሎ ለጥቂት ጊዜ ቢፈትናትም አዲስ አበባ የነበሩ ቅርብ ዘመዶች ጋር በመሄድ፣ በወቅቱ ይታተሙ የነበር ታዋቂዎቹን “አዲስ ዘመን” እና “የዛሬይቱ ኢትዮጵያ” ጋዜጦችን እንዲሁም ሌሎች መጻህፍትን በማንበብ አዲስ አበባን እና አዳሪ ትምህርት ቤትን እንደተላመደቻቸው ትገልጻለች።

መዓዛ የ10ኛ ክፍል ተማሪ እያለች በደርግ መንግስት በታወጀው የእድገት በሕብረት ዘመቻ በትግራይ ክልል ውቅሮ ተሰማርታ በውቅሮ የገበሬ ማህበራት እንዲመሰረቱ የተሳተፈችባቸውን ስድስት ወራት በህይወቷ ኃላፊነትን የተማረችባቸው እንደሆኑ አድርጋ ትወስዳቸዋለች።

የእድገት በሕብረት ዘመቻን አጠናቃ ወደአዲስ አበባ በመመለስ በቅድስተ ማርያም ትምህርት ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቃለች። ከዚያም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን በመቀላቀል የሥነ ልሳን ትምህርት ተከታትላለች። በወቅቱ ተጧጡፎ የነበረው የቀይ ሽብር ዘመቻ አስከፊ ገጽታ የፍርሃት ድባብ በተማሪዎች ላይ አሳድሮ እንደነበር ታስታውሳለች።

መዐዛ የስነ ልሳን ትምህርቷን ብዙም ባትወደውም አብረው ለሚሰጡ የሥነ ጹሁፍ ትምህርቶች ፍላጎት ስላሳደሩባት በሥነ ልሳን ትምህርት ገፋችበት። መዓዛ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለች ነው እንግዲህ በአንድ አጋጣሚ ከሬድዮ ጋር የተዋወቀችው። በወቅቱ በዩኒቨርስቲ አብራት በአንድ ክፍል የምትኖር ጓደኛዋን ተፈሪ ዓለሙ እና አስታጥቃቸው ይሁን የተባሉ የትያትር ጥበባት ተማሪዎች ለራዲዮ ፕሮግራም ፈልገዋት በሄዱበት አጋጣሚ ለራዲዮ ፕሮግራም የተፈለገችው የመዓዛ የተማሪዎች መኖሪያ ደባል በዕለቱ ባለመገኘቷ የትያትር ተማሪዎቹ መዓዛን በጓደኛዋ ምትክ በራዲዮ ድራማው ላይ ተከታ እንድትሳተፍ በጠየቋት ወቅት ነበር። ከጥቂት ማንገራገር በኋላ ጥያቄውን የተቀበለችው መዓዛ በወቅቱ ታዋቂ በነበረው የ’እሁድ ፕሮግራም’ የተባለ የመዝናኛ ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን የሚያቀርብ የራዲዮ ፕሮግራም ላይ መቀረጽ ጀመረች። በዚህ አጋጣሚ የጀመረው የራዲዮ ፕሮግራም ጉዞ ነው እንግዲህ ለዓመታት ወደዘለቀው የራዲዮ ፕሮግራም አቅራቢነት፣ አዘጋጅነት በኋላም ደግሞ የራዲዮ ጣቢያ ባለቤትነት የመራት።

መዓዛ ከዩኒቨርስቲ ከተመረቀች በኋላ በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር በስፖርት ዘጋቢነት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ግንኙነት ክፍል ውስጥ የሰራች ሲሆን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በነበራት ቆይታ ብዙም ደስተኛ ባትሆንም ጥሩ ልምዶችን እንደቀሰመች ትገልጻለች። ከባህል ሚኒስቴር በመልቀቅ የብሄራዊ ባንክ ‘ብሪቱ’ መጽሄት ዋና አዘጋጅ በመሆን አጫጭር ልቦለዶችን እና የፋይናንስ ዜናዎችን መጻፍ ጀመረች ። በመቀጠልም በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ሲቋቋም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሬስ እና መረጃ ዋና ዳይሬክተር ውስጥ ለአራት አመታት ከሰራች በኋላ ለሥራው ቢሮክራሲያዊ ባህሪ እንደማትሆን ስለተረዳች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደለቀቀች ትናገራለች።

ከዚህ በመቀጠል ነው መዓዛ ባለቤቷ አበበ ባልቻ አዘጋጅ በሆነበት በኤፍ ኤም 97.1 ጣቢያ ቅዳሜ ከሰዓት በሚተላለፈው የ’ጨዋታ’ ፕሮግራምን ከሌሎች ዕውቅ ባለሞያዎች ጋር ማዘጋጀት ጀመረች። በዚህ ሥራ ውስጥ እያለች መንግስት ለሁለት የግል ራዲዮ ጣቢያዎች ፍቃድ ለመስጠት ፍላጎት

እንዳለው ሲያሳውቅ ከብዙ ማመንታት በኋላ ባለቤቷ ማመልከት እንዳለባት አሳምኗት ከልጅነት ጓደኛዋ ተፈሩ አለሙ ጋር ማመልከቷን ያወሳችው መዓዛ ከብዙ እልህ አስጨራሽ ትግል፣ የመውደቅ እና የመነሳት ጉዞ እና በብዙ ባለሞያዎች ድጋፍ በኋላ ሸገር 102.1 ኤፍ. ኤም. ሬድዮ ጣቢያ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም አየር ላይ ዋለ። በፕሮግራሞቹ ይዘት እና በአቀራብ ስልቱ አዲስ ነገር ይዞ ብቅ ያለው ሸገር 102.1 ኤፍ. ኤም. ሬድዮ ጣቢያ ከተመሰረተ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በየሳምንቱ ቅዳሜ የሚተላለፈውን 'ጨዋታ እንግዳ' እና የእሁድ ጠዋት ' ሸገር ካፌ' ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት እና በማቅረብ ትገኛለች ። በዚህም ከፍተኛ ተወዳጅነት፣ አድናቆት እና አክብሮትን አግኝታለች።

ከዚህ በመቀጠል ነው መዓዛ ባለቤቷ አበበ ባልቻ አዘጋጅ በሆነበት በኤፍ ኤም 97.1 ጣቢያ ቅዳሜ ከሰዓት በሚተላለፈው የ'ጨዋታ' ፕሮግራምን ከሌሎች ዕውቅ ባለሞያዎች ጋር ማዘጋጀት ጀመረች። በዚህ ሥራ ውስጥ እያለች መንግስት ለሁለት የግል ራዲዮ ጣቢያዎች ፍቃድ ለመስጠት ፍላጎት እንዳለው ሲያሳውቅ ከብዙ ማመንታት በኋላ ባለቤቷ ማመልከት እንዳለባት አሳምኗት ከልጅነት ጓደኛዋ ተፈሩ አለሙ ጋር ማመልከቷን ያወሳችው መዓዛ ከብዙ እልህ አስጨራሽ ትግል፣ የመውደቅ እና የመነሳት ጉዞ እና በብዙ ባለሞያዎች ድጋፍ በኋላ ሸገር 102.1 ኤፍ. ኤም. ሬድዮ ጣቢያ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም አየር ላይ ዋለ። በፕሮግራሞቹ ይዘት እና በአቀራብ ስልቱ አዲስ ነገር ይዞ ብቅ ያለው ሸገር 102.1 ኤፍ. ኤም. ሬድዮ ጣቢያ ከተመሰረተ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በየሳምንቱ ቅዳሜ የሚተላለፈውን 'ጨዋታ እንግዳ' እና የእሁድ ጠዋት ' ሸገር ካፌ' ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት እና በማቅረብ ትገኛለች ። በዚህም ከፍተኛ ተወዳጅነት፣ አድናቆት እና አክብሮትን አግኝታለች።

ወደፊት ሸገር ኤፍ. ኤም. ሬድዮ ጣቢያን ወደ ቴሌቪዥን ከዛም ወደሲኒማ የማሳደግ ህልም ያላት መዓዛ በኢትዮጵያ ውስጥ ሴት ሆኖ መኖር ተጨማሪ ፈተና እንደሚረጋገ ትናገራለች። ሴቶች የሚገባቸውን ቦታ አላገኙም የምትለው መዓዛ በኢትዮጵያ ሴቶችን ከአካላዊ ውበታቸው ላይ ብቻ የማተኮር አዝማሚያ ተገቢ እንዳልሆን እና ሴቶች ከውበት እና ቁመና ባለፈ ያላቸውን ጥንካሬ እና ብርታት መወሳት እንዳለበት ታሳስባለች ።

ለሴቶችም "በትምህርት ቤት ወይም በራሳቸው ንባብ አሊያም ደግሞ እርስ በእርስ በመማማር ሴቶች ራሳቸውን እንዲያስተምሩ እመክራለሁ። በባህል፣ በልማድ፣ በሃይማኖት ወይም በአጠቃላይ በህብረተሰቡ የተቀመጡ መለኪያዎችን ወይም ገደቦችን መቀበል የለባቸውም። ራሳቸውም በራሳቸው ላይ ገደብ ማስቀመጥ ከቶ አይገባቸውም። ሁሉ ነገር ወዲያውኑ አይሳካምና የሚገልጉት ነገር ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል መረዳት፤ ውስጣቸውን ማድመጥ አለባቸው።" በማለት ለኢትዮጵያ ሴቶች ምክሯን ትሰጣለች።

## ሰሎሜ ታደሰ ምህረቱ



ሰሎሜ ታደሰ የማህበራዊ ፍትሕ ተሟጋች፣ የሴቶች መብት ተሟጋች፣ የተዋጣላቸው አግባቢት (Lobbyist)፣ ሥራ ፈጣሪ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢ እንዲሁም የቀድሞው ኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የመጀመሪያዋ ሴት ሥራ አስኪያጅ ናት። ሰሎሜ ታደሰ የተወለደችው ትግራይ አክሱም ውስጥ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪያዋን በዓለም አቀፍ ግንኙነት በአሜሪካ፣ ሁለተኛውንም በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ በኔዘርላንድ አምስተርዳም ዩኒቨርሲቲ ሠርታለች። ሰሎሜ የመንግሥት ቃል አቀባይ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የሚዲያና የፖለቲካ አማካሪ በመሆን አገልግላለች። ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጀንደር ዲፓርትመንትም አማካሪ በመሆን፣ እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ሠርታለች።

ሰሎሜ "ኢመርጅ" የተሰኘው የቢዝነስ ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅም ነች። በእንግሊዝ ዓለም አቀፍ ድርጅት ዲፊድ (DFID) የሚደገፈው 'የኛ' ፕሮሞሽን ማኔጂንግ ዳይሬክተርም ነበረች። ሰሎሜ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ጥምረትን በመመሥረት እንደ "አንድ ብር ለአንድ ወገን" ያሉ ስኬታማ የዕርዳታ ዘመቻዎችን በመምራትም አስተዋፅኦ አድርጋለች። "የኛ" በወጣት ሴቶች ዙሪያ የአመለካከት ለውጥ ማምጣትን ግቡ ያደረገ ስኬታማ ፕሮጀክት ነበር። 'የኛ' በሴቶች ዙሪያ የሚንፀባርቁ አመለካከቶች፣ እምነቶችና ምግባሮች ላይ ሐሳቦች እንዲንሸረሸሩ የሚያስችል የሚዲያ ሥራ የነበረ ሲሆን፣ በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ ብቻ ከስምንት ሚሊዮን በላይ የሬዲዮ ድራማ ተከታታዮች እንደነበሩት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሰሎሜ ታዋቂ ማህበራዊ ቀስቃሽ እና አንደበተ ርቱዕ፣ የልኅቀት አስፈላጊነት አሳሳቢም ናት። በተባበረ የሴቶች ሃይል፣ የሚያምኑት ሰሎሜ በሴት መር ተቋማት እንዲሁም በግላቸው የሴቶችን አጀንዳዎች በማራመድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት።

የሴቶች ፖለቲካ ፓርቲ እና የሴቶች ዩኒቨርሲቲ የማቋቋም ራእይ ያላት ሰሎሜ የሴትነት ደጀን ናት ይላሉ ወዳጆቿዋ። ጾታዊ እኩልነትን በዚች አገር ለማምጣት ከሚፋለሙት የጦር አበጋዞች መካከል የድኅረ ሚሊየንየሞቹን ትወክላለች። ለብዙ ወጣት ሴቶች አርአያ እና የ ተነሳሽነት ምንጭ ናት።

# ሜሪ አርሞዴ (1923-1981 ዓ.ም)



በ1940ዎቹ ና በ 50ዎቹ ዘመናዊ ሙዚቃ፣ ፋሽን ና የምሽት ህይወት አዲስ አበባ ውስጥ በተለይ አራዳ አካባቢ ሲያብብ፥ ከዚያ ጋር ተያይዞ ስማቸው በዋናነት ይጠቀሱ ከነበሩት መካከል ሜሪ አርምዴ አንዷ ነበረች። በክራር ጨዋታዋ እና በወፍራም ድምጿ በማንጎራጎር የምትታወቀው አንጋፋዋ ሜሪ አርምዴ ማንጎራጎር የጀመረችው በልጅነቷ ነው። ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ገና የ13 ዓመት ታዳጊ የነበረችው ሜሪ አምባላጌ ላይ ከነበረው የአርበኛ ብላታ ጎሩይ ጦር ጋር በመቀላቀል በዘፈኑዋ እና በሽለላዋ የአርበኞቹን ወኔ እየቀሰቀሰች አዋግታ ነበር። በአንድ አውደ ውጊያ ላይም እግሯን ተመትታ ተጎድታ ነበር።

ባንዲት አጋጣሚ ከተዋወቋት ፈረንሳዊት ወዳጇ ዘመናዊ ዳንሶችን እና የፀጉር አሰራር፣ የልብስ ዲዛይን ተምራ ሌሎችን ማሰልጠን ችላ ነበር። ሆቴሏም ውስጥ የዳንስ ውድድሮች ይካሄዱ ነበር። ሜሪ በድምጻዊነቷና ክራር ተጫዋችነቷ በ1940ዎቹና 50ዎቹ በመላው ኢትዮጵያ ተፅዕኖ ፈጣሪ ነበረች። አስተሳሰቧ፣ ለሀገር ያላት ቀናኢ አመለካከትና ዘመናዊነቷ በብዙዎች ዘንድ የተመሰከረላት ነው። በአንድ ወቅት እውቋ የደቡብ አፍሪካ የታዋቂዋ ደቡብ አፍሪካዊት የአፓርታይድ ስረዓት ታጋይና ሙዚቀኛአቀንቃኝ ማሪያ ማኬቫ ወደ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጉባኤ ተጠርታ መጥታ ነበር። በመጣችበትም ወቅት ሜሪ አርምዴን አፈላልጋ አግኝታት ነበር።

ሜሪ አርምዴ ምንም እንኳ ጎስቋላ ቤት የምትኖር በኢኮኖሚም ደረጃ ድሀ የምትባል ብትሆንም ከማሪያ ጋር በተገናኙበት ወቅት የበድሉ ሕንጻን መኖሪያ ቤቷ መሆኑን አሳየቻት። ይህ ድርጊቷ ኢትዮጵያውያን ኩሩ መሆናቸውንና ስብዕናቸውን እንደሚያስቀድሙ ያሳየችበት መንገድ ነበር።

“ለምን ገንዘብ አልጠየቅሻትምና ቤትሽን የኔ ነው አላልሻትም በሚል” ከጋዜጠኞች ለቀረበላት ጥያቄ ቸግሮኛል እርጂኝ ብላት ኖሮ ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ድሃ ናቸው የሚል አንድምታ ትይዝና ስማችንንና ክብራችንን ዝቅ ታደርገው ነበር በማለት ገልጻለች። ታዋቂዋ የክራር ንግሥት ሜሪ አርምዴ ጽኑ የአርነት መንፈስ ከነበራቸው ኢትዮጵያውያን ሴቶች መካከል የምትመደብ ነበረች። ሴቶች የሚለብሱትን ልብስ እራሳቸው መወሰን በማይችሉበት ዘመን ስፌት ተምራ በመምጣት የምትፈልገውን አይነት ልብስ እየሰፋች ለራሷም ለሌሎች ሴቶችም እንደፍላጎታቸው ያለበሰች እንስት ነበረች። የመጀመሪያውን ቬሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋወቀች እንዲሁም የመጀመሪያውን የጸጉር ተኩስ ለኢትዮጵያዊያን ሴቶች ያስተዋወቀችው ሜሪ ነበረች።

# ዓለም ፀሐይ ወዳጆ



ዓለም ፀሐይ ዘርፈ ብዙ የሆነች የጥበብ ፈርጥ ናት! የተውኔት ጸሐፊ፣ የቲያትር አዘጋጅ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ ተዋናይ፣ ገጣሚ ከመሆኗም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሕጻናት ቲያትር መስራች እንዲሁም በውጭው ዓለም በተለይም በአሜሪካ ኢትዮጵያዊ የጥበብ ስራዎች ከኢትዮጵያዊያን ልቦች እንዳይጠፉ በብርቱ የምትንቀሳቀስ የጥበብ አድባር ናት።

ገና የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሆና አቻዎቿ ከፊደላት ጋር ለመተዋወቅ በሚዳከሩበት እድሜ እርሷ ግን ተሻግራ ሄዳ ብቻዋን ቁጭ ብላ ከጥበብ ጋር ስታወጋ ነበር። በውስጧ የበቀለችው እንቡጥ ጥበብ በስነ ጽሁፍ እየዳበረች ከእድሜዋ እኩል ተመንድጋ ግዙፍ የጥበብ ዋርካ ሰራች። ከትወና እስከ ቴአትር ዝግጅት፣ ከሙዚቃ ግጥሞች እስከ ልዩ ድርሰቶች፣ ከብሔራዊ ቴአትር እስከ አሜሪካን ድረስ በልዩ የስነ ጥበብ ችሎታዋ እንደ ማለዳ ፀሐይ ፈክታ ታይታበታለች። በትወና ብቃቷም የተመልካቹን ቀልብ የምትሰልበው ዓለምፀሐይ ወዳጆ በሴት ተዋናይ ዘርፍ የመጨረሻውን ጫፍ መንካት የቻለች ናት ሲሉም ብዙዎች ለእርሷ ያላቸውን አድናቆት ይገልጹታል። የሴትነት ገመድ እልፍ ሴቶችን ከህልማቸው እየጎተተ ቁልቁል በሚጥልበት ሰዓት ተነስታ ሁሉንም እየተጋፈጠች የሞራልዋን ሃያልነትና የታላቅነቷን ጥግ ለማሳየት በቅታለች። አይሆንም አይቻልም የሚሉ ነገሮች ፈጽሞ እረፍት አይሰጧትም። ሁሉንም ፈተናዎቿን በድል ታጠናቅቃቸዋለች።

የጥበብ ፈርጧ ዓለምፀሐይ ወዳጆ ጥቅምት 9 ቀን 1948 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደች። በፊት አውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ውስጥ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሳለች ነበር ግጥም መግጠም የጀመረችው። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከክበባት ጀምሮ የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች የተመለከቱት መምህራኖቿ አንዳች እምቅ ኃይል ከውስጧ እንዳለ ተገንዝበው ነበር። የዓለምፀሐይን ጥበብ እየኮተኮቱ ፍሬውም ያማረ እሸት እንዲሆን አድርገውታል። በሀብተ ጊዮርጊስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የነበራትን ቆይታ ካጠናቀቀች በኋላ ቀጣዩ ማረፊያዋ የመድሃኒዓለም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር። የዓለምፀሐይ የስነ ጽሁፍ ችሎታ መጎምራቱን ያበሰረችበት የመጀመሪያው ልዩ አጋጣሚ ያገኘችው ከዚህ ትምህርት ቤት ነው።በአንድ ወቅት በመላው ሀገሪቱ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተውጣጡ የስነ ጽሁፍ አርበኞች መካከል ውድድር ተካሄደ። ዓለምፀሐይ ወዳጆም ሁሉንም ጥላ ውድድሩን በአንደኝነት አጠናቀቀች። ከብዙዎች ፊት በኩራት ቆማም የመጀመሪያውን ብሔራዊ የጥበብ ኒሻን አጠለቀች። ጥሩ አጋጣሚና መልካም እድል ነበር።

የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ በውስጧ የተቀጣጠለውን የትወና ብቃት እንድታወጣ ይረዳት ዘንድ ወደ ብሔራዊ ቴአትር ደጅ አቀናች። በዚያም በውስጡ ይሰጥ የነበረውን የ2 አመት የትወና ስልጠና ወሰደች። ከዚህ በኋላ ነበር እንግዲህ አቻ ያልተገኘላት የሴት ተዋናይ ሆና የቀጠለችው። መስራት የጀመረችውም ገና ከመመረቋ አንስቶ ነበር። በብሔራዊ ቴአትር መስራት ከጀመረች በኋላ ታዲያ ብሔራዊ ቴአትር ያለ እርሷ የማይደምቅ የማይሞቅ ሆነ። እንቁና ድንቅ ሆና ለበርካታ አመታት በብሔራዊ ቴአትር ውስጥ ነግሳለች።

ባላት ነገር በቃኝ ብላ ጉዞዋን የማታቆም የትጋት ተምሳሌት በመሆኗ የሙያ ብቃቷን ለማዳበር ወደ ጀርመን፣ የሶቪየት ህብረት፣ ቡልጋሪያ እና ወደ ቼኮስላቪያ በማቅናት ብቁ የሚያደርጓትን የሙያ ስልጠናዎች ወስዳለች። በባህል ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የባለሙያዎች ምክር ቤት ዓለምፀሐይ ወዳጆን መሪ ተዋናይ አድርጎ ሰይሚታል።ከምግባር እስከ ተግባር ሁሉን አድሎ የሰጣት ይህቺ የጥበብ ሙዳይ በውስጧ ከያዘቻቸው እንቁ ተሰጥኦዎቿ መካከል አንዱ የሙዚቃ ግጥም ድርሰቶቿ ናቸው። በዘመኑ እውቅና ተወዳጅ ከነበሩት ድምጻውያን መካከል የእርሷን ደጅ ያልጠና የለም ብሎ ለማለት ይቻላል። ከ50 በላይ ለሚሆኑ ድምጻውያን የሙዚቃ ግጥሞችን በመስራት አጃኢብ የሚያሰኙ ልዩ ስጦታዎችን አበርክታለች። ጥላሁን ገሰሰ፣ ሙሉቀን መለሰ፣አስቴር አወቀ፣ መልካሙ ተበጀ፣ ነጻነት መለሰ፣ ሂሩት በቀለ፣ ማህሙድ አህመድ፣ቴዎድሮስ ታደሰ፣ ዳዊት መለሰ፣ ኩኩ ሰብስቤ፣ በዛወርቅ አስፋው፣ ፀሐዬ ዮሃንስ ኧረ ስንቱ ይጠቀሳል። ከእነዚህ መሃከል ለአንጋፋው ድምጻዊ የክብር ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ የጻፈችው «ኢትዮጵያ» የተሰኘው ሙዚቃ ዓለምፀሐይ የችሎታዋን ልክ ያሳየችበት ግሩም ድንቅ ስራ ነበር።

ዓለምፀሐይ ወዳጆ በጥበብ ሥራዎቿ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዋም ትታወቃለች። ፖለቲካው በሕዝቡ ላይ የሚጭነውን ቀንበር አሜን ብሎ ለመቀበል ውስጧ አይፈቅድላትም። ሁሉንም ነገር እንደ አመጣጡ ከመጋፈጥ ወደኋላ ብሎ ነገር አታውቅበትም። በደርግ ዘመን በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከትምህርት ቤት ጀምሮ የተማሪዎች መሪ ነበረች። የተማሪዎች የመብት ጥያቄና አመጽ ሲያስተባብሩ ከነበሩት መካከል አንዷና ዋነኛዋ ዓለምፀሐይ ወዳጆ ናት። በወቅቱ ትሰራበት የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ባለሙያዎች አንድ ትልቅ ጥያቄ ነበራቸው። «በመንግስት ስር ሆነን ደሞዛችንም በመንግስት ይከፈለን አሊያም የሰራተኞች ማህበር ይጠቅልለን» የሚል የመብት ጥያቄ ይዘው መንግስትን በማስፈቀድ ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ። በእለቱ ሰልፉን ተገን በማድረግም ኢህአፓ ውስጥ ለውስጥ እየገባ ወረቀት መበተን ጀመረ። በከተማው ውስጥም ሌላ ትርምስ ተፈጠረ። በወቅቱ ዓለምፀሐይ አያቷ አርፈው ሃዘን ላይ የነበረች ቢሆንም መንግስት ይህን ሴራ የጠነሰሱት እነ ዓለምፀሐይ ናቸው በሚል ይፈልጋት ጀመር። በዚህን ሰዓት ታዲያ እንዳትታወቅ እራሷን ወደ ባላገር ሴትነት ቀይራ ለስድስት ወራት ሌላ ሰው መስላ ነበር ያሳለፈችው። አንድ ቀን ግን ታማ ግዴታ ሆስፒታል መሄድ ስለነበረባት ወደዚያው አመራች። ከሆስፒታሉ ውስጥ ድንገት ከምታውቃቸው ሰዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝታ ቢጠሯት ጊዜ ዓለምፀሐይ አይደለሁም በማለት እራሷን ስለመካድዋ ታስታውሳለች። ዓለምፀሐይ ወዳጆ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አያስፈልግም ብላ ባመነችባቸው ጉዳዮች የነበራት ትግል የሚበርድ አልነበረም።

በውስጧ የነበረው ግለት በኢህዴግ መንግስትም አልበረደም። የዚህን ጊዜ ግን ተሸሽጋም የማታመልጠው ነበርና የስደትን ዳና ተከትሎ መሄድ የግድ ሆነባት። ሆድ እየባሳት የብሔራዊ ቴአትርን ደጅ በናፍቆት ተሰናብታው ጉዞዋን ጀመረች። ዓለምፀሐይ ኑሮዋን በአሜሪካን ካደረገች በኋላ ለአፍታም ቢሆን ከጥበብ መንገድ ለመራቅ አልቻለችም። ምናልባትም ለኑሮዋ ምቾችን ሊያስገኙላት የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ በመተው ሁለተናዋን ለጥበብ መገበርን መርጣለች። በውስጧ እየተንቀለቀሉ እረፍትን የማይሰጧትን የጥበብ ሃሳቦች በመከተል ያልሞከረችው ነገር አልነበረም። ጋዜጣ እያሳተሙ ማሰራጨት፣ የኪነ ጥበብ ምሽት ማዘጋጀት፣ የተለያዩ ማህበራትን ማቋቋም በሁሉም ላይ ያላትን አቅም በሙሉ በማሟጠጥ ሃሳቧን ከግብ ለማድረስ ትግል አድርጋለች። ጥበብ መክና እንዳትቀር ካላት የተለየ ጉጉት የተነሳ መጽሐፍ የማሳተም አቅሙ እያላቸው ነገር ግን በገንዘብና በተለያዩ ምክንያቶች ለማሳተም ያልቻሉትን ጸሐፊያን ሌሎችን በማስተባበር ህልማቸውን እውን አድርጋለች።

በዚህም ሶስት መጽሐፎች ለመታተም በቅተዋል። ከሰራቻቸው ትልልቅ ሥራዎች መካከል አንዱ በሀገረ አሜሪካን ምድር "ጣይቱ የትምህርትና የባህል ማዕከል" የተሰኘ የኪነ ጥበባት ማዕከል ማቋቋም መቻሏ ነው። በርካታ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን እንዲሁም የጥበብ ሰዎችን ወደ አንድ የጥበብ ማዕድ አሰባስባለች። ለ27 አመታት ያህልም ኑሮዋን ከዚያው በማድረግ ቆይታለች። እንቁዋ የጥበብ ሴት ከዚህ ሁሉ በኋላ የናፈቃትን የሀገርዋን አፈር ለመርገጥ የበቃችው ከጥቂት አመታት በፊት ነበር። የፖለቲካ እስረኛ ሆነው በውጭ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ የተደረገው የምህረት አዋጅ ለእርሷም ጥሩ አጋጣሚን ፈጥሮላታል። ወደ ሀገሯ በገባችበት ወቅትም የቀድሞ የሙያ አጋሯቿ ጨምሮ በብሔራዊ ቴአትር ሞቅ ደመቅ ባለ ዝግጅት አቀባበል አድርገውላታል። በዚህ ዝግጅት ላይ ዓለምፀሐይ ንግግር ለማድረግ ከመድረኩ ላይ ወጣች። ዳግም ሀገሯን ለማየት በሙብቃቷና በነበረው የፍቅር አቀባበል የደስታ ሲቃ እየተናነቃት "ቀድሞም ቢሆን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊ ተስፋ ቆርጬ አላውቅም ነበር" ስትል ውስጧ የነበረውን የተስፋ እምነት ትክክል መሆኑን አረጋገጠች። ዓለም ፀሐይ ወዳጆ በኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ታሪክ ውስጥ ደረጃ የሚሰጣት ሳይሆን የደረጃ ክልሉን ጣራ ጥሳ ቀድማ በመድረኩ ላይ የዘበነችበት "እቴጌ" ናት፣ ለብዙ የ ጥበብ ሰዎች የ ንሸጣ ምንጭ እና አርአያ መሆንም ችላለች።

## የምወድሽ በቀለ



ደራሲ፣ ገጣሚ እና ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለ አንጋፋ ጸሃፊና የሴቶች መብት ተሟጋች ናቸው። የምወድሽ የተወለዱት በ1960 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አፍሪካ አንድነት ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ ከተማ ት/ቤት ተከታትለዋል። የምወድሽ የኢትዮጵያ የፌደራል ፖሊስ ጋዜጣ በሆነው የፖሊስና እርምጃ ጋዜጣ ውስጥ ለ26 ዓመታት ሰርተዋል። በዚህም በዘጋቢነት እና በወንጀል ምርመራ ጋዜጠኝነት ከዚያም በአርታዒነት የሰሩ ሲሆን በዋና አርታዒነት ደረጃ በመስራት የመጀመሪያዋ ሴትም ናቸው። ለዐሥር ዓመት ደጋሞ የፖሊስ እና እርምጃው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና የፕሬስ ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል።

የምወድሽ በ19 ዓመታቸው ፣ በባህልና ስፖርት ሚኒስተርበ 1979 ዓ.ም በተዘጋጀው የሀገር አቀፍ የግጥም ውድድር አሸንፈዋል። በ 1990 ዓ.ም “የባከነ ጊዜ” የግጥሞች ስብስብ መጽሀፋቸውን ያሳተሙ ሲሆን፣ በባህልና በተለያዩ ምክንያቶች በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ጎልተው የታዩበት ስራ ነበር። ደራሲ፣ ገጣሚ እና ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለ ስምንት ልቦለድ፣ግጥምና አጫጭር ታሪኮችን የያዙ መጽሐፎችን በግላቸው ጽፈዋል። ስድስት ደግሞ ከሌሎች ጸሐፊዎች ጋር በመሆን አሳትመዋል።

የምወድሽ ሴት ጸሀፊያንን ለመደገፍ በማሰብ የግጥም ምሽቶችን ያዘጋጁ ነበር። የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ፕሬዚዳንት ነበሩ። አሁን የቦርድ ሰብሳቢ ናቸው። አንጋፋዋ ጋዜጠኛና ደራሲ “የሴቶች ይችላሉ” የሚል የበጎ አድራጎት ድርጅት መስርተው በ ዳይሬተርነት እያገለገሉ ይገኛሉ። ማኅበሩ ሴቶች ያላቸውን ሚና በመገናኛ ብዙኃን ለማጉላት፣ ሴቶች ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ተሳትፎ እና ሚና ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል።

የምወድሽ ዘመናቸውን የ ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ፣ የሴቶችን መብት ለማስጠበቅ እንዲሁም ሴቶችን ከሚደርስባቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች ማላቀቅና ተሳትፏቸውን ከፍ ለማድረግ የተለያዩ የ ስነ ፅሁፍ፣ የ ጋዜጠኝነት እና የ በጎ አድራጎት ስራዎችን የ ሰሩ ዝምታ ሰባሪ እንስት በመሆን ለብዙ ሴቶች አለኝታ መሆን ችለዋል።

## ፊርማዬ ዓለሙ



ፊርማዬ በአማርኛ ሥነ ግጥም የገዘፈች እንስት ነበረች። በሳል ገጣሚና የግጥም ፈርጥ የነበረችው ፊርማዬ አለሙ ጥቅምት 27 ቀን 1948 ዓ.ም ሆሳዕና ከተማ ልዩ ስሙ "ዘበኛ ሰፈር" እየተባለ በሚጠራ ቦታ ተወለደች። ፊርማዬ መደበኛ ትምህርቷን የጀመሩት ጊምቢቹ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሲሆን ቀጥሎ በወቅቱ ሆሳዕና ራስ አባተ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ይባል በነበረው በአሁኑ የካቲት 25 ተከታትላለች።

ገና በታዳጊነቷ ዘወትር አርብ በትምህርት ቤቷ ይዘጋጁ በነበሩት የክርክር ፕሮግራሞች ላይ ንቁ ተሳትፎ ታደርግ ነበር። የመጀመሪያ ግጥም የሞከረችው የስምንት ዓመት ልጅ ሳለች ነበር። ፊርማዬ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለች እድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻን በመቀላቀል በሐረርና በሆሳዕና ዘማች ሆናአገልግላለች።ከዘመቻ በኋላም ወደ ነርሶች ማሰልጠኛ ገብታ የነበረ ቢሆንም ሙያው የነፍሷ ጥሪ ባለመሆኑ አቋርጣለች።

ከልጅነቷ ጀምሮ ግጥም ትወድ ስለነበርም በተፈጥሮ ያገኘችውን የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌ በትምህርት ለማዳበር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማታው መርሀ ግብር ተምራ በኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ በ1987 ዓ.ም በዲፕሎማ ተመርቃለች። ለእውቀት የማትቦዝነው ፊርማዬ ተመልሳ በ1988 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲው በመግባት በዲግሪ መርሐግብር ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ጥቂት ሲቀራት ነበር  በ 43 አመቷ በ 1993 ሞት የቀደማት።

ፊርማዬ በሥነ-ጽሁፍ ችሎታዋ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መጣጥፎቿንና ግጥሞቿን በኢትዮጵያ ሬድዮ ፣ በለገዳዲ የትምህርት ማሰራጫ፣ በኢቲቪ በማቅረብ በኢትዮጵያውያን ህሊና ውስጥ የማይረሳ ትዝታን ትታ አልፋለች። ከተወዳጅ ግጥሞቿ ጥቂቶቹንም የ "አፍሪቃ ክራሞት" በተሰኘውና በ1992 ዓ.ም በታተመው መጽሐፍ አበርክታልን አልፋለች።

ገጣሚት ፊርማዬ ዓለሙ ከተለያዩ ደራሲያን ጋር በመሆን በ1990 ዓ.ም. "እኛ" 170 ግጥሞች በተሰኘ የግጥም መድብል አማካኝነት 26 ስራዎቿን ለህትመት አብቅታለች።

ፊርማዬ በሞት ከተለየችን ከሌላዋ ደራሲ አረጋሽ ሰይፉ ጋር በመሆን በ1989 ዓ.ም ሴት ደራስያንን በማሰባሰብ የሴት ደራስያን ማህበርን በማቋቋምና በማጠናከር አስተዋጽኦ አድርጋለች። በጊዜው ማህበሩ ቢሮ ስላልነበረው የመኖሪያ ቤቷን ጭምር እንደ ቢሮ ትጠቀምበት ነበር።  አረጋሽ ካለፈች በኋላም ኃላፊነቱን በመረከብ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ማህበሩን እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ስትመራ ቆይታለች።

## ህይወት ተፈራ



ህይወት ተፈራ ተወዳጅ ኢትዮጵያዊት ደራሲ እና የቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) አባል ነበሩ። ህይወት ተወልደው ያደጉት በምስራቅ የኢትዮጵያ ክፍል በሐረር ከተማ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሐረር ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በማቅናት  ከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኋላም በ ካናዳ ተከታትለዋል።

ህይወት ተፈራ በ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ንቁ የ ፖለቲካ ተሳትፎ አድርገዋል። በ ፖለቲካ ተሳትፏቸውም ምክንያት ከ 1970_1978 ዓ.ም. ድረስ በ ደርግ መንግስት ታስረው ነበር። ከእስር ከተፈቱ በኋላ መጀመሪያ ጣልያን ቀጥሎ ካናዳ ኑረዋል። ካናዳ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በተለያዩ የስራመስኮች ልምድ አግኝተዋል። በመጀመሪያ አስተባባሪ ሆነው “ፒፕል ቱ ፒፕል ካናዳ” የተባለ ድርጅት ውስጥ ለዓመታት አገልግለዋል። “ሴንተር ፎር ውሜን” የተባለ ድርጅትም  ውስጥ 2 ዓመታት ከጥናት ጋር የተያያዙ ስራዎችን ሰርተዋል። ቀጥለውም በዚያው በካናዳ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ለረጅም ግዜ ሰርተዋል። ደራሲ ሕይወት ተፈራ ከ26 ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላጠቅልለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሶስት ተወዳጅ መጽሃፍትን ጽፈዋል።

እነኝህም የመጀመሪያው “Tower in the sky” ሁለተኛው “Mine to win” እንዲሁም “ምንትዋብ” የሚሉ ናቸው። Tower in the sky በጣም የተወደደ መጽሃፍ ሲሆን የ 19 60 እና የ 70 ዎቹን  ትውልድ ማዕከል አድርጎ የቀረበ ግለ ታሪክ ነው። በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን ያገኘው በደፋር አዕምሮና በሰከነ ዕድሜ ታሪኩ ሳይዛባ በመጻፉ ብቻ አይደለም። ከሁሉም በላይ ይዞት በመጣው ምክንያታዊ አስተሳሰብ ጭምር ነው። ጸሐፊዋ ይህንን መጽሐፍ የጻፉት በሕይወታቸው ላይ ትልቅ አሻራ ያሳረፈባቸውን የኢሕአፓ አመራር የነበረውን ጌታቸው ማሩ የተባለ ዝነኛ ወጣት አደራ ተሸክመው ነው። እርሳቸው እንደሚገልጹት “መጽሐፉን የፃፍኩት ያለምክንያት ከመጠፋፋትና አላስፈላጊ መስዋእትነት ከመክፈል በመውጣት እንነጋገር እንወያይ የሚለው የጌታቸው ማሩ ሐሳብ በውስጤ ስላለ ነው፤” ብለዋል።መጽሐፉ በብዙዎች ዘንድ የደርግን ዘመን ከተረኩ ጥቂት እውነተኛ ዘገባዎች መካከል አንዱ ነው።

ሁለተኛው መጽሃፍታቸው “Mine to Win” ይሰኛል። መፅሃፉ ስለ ሀገር በቀል እዉቀት የሚያትት ነዉ። ስለ ቅኔና ተያያዥ ጉዳዮች ያሳያል። ረጅም ጥናት የተደረገበት ስራቸው ነዉ። ሶስተኛው “ምንትዋብ” የሚባለው ሲሆን ታሪካዊ ልብወለድ መፅሐፍ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ሥልጣን ተቆናጥጠው፣ ሀገርን መምራት የቻሉ ሴቶች ጥቂት ናቸው፤ ከአንድ እጅ ጣት ቁጥር አይልቁም። ንግስት ሳባ፣ እቴጌ መስቀል ክብራን፣ ኤቴጌ ኢለኒ፣ ወዘተ። ከነዚህ ሴቶች ተርታ የምትሰለፍ ናት፡- የቋራዋ ምንትዋብ።  በ18ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ህያው አሻራ ትታ ያለፈች ንቁ፣ ሃይለኛና ተራማጅ መሪ እንደነበረች ይነገርላታል። ሕይወት ተፈራ፤ ያንን የምንትዋብን የንግስና ዘመን “የታሪክ መጋረጃ” በምንትዋብ ገልጠው ለማሳየት ሞክረዋል። በ ተመራማሪዎች እይታ ምንትዋብ ስለ ኢትዮጵያ ሴት መሪዎች ማወቅ የሚሹ ሁሉ ማንበብ ያለባቸው ስራ ነው።

ህይወት ተፈራ ራሱን አርነት ያወጣ መንፈስ ባለቤት ናቸው። በሂዎታቸው ጎዳና ወገንተኝነት፣አስመሳይነትና አድርባይነት የሚባሉት እኩዮች የሉም። ምንም እንኳ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡለት ትግል በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ጓዶቻቸውን ቢያሳጣቸውም መጽሃፍቶቻቸው ላለው እና ለመጪው ትውልድ መማሪያዎች ሆነው ይቀጥላሉ፣ ትውልድም በአርዓያነት ሲዘከራቸው ይኖራል።

# መዓዛ መንግስቴ



መዓዛ መንግስቴ ትውልደ ኢትዮጵያዊት ደራሲ ናት። በኢትዮጵያ ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንደ ስደት፣ ጦርነትና አብዮት ባሉ ጭብጦች ላይ ጽፋለች። መዓዛ በ1971 ዓ.ም በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ተወለደች። አራት አመት ሲሞላት የወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ለቤተሰቧ ደህንነት አስጊ ስለነበረ መላው ቤተሰብ ሃገር ጥሎ ተሰደደ። በመጀመሪያ ናይጄሪያ ከቆዩ በኋላ ሰባት ዓመት ሲሞላት ወደ አሜሪካ በማቅናት ትምህርቷን እዚያው ተከታትላለች በከፍተኛ ትምህርትም ስነ ጽሁፍ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ አጥንታለች። ለመፃፍ ብዕር ያነሳችው ግን ቆየት ብላ ነው። በአንድ ጠዋት ጋዜጣ ስታገላብጥ አንድ ፎቶግራፍ ቀልቧን ይይዘዋል። በርከት ያሉ እናቶች የልጆቻቸውን ፎቶ ይዘው ሲያለቅሱ የሚያሳይ ምስል ነበር። በደቡብ አሜሪካዊት ሀገር የአንድ ወታደራዊ አገዛዝን ከስልጣን መወገድ አስመልክቶ የተደረገ ክብረበዓልን የሚዘግብ ፅሁፍ ነበር። ያ የጋዜጣ ላይ ፎቶ ውስጣዊ መነቃቃት ፈጥሮባት ስለ ሀገራቸው ተመሳሳይ የእናቶች እጣ ፈንታ እንድታስብ እድል ሰጣት። በርግጥም በኢትዮጵያም እንዲሁ የጠፉ እና የሞቱ ልጆቻቸውን ፎቶግራፍ ይዘው የሚያለቅሱ እናቶች አሉ። በአብዮቱ ዘመን ያልተነገሩ በርካታ የቤተሰቦች በተለይም የሴቶች የሀዘን እና የማጣት ስንክሳሮች አሉ። ሁሉም ኢትዮጵታዊ ቤተሰብ ውስጥ የገባ መቼም ጥቁር ታሪክ አለ በማለት ይህንኑ ታሪክ ለመፃፍ ውስጣቸው ወጠነ። “Beneath the Lion’s gaze” ለሚለው እምር ስራም መነሻው ይሄው ፎቶግራፍ ነበር።

“Beneath the Lion’s gaze” የተባለው የመዓዛ መጽሀፍ ትኩረቱን አንድ ቤተሰብ ላይ አድርጎ በወታደራዊ ሶሻሊስት ኢትዮጲያ ላይ መቼቱን ያደረገ መጽሃፍ ነው። በብዙኃን ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፎ ለበርካታ ሽልማቶችን ለማግኘት በቅቷል።

በፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ በፖርቱጊዝ፣ በጀርመን፣ በኢጣልኛ፣ በደች፣ በ ስዊድን ቋንቋዎች ተተርጉሞም ለንባብ በቅቷል። በዘ ጋርዲያን ከ10 ምርጥ ወቅታዊ የአፍሪካ መጽሃፎች አንዱም ሆኖ ተመርጧል። በ2010ዓ.ም በክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር፣ ቦስተን ግሎብ እና ሌሎች ህትመቶች ከምርጥ መጽሃፎች አንዱም ተብሎ ተሰይሟል።

ሁለተኛው ስራዋ “The shadow king” የሚል ሲሆን ስለ ጣልያን ወረራን ታሪክ ያወሳል። የጦርነት አስከፊ መዘዝም መሪ ጭብጡ ነው። ይህ መጽሀፍ ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ሴት የነፃነት ታጋዮችን የሚዘክር ነው። መጽሃፉ ለነፃነት በተደረገው ትግል ላይ የጥቂት ወንዶች ሚና በጎላበት ሁኔታ ሴት የነፃነት ታጋዮች ከታሪክ መዝገብ በመፋቃቸው ግዙፍ አስተዋፅኦቸውን ለማሳየት አስርት አመታትን ወደ ኋላ ያስቃኛል። ባልተለመደ መልኩ ታሪኩን ከጣሊያናዊ አንፃርም ይመለከታል። መዓዛ ይህንን ከሁለት ተፃራሪ ቡድኖች አንፃር አንድን ሁኔታን መመልከትን በመጀመሪያው መፅሀፏቸውም ተግብረውታል። እንደደራሲ ከመጥፎውም ከመልካሙም እግር ስር ቁጭ ብለን ሀቃቸውን መጻፍ ይገባናል የሚል አቋም አላቸው። መጽሃፉ በ2012 ዓ.ም በተካሄደው የቡከር ሽልማት የእጩነት ዝርዝር ውስጥ ገብቶ ነበር።

መዓዛ የፉል ብራይት ፌሎሺፕ እኤአ አሸናፊ ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከተመረጡ ልብወለድ ደራሲዎች ውስጥ ምርጧ በመሆን በ2010 ተጨማሪ ሽልማቶችን ወስዳለች። የክሬቲቭ ካፒታል አዋርድ የሥነ ጽሁፍ የልብወለድ ሥራዎች ደራሲ በመሆን በ 2011 ዓም ተሸልማለች።

መዓዛ መንግስቴ፤ በተለያዩ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሥራዎችንም ታካሂዳለች። “ዘ ወርድስ ዊዛውት ቦርደርስ” የተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከሰቱ ግጭቶች የሚፈናቀሉ ሕፃናትና ወጣቶችን መብት የሚያስከብር ተቋም ሐላፊ ሆናም አገልግላለች። በበአሁኑ ወቅት በኒዮርክ ዩኒቨርስቲ በኪዊንስ ኮሌጅ በፈጠራ ስነ ጽሁፍ አጻጻፍ ዘዴ መምህር ስትሆን፤ በፕሪስተን ዩንቨርስቲ በሊዊስ ሴንተር ኦፍ አርትስ ኮሌጅም በመምህርነት እየሰራች ነው።

## ጸዳለ ለማ



ጸዳለ ለማ የአዲስ ስታንዳርድ መጽሄት መስራችና ተጽዕኖ ፈጣሪ ኢትዮጵያዊት ጋዜጠኛ ነች። ጸዳለ በህትመት ጋዜጠኝነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በበይነመረብ ጋዜጠኝነት ከስቶኮልም ዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ተከታትላ አጠናቃለች።

ጸዳለ ለማ ጋዜጠኝነትን የጀመረችው እኤአ በ1992 ዓ.ም ሲሆን እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ሶስት የሀገር ውስጥ ጋዜጦች ሰርታለች። ከሰራችባቸው ጋዜጦች መካከል በወቅቱ ታዋቂ በነበረው አዲስ ትሪቡን ጋዜጣ ሲሆን በዚያም ከፍተኛ ዘጋቢ በመሆን ሰርታለች። ከ1997 ምርጫ በኋላ በተፈጠረው አለመረጋጋት ፣ የጋዜጠኝነት ሥራን በመተው አዲስ አበባ በሚገኘው የእስራኤል ኤምባሲ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ሰርታለች። ጸዳለ በመጀመሪያ የኮሙዩኒኬሽን ኤክስፐርት በመሆን ከዚያም የክልል ፖለቲካ ጉዳዮች እና የአምባሳደሩ የሚዲያ አማካሪ በመሆን ሰርታለች። በ 2002 ዓ.ም ከእስራኤል ኤምባሲ ወጥታ በጋዜጠኝነት ሙያ የወደፊት ተሳትፎ ላይ ጥናት አድርጋለች ። ከአንድ አመት ጥናት በኋላም  እኤአ የካቲት 2011 ላይ አዲስ ስታንዳርድ ወርሃዊ መጽሔት አቋቋመች። ፅዳለ ላለፉት አስር አመታት አዲስ ስታንዳርድ መፅሄትን በኢትዮጵያ የነጻ ሚዲያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተፅዕኖ ካላቸው መፅሄቶች አንዱ እንዲሆን አድርጋዋለች።  እኤአ በ2014 በአህጉሪቱ አፍሪካ ከ50 Rising Stars" መካከል አንዷ ሆና ተመርጣለች። በ 2015 የባንዱንግ ዓለም አቀፍ አማካሪ ቦርድ አባል ሆናለች። ጸዳለ ከሴቶች መብት ጋር በተያያዝ የተለያዩ መድረኮችን አዘጋጅታለች። በትጋቷ እና በቁርጠኝነት የምትታወቅ አርአያ ጋዜጠኛ ነች።



# ሴት ተመራማሪዎች

# ሶስና ሀይሌ (ፕሮፌሰር)



ፕሮፌሰር ሶስና ሀይሌ ይባላሉ። የቁስ ሳይንስና የምህንድስና ሊቅ ሲሆኑ፤የመጀመሪያውን ጠጣር የአሲድ ነዳጅ ለዓለም ያስተዋወቁ ሳይንቲስት ናቸው። በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆኑት ፕሮፌሰር ሶስና ኃይሌ የተወለዱት በ1958 ዓ.ም በአዲስ አበባ ነው። ፕሮፌሰር ሶስና የህጻንነት ዘመናቸውን ለተወሰኑ ዓመታት በአዲስ አበባ ያሳለፉ ሲሆን በትምህርታቸው ጠንካራ ከሚባሉት ተማሪዎች መካከል የሚመደቡ ነበሩ። በኢትዮጵያ በ1966 ዓ/ም በነበረው አብዮት አባታቸው እውቁ የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ የደርግን መንግስት በመቃወማቸው የጥቃት ሰለባ በመሆን ክፉኛ ቆስለው ለህክምና ከነ ቤተሰባቸው ሀገር ለቀው በመውጣቸው ፕሮፈሰር ሶስናም በ 10 ዓመታቸው አብረው ወደ አሜሪካ ተሰደዱ።

በ1978 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪቸውን በማሳቹሴትስ የቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት በማቴሪያል ሳይንስና በኬሚካል ምህንድስና ማግኘት የቻሉ ሲሆን፤ ሁለተኛ ዲግሪቸውን ደግሞ በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ማሳካት ችለዋል። ፕሮፌሰር ሶስና የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ወዳገኙበት የማሳቹሴትስ የቴክኒሎጂ ኢኒስቲትዩት በማቅናት በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት ዶክትሬት (PhD) ትምህርታቸውን ለመማር እንዲያስችላቸው በሚወዱት የማቴሪያል ሳይንስና የኬሚካል ምህንድስና ዘርፍ መመረቅ ችለዋል። ዶ/ር ሶስና ከዚህ የተሳካ የትምህርት ጉዟቸው በኋላ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ካገኙበት የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ከማምራታቸው በፊት ሲያትል በሚገኘው በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት አገልግለዋል። በዚህ የሶስት ዓመት ቆይታቸውም ሀገራቸውን የሚያኮራና አፍሪካንም የሚያስጠራ ትልልቅ የምርምር ስራዎችን ለመስራት በቅተዋል።

በንድፈ ሀሳብ የቀሰሙትን ዕውቀት ወደተግባር ለመለወጥም በታዳሽና በዘላቂ የሀይል አቅርቦት ቴክኖሎጂ ዘርፍ በርካታ ምርምሮችን አድርገዋል።በጎርጎሪያኑ 1990ዎቹ መገባደጃ ላይም «ሱፐር ፕሮቶኒክ» የተባለ አዲስ ውህድ በመጠቀም የመጀመሪያውን ጠጣር የአሲድ ነዳጅ በእንግሊዝኛው አጠራር «ሶሊድ አሲድ ፊውል ሴል»በመፍጠር ለዓለም አስተዋውቀዋል።እሳቸው እንደሚሉት ፈጠራው ከሀይል አማራጭነቱ በተጨማሪ የአካባቢ ብክለትን የሚከላከል ጭምር ነው።

ፈጠራው በመላው ዓለም እየጨመረ የመጣውን የኤለክትሪክ ሀይል ፍላጎት ለማሟላት አስፈላጊ ሲሆን፤፤እንደ ኢትዮጵያ ታንዛኒያና ዩጋንዳ ላሉ ብዙ የፀሐይ ብርሃንና የውሃ ኃይል ላላቸው የምስራቅ አፍሪቃ ሀገራት የኤለክትሪክ ሀይል አቅርቦትን ለማሻሻል የሚያስፈልገው፤የተሻለ የኤሌክትሪክ ፍርግርግ ወይም ደግሞ የሀይል ማከማቻ ቢሆንም፤ በተለያዩ ሁኔታ የውሃ መቀነስ ቢያጋጥም፤እሳቸው የፈጠሩት የሀይል አማራጭ እንደ ባትሪ ሊያገለግል እንደሚችልም ያስረዳሉ።

ሳይንቲስቷ ከጎርጎሪያኑ 1993 ጀምሮ በዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት፣ከ1996 ጀምሮ በካሊፎርኒያ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቁሳቁስ ሳይንስ ፕሮፌሰር በመሆን ለ 18 ዓመታት ያገለገለሉ ሲሆን፤ በ2012 ዓ/ም በኢንጂነሪንግ እና በተግባራዊ ሳይንስ ክፍል ውስጥ ሊቀመንበር ሆነው ከተሾሙ ሁለት የመጀመሪያ ሴቶች አንዷ ናቸው። ከ 2015 ዓ/ም ወዲህ ደግሞ በችካጎ በኖርዝ ዌስት ዩኒቨርስቲ በማስተማር ላይ ይገኛሉ።ከዚህ የማስተማር ስራቸው በተጨማሪ በፈጣን ባትሪዎች ፣መፈተሻዎች ወይም «ሴንሰሮች» የኤለክትሪክ ፓምፖች እና ጠጣር የአሲድ ነዳጅ ላይ፣ «ቴርሞኤሌክትሪክ» እና «ፌሮኤሌክትሪክ»በተባሉ ሙቀትና ብረት ነክ ኤለክትሪካዊ ቁሶች ላይ፣ እንዲሁም ለአነስተኛና ተንቀሳቃሽ የሀይል ማመንጫዎች በሚሆኑ የመሣሪዎች ላይ ምርምር ያደርጋሉ።አነስተኛ ዋጋ ባላቸው ግብዓቶች ላይ እሴት በመጨመር ወደ ምርት እንዲለወጥም ይሰራሉ። እነዚህ ስራዎቻቸው የሀይል አቅርቦትና አማራጭ መስክ ወደ አዳዲስ ግንዛቤ እና አፈፃፀም እንዲሄድ አድርጓል።ከዚህ በተጨማሪ የፕሮፌሰር ሶስና ስራዎች በዓለም ላይ እያደገ የመጣውን የኃይል ፍላጎት ለማርካት ነፋስንና የፀሐይ ብርሃንን በመጠቀም ረገድ አዳዲስ መንገዶችን ፈጥረዋል።

ፕሮፌሰሯ ከ290 በላይ የምርምር ጽሁፎች ያሳተመሙ ሲሆን 20 የሚሆኑ ደግሞ የፈጠራ ባለቤትነት መብቶችን ይዘዋል ። በሙከራና በንድፈ-ሃሳባዊ ምርምር አማካኝነት መሰረታዊ የሳይንስ ዕውቀትን በማስጨበጥ ለሙያው ላባረከቱት አስተዋፅኦ በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል።ከነዚህም ጥቂቶቹ በሳይንሱ ዘርፍ ለሰው ልጆች ህይወት መሻሻል ላበረከቱት አስታዋፅኦ በጎርጎሪያኑ 2010 ካገኙት የሰብአዊነት ሽልማት ጨምሮ፤ በጎርጎሪያኑ 1994 የብሔራዊ ሳይንስ ፋውንዴሽን ብሔራዊ የወጣት ተመራማሪ ሽልማትን፣በ1997 ቲ ኤም ኤስ ሮበርት ላንሲግ ሃርዲ ሽልማትን፣በ2000 ዓ/ም ከአሜሪካ የሴራሚክ ማኅበረሰብ ሽልማትን፣ በ2001 ዓ/ም የጄ.ቢ.ዋግነር ሽልማት ከኤለክትሮ ሜካኒካል ማኅበረሰብ ተሸልመዋል። በማስተማርና በማማከር ስራ ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የቁስ ሳይንስና የምህንድስና የሳይንስ ሊቃውንት በአሜሪካዊ የቁስ ሳይንስ ሊቅ ዴቪድ ተርንቡል ስም በሚሰጠው ሽልማትም የ2020 ተሸላሚ ናቸው።

ፕሮፌሰር ሶስና ሀይሌ በርትቶ በመስራት የሚያምኑ ሳይንቲስት፣ እናት፣አማካሪና መምህር ሲሆኑ፤ የወላጆቻቸው ትልቅ ድጋፍ የስኬታቸው ቁልፍ መሆኑን ይገልፃሉ።ስኬትና ስራ መጨረሻ የለውም የሚሉት ፕሮፌሰር ሶስና፣ የወደፊት ተመራማሪዎችን ወደዚህ ዘርፍ እንዲገቡ ተነሳሽነት ፈጥረዋል።

## ሰገነት ቀለሙ (ፒ.ኤች.ዲ)



ዶክተር ሰገነት በግብርና ምርምር፣የነፍሣት አካላት እና አካባቢ ጥናት ፈር ቀዳጅ ተመራማሪ ናቸው። ጎጃም - ፍኖተሰላም ከተማ ነው ተወልደው ያደጉት። ዶ/ር ሰገነት የቤተሰቦቻቸውን የግብርና ምርት አካባቢው በሚገኝ ቅርብ ገበያ እየወሰዱ ይሸጡ ነበር። በዚያን ጊዜም ሰብሎቹን ለማምረት ከፍተኛ ጉልበት እንደሚያስፈልግና በአዝዕርቱ ላይ የሚከሰቱ በሽታዎች በትርፋማነቱ ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመገንዘብ በቁ። የህይወት ዘመን ምርምራቸውንም በእፅዋት ሞሎኪዩላር ፓቶሎጂ እንዲጀምሩ ያደረጋቸው አጋጣሚ የተፈጠረው ግን የአንበጣ መንጋ በመንደራቸው ያለውን አዝእርት ሙሉ በሙሉ በማውደሙ ምክንያት ርሃብ በተከሰተ ወቅት ነበር። ከዚያን ወቅት ጀምሮ ዶ/ር ሰገነት ህይወታቸውን ሙሉ ርሃብን በመዋጋት፣ የሰብል ምርታማነት በማሳደግ እና ኋላ ቀር የግብርና ስርአተ-ምርትን በማሻሻል ላይ አትኩሮት እና ምርምር ላይ አደረጉ።

የመጀመርያ ዲግሪያቸውን በ1979 በእፅዋት ሳይንስ ከ አለም ማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በ1985 ከሞንታና ዩኒቨርስቲ በ Plant Pathology፣ እንዲሁም የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በ1992 ከካንሳስ ዩኒቨርስቲ በ molecular biology and plant pathology አግኝተዋል። ዶ/ር ሰገነት የድህረ-ዶክትሬት ምርምራቸውን በኮርኔል ዩኒቨርሲቲ “ሞሎኪዩላር ዲተረንትስ ኦፍ ፓቶጀነሲስ” ላይ ትኩረት በማድረግ አጥንተዋል።

በሥራ መስክ እአአ ከ1992--2007 እንደ ሲኒየር ሳይንቲስት ሆነው በCIAT(Center for Tropical Agriculture) ኮሎምቢያ ውስጥ ያገለገሉ ሲሆን በኮሎምቢያ ጥቁር ሳይንቲስት እርሳቸው ብቻ ነበሩ። ከ እአአ 2007 እስከ 2013 ድረስ የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ባዮሳይንስ ማዕከል (BecA--Biosciences eastern and central Africa Hub) ዳይሬክተር በመሆን ያገለገሉ ሲሆን ከ 2013 ጀምሮ  የአለም አቀፉ ነፍሳት ፊዚዮሎጂና ኢኮሎጂ ማዕከል የመጀመሪያዋ ሴት ዳይሬክተር ጄነራል ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

ዶ/ር ሰገነት ለአመርቂ ስራዎቻቸው በርካታ ሽልማቶችን እና እውቅናን ያገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ እአአ በ 2011 የሶስተኛው ዓለም የሳይንስ አካዳሚ ሽልማት (TWAS prize) የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት ተሸላሚ፣በ2013 የአመቱ ምርጥ ሳይንቲስት፣ በ2014 የፎርብስ ምርጥ 100 ተጽዕኖ ፈጣሪ አፍሪካዊያት ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል፣ 2014 የሎሬአል-ዩኔስኮ ሽልማት፣ በ 2016 ከቴል አቪቭ ዩኒቨርሲቲ እሥራኤል ውስጥ የክብር ዶክትሬት፤ በመስከረም 2018 በሴቶች የኢኮኖሚ ፎረም ከፍተኛ የሆነውን የአስርት ዓመታቱ ምርጥ ሴት ሽልማትን አግኝተዋል፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቅርንጫፍ የሆነው ዩ ኤን ውሜን በ 2020 የዓለማችን ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰባት ሴት ተመራማሪዎችን ይፋ ባደረገበት ዝርዝሩ ከሰባቱ ስመጥር ተመራማሪዎች መካከል ኢትዮጵያዊቷ ዶ/ር ሰገነት ቀለሙን አካቷቷል። በ 2022 ደግሞ ከፍተኛ ክብር ያለውን የአለም አቀፍ የክብር ኤሊስ አይስላንድ የክብር ሜዳልያ ተሸልመዋል።

ባለምጡቅ አእምሮ ባለቤት የሆኑት ዶ/ር ሰገነት ሴትነት ፈተና ከሆነባት ኢትዮጵያ ወጥተው በሳይንስ ዘርፍ አሉ ከተባሉት እንስቶች አንዷ በመሆን ለብዙ ሴቶች አብነት እና አርአያ መሆን ችለዋል።

## የዓለም ፀሐይ መኮንን (ፕሮፌሰር)



ፕሮፌሰር የዓለም ፀሐይ መኮንን በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሮፌሰር ናቸው። በጥንካሬያቸውና በታታሪነታቸው የሚታወቁት እኚሁ ተመራማሪ ታሪክና ተሞክሮ የራስን ምርጫና የሥራ ዓለም በመተው ቅድሚያ ለቤተሠብ የሚለውንና የተፈጥሮ ሣይንስ ዘርፍን ለወንዶች የሚያስቀድመውን ዘልማድ የሻሩ ብርቱ ሴት ናቸው።

ፕሮፌሰር የዓለም ፀሐይ መኮንን በአሰላ ከተማ በ1947 ዓ.ም ነው የተወለዱት። በአባታቸው የፖሊስ መኮንንነት ሙያ ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ለማደግ ተገደዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በደሴ እና በጎጃም ፍኖተ ሠላም ከተሞች ተከታትለዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ነው የተማሩት።

ለሣይንስ ትምህርት ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸው እኚሁ ብርቱ ሴት ከክፍላቸው ከፍተኛውን ውጤት በማዝመዝገብ የተማሪዎች ሁሉ ቁንጮ እንደነበሩ ይጠቀሣል። ምንም እንኳ እርሳቸው በተማሩበት የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመን መፅሀፍና  ቤተመፃህፍት ብርቅ ቢሆኑም፤በየአጋጣሚው  የሚያገኟቸውን መጻሕፍት በማንበብና ከመምህራን የሚያገኙትን ዕውቀት በመጠቀም በሂሳብና ፣ በተፈጥሮ  ሳይንስ  የተሻለ እውቀት ለመጨበጥ ሞክረዋል።ያ በመሆኑ በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ይቅርና የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ  በቅጡ ባልዳበረት በዚያ ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት አጠናቀው፣ በ1964 ዓ/ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ-ህይወት ትምህርት ክፍልን በ16 ዓመታቸው ተቀላቅለዋል። የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ሣሉም

በጊዜው የነበረውን የመንግሥት ዕድገት በሕብረት ዘመቻ ተቀላቅለዋል። በትውልድ ቦታቸው ኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ውስጥ የተመደቡ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥነ ሕይወት ትምህርት በማስተማር ለወገናቸው ያላቸውን አለኝታነት አሥመስክረዋል። ከዘመቻው መጠናቀቅ በኋላም በጊዜው በነበረው የፖለቲካ ትኩሣት ምክንያት ትምህርታቸውን መቀጠል አልቻሉም። በመሆኑም አራት ዓመታትን ይፈጅ የነበረውን ትምህርት በሰባት ዓመታት ለማጠናቀቅ ተገደዱ።

የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው በረዳት መምህርነት እዚያው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲያስተምሩ ቆይተው ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በእንስሳት ጥናት/zoology/ ዘርፍ በድህረ ምረቃ ፕሮግራሙ የመጀመሪያዋ ሴት ተመራቂ በመሆን በ 1980 ዓ.ም አጠናቀዋል። በማስከተልም ጀርመን ሃገር ወደሚገኘው ሐይደልበርግ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት በሰውልጆች የሰውነት ውቅር ወይም "Human Physiology" እኤአ በ 1992 የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ማግኘት ቻሉ።

ወደሃገራቸው በመመለስም ሥነ ህይወት ትምህርት ክፍል ውስጥ ረዳት ፕሮፌሰር በመሆን ሥራቸውን የቀጠሉት እኚሁ ሴት ተመራማሪ ተባባሪ ፕሮፌሰር ከዚያም በጥር 2001 ዓ.ም የ ሙሉ ፕሮፌሰርነትን ማዕረግን ለመቀዳጀት በቅተዋል። ፕሮፌሰር ያለምፀሃይ የህክምና እና የአመጋገብ ዋጋ ባላቸው እጽዋት፣ በእፅዋት ተዋፅኦዎችና ቫይታሚኖች፣ በሰዎች ህዋስና የሰውነት ውቅር ላይ፣ደህንነቱ የተጠበቀ የተፈጥሮ ሀብት እና ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ ላይ ያተኮሩና በሌሎችም ጉዳዮች ከ 100 በላይ ሳይንሳዊ ጽሑፎችን ያሳተሙ ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው።

ባለፉት አራት አስርት ዓመታት ባስተማሩበት የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲም በርካታ ተመራማሪ ወጣቶችን አፍርተዋል።ከማስተማር እና የምርምር ስራቸው በተጨማሪ በ ዩንቨርሲቲው የሥነ-ህይወትና የበሽዎች ምርምር ትምህርት ክፍልና የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የስርዓተ ፆታ ሀላፊ፣ እንዲሁም አክሊሉ ለማ ፓቶባዮሎጂ ተቋም ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል ። የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የስርዓተ ፆታ ሀላፊ በነበሩበት ግዜ "የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ለሴቶች ከባድ ነው" የሚለውን ትክክል ያልሆነ አባባል ሰብረው ወደ ተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ክፍል የሚመጡ ሴት ተማሪዎች ቁጥር እንዲጨምር ጉልህ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ፕሮፌሰሯ በመስኩ እያበረከቱ ላሉት አስተዋጽኦም ከተለያዩ ተቋማት በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከነዚህም ውስጥ የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ዓለም አቀፍ የወርቅ ሜዳሊያና የሰርተፊኬት ሽልማት፣ከዓለም አቀፍ የገጠር መልሶ ግንባታ ተቋም የላቀ ስኬት ሽልማትና የጀርመኑ አሌክሳንደር ፎን ሁምቦልት ፋውንዴሽን ሽልማት፣ የ2007 ዓ.ም ምርጥ ሴት ሳይንቲስት የአፍሪካ ህብረት የክዋሜ ንክሩማህ ሳይንሳዊ ሽልማት አሸናፊ ጥቂቶቹ ናቸው። ከ እአአ 1999 ጀምሮ የኒው ዮርክና የሳይንስ አካዳሚና የጀርመን የሃይድልበርግ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ አካዳሚ አባል ሲሆኑ፣ ከ እአአ 2005 እስከ 2007 በአፍሪካ ከሰሃራ በታች ላሉ የቀጠናው ሀገሮች የዓለም አቀፍ የግብርና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ዋና ጸሐፊና አስተባባሪ ሆነው ሰርተዋል።የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ መስራችና የቦርድ አባልም ናቸው።

ደከመኝና ሰለቸኝ የማያውቁት እኚሁ ተመራማሪ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ወደ ውስጥ ማየት ፣ ነገሮችን በበጎ መንፈስ መመልከት እንዳለባቸው እና ተስፋ መቁረጥ እንደሌለባቸው ይመክራሉ። በአሁኑ ጊዜ በ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው የሥነ ህይወት ተመራማሪ የሆኑት የቀለም እናት የዓለምፀሐይ መኮንን ለብዙ ወጣት ተማሪዎች እና ተመራማሪዎች አርዓያ መሆን ችለዋል።

## ዶክተር ተዋበች ቢሻው



ዶክተር ተዋበች በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የጤና መኮንን ናቸው። ዶ/ር ተዋበች ቢሻው ወልደማሪያም ግንቦት 4 ቀን 1938 ዓ.ም ሰኮሩ ከተማ ጅማ አውራጃ ከፋ ክፍለ ሀገር ተወለዱ። አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ የልጃገረዶች ት/ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሚያዚያ ሃያ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተምረዋል። በቀጣይ በአዲስ አበባ በመምህርነት በሰርተፊኬት ከመምህራን ተቋም ተመርቀው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጤና አጠባበቅ የባችለር ኦፍ ሳይንስ ዲግሪ አግኝተዋል። በቀጣይም በጤና አጠባበቅ ትምህርት ከፍተኛ ዲፕሎማና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከሎማ ሊንዳ ዩንቨርስቲ ካሊፎርንያ አሜሪካ ተከታትለዋል።

ዶ/ር ተዋበች ቢሻው በጤናው ዘርፍ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በተለያዩ ደረጃዎቸ በጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አመራር ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅዎ ያደረጉ ሲሆን በተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት ውስጥ የኢትዮጵያን ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የህንድ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በማገዝ የጤና አገልግሎቱ የተሳለጠ እንዲሆን ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል። በተለይም የእናቶችን ሞት ለመቀነስ በተደረጉ ስልቶችን እንዲተገበር በማድረግ አስተዋፅዎ አድርገዋል።በሌላ መልኩ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበረሰብ ያለውን እውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለአገሪቱ እድገት ሽግግር ለማሳለጥ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም በመመስረት በስራ አስኪያጅነት የመሩ ሲሆን የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበርን ከመሰረቱት አንዷ ሴት በመሆን ለሶስት ጊዜ በፕሬዚዳንትነት አገልግለዋል፡ በዚህም በየሦስት ዓመቱ በሕዝብ ጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ላይ የሚመክረው የዓለም ጤና አጠባበቅ ማኅበራት ፌዴሬሽን 13ኛውን ጉባዔውን አዲስ አበባ እንዲያካሂድ አድርገዋል።

በሙያቸው ለህዝብ እና ለሀገር ባበረከቱት አስተዋፅኦ ልዩ ልዩ ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከራሳቸው ትጋት በመነሳት “ለሴቶች ቦታ መስጠት አለብን ስንል ልመና አይደለም ፤ መብት ነው!” ይላሉ ዶ/ር ተዋበች ቢሻው። እርሳቸው ተማሪ በነበሩበት ግዜ የጤና መኮንንነት ትምህርት ለሴቶች የማይፈቀድ በመሆኑ በብዙ ፈተና ውስጥ አልፈው ሴቶች ከማንም የማያንሱ መ ናቸውን በትምህርት ውጤታቸውም ሆነ በሥራ ህይወታቸው ያስመሰከሩ ሰው ናቸው።

ዶ/ር ተዋበች በጤናው ዘርፍና በሌሎች መስኮች ላበረከቱት አስተዋፅዎ በአገር አቀፍና በአለም አቀፍ በርካታ የእውቅና ሽልማቶች ያገኙ ተምሳሌት መሪና የመብት ተቆርቋሪ ናቸው። እናት ባንክም ጎፋ ገብረኤል አካባቢ የከፈተውን ቅርንጫፍ ለበርካታ ሴቶች አርዓያ በሆኑት ታላቅ ኢትዮጲያዊት ዶ/ር ተዋበች ቢሻው ስም ሰይሞላቸዋል። የ 78 አመቷ ዶክተር ተዋበች በኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ በተለይ በህፃናትና በእናቶች ጤና አጠባበቅ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ትልቅ አስተዋፆ ያደረጉ የህክምና ባለሙያ እና የብዙዎች አብነት ናቸው።

## ትምኒት ገብሩ (ፒ.ኤች.ዲ)




ዶ/ር ትምኒት ገብሩ ዓለምን በፍጥነት እየለወጠ ያለው ሰው ሠራሽ ልህቀት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ወይም ኤአይ) ውስጥ አሉ ከሚባሉ ጥቁር ሴት ባለሙያዎች መካከል አንዷ ነች። ዶ/ር ትምኒት በ1975 ዓ.ም በአዲስ አበባ የ ተወለደች ሲሆን የናዝሬት ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረች። አስረኛ ክፍል ስትደርስ ወደ አየርላንድ አቀናች። የሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የዩኒቨርስቲ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው አሜሪካ ነው። ትምኒት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪዋን በኤሌክትሪክ ምህንድስና ከስታንፎድ ዩኒቨርሲቲ አገግኝታለች። ዶ/ር ትምኒት እ.ኤ.አ በ2017 የዶክትሬት ዲግሪዋን ከስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ አግኝታለች።

መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከህብረተሰቡ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያፈሱት ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ትኩረቷን ይስባታል። ዶ/ር ትምኒት ገብሩ በ Google AI (የጉግል ሰው ሠራሽ አስተውሎት) የምርምር ማዕከል ውስጥ ከፍተኛ ተመራማሪ ነበረች። በቆይታዋም የሰው ሠራሽ አስተውሎት ሥነ ምግባር ላይ ምርምር በሚያደርገው ቡድን ውስጥ የቡድን መሪ ነበረች። ከዚህ በተጨማሪ Black in AI የተባለው ጥቁሮች በሰው ሠራሽ አስተውሎት ምርምር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለመጨመር የሚሠራ ድርጅት ተባባሪ መሥራች ነች። የዶ/ር ትምኒት ገብሩ ምርምር የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ሊኖረው ስለሚገባ ሥነ ምግባር እና አድልዎና መገለል በሚደርስባቸው ማኅበረሰቦች ላይ ሊያደርስ ስለሚችለው ጉዳት ላይ በዋንኛነት ያተኩራል።

የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ በተለይም ሥር የሰደደውን መድልዎና መገለል ከግምት በማስገባት ሊያደርስ ስለሚችለው ጉዳት በቂ ትኩረት እንዲያገኝ ከማድረግ ረገድ የዶ/ር ትምኒት ሥራ ቁልፍ ሚና አለው። የምርምር ሥራዋ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ሥርዓቶች ዝግጅት ላይ ይበልጥ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የመኖሩን አስፈላጊነት አፅዕኖት ሰጥቶ ይሞግታል። ከዚህ በተጨማሪ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ኃላፊነት በተሞላ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል እና ሁሉንም የሰው ልጅ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ለማረጋገጥ ሥነ ምግባራዊ ማሕቀፍ መዘጋጀት እንዳለበት በምርምር ሥራዎቿ አመላክታለች።

ዶ/ር ትምኒት ገብሩ በቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ድምጿን ያሰማች የብዝኃነትና የአሳታፊነት መብት ተከራካሪ ነች። በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ላይ የሚታየውን የብዝኃነት አለመኖር ተቃውማለች። ከዚህ በተጨማሪ ሴቶችና ነጭ ያልሆኑ ሰዎች በአመራር ቦታ ላይ መታየት እንዳለባቸው ሽንጧን ገትራ ስትከራከር ቆይታለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለወጣቶችን የኮዲንግ ሥልጠና የተሰጠበት 'አዲስ ኮደር' የተሰኘ ፕሮጀክት ነበራት። ከዚህ በፊትም በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ በተካሄደ የአይሲቲ ኮንፈረንስም ተሳትፋለች። ከኢትዮጵያ የወጡ የሰው ሠራሽ ልህቀት ባለሙያዎችን በብላክ ኢን ኤአይ አካትታለች።

ዶ/ር ትምኒት ገብሩ Computing Machinery's Grace Hopper Award እና Anita Borg Institute's Social Impact Award የተባሉትን ሽልማቶች ጨምሮ በርካታ ሽልማቶችን አግኝታለች። ከዚህ በተጨማሪ Fast Company በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴት ሲላት MIT Technology Review ደግሞ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሆኑት ሰዎች መካከል አንዷ ናት በማለት ዕውቅና ሰጥተዋታል። እአአ በ 2022 ታይም የዓመቱ 100 ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ዝርዝር ውስጥ አካቷታል። የዶ/ር ትምኒት ገብሩ ሥራዎች በሰው ሠራሽ ቴክኖሎጂ ውስጥ ሴቶችና ጥቁሮች ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ፍትሐዊና ርትዓዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

## ረድኤት አበበ (ፒ.ኤች.ዲ)



ዶ/ር ረድኤት ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ነው። እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በሃገሪቱ የትምህርት ስርዓት ውስጥ አድጋ የተማረችው ረድኤት፣ አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ትምህርት ቤት (ICS) በየዓመቱ ለአራት ተማሪዎች የሚሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ ስኮላርሺፕ በማሸነፍ ትምህርቷን በዛ ተከታትላለች። በICS የ2ተኛ ደረጃ ትምህርቷ በግሩም ውጤት በማጠናቀቋ ነበር በሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ደረጃ የነጻ ትምህርት ለመከታተል ወደ አሜሪካ ያቀናችው። ለከፍትኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ አቅንታ ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በሂሳብ ዲግሪዋን ይዛለች። ትምህርቷን እዛው ሃርቫርድ ቀጥላ በተግባራዊ ሂሳብ ሁለተኛ ዲግሪዋን ይዛለች።

ቀጥላም ሁለተኛ የማስተርስ ዲግሪዋን ከካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ባገኘችው ነጻ የትምህርት እድል በሙሉ ሂሳብ ዘርፍ ይዛለች። በመቀጠልም የዶክትሬት ድግሪዋን በኮምፒዩተር ሳይንስ ከኮርኔል ዩኒቨርሲቲ ይዛለች። ረደኤት ከ ኮርኔል የኒቨርሲቲ በኮምፒዩተር ሳይንስ ዶክትሬት በመያዝ የመጀመሪያዋ ጥቁር ሴት ነች።

የረድኤት የምርምር ትኩረቶች ኮምፒውተር ሳይንስ እና ሰው ሰራሽ ክህሎት እንዲሁም ይሄው መስክ በማህበረስብ ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ ማጥናት ላይ ነው። በተለይም በ ሰው ሰራሽ የልህቀትና ስልተ ቀመሮች ጋር ተያይዞው የሚምጡ ከአድሎና እኩልነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት አዳዲስ ስልቶችን መቀመር ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። ከዚህም ጋር በተያያዝ 2 ድርጅቶችን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ለቃውንት ማለትም ከ ዶ/ር ትምኒት እና አበባ ጋር መስርተዋል። ተቋሞቹ ጥቁር ሴቶች በዘርፉ እንዲተሳሰሩ እና እንዲተባበሩ መንገድ ከመከፈታቸውም ባሻገር በአፍሪካውያን ባለሙያዎች የሚሠሩ ምርምሮችን ተደራሽ ለማድረግ ይጥራሉ።

ዶ/ር ረድኤት በ2011 ዓ.ም በሃርቫርድ ዩኒቨርሲት ጀማሪ ተመራማሪ ተብላ ተመርጣለች። ከ 2012 ዓ.ም ደግሞ በበርክልይ ዩኑቨርሲቲ ኦፍ ካሊፎሪኒያ በረዳት ፕሮፌሰርነት በዩኒቨርሲቲው የኤሌክትሪክ ምህንድስና እና ኮምፒዩተር ሳይንስ ትምህርት ክፍል የመጀምሪያዋ ጥቁር ሴት ፕሮፌሰር ሆናለች። ምንም እንኳን የ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዘርፍ ለጥቁሮች ያውም ለሴቶች ፈታኝ ቢሆንም፣ ፈተናውን ሁሉ ተቋቁማ ዓለም አሉኝ ከምትላቸው ባለሙያዎች አንዷ ለመሆን የነቃቸው ዶ/ር ረድኤት ለብዙወች የመነቃቃት እና ምንጭ ነች።



# ሴቶች በሥራ ፈጠራ እና ንግድ

## ጽዮን ሚካኤል አንደም (1915 - 2015 ዓ.ም)



ታሪካቸው ካልተነገረላቸውና እምብዛም በሕዝብ ዘንድ ከማይታወቁት የታላላቅ ስራዎች ባለቤት ከሆኑ ሴቶች መካከል አንዷ የሆኑት የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ባሕላዊ አልባሳት ፋሽን ዲዛይነር፣እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም አንዷ ናቸው።እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም፤ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ባሕላዊ አልባሳት ፋሽን ዲዛይነር፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል፣ የሴቶች ማኅበር፣ ማየት የተሳናቸውና ቼሻየር ሆም ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች መስራችና የቀድሞው የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ ሊቀመንበር ጄኔራል አማን አንዶም ታላቅ እህት ናቸው።

የእናታቸው የልብስ ስፌት ሙያ ነበር ገና በ12 ዓመት እድሜያቸው ከስፌት ጋር ያስተዋወቃቸው። የልብስ ስፌት ሙያ ተሰጥጾአቸውን ያዩት አባታቸው ስጦታ ብለው የስፌት መኪና ገዝተው ሰጧቸው። በዚያም ለአሻንጉሊቶቻቸው ልብስ እየሰፉ ቀስ በቀስም የራሳቸውን ልብስ ሰፍተው እስከመልበስ የሚያደርስ ባለሙያ ሆኑ። እማማ ጽዮን በራሳቸው ይህንን ያህል ርቀት ይሂዱ እንጂ ኋላ ላይ አባታቸው አስተማሪ ቀጥረውላቸውም ልብስ ስፌት እንዲማሩ አድርገዋቸዋል።

በወቅቱ ፋሽን የሚባል ነገር ባይኖርም የአገራቸውን ጥበብ ሲያዩትም ሲለብሱትም እጅግ ያስውባቸው ስለነበር ለምን በተለያየ ፎርም አልሰራውም ብለው ተነሱ፤ በዚህም አንድ የአገር ባህል ልብስ ይሰሩና ደረቱና እጅጌው ላይ ጥበብ እያስገቡ ሌላ ገጽታን ይፈጥሩለት ያዙ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ ተወደደላቸው። በ5 ሳንቲሜትር የተለመደውን የጥበብ አሰራር እሳቸው ወደ 50 ከዚያም ቀስ ብለው እስከ ሶስት ሜትር ርዝመት ያለው ጥበብ በመስራት የመጀመሪያዋ ዲዛይነር ሆኑ።

በወቅቱ ሴቶች በጣም ተማሩ ከተባለ 8ተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበር፤ እሳቸው ግን አጋጣሚው ተመቻችቶላቸው በእንግሊዝ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍል የመድረስን እድል አግኝተዋል።

ይህ ሁኔታ ታክሎበት በራሳቸው የሚተማመኑ፤ ለሚሰሩት ስራ ሙሉ ኃላፊነትን የሚወስዱ ልበ ሙሉ ሴት አድርጓቸዋል። በወቅቱ ልብስ ሰፍቶ ለሌሎች ሰዎች መሸጥ በጣም ነውር የነበረ በመሆኑ እማማ ጽዮን የሰሯቸውን ልብሶች ራሳቸው ነበር የሚለብሷቸው። አልፎ አልፎ የ ንጉሳውያኑ ቤተሰቦች ቢያሰሯቸውም ገንዘብ መቀበል እንደነውር ስለሚታይ በነጻ ነበር የሚሰጧቸው።

እማማ ጽዮን ወርቃማ እጆች ያዩ ሰወች ቀስ በቀስ ፍላጎታቸው በጣም እያደገና ቤት ውስጥ መስራት የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሲደርሱ ሱቅ ከፍተው መስራት ጀመሩ። በወቅቱ ሴት ልጅ ከቤቷ ወጥታ አደባባይ ሱቅ መቆም በራሱ አስቸጋሪ የነበረ በመሆኑ ብዙ ተቸግረው ነበር። ነገር ግን የደንበኞቻቸው ማበረታታት ስራቸውን እንዲገፉበት አደረጋቸው። እማማ ጽዮን ባለቤታቸው ዲፕሎማት ስለነበሩ ለውጪው ዓለም ቅርብ ነበሩ። አጋጣሚውንም በመጠቀም ፈረንጆች ባህላዊ ልብሳችንን እንዲያውቁ የላቀ ጥረት አድርገዋል። በዚህም ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳውቀዋታል።

እማማ ጽዮን ከፋሽን ዲዛይነርነታቸው ባሻገር በ ሰብዓዊ እንቅስቃሴዎቻቸው እና በሴቶች መብት ተሟጋችነታቸው ይታወቁ ነበር። በተለይ በ ደርግ መንግስት ታስረው ለ 7 አመት እስር ቤት በ ቆዩበት ግዜ በርካታ ሰብዓዊ ተግባራትን ፈጽመዋል።

መጀመሪያ እስር ቤት ሲገቡ ቢደናገጡም እስር ቤት የተወለዱ ልጆችን በማስተማር፣ ልብሳቸውን በመስፋት በ ቅዱስ ተግባር አሳልፈዋል። መጀመሪያ አካባቢ በራሳቸው ወጭ ነበር ልብስ የሚሰፉት ነገር ግን ይህንን የሰሙ ውጭ አገር የሚኖሩ ልበ ቀናዎች ጨርቅ እና ሌሎች ግብአቶችን ይልኩላቸው ጀመር። በዚህም ለ 20 ልጆች ልብስ ከማቅረብ በተጨማሪ እናቶቻቸውንም ልብስ ስፌት እንዲያስተምሩ አስችሏቸዋል። እማማ ጽዮን በእሌኒ ባርተን አማካይነት ወደ ቀይ መስቀል ስራም ገብተዋል። የመጀመሪያውን የበጎ አድርጎት ድርጅትም በማቋቋም ለብዙዎች ተምሳሌት የሆኑም ሴት ነበሩ።

## እሌኒ ዘውዴ ገብረ መድኅን (ፒ.ኤች.ዲ)



የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወደ ሥራ እንዲገባ በማድረግ ይታወቃሉ፣ አዳዲስ የኢኮኖሚ ፈጠራ ሐሳቦች አፍላቂ ናቸው ታዋቂዋ ኢኮኖሚስት ዶ/ር እሌኒ ዘውዴ ። አባታቸው ዘውዴ ገብረመድኅን ኢትዮጵያን ወክለው በኒውዮርክ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ ቤት በመመደባቸው ገና በ 4 ዓመታቸው ነበር ከተወለዱበት ከአዲስ አበባ ወጥተው ወደ አሜሪካ የሄዱት። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሲመጡ፣ በወቅቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት ስለነበር መላው ቤተሰቡ ወደ ሩዋንዳ በማስከተልም ወደ ቶጐ እና ማላዊ በመጨረሻም ወደ ኬኒያ ሄዱ። ዶ/ር እሌኒ የልጅነት ጊዜያቸውን በ6 ሀገራት መካከል አሳልፋፈዋል፣ በነዚህ ሀገሮች ትምህርታቸውን በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ እና በ ስዋሒሊ ተምረዋል።

ዶ/ር እሌኒ አሜሪካን ሀገር በሚገኘው ኮርኔል ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከሚችንጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ፣ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ ከስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። በ ኢትዮጵያ የሚከሰትው ተደጋጋሚ ረሀብ እረፍት የሚነሳቸው እሌኒ ስለግብርና፣ ስለምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ረሃብንም ስለ ማጥፋ፣ ምርትን ስለ ማሽጋገርና መነገድ ብዙ ተመራምረዋል ሰርተዋልም።

ዶ/ር እሌኒ በዓለም ባንክ ውስጥ ዋና ኢኮኖሚስት በመሆን ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም በኢኮኖሚስትነትና የምርት ልውውጥ ኤክስፐርት በመሆን ሠርተዋል። ከዛም በማስከተል በዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲዎች ምርምር ተቋም (IFPR) ለረዥም ጊዜ አገልግለዋል።

በአለማቀፉ የምግብ ፖሊሲ ጥናት በነበራቸው ቆይታ የሰሩት አመርቂ ስራ በአፍሪካ አገሮች የሰብል ምርቶች ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን በተለይም ብድር የማግኘት ችግር፣ ስለ ገበያው በቂ እውቀት አለመኖር፣ የመጓጓዣ እጥረት እንዲሁም የውሎች ተፈጻሚ አለመሆንን ነቅሶ ምላሽ ለመስጠት የሞከረ ነበር።

በ 1996 ዓ.ም ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በአለማቀፉ የምግብ ፖሊሲ ጥናት ማዕከል የተዘጋጀውን የኢትዮጵያን የግብርና ፖሊሲ እንዲሁም ገበያን ለማሻሻል መሰረት ያደረገ ፕሮግራምን ለመምራት ሲመጡ ። ከስራ ድርሻቸው መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ለመመስረት የሚጠቅማቸውን አማካሪ ቡድን ማዋቀር ነበር ። እቅዳቸውም ተሳክቶ በ 2000 ዓ.ም የምርት ገበያው ዋና ስራ አስኪያጅ መሆን ችለዋል።

ገበያ መኖር የአንድን ነጋዴ ምርታማነት ያሳድገዋል የሚሉት ዶ/ር እሌኒ የፈለገው ምርታማነትን የሚያሳድጉ ኢንቨስትመንቶች ቢደረጉ ለወጣው ወጭ የሚከስ ትርፍና ትርፉንም የሚፈጥር ገበያ እስከሌለ ድረስ የትም መድረስ አይቻልም ይላሉ። ዶ/ር እሌኒ Transforming the Ethiopian Economy by Becoming a Global Commodity Market of Choice የሚለውን ትልቅ ራዕይ በመሠነቅ ነበር ኢሲኤክስ (ECX) በመባል የሚጠራውን የግብይት ስርዓት የገነቡት። እንደ ዶክተር እሌኒ ገለፃም ኢሲኤክስ አራት ዋና ዋና ሚናዎችን መጫወት እንዲችል ተደርጎ ነው የተገነባው። የመጀመሪያው ነገር ምርት ገበያው የሚሸጡ ምርቶችን የጥራትና ብዛት ደረጃ ይወስናል፤ማረጋገጫ ይሠጣል። በአምራቹ ስምም በመጋዘኑ እንዲቀመጥ ያደርጋል። ይህ በተለይ የምርቱን ገዥዎችና ላኪዎች የጥራት ችግር ይፈታላቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ ለአምራች ገበሬዎች ከገዥዎች በፍጥነት (በ24 ሰዓት ውስጥ) ክፍያቸው እጃቸው ላይ እንዲደርስ የሚያስችል የገንዘብ ማስተላለፍ ሂደትን ይሠራል። ይህ መሆኑ ደግሞ ካሁን ቀደም አምራቾችና ሌሎች ሻጭ ነጋዴዎች ምርታቸውን ሸጠው ክፍያቸው ግን በፈለጉት ጊዜ ውስጥ አይከናወንም ነበር። በሶስተኛ ደረጃ ገዥና ሻጭ ፊት ለፊት ተገናኝቶና ተደራድሮ የሚገበያይበትን መድረክ ይፈጥራል። በፊት ሻጭና ገዥ ፊት ለፊት የማይገናኙበት እንደውም በመሃከል የተለያዩ ደላሎች የነበሩበት ነበር። ምርት ገበያ ይህን ነባር ቢሮክራሲያዊ አሠራር ይፈታል።

በመጨረሻ ለአምራቾችና ሻጮች በወቅቱ የምርት ዋጋ ምን ያህል እንደሆነወቅታዊ መረጃዎች በየክልሉና መንደሩ በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች እንዲሠራጩ በማድረግ ሻጮች በመረጃ ላይ የተንተራሠ ውሳኔ እንዲተገብሩ ያስችላል። የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በፈር ቀዳጅነት የሚጠቀስ ተቋም ነው። የአገሪቱን ዋና ዋና የወጪ ንግድ ምርቶች የሆኑትን ቡና፣ ሰሊጥና የመሳሰሉ ምርቶችን በማዕከል በማገበያየት ይታወቃል በ አመትም በብዙ ቢሊዮን ዶላሮች የሚገመቱ ምርቶችን እያገበያየ ይገኛል።

ዶ/ር እሌኒ የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ከለቀቁ  በኋላ ሰማያዊ ጨረቃ(Blue moon) የተባለውን በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን በ ፈጠራ፣ ግብርና እና ንግድ ላይ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች የሚያስተምር እንዲሁም የመነሻ ካፒታል ላይ የሚሰራን ድርጅት ሲመሩ ነበር። በአሁኑ ወቅት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም የድርጅቱ የአፍሪካ ዋና የፈጠራ ኦፊሰር በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

ዶ/ር እሌኒ የግብርና፣  የልማት እና የ ስራ ፈጠራ ላይ ላደረጉት አስተዋጽኦ የተለያዩ እውቅናዎችን አገኝተዋል ።  በ2002 ዓ.ም  የአመቱ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ተብለው ተሸልመዋል፣ በ2004 ዓ.ም ያራ ኢንተርናሽናል ዘላቂነት ላለው የምግብ ምርት እና ፍትሃዊ ክፍፍል የያራ ሎሬት ሽልማትን ተሸልመዋል። የአፍሪካ የባንክ ስራ ቁንጮ የተባሉ ሲሆን በካምፕ ዴቪድ በተካሄደው  የቡድን 8 የአለም መሪዎች ስብሰባ ላይ ንግግር አድርገዋል። በተጨማሪም በኒው አፍሪካን መጋዚን፣ ተጽኖ ፈጣሪ 100 አፍሪካዊያን እንዲሁም አፍሪካን የሚቀርጹ 50 ሴቶች ውስጥ ተካትተዋል።

በወንዶች የበላይነት በተያዘው ምጣኔ ሃብት እና የምጣኔ ሃብት ትምህርት ውስጥ ስኬታማ የሚባል ሕይወት ካላቸው አፍሪካዊ እንስቶች መካከል ግንባር ቀደሟ በመሆን የብዙዎች አርአያ ሁነዋል።

## ሚሚ አለማየሁ



ሚሚ አለማየሁ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት እና የገበያ ባለሞያ እና የልማት አስፈጻሚ ናቸው ። ወደ አሜሪካ የተሰደዱት በልጅነታቸው ሲሆን በ ዜግነት አሜሪካዊ ናቸው። አንዱ የ ሂወት መርኅቸው ያለመታከት መማር የሆነው ሚሚ ምዕራብ ቴክሳስ ከሚገኘው የኤኤንድኤም ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የያዙ ሲሆን ተፍትስ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኘው ፍሌቸር ስኩል ኦፍ ሎው ኤንድ ዲፕሎማሲ ደግሞ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በአለም አቀፍ ንግድ እና አለም አቀፍ ህግ አግኝተዋል።

“ወቅቱ የአፍሪካ ነው!” የሚሉት ሚሚ ለረጅም አመታት በአፍሪካ እድገት ላይ በተለይም ከአፍሪካ የንግድ ድርጅቶች እና ኩባንያዎች ጋር በቅርበት በመስራት ይታወቃሉ። ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ ሚሚ አለማየሁ ከአሜሪካ መንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት አንዷ ነበሩ። እአአ በ2010 ዓ.ም ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በእጩነት አቅርበዋቸው በሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ የሙሉ ድምፅ ድጋፍ በባሕርማዶ የግል ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን (OPIC) ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ተሾሙ።

በተጨማሪም ሚሚ በሪፐብሊካኑ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ ተሾመው የአፍሪካ ልማት ባንክ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ተወላጅ አሜሪካዊት ዋና ዳይሬክተር ሆነው ሠርተዋል። ሚሚ  ለአሜሪካ በአፍሪካ ከፍተኛ የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን ከአፍሪካ ልማት ባንክ በፊት Trade links የሚባለውን የንግድ አማካሪ ድርጅት መሥራች ሆነው አዳዲስ ገበያዎችን ለሚፈጥሩ ደንበኞች በማማከር እና  አፍሪካ ውስጥ ንግድን በማስፋፋት ሲሠሩ ቆይተዋል። ሚሚ በልማት፣ ኃይል አቅርቦት እና በአፍሪካ ዙሪያ ባሉ የመሰረተ ልማት ንብረቶች ላይ በሚያተኩረው ብላክ ራይኖ ግሩፕ ተብሎ የሚጠራው የኢንቨስትመንት መድረክ ውስጥ የሥራ አመራር ዳይሬክተርና የቦርድ ዳይሬክተርም አባልም ነበሩ።

ሚሚ በ አሁኑ ወቅት የማስተርካርድ የህዝብ እና የግል ሰብአዊ እና የልማት የአጋርነት ቡድን ከፍተኛ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። በዚህም ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር የማስተካርድን ማህበራዊ ተጽዕኖ አጋርነት እና የገንዘብ ስምምነቶችን ያስተዳድራሉ። እኤአ በ 2021 ደግሞ የትዊተር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ተመርጠዋል።

## ፍሬዓለም ሽባባው



ፍሬዓለም ሽባባው የተወለዱት አዲስ አበባ ሲሆን ያደጉት ደግሞ ቻግኒ ነው። ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በባህርዳር ከተማ አጠናቅቀው ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ አቅንተው ከካሊፎርኒያ ሜሪት ኮሌጅ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ እንዲሁም ከደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ በሂውማንና ሶሻል ስተዲስ የመጀመሪያ ዲግሪና በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በዴቨሎፕመንት ስተዲስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሠርተዋል። ፍሬዓለም ሽባባው የኢትዮጵያ ስኩል ሚል ኢኒሼቲቭ መሥራች ባለቤትና ዋና ዳይሬክተር እና የሦስት ልጆች እናት ናቸው ፍሬዓለም በሪል ስቴት ልማት ለመሰማራት ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ   በኋላ ወደ ሌላ ዓይነት ልማት አተኩረዋል።

የመጀመሪያ ልጃቸው ሶስት አመት ሲሞላው ፍሬአለም ለሱ የሚሆን ትክክለኛ ትምህርት ቤት ለማግኘት ቢሞክሩም ከደህንነት እና ጥራት አንፃር የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት ማግኘት አልቻሉም። ከዚህ ፈተና ጋር የተጋፈጡት ፍሬአለም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው ፈተናውን ወደ መልካም እድል ቀይረዋል።

ምንም እንኳ ፍሬዓለም የግል ትምህርት ቤት የመጀመርን ሀሳብን በአእምሯቸው እና በልባቸው ቢወጥኑም የመነሻ ካፒታል እንዴት እንደሚያገኙ እርግጠኛ አልነበሩም ። ከዚያ አንድ ያልተለመደ እና ፍሬ ‘መለኮታዊ ጣልቃገብነት’ ሲሉ የሰየሙት አንድ ነገር ተከሰተ። መንግሥት ትምህርት ላይ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ነፃ የ መሬት እና መሰል ድጋፎችን እንደሚያደርግ አስታወቀ። ይህም የፍሬአለምን እቅድ እዉን ሆኖ የባህር ዳር አካዳሚን በ2001 ዓ.ም. በ50 ተማሪዎች ተወለደ። ትምህርት ቤቱ አሁን ባለበት ደረጃ 2700 ተማሪዎችን ያስተናግዳል እና 230 የሙሉ ጊዜ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን 65 በመቶው ሴቶች ናቸው።

ፍሬዓለም ሽባባው በባህር ዳር ከተማ የግል ትምህርት ቤት እየመሩ ባለበት ወቅት አንድ የአምስት ዓመት ሕፃን ወደ እርሳቸው ቀርቦ ምንም አቅም ባይኖረውም በትምህርት ቤቱ እንዲመዘግቡት ጠየቃቸው። ተማሪው ተመዝግቦ እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ ጥሩ የትምህርት እንቅስቃሴ ቢያሳይም ባዶ የምሳ ዕቃ ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት የዘወትር ተግባሩ ነበር።

ፍሬዓለም ይህንን እውነታ ሲያውቁ የተሰማቸው ስሜት ከባድ እንደነበረ ያስታውሳሉ። ይህ ጉዳይ በአፋጣኝ መፍትሄ እንዲፈልጉ አነሳሳቸው። ክስተቱ ስለ አጠቃላይ የአመጋገብ ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የተንሰራፋ የተማሪዎች የተመጣጠነ የምግብ እጦት እና በትምህርት ውጤታቸው ላይ እያሳደረ ያለውን ተፅዕኖም ጭምር እንዲመራመሩ አደረጋቸው።

ፍሬዓለም ከዚህ መሰረታዊ ጥናት በኋላ በባህር ዳር እና በሰበታ የሚገኙ ተማሪዎችን ለመመገብ የሚያስችል ፕሮጀክት ነድፈው አሳኩ። በኢትዮጵያም የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ እንቅስቃሴን ጀመሩ። የተማሪዎች ምገባ የ አንድ ወቅት የ ዘመቻ እንቅስቃሴ ሆኖ እንዳይቀር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ዘላቂ ምገባ እንዲኖር የ ሀብት ማሰባሰብን አስተባብረዋል።

ፍሬዓለም የተማሪዎች ምገባ፣ የልጆች የአመጋገብ/«ኒውትሪሽን» እጥረትን ማስወገድ፣ የመንግስትን ትኩረት እንዲያገኝ የ ውትወታ፣ የ ማንቃት እና ሰርቶ የማሳየት ወደር የለሽ ተግባር ፈጽመዋል። የ ፍሬዓለም አዕምሮ የመፍትሔ ሀሳቦችን ለማመንጨት የማይቦዝን ነው። በትምህርት ዘርፍ ፕሮጀክት ነድፈው የተማሪዎች ምገባን በይፋ ጀመሩ፤ መንግሥትም፣ ሀሳባቸውን ተቀበለ፤ ነገር ግን ልጆች ተጸንሰው፣ ከዚያ ተወልደው ሁለት ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚገጥማቸው የ ምግብ ችግር አስቀድሞ መቀረፍ እንዳለበት ያምናሉ። ሀሳባቸውንም ለመንግሥት አቅርበው፤ "ሰቆጣ ዲክላሬሽን" ብለው በመሰየም ከመንግሥት ዕውቅናን አግኝተው 52% የነበረውን የአዕምሮ መቀንጨር በ2030 ዓ.ም. ወደ ዜሮ ለማምጣት ዘመቻውን ይጀምራሉ። ተሳካላቸውም፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዚህ አኩሪ ሥራቸው ዕውቅናን የሰጣቸው ሲሆን፤ አራት የአፍሪካ ሀገራትም ይኼንን ልምድ በመቅሰም ተግባራዊ አድርገውታል።

ፍሬዓለም ለትምህርት እና የተማሪዎች ምገባ ካበረከቱት አስተዋስጽኦ በተጨማሪ የሴት የስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ "የአማራ ክልል የሴቶች ስራ ፈጣሪዎች ማህበር ማህበር"ን አቋቁመዋል።

የመጀመሪያዋም ዋና ስራ አስፈጻሚ ነበሩ። በመንግስታዊ አገልግሎት ደግሞ የሰላም ሚንስትር ሚንስቴር ድኤታ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን በ አሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ናቸው።

ፍሬዓለም ሽባባው ለመፍትሔ የተጠራች ነፍስ ያላቸው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከድህነት እና ከተመጣጠነ ምግብ እጦት ጋር እያደረገች ያለውን የማያቋርጥ ትግል በ ግንባር ቀደምትነት ከሚመሩት ውስጥ የሚመደቡ አርአያ ሰብ ናቸው።

# ቤቴልሄም ጥላሁን



“የአፍሪካ ስቲቭ ጆብስ” በመባል የምትታወቀው ቤቴልሄም ከትንሽ ተነስቶ በአፍሪካ ውስጥ ፈጣን እድገት ካላቸው የጫማ አምራች ኩባንያ መካከል አንዱ የሆነውን ሶል ሬብልስ መስራች ናት ። ለበርካቶች ስራ በመፍጠር ማህበርሰቧን በመርዳቷ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ባህል በአለም መድረክ በማስተዋወቅም ጉልህ አስትዋጽኦ አበርክታለች።

በ1997 ዓ.ም ቤቴልሄም ከፍተኛ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀችበአካውንቲንግ ተቀጥራ የመስራት እድል ብታገኝም ቋሚ ሰራተኛ አይደለሽም ተብላ ከስራ መቀነሷ የ ራሷን ስራ እንድታውጠነጥን አደረጋት። ምንም እንኳ ብዙ የ ስራ ሀሳቦች በውስጧ ቢኖሩም ስራዎቹን እውን የምታረግበት የ መነሻ ገንዘብ አልነበራትም። ከብዙ ማሰብ በኋላም ብዙ መነሻ ገንዘብ የማይጠይቅ ጫማ የመስራት ሃሳብ ይመጣላታል። በግዜው በተለምዶ ጋዴ ወይም በረባሶ የሚባል አገልግሎት ከጨረሱ የመኪና ጎማዎች የሚሰራ ጫማ ብዙ ሰው እንደሚጠቀመው እንዲሁም ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይም አስተዋለች። በባህላዊ መንገድ ጥቅም ላይ ይውል የነበረውን በረባሶ ጫማ በዘመናዊ መንገድ አምርቶ ለዓለም ገበያ ለማዋል አለመች። ከራሷ ፣ ከቤተሰብ እና ጓደኞቿ ባሰባሰበችው ገንዘብም በአያቷ ቤት ግቢ ውስጥ ስራ ጀመረች።

የመጀመሪያውን ጫማ ጎማ ገዛች ነገር ግን  እንዴት እንኳን እንደሚቆረጥ አታውቅም ነበር። መጀመሪያ የሰራቸው ጫማ ሶስት ሶስት ኪሎ ይመዝኑ ነበረ። ታድያ እንዲህ እንዲህ እያለች ጫማዉን ወደ ማስተካከል የደረሰችው ስራ ፈጣሪ ቀጣዩ ፈተና ጫማዎቹን ወደ አለም አቀፍ ገበያ ለማስገባት መንገዶችን መፈለግ ነበር። በዛን ጊዜ ኢንተርኔት እንደዚህ ሳይስፋፋ ኢንተርኔት ካፌ ብቻ እንደነበረ የምታስታውሰው ቤተልሄም ኢሜይልን ወደ ውጪ ድርጅቶች መድረሻ አማራጭ እንደተጠቀመች ታስታውሳለች።

“Urban Outfitter” እንዲሁም “Amazon” ለሚባሉት ድርጅቶች ኢሜይል ማድረግ ጀመረች። ለመጀመርያ ጊዜ ምላሽ ያገኘችው 2000 ኢሜይሎች ከላከች ቦሀላ ነበር። ከዛ ቡኃላ ደግሞ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ለመቀበል 2 አመት ያክል ጠብቃ ነበር።

ቀስ በቀስም ሶል ሬብልስ  በአለም ገበያ መታወቅ ጀመረ። በተለይ ለአካባቢ ጥበቃ የሚያደርገው አስተዋጽኦና ትርጉም የጫማውን ተቀባይነትን ከፍ አደረገው። “ሶልሬብልስ” በድረ- ገጽ ግብይትን በማከናወን ከአፍሪካ ቀዳሚ የጫማ ማምረቻ ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የአፍሪካው ናይክ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል።  ከዚህ በተጨማሪም በዎርልድ ፌር ትሬድ ፌዴሬሽን የተመዘገበ የመጀመሪያው እና ብቸኛው በአፍሪካ የተመሰረተ ድርጅት ሆነ። በማደግ ላይ ካሉ አገሮችም የወጣ የመጀመሪያው አለማቀፍ የጫማ ኩባንያ ነው ። በአሁን ሰዓት “ሶል ሬብልስ” ወደ 50 የሚሆኑ አገራት ላይ ምርቶቹን ያከፋፍላል።

ቤተልሔም ፣ በ ‘ሶል ሬብልስ’ ጫማ ፋብሪካ ያገኘችውን እውቅና እንዲሁም ልምድ ቀምራ ወደ ቡናው ዘርፍም ጎራ ብላለች። በቡናው ዘርፍ ‘ጋርደን ኦፍ ኮፊ’ የሚባል ኮፊ ሀውስ ገንብታ እየሰራች ትገኛለች። በዚህም የዝግጅት ሂደቱ በባህላዊ መንገድ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ለውጭ ሀገር ገበያ ታቀርባለች። በዚህም የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ በአገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ የራሱን አስተዋጽኦ መጫወት የሚችል ነው። በዚህ ብቻ በቃኝ ያላለችው ሥራ ፈጣሪዋ፣ የኢትዮጵያውያን ብቸኛ ተወዳጅ ምግብ የሆነውን ጤፍ እሴት በመጨመር የጤፍ ችብስ እና የተለያዩ ምርቶችን በማዘጋጀት ለዓለም ገበያ እያስተዋወቀች ትገኛለች።

አሁን ደግሞ ምርቶችን አምርቶ ወደ ገበያ ከማቅረብ ወጣ ብላ የባንክ መስራች ሆና ወደ ፋይናንሱ ዘርፉ ተቀላቅላለች።በምስረታ ላይ ያለው ሰላም ባንክን ከመሰረቱት መካከል ሥራ ፈጣሪዋ ቤተልሔም አንዷ ናት። ባንኩ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል ላይ ያተኮረ ነው። ቤተልሔም በአጭር ጊዜ ውስጥ ባስመዘገበቻቸው ስኬታማ የንግድና የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች የተነሳ በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ለመቀዳጀት በቅታለች። በፎርብስ መጽሔት ከ20 ተፅዕኖ ፈጣሪ ወጣት ሴቶች መካከል አንዷ ለመሆን የበቃችበት ጊዜ ይታወሳል። ከዚያም ከአሥር ዋና ዋና ተፅዕኖ ፈጣሪና ስኬታማ አፍሪካዊ ሴቶች ተርታ ተመድባለች። በ 2007 ዓ.ም. ከ100 ፈጣሪ ሰዎች መካከል ማለትም እንደ ማርክ ዙከርበርክ (የፌስቡክ መሥራች)፣ እነ ቢል ጌትስ (የማይክሮሶፍት የጋራ መሥራች) ተርታ ስሟ ሊሰፍር በቅታለች። ከዚህም በሻገር የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (ዩኤንዲፒ) የበጎ ፈቃድ አምባሳደር በመሆን ተመርጣ አገልግላለች። ከዚህም አልፎ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2017 ዓ.ም. “የአፍሪካ የሴቶች መሪ” በሚል ዘርፍ ልዩ ሽልማት አግኝታለች። የቤተልሄም ታሪክ ማንኛውም ሰው ከየትኛውም ችግር፣ ሁኔታ፣ መከራ፣ አስተዳደግ እና ድህነት ወጥቶ የሚፈልገው ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚችል ማስተማሪያ ነው።

## ፀደይ አስራት



ፀደይ “የአፍሪካው ስታርባክስ” እየተባለ የሚሞካሸውን በ ኢትዮጵያ የመጀሪያውን የ ተቀነባበረ ዓለም አቀፍ የቡና ንግድ “ካልዲስ ኮፊን” የመሰረተች ስራ ፈጣሪ ነች። መለያ መታወቂያዋ ካልዲስ ኮፊ ነው። አሁን ላይ ስሟ በካልዲስ ጎልቶ ይጠራ እንጂ በፋሽን ሞዴሊንግ ኢንዱስትሪውም ብዙዎች ያውቋታል። ወይዘሮ ፀደይ የተወለደችው በ1968 ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በካቴድራል ካቶሊክ ትምህርት ቤት የተከታተለች ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት ተከታትላለች። ከ ልጅነቷ ጀምራ በ ንግድ እና ፋሽን ትሳብ የነበረችው ፀደይ በ 17 አመቷ የ ፋሽን ኢንዱስትሪውን ተቀላቅላ በ24 አመቷ የራሷን የልብስ ሱቅ እንድትከፍት አድርጓታል። በስድስት ወር ውስጥ የከፈተችው ሱቅ ስኬታማ ስለነበረ ሁለተኛ ቅርንጫፍ ከፍታለች። ሆኖም የልብስ መሸጫዎቿ በልማት ምክንያት ሲፈርሱባት ይህን ስራ በመተው በባለቤቷ ካፕቴን ኤልያስ ሀሳብ አመንጪነት ወደ ካፌ ስራ በመግባት የራሷ ብራንድ የሆነውን ካልዲስ ኮፊን በ 1996 ከፈተች።

ካልዲስ ኮፊ በ30 ሰራተኛ የተጀመረ ሲሆን፤ በወቅቱ ይሄ የሠራተኛ ቁጥር ብዙ ቢሆንም ሰው ሲኖር ሰው ይመጣል ብለው ስለሚያምኑ መልካም ነገሮችን አምጥቶላቸዋል። በዚያ ላይ ሀሳቡ አዲስ በመሆኑ ከተከፈተበት ዕለት ጀምሮ ተወዳጅነትን አትርፏል። ተጠቃሚው በመበራከቱ ደግሞ ሰራተኛው መብዛቱ ጠቅሟቸዋል። አሁን ቅርንጫፎቹ አሜሪካ፤ ለንደንና አውስትራሊያ ያሉትን ጨምሮ 40 ደርሰዋል። የሠራተኞቹም ብዛት ከሁለት ሺህ በላይ ደርሷል። ወይዘሮ ፀደይ ካልዲስ የተጀመረበት፣ ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በወቅቱ ገበያ በጣም ትልቅ ብር እንደነበረ ያስታውሳሉ። ሆኖም ዛሬ የወተት ላም ፋብሪካውን ጨምሮ ሁለት ሼር ካምፓኒዎች ስላሉት ካፒታሉ ይሄን ያህል ነው ብሎ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም በብዙ እጥፎች አድጓል።

በዚህ ብቻ አላበቃችምበ 38 ሚልዮን ብር ሎሪ አግሮ ኢንደስትሪ የወተት ማቀነባበሪያን በመክፈት 175 ሰዎችን ቀጥራ ታሰራለች፣ በሌላም በኩል 3ሚልዮን ብር ወጪ የተደረገበት የዶሮ እርባታ ድርጅትም አላት፣ጉስቶ የሚል ስያሜ ያለዉ የጣልያን ቅንጡ ሬስቶራንትም ባለቤት ናት፣ከዚህ በተጨማሪ ባለቤትዋ የሚያስተዳድረዉ 1.5 ሚልዮን ዶላር የፈጀ ትልቅ ሬስቶራንት በዱባይ አገር አላት። ሴቶችን ማብቃት የወይዘሮ ፀደይ የሰርከ መመሪያ ነው። ወይዘሮ ፀደይ “እኔ ካልዲስን የከፈትኩት ተሰጥቶኝ ነው። እኔስ የተሰጠኝን የጋራ የማደርገው ምን ሰጥቼ ነው” በሚል ወተት የሚያቀርቡላቸውን የሱልልታ እናቶች በዶሮ እርባታ በማደራጀት በቀን ከአራት ሺህ በላይ እንቁላል ለካልዲስ ካፌ በማቅረብ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጋለች። 50 ሴት ልጆችንም በዩኒቨርሲቲ በማስተማር ማህበራዊ ሃላፊነቷን እየተወጣች ትገኛለች።

## ሳራ መንክር



ሳራ ሥራ ፈጣሪ እና የምግብ ፖሊሲ ባለሙያ ነች። አዲስ አበባ ውስጥ ተወልዳ ያደገች ሲሆን ወደ አሜሪካ ያመራችው በ1970ዎቹ ነበር። በኋላም ሴቶች በሚማሩበት ማውንት ሆዮኬ ኮሌጅ እንዲሁም በለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በኢኮኖሚክስ እና በአፍሪካ ጥናቶች እንዲሁም ከኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪ አግኝታለች።

በስራ አለም በጣም አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ከሚቀጥሩ ተቋማት መካከል አንዱ በሆነው ዎል ስትሪት የመጀመሪያውን ስራዋን ሀ ብላ ጀመረች። በዚያ ወቅትም በነዳጅ እና ጋዝ ሽያጭ ላይ ለተሰማራ ኩባንያ ነበር ትሰራ የነበረው። በ29 ዓመቷ በዎል ስትሪት ያላትን ሥራ በመተው ‘ግሮ ኢንተለጀንስ’ የተሰኘ ኩባንያ መሰረተች። በወቅቱ የምግብ ዋስትና ላይ ለመስራት በመወሰን ሥራዋን ስታቆም “ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተሳስራት ሥራ” እንደሚሆን ተናግራ ነበር።

ግሮ ኢንተለጀንስ በዓለም ላይ የሚታየውን የግብርና እና ምግብ ነክ መረጃዎች ክፍተት ለመሙላት በ2014 (እ.ኤ.አ) የተመሰረተ ተቋም ነው። ይህ ተቋም የሰው ሰራሽ አስተውሎት እና ስልተ-ቀመሮችን በመጠቀም የአለምን የግብርና መረጃዎች በማሰባሰብ፣ በማዋቀር፣ በመተንተን እና ትርጉም ባለው መልኩ በማደራጀት ለደንበኞች የማቅረብ ስራ ላይ ተሰማርቷል። ከአፈር ጥራት ጀምሮ እስከ አየር ንብረት ለውጥ ድረስ ያሉ የምግብ ምርት ላይ ተፅእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ተለዋዋጮች (variables) ላይ በመመስረት ግዙፍ መረጃዎችን የሚያጠናቅር ድርጅት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የተዋቀሩና ያልተዋቀሩ ለሕዝብ ተደራሽ የሆኑ መረጃዎችን ለምሳሌ:- ከናሳ የሚገኙ የሳተላይት ምስሎችን፣ የሀገራት የጉሙሩክ መረጃዎችን፣ የሀገራት የፍላጎት እና አቅርቦት ዘገባዎችን ይሰበስባል።

የቃረማቸውን መረጃዎች በ ሰው ሰራሽ አስተውሎት በመጠቀም እና የትንበያ ሞዴሎችን በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ያቀርባል። ይህ ትንበያ በግብርናው ምህዳር ውስጥ ያለውን ለውጥ በመገንዘብ ባለድርሻ አካላት ውሳኔዎችን ማድረግ እንዲችሉ ትልቅ አቅም ይፈጥርላቸዋል። ድርጅቱ በአሁነ ወቅት አርሶ አደሮች እና መንግስታት በግብርናዉ ዘርፍ የተሻለ ውሳኔ ማሳለፍ እንዲችሉ የሚያግዝ ሲሆን በግብርና እና በከባቢ አየር ስጋት ዙሪያ በአለማችን በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ የመረጃ ተንታኝ ተቋማት መካከል አንዱ ነው።

የሳራ እቅድ በ ግብርናና በከባቢ አየር ስጋት ዙሪያ መረጃ ከመተንተን ባሻገር የአገራትና ምግብ አምራች ድርጅቶች የምግብ ሰንሰለታቸውን እንዲያስተካክሉ የሚያስችል ዘዴን መፍጠርና የአየር ለውጥ ፈተናን ለመቅረፍ እርዳታ ማድረግ ነው። ይህ እቅዷም የኢንቨስተሮችን ቀልብ ለመሳብ በቅቷል። በቅርቡም ተቋሙ 85 ሚሊዮን ዶላር ከኢንቨስተሮች ማግኘት መቻሉ ተገልጿል።

ሳራ በ 2006 በዎርልድ ኢኮኖሚማክ ፎረም ወጣት አለማቀፍ መሪ በመባል ተሰይማለች። ሰው ሰራሽ ልህቆትን እና የመረጃ ሳይንስን በማጣመር የምግብ አቅርቦት ሰንሰለትን ለመረዳት በመሞከር ቀዳሚነቱን ትይዛለች ። ታይም መጽሔት በትምህርት ፣ በሳይንስ ፣ በኢኮኖሚክስ በሌሎች ዘርፎች ጨምሮ በ2021 በዓለም ላይ እጅግ ተጽእኖ ፈጣሪ ያላቸዉን የ100 ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ሰባት አፍሪካውያንን አካቷል። ከዚህም ዝርዝር ውስጥ ኢትዮጲያዊቷ ሥራ ፈጣሪ እና የምግብ ፖሊሲ ባለሙያ ሳራ መንክር ተካታለች።

## ሳምራዊት ፍቅሩ



ሳምራዊት የተዋጣላት የኮምፒዩተር ተመራማሪ፤ የስራ ፈጣሪ እንዲሁም ነጋዴ ናት ። ራይድ የተሰኘውን በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ተገልጋይ ያለውን መተግበሪያ የሰራው የሃይብሪድ ዲዛይን መስራች እና ዋና ስራ አስኪያጅ ናት። ሳምራዊት ፍቅሩ ተወልዳ ያደገችው ዝነኛ አትሌቶች በሚፈልቁባት አሰላ ከተማ ሲሆን እርሷም በልጅነቷ ሩጫውን ጀማምራው ነበር። ወደ በኋላ ግን በአባቷ ግፊት ለትምህርቷ ቅድሚያ በመስጠት ሩጫውን አልገፋችበትም። እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቷን ያጠናቀቀችውም እዚያው አሰላ ከተማ ነበር። በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ እና ሒልኮ የኮምፒዩተር ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ የሶፍት ዌር ኢንጅነሪንግ ትምህርት ተምራለች።

ከትምህርቷ ጎን ለጎንም በሁለት የሥራ መስኮች ተሰማርታ ነበር። በአንድ ኩባንያ ውስጥ ሲስተም አናሊስት እንዲሁም በሙዚቃ ድርጅት ውስጥ ሴልስ ማኔጀር ሆና ታገለግል ነበር።

በምትሰራባቸው የስራ ቦታዎችም ያሉትን ችግሮች በማጥናት የተለያዩ የሶፍትዌር ውጤቶችን ያቀረበች ሲሆን ይህንንም በምታስተዋውቅበት ወቅት የገጠሟትን እክሎች እንደ ተሞክሮ ወስዳ በ40,000 ብር መነሻ ካፒታል ከጓደኞቿ ጋር በመሆን ሀይብሪድ የተሰኘ የሶፍትዌር ኩባንያ አቋቋመች። ቢሮዋን እንደከፈተችም በቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ የተመለከተችውን ችግር የሚቀርፍ ፕሮግራም ፈጠረች። የሰራችው ፕሮግራም ማሽኑ ጥገና ሲያስፈልገው ቀደም ብሎ የሚያስጠነቅቅና ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያሳውቅ ከኪሣራም ነፃ የሚያደርጋቸው ነበር። ነገር ግን የሥራ ውጤቷን ለፋብሪካዎቹ ብታሳይም በጎ ምላሽ አላገኘችም። አምነው ሊቀበሏት አልቻሉም።

ሳምራዊት ቴክኖሎጂ ላይ ሴት ስትገኝ ትንሽ ጥርጣሬ ስላለ ብዙ አስቸጋሪ እና ተስፋ አስቆራጭ ጊዜዎች እንዳሳለፈች ትናገራለች። ሥራወቿ ተቀባይነት ባያገኝም ተስፋ አላስቆረጣትም። በስራ ላይ ተጠምዳ አምሽታ በምትወጣ ጊዜ ያለውን የትራንስፖርት ብሎም ተያያዥ የደህንነት ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ተገቢውን ጥናት በማካሄድ የአጭር የፅሁፍ መልእክት (SMS) የሚጠቀም ፕሮግራም መሥራት ጀመረች። ይህንንም ጥናት ስታካሄድ በተለይ ሴቶች ያለምንም እንግልት እና ፍራቻ የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት እንደሚቸገሩ በመረዳት ባሉበት ቦታ ሆነው የታክሲ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ነው። በከተማ ውስጥ የሚታየውን የትራንስፖርት ችግር የመቅረፍ ዓላማ ይዛ የተነሳችው ሣምራዊት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ተገቢውን አገልግሎት ማድረስ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን የሥነ ምግባር ስልጠና በመስጠት ወደ አገልግሎቱ ማስገባት ችላለች።

ራይድ የትራንስፖርት አገልግሎትን ስትጀምረው በአጭር የጽሁፍ መልእክት (sms) የተመዘገቡ አሽከርካሪዎችን ከደንበኞች ጋር በማገናኘት ነበር። አገልግሎቱን ማግኘት የምትፈልግ/የሚፈልግ ደንበኛ ወደ 8200 ቴክስት በመላክ ያለችበትን/ያለበትን ቦታ ታሳውቃለች/ያሳውቃል። የተዘረጋው ስርአትም ይህን አገናዝቦ በቅርብ የሚገኝ/ትገኝና ፈቃደኛ ለሆነ/ች አሽከርካሪ ያሳውቃል። ከዚያም የደንበኛ ስልክ ቁጥር አሽከርካሪ ጋር ይደርስና በስልክ ዋጋውን እንዲነጋገሩ ይደረጋል። ይህ አገልግሎት እንዲዘምንና ወደ መተግበሪያ (app) እንዲያድግ ከማድረጓ በፊትም ከግብር ነፃ ቢጫ ሜትር ታክሲዎች በመንግስት ድጋፍ ሲገቡ ማሟላት የሚገባቸውን ጥራት በተመለከተ የትራንስፖርት ሚኒስቴርን በማማከር እገዛ አደረገች።

በዚሁም መሰረት በኋላ ላይ ራይድ ተብሎ የተሰየመውን መተግበሪያ ፈጠረች። ራይድም በሶስት አመታት ውስጥ ብቻ ከአጭር የጽሁፍ መልእክት መተግበሪያነት ወደሁሉን አቀፍ የበይነ-መረብ እና የስልክ ጥሪ መተግበሪያነት አድጓል። በዚህም አገልግሎት ማንኛዋም ግለሰብ ተጠቃሚ መሆን ስትችል በተጨማሪም ለሰራተኞቻቸው የትራንስፖርት አገልግሎትን ለሚፈልጉ ድርጅቶችም የኮርፖሬት አገልግሎትንም ማስተዋወቅ ችላለች።

በአሁኑ ሰአት ራይድ ከ70,000 በላይ ሹፌሮቸን ይዞ ፡ ከ5 ሚሊዮን በላይ ደንበኞችን አገልግሎት ሰጥቶ ከ500 በላይ ድርጅቶችን ይዞ የሀገራችችን የትራንጋርት ኢንደስትሪ ፈር ቀዳጅ መሆን ችሏል። ሳምራዊት አዲስ ሃሳብን ላለመቀበል የሚገፋው አሰራር ሳይበግራት፣ መነሻ ሃብት ሳይኖራት፣ በግዜው የነበሩ ሃሳቦችን፣ ቴክኖሎጂዎችን እና የራሷን ፈጠራ ተጠቀማ ለብዙዎች የሚተርፍ የስራ እድል የሚያበረክት እና ምሳሌ የሚሆን ድርጅት ገንብታለች። ሳምራዊት ሴትነት፣ ወጣትነት እና ጀማሪነት የሚፈጥሩትን ፈተናዎች ተቋቁማ ለብዙ ወጣት ሴቶች ምሳሌ ሆናለች።

## ቤተልሄም ደሴ



ቤተልሄም ደሴ ብዙዎች ኢትዮጵያዊት “ቴክ ንግስት” እያሉ ይጠሯታል። አንዳንዶች ደግሞ ወጣቷ የቴክኖሎጂ ፈር ቀዳጅ የሚል ስያሜን ሰጥተዋታል። ቤተልሄም የተወለደችው በ1991 ዓ.ም. በሀረር ከተማ ነው። ከቴክኖሎጂ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀችው በበልጅነትዋ የአባትዋ ኤሌክትሮኒክስ ሱቅ ውስጥ ስትሰራ ነው። የ9 አመት ልደቷን ለማክበር አባቷን ገንዘብ ስትጠይቀው ፡ ትንሽ እንዳነሰው እና ስራ እንደበዛበት ሲነግራት ነበር ለማገዝ ሱቁ ውስጥ ለመስራት የወሰነችው ፡ ታድያ በዚህ አጋጣሚ ለደንበኞች የሬድዮና የቪድዮ መልክቶች እየላከች እስከ 1,600 ብር ታገኝ የነበረችው ቤቴልሄም ከዚህ በኋላ ነበር ስለ ኮምፒዩተር የማወቅ ፍላጎቷ እየጨመረ የመጣው ፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የቪዲዮ ቅንብር ፡ ኮምፒዩተር ጥገናና ፡ ሶፍትዌር መጫንን ማወቅ ቻለች ፡ በ10 አመቷ የኮምፒዮተር ኮዲንግ ቋንቋን ተለምምዳ ድረ-ገጽ መገንባት ቻለች።

ቤቴልሄም ተፈጥሯዊና እጅግ አስደናቂ የሆነ የቴክኖሎጂ እና ኮዲንግ ችሎታ እንዳላት ለሁሉም አሳየች። ችሎታዎቿ እና ዝናዋ እያደገ ስመጣ በተለያዩ የዜና ምንጮች ታሪኳ ተዘገበ። በወቅቱ ልጅ እያለች ያገኘቻት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እርሷና ቤተሰቦቿ ወደ አዲስ አበባ መጥተው እንዲኖሩ ጋበዟቸው። መንግስት የቤተልሄምን የትምህርት ወጪ በመሸፈን በኢትዮጵያ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሚስጥራዊ የሶፍትዌር ማበልጸጊያ ፕሮጄክቶች ላይ እንድትሰራ ተደረገ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተልሄም ክህሎቶቿን ጥቅም ላይ በመዋል ስራ ተጠምዳ ቆይታለች፤ አራት የሶፍትዌር ፕሮግራሞችን አበልጽጋ የኮፒራይት የተቀበለች ሲሆን ከእዚህም ውስጥ ገና 10ኛ ክፍል እያለች የፈጠረችው ዲጂታል ላይብረሪ አንዱ ነው።ፕሮግራሙ ውስን የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸው ለመማር የሚያስፈልጋቸውን መረጃዎች እንዲያገኙ የሚያስችል ነው።

ቤተልሄም መንግስት የወንዞችን አቀማመጥ በመለየት የመስኖ ስርዓቶችን ለመከታተል የሚያስቸለው መተግበሪያም ፈጥራለች። ስማርት ስልክ ያለው ማንኛውም የግብርና ባለሙያ ለመተግበሪያው አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል። የሰነድ እና የቁሳቁስ አያያዝ ስርዓት እና ወላጆችን እና መምህራንን በአንድነት የሚያገናኝ አስኳል የተሰኘ ዲጂታል የመማሪያ መድረክ ካበለጸገቻቸው ውስጥ ይጠቀሳሉ።

ቤቴልሄም አሁን ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) የምርምር ማዕከል በሆነው አይኮግ ላብ (ICog Lab) ውስጥ በፕሮጄክት ስራ አስኪያጅነት ትሰራለች። እሷ “ለአፍሪካ ቀጣዩ ታላቅ ነገር ቴክኖሎጂ ነው” ብዬ አምናለሁ” ትላለች። “አፍሪካ ውስጥ ያለን ታላቅ ነገር ወጣቱ ትውልድ ነው። ስለዚህ፣ ወጣቱን ትውልድ በቴክኖሎጂ ካሰለጠነው፣ ረጅም ዕድሜ ያለው ነገር ለመገንባት እንችላለን።” የምትለዋ ቤቴልሄም ቀጣዩ የኢትዮጵያ ትውልድ እነዚህን አጋጣሚዎች ለመጠቀም የሚያስፈልገውን ክህሎት ለማስጨበጥ ትፈልጋለች።

ቤቴልሄም ሴት ልጆች በመስኩ ያላቸውን ተሳትፎ ለመጨመር ለመጨመር የተለያዩ ፕሮጄክቶች ላይ ትሰራለች። የ“Anyone Can Code” መስራች እና ዋና ስራ አስፈፃሚ ናት። ይህም ከአይኮግ ላብ ጋር በመተባበር ሲሆን ከስድስት እስከ አሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ሕፃናት ከሮቦቲክስ እና ኤአይ እስከ ፕሮግራሚንግ ባሉ ርዕሶች ላይ ታሰለጥናለች። በኩዱ ቨንቸር የኩዱ

ሴቶች መርሃ ግብርን በአጋርነት ትሰራለች። ሌላው "ሶልቭ አይቲ" በሚባል ፕሮጀክት ከ18 እስከ 28 ዓመት ዕድሜ ያሉ በርካታ ወጣቶችን በማስተማር ፣ በማሰልጠን እና ድጋፍ አግኝተው ውጤታማ እንዲሆኑ ትሰራለች።

ከአሜሪካ ኤምባሲ አዲስ አበባ ጋር በመተባበር "Girls Can Code" ፕሮጀክት ሴት ልጆችን አሰልጥናለች። በቴክኖሎጂ ውስጥ ሴት አርኣያዎች ያለመኖራቸውን ክፍተት በአጽንኦት ትገልጻለች። ቤቴልሄም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ምህንድስና የተማረች ስትሆን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2019 በኳርትዝ አፍሪካ ከወጣት አፍሪካውያን የስራ ፈጣሪዎች አንዷ ሆና ተሰይማለች። በተጨማሪ ከተለያዩ ተቋማትም ዕውቅና የተቸራት ሲሆን በአለም አቀፍ መድረኮች በመገኘትም ልምዷን በማካፈል እና በመሳተፍ በቴክኖሎጅው ዘርፍ ትላልቅ ሥራዎችን ከሰሩ ባለሞያዎች ጋር ውጤታማ ግንኙነትን መስርታ ተሰጥኦ እና ብቃቷን አስመስክራለች።

በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ 3 ነገሮች ጥቀሺ ተብላ ስትመልስ፡-"ፅናት፣ ትእግስት እና ሁሌም ተማሪ መሆን አለብን" ያለችው ቤቴልሄም ወደ ህልም እና ወደ ስኬት መድረስ እንደሚቻል በ ተግባር ያሳየች የወጣቶች አርአያ ነች።




# ሴቶች በስፖርት ዓለም

# ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ




የወቅቱ ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት የሆነችው አትሌት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ በኦሎምፒክ ታሪክ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነች ጥቁር አፍሪካዊ ሴት የረጅም ርቀት ሯጭ ናት። አስር ልጆች ካሏቸው ቤተሰቦቿ ሰባተኛ ልጅ የሆነችው ደራርቱ በ1969ዓ.ም. አርሲ ዞን በቆጂ በተባለች መንደር ተወለደች። በከፍታማው የአርሲ ምድር በልጅነቷ ከብቶችን በመጠበቅ ታሳልፍ ነበር። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን እየተከታተለች ሳለም የሩጫና ፈረስ ግልቢያን ጨምሮ የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ትሳተፍ ነበር። የመጀመሪያውን አስደናቂ ድሏንም በ400 ሜትር ሩጫ የትምህርት ቤቱን ታዋቂ የወንድ ሯጭ በማሸነፍ የጀመረች ሲሆን በማስከተልም የአርሲ ክፍለ ሃገርን በመወከል በሃገር አቀፍ ውድድር በመሳተፍ በ1,500 ሜትር የነሃስ ሜዳሊያ ለማሸነፍ በቃች።

በክልላዊ ውድድሮች ጎልታ መታየት የጀመረችው ደራርቱ ትኩረቷን በፍጥነት ወደ ሀገር አቀፍ ደረጃ አሳደገች። በ17 አመቷም በፖሊስ ክለብ ተመልምላ ፕሮፌሽናል የአትሌቲክስ ስልጠናዎችን ጀመረች። እ.ኤ.አ በ1990ዎቹም አለማቀፍ እውቅናንና ስኬትን ማስመዝገብ ጀመረች። በቡልጋሪያ የ10,000 ሜትር ሪከርድን በማሻሻል ያሸነፈችበትና በተመሳሳይ ርቀት በግብፅ ካይሮ ድልን ያስመዘገበችባቸው ውድድሮች ከስኬቶችዋ ተጠቃሽ ናቸው።

ደራርቱ በባርሴሎና ኦሎምፒክ በ10, 000 ሜትር ያስመዘገበችው ድል በአፍሪካዊት ሴት የተመዘገበ የመጀመሪያው ወርቅ ሆኖ በታሪክ መዛግብት በደማቁ ሊፃፍ በቅቷል። የ23 አመቷ ፍልቅልቅ በወቅቱ ከድሏ በኋላ የሃገሯን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ለብሳ አንድ ዙር ሙሉ ስትሮጥ ስሟም አብሮ ከአለማችን ድንቅ አትሌቶች ተርታ ላይፋቅ በደማቁ ተመዘገበ።

በአጭር አመታት የሩጫ ህይወቷ 35 የወርቅ፣ 12 የብር፣ እና 15 የነሃስ ሜዳሊያዎችን ለማሸነፍ የበቃች የጀግኒቶች ቁንጮ መሆን ችላለች። በስፖርቱ ላሳየቸው ተምሳሌታዊ ስራዋም ከደቡብ አፍሪካዊው የትምህርት ተቋም ዌስተርን ኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ልታገኝ ችላለች። ብርቱዋና ፍልቅልቋ አትሌት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ።

እ.ኤ.አ. በ 2004 በአቴንስ ኦሊምፒክ ነሐስ ካገኘች በኋላ ትኩረቷን ወደ ማራቶን ቀይራ በተመሳሳይ አስደናቂ ስኬት አስመዘግባለች። አሁን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በመምራት ላይ የምትገኘው ደራርቱ ቱሉ በለንደን፣ በቶኪዮ እና በኒውዮርክ የማራቶን 3 ድሎችን አስመዘግባለች ። ወጣት አትሌቶች በተለይም ሴት ልጆች ህልማቸውን በነጻነት እንዲከተሉ በማበረታታት የነበራትን አቋም አጠናክራ ቀጥላለች። ደራርቱ ቱሉ በአሁኑ ወቅት በሴት አፍሪካውያን ሯጮች በተለይም በኢትዮጵያውያን የበላይነት ፈር ቀዳጅ ተደርጋ ትጠቀሳለች። በባርሴሎና ኦሊምፒክ ያስመዘገበችው ድል አፍሪካውያን አትሌቶች በዓለም አቀፍ መድረክ ያላቸውን አቅም እድያሳዩ በር ከፍቷል፣ ለላቀ ደረጃ እንዲጥሩ እና በችሎታቸው እንዲያምኑ አድርጓል። አትሌት ደራርቱ ከ አንጸባራቂ ድሎቿም ባሻገር ወደ ስፖርት አመራርነትም በመምጣት በስፖርት አመራር ፍትሃዊ የጾታ ስብጥር እንዲኖር እና የነገነውን የሥርዓተ ፆታ ልዩነት ለማጥበብ እየሰራች ትገኛለች። የደራርቱ አመራር መሰል ሴቶችን ወደስፖርቱ አመራርነት እንደሚያመጣ እና የ ሴቶችን ተሳትፎ እንደሚያጠናክር እሙን ነው። ደራርቱ የድል፣ የጥንካሬ፣ የርህራሄ፣ የእናት አገር ማሳያ፣ የምንግዜም የሀገር ባለውለታ ናት።

# ፋጡማ ሮባ




አትሌት ፋጡማ ሮባ በአትላንታ ኦሊምፒክ የሴቶች የማራቶን ውድድር በማሸነፍ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ማድረግና በሴቶች የኦሊምፒክ ማራቶን ውድድርን ያሸነፈች የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት አትሌት ነች። ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ፋጡማ ሮባ በአትላንታ ኦሊምፒክ የሴቶች የማራቶን ውድድር በማሸነፍ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ማድረግ ከመቻሏም በላይ ሴቶች በኦሊምፒክ በተለይም ደግሞ በማራቶኑ ዘርፍ ግንባር ቀደም ሆነው ሲወጡ ያሳየች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ብሎም አፍሪካዊት ናት። ፋጡማ ሮባ እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም በአርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ ሁሉሌ ካራ በሚባል ስፍራ ነው የተወለደችው። በትምህርት ቤት ውስጥ በሚዘጋጅ የሩጫ ውድድር ላይ ግን ንቁ ተሳታፊ ነበረች።ከዚያ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ተመርጣ በወቅቱ አውራጃ ወደሚባለው፣ ከዚያ ደግሞ ክፍለ ሀገር ለሚባለው እርከን ውድድሮችን ማድረግ ጀመረች። እንዲህ እንዲህ እያለች ለስፖርቱ ፍቅር እያደረባትና የተሻለ ነገር ሠርታ ጥሩ ደረጃ ላይ በመድረስ ሀገሯን የማስጠራት ህልም ያደረባት፤ ይህንንም ህልሟ እውን ለማድረግ በቀጥታ አዲስ አበባ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክፍል ገባች።

ፋጡማ ትልቁን ታሪክ ለመስራትና ለበርካታ አፍሪካውያን ሴት አትሌቶች ምሳሌና የይቻላል ምልክት ለመሆን ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፋለች። ከአትላንታ ኦሎምፒክ አንድ ዓመት በፊት 1995 እኤአ ስዊድን ላይ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና አገሯን ወክላ ተሳታፊ ብትሆንም 19ኛ ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው። ይሁን እንጂ ይህ ጥሩ የማይባል ውጤት ትልቅ ታሪክ ከመስራት ተስፋ አላስቆረጣትም። በቀጣይ ዓመት ኦሎምፒክን እንድትሳተፍ የሚያደርግ ድል በጣልያን የሮም ማራቶን አሸንፋ ወደ አትላንታ በማቅናት አይረሴውንና ታሪካዊውን ድል ለማኖር በቅታለች። ከአትላንታ ጣፋጭ የኦሎምፒክ ድል ቀጥሎ ባሉ ዓመታትም እ.ኤ.አ ከ1997 እስከ 1999 ድረስ በቦስተን ማራቶን ለሶስት ተከታታይ ዓመት ማሸነፍ ችላለች።

የኦሎምፒክ ድሏ በኢትዮጵያና በአፍሪካ የሴቶች ማራቶን ቀዳሚ የሆነችውን የፋጡማን ታሪክ ለመድገም ኢትዮጵያ አሥራ ስድስት ዓመታትን ጠብቃለች። የፋጡማ የኦሎምፒክ ድል በማራቶን ከ16 ዓመት በኋላ ቲኪ ገላና እኤአ በ2012 ለንደን ኦሎምፒክ ላይ ደግማለች። በአለም ካሉ ጀግና ሴቶች ጋር ተወዳድሮ ማሸነፍ ከባድ ነው።እልህ አስጨራሽ ልፋትን ይጠይቃል። ፋጡማ ይህንን ድል ለማየት ብዙ ዋጋ ከፍላለች፣ ለብዙ አትሌቶች የጽናት እና ትጋት ምሳሌ መሆን ችላለች።

# ጥሩነሽ ዲባባ




ጀግናዋ አትሌት ኮማንደር ጥሩነሽ ዲባባ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በአውሮፓውያኑ 2005 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት "በሴቶች ረጅም ርቀት ሩጫ ታሪክ ማንኛውም መሰናክል የማያቆማት ጠንካራ አትሌት" ሲል ይገልጻታል። በመስከረም 21 ቀን 1978 ዓ.ም. በኢትዮጵያ በአርሲ ክፍለ ሀገር በቼፋ ወረዳ ተወለደች። ጥሩነሽ ለቤተሰብዋ ከአምስቱ ሶስተኛ ናት። የጥሩነሽ ቤተሰቦች የረጅም ርቀት አትሌቶች ናቸው። አክስቷ ደራርቱ ቱሉ ሁለት ጊዜ የኦሎምፒክ እና አንድ ጊዜ ደግሞ የ 10000 ሜትር አሸናፊ እና የብዙ አገር አቋራጭ ውድድር አሸናፊ ነበረች። ሌላ አክስቷም በቀሉ ዲባባ ጥሩ ሯጭ ነበረች ። ጥሩነሽ ዲባባ የቤተሰብዋን ፈለግ መከተል የጀመረችው እድሜዋ ከፍ ካለ በኋላ ነው።

ጥሩነሽ ዲባባ ከ ሯጭ ቤተሰብ ብትፈጠርም ለመሮጥ ግን ምንም ፍላጎት አልነበራትም። ደራርቱ ቱሉ በባርሴሎና ኦሎምፒክ በ 10000 ሜትር ባሸነፈች በሰባት አመቱ ጥሩነሽ ወደ አዲስ አበባ በ 2000 ዓ/ም መንገድ ጀመረች። አክስቷ በቀሉ ዲባባ አባል ከሆነችበት ከእስረኞች ማረሚያ ፖሊስ ቡድን ስፖርት መስሪያ ክበብ ውስጥ አስመዝግባት ልምምድ ቀጠለች። ጥሩነሽ ዲባባ በ 14 አመት እድሜዋ በጣም ወጣት እና ሰውነትዋም ተሰባሪ ይመስል ነበር። ብዙዎችም በሩጫ ምንም ተስፋ እንደሌላት እና ሩጫው የሚጠይቀውን ጠንካራ ሰውነት የላትም ብለው ያምኑ ነበር። ነገር ግን ጥሩነሽ ዲባባ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ምርጥ የረጅም ርቀት ሯጮች አንዷ ለመሆን በቃች። በ 5000ሜትር የአለም ክብረ ወሰን ባለቤት ስትሆን በ5000 ሜትር እና በ10000 ሜትር የኦሎምፒክ ውድድር አሸናፊ ናት። ጥሩነሽ አራት የአለም አቀፍ ውድድር እና አምስት የአገር አቋራጭ ውድድር አሸነፊ ናት። በቅጽል ስም "Babyface destroyer" (የሕጻን ፊት ያላት ደምሳሽ) በማለት ይጠሩዋታል። ጥሩነሽ ዲባባ የመጀመሪያ አለም አቀፍ የውጪ ውድድር ያደረገችው እ.አ.አ በ 2001 በአለም አቀፍ አትሌቶች ውድድር ላይ ነው። ውድድሩን ስታካሂድ የ 15 አመት ልጅ ነበረች በዚህ ውድድር አምስተኛ በመሆን ጨርሳለች። በ 2003 በተደረገው የአፍሮ ኤሽያ ውድድር ላይ በ 5000 ሜትር የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆናለች። የጥሩነሽ ዲባባ አስደናቂ ውጤቶች ማምጣት የጀመረችው በአለም አቀፍ አትሌቶች ውድድር ላይ እ.አ.አ በ 2003 2005 እና 2007 ላይ ነው። ጥሩነሽ እ.አ.አ በ 2003 በ 5000 ሜትር ተሰፈንጥራ በመውጣት የስፔይኗን ማርታ ዶሚኒጌዝ እና የኬንያዋን ኤዲት ማሳያ ቀድማ ስትገባ በወቅቱ የታወቀች አትሌት ባለመሆኗ ውድድሩን ያስተላልፉ የነበሩት እንግሊዛዊ ስቲቭ ክራም እና ብሬንዳን ፎስተር ውድድሩ 100 ሜትር እስኪቀረው አንድም ጊዜ ስሟን ሳይጠሩ ቀርተዋል።

ጥሩነሽ ዲባባ በአገር አቋራጭ ሩጫም የተሳካ ውጤት አምጥታለች። ጥሩነሽ ዲባባ አለም አቀፍ አትሌቲክስ ውድድር ባሰናዳው አለም አቀፍ የአገር አቋራጭ ውድድር አምስት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ነች። በ ነሐሴ 15 2008 በቤጂንግ ኦሎምፒክ በተደረገው የ 10 000 ሜትር ውድድር በ 29:54.66 በመግባት በውድድሩ አንደኛ በመውጣት የአዲስ ክብረ ወሰን ባለቤት ለመሆን በቅታለች። ከአንድ ሳምንት በኋላ በነሐሴ 22 2008 በ 5000 ሜትር መሰረት ደፋርን ቀድማ በመግባት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ለመሆን በቅታለች። በዚህ ኦሎምፒክ በሁለት ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘቷ በአለም የመጀመሪያዋ የሴት አትሌት ሆናለች። በ2012 በለንደን በተካሄደው የ10000 ሜትር የኦሎምፒክ ውድድሩን በማሸነፍ በኦሎምፒክ ያገኘችውን የወርቅ ሜዳሊያ ቁጥር ወደ ሶስት ከፍ አድርጋለች። በመሆኑም በኢትዮጲያ ውስጥ እጅግ ውጤታማ የሆነ አትሌትነትን ቦታ ከቀነኒሳ በቀለ ጋር ተጋርታለች።

አትሌቷ አገሯን በወከለችባቸው አራት ኦሊምፒኮች (አቴንስ፣ ቤጂንግ፣ ለንደን እና ሪዮ ኦሊምፒኮች) 3 የወርቅ እና 3 የነሃስ ሜዳሊያዎችን አግኝታለች። ይህም በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ በመድረኩ እንድትሆን አስችሏታል። ከረጅም ርቀት የምንጊዜም ስኬታማ የዓለም አትሌቶች አንዷ የሆነችው ጥሩነሽ ዲባባ ከኦሊምፒክ ባሻገር በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም 5 የወርቅ እና 1 የነሃስ ሜዳሊያዎችን እንዲሁም በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና እና የአፍሪካ ቻምፒዮናዎች 6 የወርቅና 3 የብር ሜዳሊያዎችን

በማጥለቅ በአትሌቲክስ ሕይወት ወደር የሌለው ስኬት በመጎናፀፍ የአገሯን ባንዲራ አውለብልባለች። ህዳር 25፣ 2013 ዓ.ም 75ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ያከበረው  አትሌቲክስ ዊክሊ በአትሌቲክስ ዘርፍ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባን በሴቶች እና ዩዜን ቦልትን በወንዶች ታላላቅ አትሌቶች ብለው መርጠዋቸዋል።

## መሰረት ደፋር




መሰረት ደፋር  ህዳር 19 ቀን 1983 ዓ.ም. ተወለደች።  በ3000 ሜትሮች እና በ5000 ሜትር ውድድሮች ላይ በዋናነት የምትወዳደር ኢትዮጵያዊት የረጅም ርቀት ሯጭ ናት። በኦሎምፒክ እና በአለም ሻምፒዮና ከ5000 ሜትር በላይ የወርቅ ሜዳሊያዎችን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ አለም አቀፍ ውድድሮች ሜዳሊያዎችን ለአገሯ አስገኝታለች። እ.ኤ.አ. በ2007 በብራስልስ ቤልጂየም ትራክ ላይ፣ ከ9 ደቂቃ ባነሰ ጊዜ (8፡58.58) የ2 ማይል ሩጫ ያስመዘገበች ብቸኛ ሴት ሆናለች።  መሰረት ደፋር  በ2012 የለንደን ኦሊምፒክ እና በ2004 አቴንስ ኦሊምፒክ ወርቅ እና በ2008 የቤጂንግ ኦሊምፒክ የነሐስ ውድድር በ5,000 ሜትር በኦሎምፒክ ጨዋታዎች ውጤታማ ሆናለች። እ.ኤ.አ. በ 2005 በሄልሲንኪ ሻምፒዮና ብር እና በ 2007 በኦሳካ ሻምፒዮና ላይ ወርቅ በመውሰድ በዓለም ሻምፒዮና ተመሳሳይ ስኬት አግኝታለች።

መሰረት ደፋር በ5000 ሜትሮች፣ በ3000 ሜትሮች እና በሁለት ማይል ሩጫ የቤት ውስጥ ሪከርዶችን አስመዝግባለች። ከ2004 እስከ 2010 በአይ.ኤኤ.ኤፍ ( IAAF) የአለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና አራት ተከታታይ የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማግኘት የ3,000 ሜትር የቤት ውስጥ ውድድርን ተቆጣጥራለች።በተጨማሪም በሁሉም አፍሪካ ጨዋታዎች የሁለት ጊዜ ሻምፒዮን በመሆን በአፍሪካ ሻምፒዮና የአራት ጊዜ የሜዳሊያ ባለቤት ሆናለች።

በአለም ጁኒየር ሻምፒዮና የሁለት ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ነች። ኢትዮጵያዊቷ የረጅም ርቀት ሯጭ መሰረት ደፋር ጉዞ የጀመረችው በልጅነት ህልም ነው። "ከትንሽ ልጅነቴ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ ለመሮጥ ህልም ነበረኝ" ስትል ታስታውሳለች። "ምናልባት አንድ ቀን በትላልቅ ስታዲየሞች ላይ ተጫውቼ ትልቅ ሜዳሊያዎችን እንደምወስድ ለራሴ በመንገር በጫካ ውስጥ ሮጬ ነበር። ያለማቋረጥ የማስበው ነገር ነበር።" መሰረት ደፋር ባለፉት አስር አመታት ህልሟን እውን አድርጋለች፣ ይህም በታሪክ እጅግ ስኬታማ ከሆኑ ሴት አትሌቶች አንዷ ሆናለች። የእሷ ታሪክ ልክ እንደ ሃይሌ ገብረስላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ እና ጥሩነሽ ዲባባ ለወጣት ኢትዮጵያውያን ሯጮች ትልቅ መነሳሳት ሆኖ ያገለግላል።

መሰረት ደፋር በ2002 ዓ.ም በኪንግስተን ጃማይካ በ3000ሜ እና በ5000ሜ. የአለም ጁኒየር ሻምፒዮን ሆነች ። በ2004 በቡዳፔስት ሀንጋሪ የአለም የቤት ውስጥ የ3000ሜ ሻምፒዮን ሆነች። በአቴንስ 2004 ኦሊምፒክ የ5000ሜ ተጠባባቂ ተብላ የተያዘችው መሰረት በመጨረሻው ደቂቃ በቡድኑ ተጠርታለች። በማጣሪያው ዙር አጠቃላይ ምርጡን ሰዓት በማስመዝገብ የምርጫውን ትክክለኛነት አረጋግጣለች። መሰረት ደፋር በ2006 በሞስኮ እና በ2008 በቫሌንሺያ የ3000ሜ. ውድድር በማሸነፍ በአይኤኤኤፍ የአለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና ማስደነቁን ቀጥላለች። ከነዚህ ድሎች መካከል በ2007 በኦስካ በ5000ሜ. የመጀመርያውን የአለም ሻምፒዮና ሻምፒዮናዋን አስመዝግባለች። በተጨማሪም በኖርዌይ ኦስሎ የ5,000ሜ. ይህም በ2007 የአይኤኤኤፍ የአመቱ ምርጥ አትሌት እንድትባል አድርጓታል። በ2008 የቤጂንግ ጨዋታ የኦሎምፒክ ሻምፒዮንነቷን ለማስጠበቅ የተወዳደረችብትሆንም በሶስተኛነት ውድድሩ አጠናቃለች።

የመሰረት ደፋር ታሪክ የህልም እና የቆራጥነት ሃይል ማሳያ ነው። ከትንሽ ልጅ በትልቅ ህልም በጫካ ውስጥ ከምትሮጥ እስከ አለም እውቅ አትሌት ድረስ ጉዞዋ ለሚመኙ ሯጮች መነሳሳት ነው። ከፍተኛ ፉክክር ቢያጋጥማትም ያላሰለሰ ጥረትና ትጋት በማደረግ ለደረሰችበት ከፍታ በቅታለች። መሰረት ደፋር ታሪኳን እና ውጤቶቿን በማካፈል ተተኪው የኢትዮጵያ አትሌቶች ትልቅ ህልም እንዲኖራቸው እና ለታላቅነት እንዲተጉ ታደርጋለች። የእርሷ ትሩፋት ባገኘችው ሜዳሊያዎች ብቻ ሳይሆን እንደ አርአያ እና የተስፋ ብርሃን በሚመለከቱዋት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወጣት ሯጮች ነው።

## ሎዛ አበራ




በኢትዮጵያ የሴቶች እግር ኳስ ታሪክ ስኬታማዋ ሴት እግር ኳስ ተጨዋች የሆነችው ሎዛ አበራ ሴት ልጅ ማዕድ ቤት እንጂ ከወንዶች እኩል ውስጧ የሻተውን ማድረግ በማትችልበት ማሕበረሰብ ውስጥ ብታድግም ሕልሟን ከማሳካት አላገዳትም። የደቡብ ክልል ከምባታ ጠምባሮ ዞን ዋና ከተማ ዱራሜ ተወልዳ ያደገችበት ከተማ ነው። ልጅ ሆና እግር ኳስ ጨዋታ እጅግ ትወድ ስለነበር መጫወትና መመልከት ማዘውተርን ተያያዘችው። ከእግር ኳስ በተጨማሪ በልጅነቷ በትምህርት እጅግ ጎበዝና ፀባየ ሰናይ ተማሪ ነበረች።ክፍል ውስጥ በምታደርገው ንቁ ተሳታፎና የደረጃ ተማሪ በመሆኗ በመምህራኖቿ የምትወደድ ተግባቢና ታታሪ በመሆን ጥሩ የልጅነት ጊዜ አሳልፋለች።

ባደገችበት አካባቢ ያለው ሌሊሶ የተባለው ሰፊ የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ዛሬ እሷ በእግር ኳስ መስክ ታላቅ ስኬት ለመጎናፀፍ ያስቻላት መነሻዋ ነው።ከአቻዎቿ ጋር ጨርቅ ኳስ እያዘጋጁ በዚያ አቧራማ ሜዳ የእግር ኳስ ፍቅር ጥማታቸውን ማርካት ጀመሩ።ያሜዳ ለእርሷ ዛሬ ለተገኘችበት ቦታና ለተጎናጸፈችው ስኬት ምክንያት፣ ለጥበበኛ እግሮቿ ጥንካሬና ክህሎት ዋንኛ ትምህርት ቤትም አጋጣሚም ሆኗል።

እግር ኳስ ከስኬቷ ጫፍ ላይ የሚያደርሳት መክሊቷ መሆኑን ያኔ ፈፅሞ አታውቀውም።በትምህርቷ በርትታ ወደፊት የህክምና ሳይንስ በማጥናት የሰው ልጆችን ከህመም ለማዳን እና ከስቃይ ለመታደግ ሀኪም ለመሆን ተመኝታም ነበር። ህይወት ግን የአንቺ የስኬት ስፍራ የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ነው አለቻት። በወረዳ፣በዞን፣ በክልል፣ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ውድድሮች

ላይ በመሳተፍ ታላቅ ዝናና አድናቆትን አትርፋለች።ኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ተጫዋቿ ሎዛ አበራ። በኢትዮጵያ ፕሪሜር ሊግ የዞንና የክልል እግር ኳስ ቡድኖች ላይ በመሳተፍ ባሳየችው ድንቅ ብቃት ክለቦች ዓይናቸውን አሳረፉባት።በዚህም በሃዋሳ ከነማ፣ደደቢት፣አዳማ ከነማ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ኳስ ክለቦች ተዛዋውራ ተጫውታለች።ወደ ሲውዲን በማቅናትም በሁለት የተለያዩ ክለቦች በመጫወት ስኬቶችን ተጎናፅፋለች።

በአገር አቀፍ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ የእግር ኳስ ውድድሮች ላይ በምታደርገው ማራኪ ጨዋታ ብዙዎች አድናቆትን የቸሯት፣ በታላላቅ ውድድሮች ላይ ሽልማትና ክብር የተቀዳጀች ለአራት ተከታታይ ዓመታት ኮከብ ግብ አግቢ በመሆን ተሸልማለች፣ አራት ጊዜ ከቡድኗ ጋር የሻምፒዮንነት ክብር ተቀዳጅታለች፣ በሲዊዲን ባስመዘገበችው ድንቅ ችሎታ  የዓመቱ ኮከብ ተጫዋችነትና ኮከብ ግብ አግቢነት ክብርና ሽልማት ተበርክቶላታል፣ የኢቢሲ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች ሽልማት አሸናፊም ናት። ቢቢሲም ከዓመቱ 100 ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴቶች መካከል አንዷ አድርጎ መርጧታል። ሴቶች በተለያዩ መስኮች የራሳቸውን ያልተቆጠበ ጥረት ካደረጉ ከፍ ያለ ውጤትና ስኬት ማስመዝገብ ይችላሉ፤ ለዚህም ማመንና ለስኬታቸው መጣር ይገባቸዋል የምትለው ሎዛ በዓለም ላይ ስኬታማና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰዎች በአንድ በተለየ መስክ ሳይሆን ተፈጥሮ ባደላቸው ክህሎታቸው በራሳቸው ጥረት ባደረጉት ጥረት ያገኙት ስኬት መሆኑን ትገልፃለች።



## ሴት አውሮፕላን አብራሪዎች





## ሙሉ እመቤት እምሩ



ሙሉ እመቤት እምሩ በኢትዮጵያ ብሎም በ አፍሪካ የመጀመሪያዋ አውሮፕላን አብራሪ ናቸው። ሙሉ እመቤት ገና ልጅ ሳሉ ነበር በአዲስ አበባ ሰማይስር የሚበሩትን አውሮፕላኖች ተመልክተው የአብራሪነት ፍላጎት በውስጣቸው የተፀነሰው። የሙሉእመቤት ወላጆቿ ይህን ፅኑ ፍላጎቷን ተመልክተው ወደማስልጠኛ ተቋም ቢወስዷትም ሙሉእመቤት ግን በጊዜው እድሜዋ እንዳልደረሰና 18 አመት ሲሞላት እንድትመለስ ይነገራታል። የያኔዋ ለበ መሉ ግን አላማዋን ለማሳካት በመጀመሪያ መኪና መንዳት በመለማመድ የመንጃ ፍቃድ አወጡ።

እድሜያቸው 18 ዓመት ሲሞላም በፈረንሳዊው ሙሴ ጋስቶን ቨርዲየር መምህርነት በ ጅግጅጋ ከተማ በተቋቋመው የበረራ ትምህርት ቤት የበረራ ስልጠናቸውን ከ6 ወንዶች ጋር ጀመሩ። በ 1926 ዓ.ም ትምህርታቸውን አጠናቀው የመጀመሪያዋ ሴት አፍሪካዊ አውሮፕላን አብራሪ ለመሆን ችለዋል። በ1927 ዓ.ም ደግሞ ብቻቸውን የተሳካ በረራ በማድረግ ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ሴት ሰማይ ቀዛፊ መሆን ችለዋል።

ሙሉ እመቤት እምሩ በማብረሩም ብቻ ሳይሆን አውሮፕላን ማብረርን ለተወሰነ ግዜ አስተምረዋል ይሄም በሴት የበረራ መምህርነት ቀደምት ያደርጋቸዋል። እኚህ ጀግና ሴት በረራ በፈጸሙበት ጊዜ የአውሮፕላን ጠባይ ቀርቶ አገልግሎቱ ገና ብዙ ያልተለመደበት ዘመን ስለነበር በሕዝብ ዘንድ እጅግ ተደንቀዋ ሙሉእመቤት ብልህ፣ ፈጣንና ደፋር እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ሙሉ እመቤት በዳጉለት ሙያ አገራቸውን ማገልገል መቀጠል አልቻሉም፤ ለዚህም ምክንያት የሆነው በ1928 ዓ.ም ጣሊያኖች ኢትዮጵያን መውረራቸው ነበር። ፋሽስት ወራሪዎች ስለኚህ ጀግና ሴት በረራ ችሎታ ሰምተው በስቅላት ይፈልጓቸው ስለነበር ወይዘሮዋ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በመደበቅ መኖር ነበረባቸው። ሥጋታቸው ከፍተኛ ስለነበረ ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጋር ውጭ አገር ሄደዋል እያሉ ያስወሩ ነበር። ጦርነቱ እስከሚያልቅና አገሪቱ ነፃ ወጥታ ሰላም እስከሚረጋገጥ ድረስ በስጋትና በጭንቀት እየተደበቁ መቆየታቸው ከበረራው እንዲገለሉ ከማድረጉም በላይ የወደፊት ሕይወታቸውን እንዲለውጡና ትዳር መሥርተው ቤተሰብ ማስተዳደር ላይ እንዲያተኩሩ ምክንያት ሆነ።

ስለሆነም ካቶ ዘውዴ ኪዳነወልድ ጋር ተጋብተው 6 ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ወልደው አሳድገዋል። በአፍሪካ በእንስት አውሮፕላን አብራሪነት ዘርፍ ፋና ወጊ በመሆን ለብዙዎች አርአያ በሆኑት ኢትዮጵያዊቷ ሙሉእመቤት እምሩ ስም እናት ባንክ ሃያሁለት አካባቢ የሚገኘውን ቅርንጫፉን ሰይሟል።

ዛሬም ድረስ በዓለም ላይ ስሙ የገነነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከበርካታ ስኬቶቹ መካከል በኩራት የሚነገርለት የሴቶች አብራሪዎች ጉዳይ ጀማሪ የነበሩትን የመጀመርያዋ አፍሪካዊት አብራሪ ሙሉ እመቤት እምሩ በድፍረት ከወንድ ጓደኞቻቸው ጋር የአውሮፕላን ማብረር ስልጠና መውሰዳቸው ኢትዮጵያ ከዘመናት በፊት ለፆታ እኩልነት ክብርም ዕድልም የሰጠች አገር እንደሆነች ያሳየናል።

# አሰገደች አሰፋ



አሰገደች አሰፋ ወንዶች በተቆጣጠሩት የአቪዬሽን ኢንደስትሪን ሰብራ በመግባት በርካታ መሰናክሎችን አልፋ የዛሬ 54 ዓመት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የአውሮፕላን አብራሪ መሆን የቻለች ድንቅ ሴት ናት። እንዴት ወደ አውሮፕላን አብራሪዎች ሥልጠና እንደተመዘገበች ስትጠየቅ "በአንድ ወቅት ከወንድ ጓደኞቼ ጋር ስናወራ የኢትዮጵያ አየርመንገድ የአውሮፕላን አብራሪዎች ትምህርት ቤት መከፈል ለሚችል ማንኛውም ሰው ማስተማር እንደጀመረ ስሰማ ወዲያው ለመማር ወሰንኩ" ትላለች።

በአውሮፕላን አብራሪዎች ትምህርት ቤት ተመዝግባ ሥልጠናውን መከታተል በምትጀምርበት ወቅት በትምህርት ቤቱ የነበሩ ወንድ ተማሪዎች ከቁም ነገር እንዳልቆጠሯት ትናገራለች። ምንም እንኳን በትምህርት ቤቱ ብቸኛ ሴት ተማሪ ብትሆንም በርትታ ስልጠናውን በመከታተል የአብራሪነት ስልጠናውን እንዲሁም ፈተናውን በማለፍ አውሮፕላኖችን ማብረር ጀምራ ነበር።

የአውሮፕላን አብራሪ ከሆነች በኋላ ፎቶግራፏ በጋዜጦች ላይ ተሰራጭቶ በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የነበሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስል አሰገደች ሰምተው እጅግ በማድነቅ ወደ ቤተ-መንግስታቸው አስጠርተው አነጋገሩዋት ነበር። አሰገደች ስለ ልጅነቷ ሲናገሩ እንደሌሎች ሴቶች በቤት ውስጥ ከሚሰሩ ሥራዎች በላይ በውጪ የሚከናወኑ እንደ የውሃ ዋና እና መሰል እንቅስቃሴዎችን ታዘወትር እንደነበር ትናገራለች።

አሰገደች አሰፋ ብዙ ውጣ ወረዶች ቢገጥማትም አርዓያነቶ እስከ አሁን ድረስ ብዙዎችን ማነሳሳቱን ቀጥሏል። የእርሷ ስኬት ሴቶች በአቪዬሽን ዘርፍ እንዲሁም ወንዶች በሚበዙበት በሌሎች የሙያ ዘርፎች ጭምር መስራት እንደሚችሉ ያስመሰከረች ጀግና ነበረች። የአሰገደች የጽናት እና የቆራጥነት ተምሳሌትነት በዓለም ዙሪያ ላሉ ሴቶች እንዴት መሰናክሎችን አልፎ ህልምን ማሳካት እንደሚቻልም አሳይታለች።

## አምሳለ ጓሉ (ካፒቴን)



ካፒቴን አምሳለ ጓሉ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ታሪክ የካፒቴንነት ደረጃ ላይ ለመድረስ የበቃች የመጀመርያዋ ሴት የአውሮፕላን አብራሪ ነች። ሴቶች ብዙ በማይደፍሩትና ወንዶች በእጅጉ በበዙበት የአብራሪነት ሙያ ውስጥ በመግባት ለሥራው የሚያስፈልገውን ረዥም ስልጠና ከማጠናቀቋም ባሻገር ተከታታይ ጥብቅ ግምገማዎችና ምዘናዎችን በማለፍ ፣ በ2003 ዓ.ም የመጀመርያዋ ሴት ካፒቴን (ዋና አብራሪ) ሆናለች።

በ1970 ዓ.ም ባህርዳር ውስጥ አማካይ ገቢ ከነበረው ቤተሰብ የተወለደችው አምሳለ፤ ወላጆቿ ካፈሯቸው አራት ልጆች የመጀመርያዋ ናት። ሦስት ዓመት ሲሆናት ቤተሰቦቿ ወደ አዲስ አበባ ይዘዋት የመጡ ሲሆን የመጀመርያ ደረጃ ትምህርቷን በአሳይ የህዝብ ት/ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በቦሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትላለች።

ወላጆቿ የተማሩ ስለነበሩ፣ ልጆቻቸው ትምህርታቸው ላይ በደንብ እንዲያተኩሩ ከመደገፍና ከማበረታታት ቸል ብለው አያውቁም። እሷና እህቶቿ ልጆች ሳሉ አባቷ አየር ማረፍያ እየወሰዷቸው፣ አውሮፕላን ሲነሳና ሲያርፍ ይመለከቱ ነበር። ያኔ ነው አውሮፕላን ማብረር የልጅነት ህልሟ ሆኖ በውስጧ የተጠነሰሰው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳለች ግን ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ምኞት ሳይሆን እርግጠኛ ሆነች።

በ1987 ዓ.ም የዩኒቨርስቲ መግቢያ ብሔራዊ ፈተና በመውሰድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቴክኖሎጂ ፋኩሊቲ ገብታ፣ ሥነ ህንፃ (አርኪቴክቸር) ማጥናት ጀመረች። ሆኖም የልጅነት ህልሟን አልዘነጋችም። የአንደኛ ዓመት ተማሪ ሳለች ነው የአብራሪነት ማሰልጠኛ ት/ቤት ለመግባት የመጀመርያ ሙከራዋን ያደረገችው። ነገር ግን የመግቢያ ፈተናውን በመውደቋ ሙከራዋ ሳይሳካ ቀረ። ሆኖም ተስፋ አልቆረጠችም። የህይወት ተመክሮ ስላገኘችበት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ነው የቆጠረችው።

አንዳንዴ በህይወት ውስጥ ነገሮች ላይሳኩ ቢችሉም፣ ጨርሶ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለባት ጠንቅቃ ታውቃለች። ወደ አብራሪነት ሙያ የመግባት ሁለተኛ ሙከራዋን ያደረገችው ከአራት ዓመት በኋላ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን የበረራ ት/ቤቱን የብቃት መመዘኛ ፈተና ለማለፍ ቻለች። ከዩኒቨርስቲው እንደተመረቀችም በጥድፊያ ወደ ሥልጠናው ገባች። ተጣድፋ ብትገባም በዚያው ፍጥነት አልጨረሰችም። በእሷ ጉድለት ግን አልነበረም።

በወቅቱ በተከሰተው የነዳጅ እጥረት ምክንያት የበረራ ትምህርቱ ከወትሮ የበለጠ ጊዜ ፈጀባት – ከሁለት ዓመት በላይ። ሥልጠናው ከባድና ፈታኝ ቢሆንም ቅሉ አምሳለ ግን እጅ አልሰጠችም። በህዳር 1994 ዓ.ም ትምህርቷን በስኬት በማጠናቀቅ በረዳት አብራሪነት ተመረቀች። ከስምንት ዓመት የበረራ አገልግሎት ጋር የማያቋርጥ ግምገማና ሁሉም ነገሩ እንደ አውሮፕላን የሆነ ዘመናዊ የመለማመጃ ማሽን (ሲሙሌተር ) ላይ የሚደረግ ስልጠናና ምዘና ከወሰደች በኋላ፣ጥቅምት 4 ቀን 2003 ዓ.ም የካፒቴንነት ማዕረግ ለመቀዳጀት በቃች።

ካፒቴን አምሳለ ዋና አብራሪ ከመሆኗ በፊት 4475 የበረራ ሰዓቶችን በረዳት አብራሪነት አስመዝግባለች። ከእሷ በፊትም ሆነ በኋላ የአብራሪዎች ማሰልጠኛ ገብተው የተማሩ በጣት የሚቆጠሩ ሴቶች ቢኖሩም ወደ ዋና አብራሪነት የሚያደርሰውን ረዥም የሙያ ጉዞ በስኬት በማጠናቀቅ አምሳለ የመጀመርያዋ ናት።

አምሳለ፤የቀደምቶቹን ሴት ፓይለቶች እነ ሙሉመቤት እምሩ፣ አሰገደች አሰፋ፣ ሶፍያ ገዛኸኝ፣ ሃና ወልዴና እሌኒ ታደሰን ፈለግ በመከተል፣ በኢትዮጵያ አቬሽን ታሪክ ስድስተኛዋ ሴት ፓይለት ናት። በረዳት አብራሪነት የሰሩት ቀደምት ሴት አብራሪዎች ግን ተጨማሪ ሥልጠናና መመዘኛዎችን በማሟላት እንዲሁም እልህ አስጨራሹን ተከታታይ ግምገማ በማለፍ የዋና አብራሪነት ደረጃ ላይ አልደረሱም።

በአገሪቱ የመጀመርያዋ ሴት ካፒቴን መሆን ታሪካዊ ስኬት እንደሆነ ባይካድም ለአምሳለ ግን ትልቁ ኩራቷ የልጅነት ህልሟን አሳክታ የሙያው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ መብቃቷ ነው። ቀድሞውንም ውስጣዊ ብርታት የምታገኘው የመጀመርያዋ ሴት ካፒቴን ለመሆን በነበራት ፍላጎት አልነበረም፡፤ የልጅነት ህልሟን ለማሳካትና በሙያው የላቀ ደረጃ ላይ ለመድረስ ባላት ጥልቅ ፍላጎት እንጂ።

አንዳንዶች ፈተናዎችን እንደውድቀት ቢመለከቱትም ካፒቴን አምሳለ ግን ፈተናዎችን መጋፈጥ የእድገት ሂደት አካልና የጥንካሬ ምንጭ ነው ብላ ታምናለች። በፆታዋ የተነሳ የአድልዎ ዒላማ መሆኗን፣ በጥርጣሬ መታየቷንና አሉታዊ አስተያየቶችን ማስተናገዷን አትክድም። ሆኖም እንዲያ ያለው ነቀፌታ ስሜቷን እንዲነካት ፈፅሞ አትፈቅድም። ህብረተሰብ በሂደት እንጂ በአንድ ጀምበር አይለወጥም ብላ የምታምነው አምሳለ፤ እስከዚያው ግን ቢያንስ በየግላችን ራሳችንን መለወጥ እንችላለን ትላለች።

ካፒቴን አምሳለ፤ የስኬት ታሪኳን ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ በተለይ ለወጣት ሴት ተማሪዎች በማጋራት ለወገኖቿ የድርሻዋን እያበረከተች ነው። በአዲስ አበባና ሌሎች ክልሎች ልዩ ልዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያሰናዷቸው ዝግጅቶች ላይ እየተጋበዘች፣ የህይወት ታሪኳንና ተመክሮዋን ለአዲሱ ትውልድ በማካፈል፣ ወጣቶች በህልሞቻቸው እንዲተማመኑ በማበረታታትና በማነቃቃት እያገዘች ነው።

ካፒቴን አምሳለ በዛሬው ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያድጉ ልጃገረዶችና ሴቶች የምትለግሰው ምክር እንዲህ የሚል ነው፡_ "ምንጊዜም በህይወታችሁ ውስጥ ቅድምያ የምትሰጡትን ነገር ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ። በወጣትነታችሁ ከሁሉም በፊት ለትምህርታችሁ ቅድምያ ስጡ። ላለማችሁት ነገር በሙሉ ልብና ቁርጠኝነት ትጉ። ጨርሶ ተስፋ አትቁረጡ። የልባችሁን ፍላጎት ለይታችሁ እወቁ። የመረጣችሁት ሙያ ወንዶች የገነኑበት ቢሆንም እንኳ ደፍራችሁ ግቡበት" ትላለች።



## ሴት አርበኞች





## ሸዋረገድ ገድሌ (1878-1942 ዓ.ም)



ሸዋረገድ ገድሌ በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ወረራ ጊዜ ለሀገራቸው አኩሪ ገድል በመፈጸም እና ለኢትዮጵያ ነጻነት ዋጋ በመክፈል ስማቸው ከሚነሱ ሴት አርበኞች ግንባር ቀደም ናቸው። አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የተወለዱት በ1878 ዓ.ም ተጉለት አካባቢ ሸዋ ነው። በቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ አድገው በዘመኑ የነበረውን የቤተክህነት ትምሕርት ተምረው አብዛኛውን የህይወታቸውን ክፍል በመንፈሳዊ አገልግሎት፣ በ ንግድ እና አገርን በማዘመን አሳልፈዋል። አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የመንፈሳዊ ሂወትን ከ ዘመናዊው ጋር አስማምተው ይኖሩ የነበረ ሲሆን ከመጀመሪያዎቹ የባንክ ተጠቃሚዎችና የአክሲዮን ገዢዎች፣ የፋብሪካ ተካዮች መካከል አንዷ ነበሩ። ዘይት በማምረትና በመሸጥ ውጤታማ የንግድ ሥራ ሠርተዋል። ባንክ በመጠቀምና አክሲዮን በማቋቋም ዘመናዊነትን አስፋፍተዋል። በተሠማሩበት የበጎ አድራጎት ሥራ አርዓያነታቸውን አስመስክረዋል። በመንፈሳዊው ድግሞ የጉለሌ ቅዱስ ገብርኤል ያስተከሉት እርሳቸው ነበሩ። ሸዋረገድ ወደ አርበኝነት ከመግባታቸው በፊት በንግድ ሥራ ተሠማርተው በርካታ ሠዎችን አግዘዋል። በተለይም በ1927 ዓ.ም ለተመሠረተው የቀይ መስቀል ማኅበር ንብረታቸውን ሸጠው ማበርከታቸው እና የማኅበሩ ሰብሳቢ በመሆንም ማገልገላቸው በ 1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ለወረረው ፋሽስት ምቾት የሚሰጥ አልነበረም።

የሸዋረገድ ስም ይበልጥ ከፍ አድርጎ ያስጠራው አርበኝነታቸው ነው። ኢጣሊያ ለሁለተኛ ጊዜ ሲወር መምጣቱን ሲሰማ በአዲስ አበባ ከተማ ተቆርቁሮ ዜጎች በተቋቋመው የሀገር ፍቅር ማህበር አባልነት መጀመሪያ ከተመዘገቡት ጥቂት ሴቶች መካከል አንዱ ነበሩ። በ1928 ዓ.ም ጣሊያን ኢትዮጵያን በግፍ ስትወር አርበኝነትን ካቀጣጠሉ ሴቶች አንዷ ናቸው። የታወቁበትን እና ለሀገር ነጻነት ዋጋ የከፈሉበትን የአርበኝነት ተጋድሎን የጀመሩት በ52 ዓመታቸው ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት በክተት አዋጅ ወደ ሰሜን ግንባር ሲዘምት ከሠራዊቱ ጋር በመሆን ዘምተዋል። ጣሊያን የመርዝ ጭስ ተጠቅሞ በፈጸመው ጥቃት የኢትዮጵያ ጦር ሲፈታ አርበኛ ሸዋረገድ እና ሌሎች ባልደረቦቻቸው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ለጊዜው ድል ያገኘ የመሰለው ጣሊያን በክብር ከፍ ብሎ ሲውለበለብ የነበረውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አውርዶ እንደ ተራ ጨርቅ ማዋረድ ጀመረ። ይህን የእብሪት ድርጊት አይተው እንዳላዩ ማለፍ ያልቻሉት ሸዋረገድ ገድሌ፣ በፋሽስት ወታደሮች ፊት ተቃውሟቸውን ለማሰማት ወደ አደባባይ ላይ ወጡ። በወቅቱ የፋሽስት ወታደሮች ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠሩት በአዲስ አበባ ከተማ አደባባይ ቀርቶ በቤት ውስጥ እንኳን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወይም የአርበኞችን ፎቶግራፍ ደብቆ የተገኘ ሰው ከባድ ቅጣት እንደሚደርስበት ስለሚታወቅ ሸዋረገድ ገድሌ ያሳዩት የአደባባይ ግልጽ ተቃውሞ የፋሽስት ወታደሮችን ያስቆጣ ተግባር ነበር። እንደተጠበቀውም ሸዋረገድን በቁጥጥር ስር አውለው በጨካኝ ሹማምንቶቻቸው ፊት አቀረቧቸው። ጀግናዋ ግን ያለምንም ፍርሃት ስለ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓለማ ክብር በሹማምንቶቹ ፊት ተናገሩ። ይህ ድፍረታቸው በሞት የሚያስቀጣ ቢሆንም በጥቂት መልካም ሰዎች ተማጽኖ የሞት ፍርዱ ወደ እስር እንዲለወጥላቸው ተደርጎ ታስረው ከቆዩ በኋላ ተለቀቁ። ከእስር ከተለቀቁ በኋላም ጠላትን በምን ዓይነት መንገድ እንደሚያጠቁ ስልት ቀየሱ።

በዚህም በጠላት ውስጥ ሠርገው ከገቡ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ዘንድ መረጃ በመሰብሰብ በዱር በገደል ተሰማርቶ ጠላትን ለሚፋለመው የወገን ጦር መረጃ ለማቀበል ወስነው ሥራ ጀመሩ። በአዲስ አበባ ዙሪያ ላደፈጡት አርበኞች መረጃውን በሚስጥር ለማድረስ እንደ እንቁላል ነጋዴ ጭድ በተነሰነሰበት ቅርጫት ውስጥ መልእክቱን ደብቀው ማመላለስ ጀመሩ። ጎን ለጎንም በተቻላቸው መጠን ለአርበኞቹ ስንቅ ያደርሱ ነበር።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም አብርሃም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶም ግራዚያኒን ለመግደል ካደረጉት ሙከራ ጋር በተያያዘ አርበኛ ሸዋረገድ ተይዘው ታሰሩ። የፋሽስት ወታደሮችም ሸዋረገድን በኤሌክትሪክ ገመድ በመግረፍ የግድያ ሙከራው እንዴት እና በማን እንደተፈፀመ እንዲናገሩ ጠየቋቸው። ሸዋረገድም የሚፈጸምባቸውን ድብደባ መቋቋም አቅቷቸው ራሳቸውን ስተው ወደቁ። ራሳቸውን ከሳቱበት ሰመመን እስኪነቁ ለአንድ ሳምንት ያህል በመኖሪያ ቤታቸው እንዲቆዩ ተደርጎ ሲነቁ እንደገና ወደተዘጋ እስር ቤት ተወረወሩ።

አርበኛዋ ሸዋረገድ በሚፈፅሟቸው በርካታና አኩሪ ገድሎች ጥርስ የነከሱባቸው የፋሺስት ሹማምንት ህይወታቸውን በእስር እንዲገፉና ቆይቶም ሞት እንዲፈረድባቸው ወስነው ነበር። ሆኖም በሰሜናዊ ምዕራብ ኢጣሊያ ወደምትገኘው አዚናራ ደሴት ታስረው እንዲቆዩ ፍርዱ በመቀየሩ የእስር ዘመናቸውን በደሴቲቱ እንዲገፉ ተወሰነባቸው። ጀግናዋ አርበኛ ሸዋረገድ ግን የቦታ ለውጥና ርቀት አልበገራቸውም። ወኔያቸውን አጠናክረው ትግላቸውን ቀጠሉ። በእስር ቤቱ የሚቀርብላቸውን ምግብ በአሳሪዎቻቸው ፊት በመድፋትና ጦማቸውን ውለው በማደርም ተቃውሞ ማድረግ ጀመሩ። ከሀገር ወጥተውም በታሠሩ ወቅት የአርበኝነት ሥራቸውን የበለጠ ይሠሩ ነበር። በተለይ በጅቡቲ የነበረ አንድ ኢትዮጵያዊ የሰጣቸውን "የይሁዳ አንበሳ" የሚል ጽሑፍና ዓርማ ያለበትን ወረቀት ከንጉሰ ነገሥቱ የተላከ የሚመስል መልዕክት እየፃፉ አርበኞች ተጋድሎ ወደሚያደርጉባቸው ልዩ ልዩ ስፍራዎች በመላክ አርበኞቹ እንዲበረታቱ አድርገውበታል። የእስር ቆይታቸው ከአንድ አመት በላይ እንደዘለቀ እንዲፈቱ በመወሰኑ አዲስ አበባ የመግባት ተመለሱ። በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ ሲገቡም ሕዝቡ ...

***"የዘበኛ ሱሪ ካኪና ገምባሌ፣***

***እንኳን ደህና መጣሽ ሸዋረገድ ገድሌ" ብሎ በመግጠም ተቀበላቸው።***

አዲስ ዓም አካባቢ ይገኝ የነበረው የፋሺስት አጣሊያ ምሽግ ኅዳር 5 ቀን 1933 ዓ.ም ሲሰበር ጠቃሚ መረጃዎችን ለአርበኞች በማሰባሰብና በርካታ እቅዶችን በመንደፍ ታላቁን ድርሻ የተወጡት ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ነበሩ። ምሽጉ ከተሰበረም በኋላ ደጀን መሆኑን ትተው ወደ ውጊያ ለመግባት በመወሰናቸው ከሻለቃ በቀለ ወያ ጦር ጋር ተሰልፈው ጠላትን ተፋልመዋል። በመቀጠልም ወደ ወሊሶ በመሄድ ከደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጦር ጋር ሆነው ተዋግተዋል። በጦርነቱ የአራት ሰዓታት ውጊያ ላይ ጠላት በጣለው ድንገተኛ አደጋ ከታላቅ ተጋድሎ በኋላ የተማረኩት አርበኛ ሸዋረገድ፣ በድጋሚ በፋሺስት ኢጣሊያ ወታደሮች እጅ በመውደቃቸው የፊጥኝ ታስረው ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። የሸዋረገድን ጀግንነት የተመለከተው ሕዝብም ...

***"የምታስፎክር ሰንጋ ገለሌ፣በጦር መካል ሳይሆኑ አያሌ፣***

***በጥይት ገዳይ ነጭ ብር ገድሌ፣የሴት ወንድ ናት ሸዋረገድ ገድሌ"***

***ብሎ ጀግንነታቸውን በማድነቅ አወድሷቸዋል።***

የጀግኖች አርበኞች ትግል ተጠናክሮ የጠላት ጦር በመጣበት እግሩ በታላቅ ውርደትና በአሳፋሪ ሽንፈት በ1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲባረር ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌም ነፃ ሆነው ተፈቱ። ከዚህ በኋላ ሕይወትን በነፃነት ማጣጣም ለእኚህ ታላቅ ሴት ትልቅ ትርጉም ነበረው። ቀድሞ የጀመሩትን አርበኞችን የመርዳት የበጎ አድራጎት ስራቸውን አጠናክረው ቀጠሉበት። በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተውም በርካታ ሰዎችን እንደጠቀሙም ይነገርላቸዋል።

አርበኛዋ ሸዋረገድ በ ፋሽስት ወረራ ግዜ  12 ጊዜ ታስረው የተፈቱ፣ እስከ ሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ነገር ግን ወደ ዕድሜ ይፍታሽ የተቀየረላቸው አርበኛ ናቸው። ሸዋረገድ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በጎ ማድረግን፣ ለሌሎች መስጠትን፣ በዓለማዊ ሕይወታቸው ሀገር መውደድን፣ ለዓላማ ጸንቶ ማሸነፍን አስተምረዋል። ግላዊ ነጻነትን ላለማስነጠቅ ጭቆናን እምቢ ብሎ መውጣት፣ ከነ ገረሱ ዱኪ እና ጃገማ ኬሎ ጋር ያደረጉት ትብብር ለአንድነት ከከፈሉት ዋጋ ውስጥ ይቆጠራል።

## ልክየለሽ በያን (1902-1972 ዓ.ም)



አርበኛ ልክየለሽ በያን በ 1902 ዓ.ም በድሮው አጠራር በከንባታ አውራጃ በሆሳዕና ከተማ ተወለዱ። በአካባቢው ወግና ባህል ያደጉት አርበኛ ልክየለሽ የአብነት ትምህርት ተከታትለው ዳዊት እስከመድገም ደርሰዋል። በነበራቸው እውቀትም ማንበብና መጻፍ፣ የሚፈልጉትን መልዕክት ማስተላለፍ ይችሉ ነበር:: አርበኛ ልክየለሽ ለአቅመ ሄዋን ሲደርሱ እንዳደጉበት ማኅበረሰብ ባሕልና ወግ ትዳር የመሠረቱት በልጅነታቸው ነበር። አርበኛ ልክየለሽ በያን የአያታቸውን ጠመንጃ ይዘው በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል ተዋግተዋል። አርበኛዋ በወቅቱ የአራት ወር ከአስራ አምስት ቀን አራስ ህፃን ልጃቸውን ለቤተሰብ በመተው የአገራቸውን ነፃነት አስቀድመው የዘመቱ አገር ወዳድ ናቸው። በጦርነቱ ጣልያን የበላይነት ሲያገኝ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተመልሰው የውስጥ አርበኛ በመሆን አርበኞችን ሲያግዙ ቆዩ። ቀንደኛ የፋሽስት ባንዳ የነበሩትን ቀኝ አዝማች ኩንቢን በ1930 ዓ.ም. በመግደል ናስማሰር ጠመንጃቸውን በመማረክ ጫካ ገቡ። ጫካ ከገቡ በኋላ በድንገት ተኩስ በመክፈት በርካታ የፋሽስት ወታደሮችን ከገደሉና ካቆሰሉ በኋላ በጊዜው አጠራር የውሃ መትረየስ የሚባለውን ማርከዋል። መትረየሱንም በወቅቱ የተሻለ እንቅስቃሴ ያደርግ ለነበረው ለራስ አበበ አረጋይ አስረክበዋል።

አርበኛዋ ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ሲዋጉ ባለቤታቸው ከጣልያኖች በተተኮሰ ጥይት ተመተው ወደቁ። ጣሊያኖች የባለቤታቸውን አንገት ቆርጠው ለመውሰድ ከፍተኛ ትግል ቢያካሂዱም ጥይት እስኪያልቅባቸው ድረስ ከተዋጉ በኋላ የባለቤታቸውን ሽጉጥ ከሬሳው ወገብ ላይ ፈትተው አራት የጣልያን ወታደሮችን ገድለዋል። የባለቤታቸውን አንገትም ከጠላት ከማስቆረጥ ታድገው በስርዓት እንዲቀበሩ አድርገዋል። አርበኛ ልክየለሽ በሌላ የጦር ሜዳ ውጊያ ዘወትር የሚይዙት የኢትዮጵያ ባንዲራ ድንገት ሳያዩት በመውደቁ ጥለውት ይሄዳሉ። ትዝ ሲላቸው «ከሞትሁም ልሙት እንጂ ሰንደቅ ዓላማዬን በፍጹም ለጣልያን አላስረክብም!» ብለው ወደ ዋሉበት ተመልሰው ዳግም ውጊያ ውስጥ በመግባታቸው ቆሰሉ። አርበኛዋ ቆስለው ከተኙበት ቦታ በጠላት ወታደሮች ተማርከው ከፍተኛ እንግልትና ስቃይ ደርሶባቸዋል። አርበኛዋ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ባደረጉት ተጋድሎና የኋላ ደጀን ሆነው ባደረጉት ድጋፍ በ1942 ዓ.ም አፄ ኃይለስላሴ ለኢትዮጵያ አርበኞች ባከናወኑት የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ ወይዘሮ ልክየለሽ በያን

በአርበኝነት ያደረጉት ተጋድሎና የከፈሉት መስዋዕትነት እጅግ ከፍተኛ ስለነበር አምስት የአርበኝነትና የጀግንነት ኒሻን ሸልመዋቸዋል። የኢትዮጵያን ዳር ድንበርን ለማስከበር በተከፈለው መስዋዕትነት ብዙውን ጊዜ የወንዶች ሚና ጎልቶ ቢጻፍም ለስኬታማነቱ ከፊትና ከኋላ ሆነው በመዋጋትና ጦርነቱ በድል እንዲጠናቀቅ ምክንያት የሆኑ በርካታ ሴቶች ውስጥ አንዷ አርበኛ ልክየለሽ ነበሩ። የአርበኛ ልክየለሽ በያን ታሪክ አሁን ላለው ትውልድ ጥንካሬን የሚያጋራ መንፈስንም የሚያነቃቃ ነው።

# ከበደች ስዩም መንገሻ (1904-1976 ዓ.ም)



አርበኛ ከበደች ስዩም መንገሻ የራስ ስዩም መንገሻ ልጅ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እና ማህበራዊ ታሪክ ውስጥ ስማቸው ከሚነሳ ሴቶች መካከል አንዷ ናቸው። ጀግናዋ ከበደች ስዩም ጥቅምት 17 ቀን 1904 ዓ.ም በትግራይ ጠቅላይ ግዛት በእንደርታ አውራጃ መቀሌ ከተማ ከልዑል ራስ ስዩም መንገሻና ከወይዘሮ ጀምበር በርሄ ተወለዱ።

ከበደች ስዩም በተወለዱበት አካባቢ ፊደል ከቆጠሩ በኋላ ገና በለጋ እድሜያቸው የልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ልጅ ከሆኑት ከደጃዝማች አበራ ካሳ ጋር ጋብቻ ፈፀሙ። ሁለቱ ጥንዶች ህይወታቸውን በመምራት ላይ እያሉ ነበር ፋሽስት ጣሊያን ሁለተኛ ወረራ የፈፀመው።

ፋሺስቶች ማይጨው ላይ በተደረገው ጦርነት በኢትዮጵያ ጦር ላይ ከባድ ጉዳት አድርሰው ወደ አዲስ አበባ ገስግሰው የወይዘሮ ከበደች ስዩምን ባለቤት ደጃዝማች አበራ ካሳንና ወንድማቸውን ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣን "... የኢጣሊያን ጦር መውጋታችሁን ካቆማችሁ በሰላም እንድትኖሩ ይፈቀድላችኋል" ብሎ በማታለል በጥይት ደብድቦ ገደሏቸው። ልጃቸውም በጠላት እጅ ተይዞ ወደ እስራት ተጋዘ። ይህ መከራ በሃገራቸውና በቤተሰባቸው ላይ ሲደርስ ወይዘሮ ከበደች ስዩም የሦስት ወር ነፍሰ ጡር ቢሆኑም የስምንት ዓመት ልጃቸውን አምሃን ይዘው የቤተሰባቸውን ደም ለመበቀልና ለሃገራቸው ነፃነት ለመፋለም ወስነው ጥቂት አርበኞችን አስከትለው እያስተባበሩ በእንሳሮ፣ በመርሐ ቤቴ፣ በሚዳና በአካባቢው እየተዘዋወሩ የአርበኝነት ተጋድሏቸውን ጀመሩ።

ግንቦት 25 ቀን 1928 ዓ.ም ሚዳ ወረዳ ውስጥ ቀኝ ገደል በተባለው ቦታ ላይ ከፋሺስት ጦር ጋር የመጀመሪያ ጦርነታቸውን አደረጉ። የፋሺስት ጦር ቁጥሩ ብዛት ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ በወታደራዊ ትጥቅም እጅግ የተጠናከረ ነበር። በመጨረሻም የኢትዮጵያ አርበኞች ጦር በአርበኛ ከበደች ሥዩም እየተመራ የዘመነ መሳሪያ ከታጠቀውና በቁጥር ከሚልቀው የጠላት ጦር ከበባ ሰብሮ መውጣት ቻለ። ይህ የአመራር ጥበባቸውና ድል አድራጊነታቸው ዝናቸውን ከፍ አደረገላቸው።

በዚያ አስቸጋሪ የጦርነት ወቅት ሱሪ በመታጠቅ በእንሳሮ፣ በመርሐ ቤቴና በሚዳ ቆላማ ቦታዎች በመውጣትና በመውረድ ለአገራቸው ነፃነት መከበር ከጠላት ጋር ውጊያ አድርገዋል። "ጥቁር ... በዚያ ላይ ሴት" ብሎ በድርብ ንቀት የሚመለከታቸውን የፋሺስትን ጦር በቁርጠኝነት እየተፋለሙ እየጣላ እንዲያከብራቸው አድርገውታል። በዚህም የተነሳ የጀግናዋ አርበኛ ከበደች ስዩም ስምና ዝና ከዳር እስከ ዳር በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ናኘ። በታላላቅ አርበኞች ሞት ምክንያት ተደናግጠው በስፍራው በዱር በገደሉ ተበታትነው የነበሩት የኢትዮጵያ አርበኞች ሁሉ በጀግናዋ ከበደች ስዩም ወኔ ተማርከው በየጎበዝ አለቃው አማካኝነት እየተፈላለጉ መደራጀት ጀመሩ።

በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የአርበኝነት ትግላቸውን በተበታተነ መልኩ ይከውኑ የነበሩት አርበኞች እየተገናኙ ይመካከሩ ነበርና አርበኛ ከበደች ስዩምም ስመጥር አርበኞች ከነበሩት ከነራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች ዘውዴ አስፋው፣ ፊታውራሪ ኃይለማርያም ማሞና ከሌሎች የአርበኞች መሪዎች ጋር እየተገናኙ በጠላት ላይ በጋራ ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ይመካከሩ ነበር።

አርበኛ ከበደች ስዩም በአገራቸው መደፈር ተቆጭተው ዱር ቤቴ ብለው ከጠላት ጋር የሚፋለሙ አርበኞችን በማስተባበር ጃርሶ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ ላይ የደፈጣ ውጊያ በማድረግ በወሰዱት እርምጃ ከጠላት ጎን ተሰልፈው የነበሩትን ባንዳዎችንና ነጭ የጦር ወታደሮችና አለቆችን በላቀ ወኔና አመራር መደምሰስ ችለዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ወልጭ በተባለው ስፍራ ላይ መሽጎ የአርበኛ ከበደች ስዩምን ጦር እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ሙከራ ያደረገው የጠላት ጦር በአርበኛዋ ጦር የሽንፈት ጽዋ ለመጨለጥ ተገዷል።

በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም ላይ የአርበኛ ከበደች ስዩም ጦር ወደ ቢሻን ጃሊ በመጓዝ ግንደበረት ላይ ካቺሱ ቡዳ ጤና ከተባለው ቦታ ላይ ሰፍሮ ከነበረው የጠላት ጦር ጋር ውጊያ አድርጎ መጠነኛ ጉዳት ቢደርስበትም የማታ ማታ ግን ድሉን የራሱ ከማድረግ ያገደው ኃይል አልነበረም።

እነዚህ የድል ሰንደቅ የተውለበለበባቸው አውደ ውጊያዎች የአርበኛ ከበደች ሥዩምን ዝና አገነኑት። አርበኛ ከበደች ሥዩም በአርበኝነት ታሪክ

ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር በውጊያ ላይ ሳሉ እርጉዝ መሆናቸውን እያወቁና የሕመም ስሜት እየተሰማቸው እንኳ ምንም ምክንያት ሳይፈልጉ ጤነኛ መስለው እልህ አስጨራሽ ውጊያዎችን መምራታቸውና ድል መቀዳጀታቸው ነበር። ሐምሌ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ከፋሺስት ኢጣሊያ ወራሪ ጦር ጋር ዱላ ቆርቻ በረሃ ውስጥ ውጊያ እያካሄዱበት በነበረበት ወቅት በጥይት እሩምታ መሐል ወንድ ልጅ ተገላገሉ። በዚያ አስጨናቂ የመከራ ወቅት "የኢትዮጵያ እድል የተገፎነት ወይንስ የነፃነት ይሆን?" በሚያስብል ሁኔታ ከወራሪው ጦር ጋር በሚፋለሙበት ወቅት የተወለደውን ልጃቸውን "ታሪክ" ብለው ስም አወጡለት።

ልጃቸው የተወለደው በጦርነት መሐል ለዚያውም የጦር መሪ ሆነው ነበርና ወላድ ሴቶች ከወሊድ በኋላ የሚደረግላቸውን እንክብካቤ አላዩም። የአራስነት ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ አንዲት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ እንዲገቡ ቢደረግም የፋሺስት የጦር አውሮፕላኖች ግን እርሳቸው ወዳሉባት ጎጆ ቤት የቦምብ ናዳ ያወርዱ ነበር። በነዚህ የቦምብ ድብደባዎችም ከእርሳቸው ጋር የነበሩ ብዙ አርበኞች ተሰውተዋል።

አርበኛ ከበደች ሥዩም አራስ ቤት ውስጥ መቆየትን እንደቅንጦት ተመልክተውት የአራስ ወገባቸው ሳይጠና ሕፃን ልጃቸውን ይዘው ከሸዋ በመነሳት ወደ ወለጋ መጓዝ ግድ ሆነባቸው። ወለጋ ከገቡ በኋላም በሆሮ ጉድሩ፣ በቡያና በሊሙ ከዚያም በጎጃም አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ወራሪውን ጦር በመዋጋት ከፍተኛ ጀብዱዎችን ፈፅመዋል።

አርበኛ ከበደች ስዩም ጎጃም ውስጥ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የነፃነት ትግላቸውን እስከ 1931 ዓ.ም ድረስ ከቀጠሉ በኋላ በወቅቱ የኢትዮጵያ አርበኞችን እየመሩ ያዋጉ ከነበሩት የጦር መሪዎች መካከል ከጥቂቶቹ ጋር በመሆን ወደ ሱዳን ሄዱ። ካርቱም ከተማ ከደረሱ በኋላም በወቅቱ በስደት እንግሊዝ ከነበሩት ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ጋር ተላልከው ወደ ግብጽ እንዲሄዱ በታቀደው መሰረት አርበኛ ከበደች ሥዩም ከልጅ ዐቢይ አበበ (በኋላ ሌተናል ጀኔራል) እና ከልጅ መርዕድ መንገሻ (በኋላ ሌተናል ጀኔራል) ጋር ወደ ካይሮ አቀኑ።

ከሁለት ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላም፣ በኢትዮጵያውያን አርበኞች ተጋድሎና በወዳጅ አገራት ድጋፍ ወራሪው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ሲሸነፍ፣ አርበኛ ከበደች ሥዩም ወደ አገራቸው ተመለሱ። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው በሸዋ፣ በወለጋና በጎጃም የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ለአገራቸው ነፃነት ሲታገሉ የነበሩት ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም በአርበኝነት ዘመናቸው በፈፀሟቸው አኩሪ ተግባራት አምስት ከፍተኛ የክብር ኒሻኖችን ተሸልመዋል። በመጨረሻም በታኅሣሥ ወር 1971 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በ2008 ዓ.ም የአርበኞች ድል 75ኛ ዓመት መታሰቢያ ሲከበር የመታሰቢያ ቴምብር ከታተመላቸው 25 ታላላቅ አርበኞች መካከል አንዷ ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም ናቸው። ኢትዮ-ጣሊያናዊቷ ዘፋኝ፣ ጸሐፊና ገጣሚ ጋብርኤላ ጌርማንዲ ስለታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም የሚከተለውን ጽፋለች። ***" ... እርሷ (አርበኛ ከበደች) ከወንዶች የላቀች መሪ እንደሆነች ብዙዎች ይመሰክሩላታል። ተወዳዳሪ አልነበራትም። አርበኞች ሁሉ ከማክበር አልፈው ያመልኳታል። እያንዳንዱ ዘመቻዋ የሚጠናቀቀው በድል ብቻ ነው። ጣሊያኖች እርሷን ለመያዝ ሞከሩ፣ ሞከሩ ... ግን አልቻሉም ..."***

ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም በሕይወት ዘመናቸው የፈፀሟቸው ገድሎች ኢትዮጵያ ነፃነቷን አስከብራ እንድትቆይ ከማስቻል አልፈው ለአሁኑ ዘመን ኢትዮጵያውያን (በተለይም ለወጣት ኢትዮጵያውያን ሴቶች) በአርዓያነት የሚጠቀሱ ናቸው።





"ብዙውን ጊዜ በባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች ተለይቶ በሚታወቅ ማህበረሰብ ውስጥ፣ እነዚህ አበረታች ሰዎች እንደ መሪ፣ አዲስ ነገር ጀማሪ እና የመብት ተሟጋች ሆነው ብቅ አሉ፣ ጽናትን እና ቆራጥነትንም አሳዩን። በታሪኮቻቸው ሴቶች በማህበረሰባቸው እና በአጠቃላይ በአገራቸው ሊጫወቱ የሚችሉተን ሚና አሳይተዋል ፤ እያሳዩም ይገኛሉ። የነዚህን አራአያ ሴቶች ጉዞ በመመዝገብ፣ አብርክቶዋቸውን ለመዘከር እና ሌሎችም ሴቶች እራሳቸውን በማብቃትና እውቀት እና ችሎታቸውን ለህበረተሰባቸው ትርጉም ያለው አስተዋጻኦ እንዲያደርጉ የማነሳሳት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ፅኑ እምነት አለን ።"



ኅብረት ለምርጫ CECOE
Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Election
Netherlands Institute for Multiparty Democracy
Funded by the European Union